መ ግ ለ ጫ ።

ብሉይ ፡ ኪዳንን ፡ ከአዲስ ፡ ኪዳን ፡ ጋር ፡ ለማስማማት ፡ አዲስንም ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ለመመርመር ፡ ከታች ፡ በገጹ ፡ ጎዳግ ፡ ተመልከት ። እንድ ፡ መጽሐፍ ፡ በምዕራፎች ፡ ይከፈላል ፤ እያንዳንዱም ፡ ምዕራፍ ፡ በቁጥሮች ፡ ይከፈላል ፤ እንደ ፡ እነዚህ ፡ ያሉትም ፡ ቁጥሮች ፡ የኃይለ ፡ ቃል ፡ ቁጥሮች ፡ ይባላሉ ።

በስተ ፡ ግራ ፡ ለብቻው ፡ የሚገኘው ፡ ቁጥር ፡ ከበላዩ ፡ ያለው ፡ የምዕራፍ ፡ ቁጥር ፡ ነው ።

በምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኘው ፡ ለእያንዳንዱ ፡ የኃይለ ፡ ቃል ፡ ቁጥር ፡ የተጠቀሰለት ፡ ሁሉ ፡ ሲጨረስ ፡ አራት ፡ ነጥብ ፡ ይገኛል ። ከአራት ፡ ነጥብ ፡ በኋላ ፡ የም ዕራፉ ፡ ሌላ ፡ የኃይለ ፡ ቃል ፡ ቁጥር ፡ ይገኛል ፤ ከዚህም ፡ ቁጥር ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ ዓቢይ ፡ ሠረገ ፡ "፡" ይታያል ።

ይህ ፡ ንኡስ ፡ ሠረገ "÷" የምዕራፉን ፡ ቁጥርና ፡ የኃይለ ፡ ቃሉን ፡ ቁጥር ፡ ሁልጊዜ ፡ ይከፍላል ። ለም ሳሌ ፤ "፪÷፮፡" ማለት ፡ ሁለተኛ ፡ ምዕራፍና ፡ ስድስተኛ ፡ የኃይለ ፡ ቃል ፡ ቁጥር ፡ ማለት ፡ ነው ።

ለእንድ ፡ የኃይለ ፡ ቃል ፡ ቁጥር ፡ ብዙ ፡ ጥቅስ ፡ ሲኖረው ፡ ከእያንዳንዱ ፡ ጥቅስ ፡ በኋላ ፡ ይህ "፡" ይገኛል ፤ ከዚህም ፡ ምልክት ፡ በኋላ ፡ ጥቅስ ፡ የተጠቀሰበት ፡ የመጽሐፉ ፡ ስም ፡ በአጭር ፡ ተጽፎአል ። ለም ሳሌ ፤ "፪ ፤ ዘፍጥ." ማለት ፡ በምዕራፉ ፡ ውስጥ ፡ ለሁለተኛው ፡ ቁጥር ፡ የተጠቀሰው ፡ የመጽሐፉ ፡ ስም ፡ አሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ መሆኑን ፡ የሚያመለክት ፡ ነው ።

ዘፍጥ.	ማለት ፡	አሪት ፡ ዘፍጥረት ።
ዘፀአ.	„	አሪት ፡ ዘፀአት ።
ዘሌዋ.	„	አሪት ፡ ዘሌዋውያን ።
ዘኍል.	„	አሪት ፡ ዘኍልቍ ።
ዘዳግ.	„	አሪት ፡ ዘዳግም ።
ኢያ.	„	መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ።
መሳ.	„	መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ።
ሩት	„	መጽሐፈ ፡ ሩት ።
፩ ሳሙ.	„	መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ፩ ።
፪ ሳሙ.	„	መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ፪ ።
፩ ነገሥ.	„	መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ፩ ።
፪ ነገሥ.	„	መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ፪ ።
፩ ዜና	„	መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ፩ ።
፪ ዜና	„	መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ፪ ።
ዕዝ.	„	መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ።
ነህ.	„	መጽሐፈ ፡ ነህምያ ።
አስቴ.	„	መጽሐፈ ፡ አስቴር ።
ኢዮብ	„	መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ።
መዝ.	„	መዝሙረ ፡ ዳዊት ።
ምሳ.	„	መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ።
መክ.	„	መጽሐፈ ፡ መክብብ ።
መኃ.	„	መኃልየ ፡ መኃልይ ።
ኢሳ.	„	መጽሐፈ ፡ ኢሳይያስ ፡
ኤር.	„	መጽሐፈ ፡ ኤርምያስ ።
ሕዝ.	„	መጽሐፈ ፡ ሕዝቅኤል ።
ዳን.	„	መጽሐፈ ፡ ዳንኤል ።
ሆሴ.	„	ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ።
ኢዩ.	„	ትንቢተ ፡ ኢዩኤል ።
ዓሞ.	„	ትንቢተ ፡ ዓሞጽ ።
አብድ.	„	ትንቢተ ፡ አብድዩ ፡
ዮና.	„	ትንቢተ ፡ ዮናስ ።
ሚክ.	„	ትንቢተ ፡ ሚክያስ ።
ናሆ.	„	ትንቢተ ፡ ናሆም ።

ከዚህ ፡ ምልክት "፡" በኋላ ፡ የመጽሐፍ ፡ ስም ፡ ባይገኝ ፡ ከአንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ሁሉ ፡ ጥቅስ ፡ እንደ ፡ ተጠቀሰ ፡ ይታወቃል ። ለምሳሌ ፤ "ዘፍጥ ፡ ፪ ፡ ፫÷፮ ፡ ፫÷፰ ።" ማለት ፡ ሁለቱም ፡ ጥቅስ ፡ ከኡደት ፡ ዘፍጥረት ፡ ተጠቀሰ ፡ ማለት ፡ ነው ።

በመጽሐፍ ፡ ስም ፡ ፈንታ ፡ "ቁ" የሚል ፡ ሲገኝ ፡ "ቁ" ማለት ፡ ከላይ ፡ በተጻፈው ፡ በዚያው ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ የኃይለ ፡ ቃል ፡ ቁጥር ፡ ማለት ፡ ነው ። "ም" ቢገኝ ፡ "ም" ማለት ፡ የዚያው ፡ መጽሐፍ ፡ ሌላ ፡ ምዕራፍ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ምናልባት ፡ ከንኡስ ፡ ሠረገ "÷" በኋላ ፡ ሁለት ፡ ቁጥር ፡ ይገኝ ፡ ይሆናል ። በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ሁለት ፡ ነጥብ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እያንዳንዱ ፡ ቁጥር ፡ ለብቻ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ይህ ፡ ምልክት ፡ "—" ሲገኝ ፡ ከፊተኛው ፡ ቁጥር ፡ እን ሥዶ ፡ እስከ ፡ ተከታዩ ፡ ቁጥር ፡ ድረስ ፡ ያሉትን ፡ ቁጥሮች ፡ ሁሉ ፡ ተመልከት ፡ ማለት ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ "፩÷፬" ማለት ፡ አንደኛና ፡ አራተኛ ፡ ቁጥሮችን ፡ ብቻ ፡ ተመልከት ፡ ማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ "፩—፬" ማለት ፡ ከአንደኛ ፡ እስከ ፡ አራተኛ ፡ ቁጥሮች ፡ ያሉትን ፡ ሁሉ ፡ ተመልከት ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በሚከተለው ፡ ገጽ ፡ የተጻፉት ፡ የቃል ፡ ማሳጠሪያ ፡ ቃሎች ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ናቸው ።

እንባ.	ማለት ፡	ትንቢተ ፡ እንባቆም ።
ሶፎ.	„	ትንቢተ ፡ ሶፎንያስ ።
ሐጌ	„	ትንቢተ ፡ ሐጌ ።
ዘካ.	„	ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ።
ሚል.	„	ትንቢተ ፡ ሚልክያስ ።
ማቴ.	„	የማቴዎስ ፡ ወንጌል ።
ማር.	„	የማርቆስ ፡ ወንጌል ።
ሉቃ.	„	የሉቃስ ፡ ወንጌል ።
ዮሐ.	„	የዮሐንስ ፡ ወንጌል ።
የሐዋ.	„	የሐዋርያት ፡ ሥራ ።
ሮሜ	„	ወደ ፡ ሮሜ ፡ ሰዎች ።
፩ ቆሮ.	„	ወደ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ ፩ ።
፪ ቆሮ.	„	ወደ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ ፪ ።
ገላ.	„	ወደ ፡ ገላትያ ፡ ሰዎች ።
ኤፌ.	„	ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ ሰዎች ።
ፊልጵ.	„	ወደ ፡ ፊልጵስዩስ ፡ ሰዎች ።
ቈላ.	„	ወደ ፡ ቈላስይስ ፡ ሰዎች ።
፩ ተሰ.	„	ወደ ፡ ተሰሎንቄ ፡ ሰዎች ፡ ፩ ።
፪ ተሰ.	„	ወደ ፡ ተሰሎንቄ ፡ ሰዎች ፡ ፪ ።
፩ ጢሞ.	„	ወደ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ፩ ።
፪ ጢሞ.	„	ወደ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ፪ ።
ቲቶ	„	ወደ ፡ ቲቶ ።
ፊልሞ.	„	ወደ ፡ ፊልሞና ።
ዕብ.	„	ወደ ፡ ዕብራውያን ።
፩ ጴጥ.	„	የጴጥሮስ ፡ መልእክት ፡ ፩ ።
፪ ጴጥ.	„	የጴጥሮስ ፡ መልእክት ፡ ፪ ።
፩ ዮሐ.	„	የዮሐንስ ፡ መልእክት ፡ ፩ ።
፪ ዮሐ.	„	የዮሐንስ ፡ መልእክት ፡ ፪ ።
፫ ዮሐ.	„	የዮሐንስ ፡ መልእክት ፡ ፫ ።
ያዕ.	„	የያዕቆብ ፡ መልእክት ።
ይሁዳ	„	የይሁዳ ፡ መልእክት ።
ራእ.	„	የዮሐንስ ፡ ራእይ ።

የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ማቴዎስ ፡ እንደ ፡ ጻፈው ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ የአብርሃም ፡ ልጅ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ትውልድ ፡ መጽሐፍ ።

፪ አብርሃም ፡ ይስሐቅን ፡ ወለደ ፤ ይስሐቅም ፡ ያዕቆብን ፡ ወለደ ፤ ያዕቆብም ፡ ይሁዳንና ፡ ወን ፫ ድሞቹን ፡ ወለደ ፤ ይሁዳም ፡ ከትዕማር ፡ ፋሬ ስንና ፡ ዛራን ፡ ወለደ ፤ ፋሬስም ፡ ኤስሮምን ፡ ፬ ወለደ ፤ ኤስሮምም ፡ አራምን ፡ ወለደ ፤ አራ ምም ፡ አሚናዳብን ፡ ወለደ ፤ አሚናዳብም ፡ ነአ ሶንን ፡ ወለደ ፤ ነአሶንም ፡ ሰልሞንን ፡ ወለደ ፤ ፭ ሰልሞንም ፡ ከራኬብ ፡ ቦኤዝን ፡ ወለደ ፤ ቦኤ ዝም ፡ ከሩት ፡ ኢዮቤድን ፡ ወለደ ፤ ኢዮቤ ፮ ድም ፡ እሴይን ፡ ወለደ ፤ እሴይም ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊትን ፡ ወለደ ።

ንጉሥ ፡ ዳዊትም ፡ ከኦርዮ ፡ ሚስት ፡ ሰሎሞ ፯ ንን ፡ ወለደ ፤ ሰሎሞንም ፡ ሮብዓምን ፡ ወለደ ፤ ሮብዓምም ፡ አቢያን ፡ ወለደ ፤ አቢያም ፡ አሣ ፰ ፍን ፡ ወለደ ፤ አሣፍም ፡ ኢዮሣፍጥን ፡ ወለደ ፤ ኢዮሣፍጥም ፡ ኢዮራምን ፡ ወለደ ፤ ኢዮራ ፱ ም ፡ ዖዝያንን ፡ ወለደ ፤ ዖዝያንም ፡ ኢዮ አታምን ፡ ወለደ ፤ ኢዮአታምም ፡ አካዝን ፡ ፲ ወለደ ፤ አካዝም ፡ ሕዝቅያስን ፡ ወለደ ፤ ሕዝቅ ያስም ፡ ምናሴን ፡ ወለደ ፤ ምናሴም ፡ አሞፅን ፡ ፲፩ ወለደ ፤ አሞፅም ፡ ኢዮስያስን ፡ ወለደ ፤ ኢዮስ ያስም ፡ በባቢሎን ፡ ምርኮ ፡ ጊዜ ፡ ኢኮንያንንና ፡ ወንድሞቹን ፡ ወለደ ።

፲፪ ከባቢሎንም ፡ ምርኮ ፡ በኋላ ፡ ኢኮንያን ፡ ሰላ ትያልን ፡ ወለደ ፤ ሰላትያልም ፡ ዘሩባቤልን ፡ ፲፫ ወለደ ፤ ዘሩባቤልም ፡ አብዩድን ፡ ወለደ ፤ አብዩድም ፡ ኤልያቄምን ፡ ወለደ ፤ ኤልያቄ ፲፬ ም ፡ አዛርን ፡ ወለደ ፤ አዛርም ፡ ሳዶቅን ፡ ወለደ ፤ ሳዶቅም ፡ አኪምን ፡ ወለደ ፤ አኪምም ፡ ፲፭ ኤልዩድን ፡ ወለደ ፤ ኤልዩድም ፡ አልዓዛርን ፡ ወለደ ፤ አልዓዛርም ፡ ማታንን ፡ ወለደ ፤ ማታ ፲፮ ንም ፡ ያዕቆብን ፡ ወለደ ፤ ያዕቆብም ፡ ክርስ ቶስ ፡ የተባለውን ፡ ኢየሱስን ፡ የወለደች ፡ የማ ርያምን ፡ እጮኛ ፡ ዮሴፍን ፡ ወለደ ።

፲፯ እንግዲህ ፡ ትውልድ ፡ ሁሉ ፡ ከአብርሃም ፡ እስከ ፡ ዳዊት ፡ አሥራ ፡ አራት ፡ ትውልድ ፡ ከዳዊትም ፡ እስከ ፡ በቢሎን ፡ ምርኮ ፡ አሥራ ፡ አራት ፡ ትውልድ ፡ ከባቢሎንም ፡ ምርኮ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ አሥራ ፡ አራት ፡ ትውልድ ፡ ነው ።

፲፰ የጌታችን ፡ የኢየሱስክርስቶስም ፡ ልደት* ፡ እንዲህ ፡ ነበረ ። እናቱ ፡ ማርያም ፡ ለዮሴፍ ፡ በታጨች ፡ ጊዜ ፡ ሳይገናኙ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፀንሳ ፡ ተገኘች ። እጮኛዋ ፡ ዮሴፍም ፡ ጻድቅ ፡ ሆኖ ፡ ፲፱ ሊገልጣት ፡ ስላልወደደ ፡ በስውር ፡ ሊተዋት ፡ አሰበ ። እርሱ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሲያስብ ፡ እነሆ ፡ ፳ የጌታ ፡ መልአክ ፡ በሕልም ፡ ታየው ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦— የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ዮሴፍ ፡ ሆይ ፡ ከእርስዋ ፡ የተፀነሰው ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ፡ እጮኛህን ፡ ማርያምን ፡ ለመውሰድ ፡ አትፍራ ። ፳፩ ልጅም ፡ ትወልዳለች ። እርሱ ፡ ሕዝቡን ፡ ከኃጢአታቸው ፡ ያድናቸዋልና ፡ ስሙን ፡ ኢየሱስ ፡ ትለዋለህ ። ፳፪ በነቢይ ፡ ከጌታ ፡ ዘንድ ፡ ፦ ፳፫ እነሆ ፡ ድንግል ፡ ትፀንሳለች ፡ ልጅም ፡ ትወ ልዳለች ፡ ስሙንም ፡ አማኑኤል ፡ ይሉታል ፡ የተባለው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሆኖ አል ፡ ትርጓሜውም ፡ ፦ እግዚአብሔር ፡ ከእኛ ፡ ፳፬ ጋር ፡ የሚል ፡ ነው ። ፳፬ ዮሴፍም ፡ ከእንቅልፉ ፡ ነቅቶ ፡ የጌታ ፡ መልአክ ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ፤ እጮኛውን ፡ ማርያምንም ፡ ወሰደ ። ፳፭ የበኵር ፡ ልጅዋንም ፡ እስከ ፡ ወለደች ፡ ድረስ ፡ አላወቃትም ፤ ስሙንም ፡ ኢየሱስ ፡ አለው ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ኢየሱስም ፡ በይሁዳ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ በን ጉሡ ፡ በኄሮድስ ፡ ዘመን ፡ በተወለደ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ ሰብአ ፡ ሰገል ፦ የተወለደው ፡ የአይ ፪ ሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ወዴት ፡ ነው ? ኮከቡን ፡ በምሥራቅ ፡ አይተን ፡ ልንሰግድለት ፡ መጥተናልና ፡ እያሉ ፡ ከምሥራቅ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ። ፫ ንጉሡ ፡ ሄሮድስም ፡ ሰምቶ ፡ ደነገጠ ፡ ኢየሩሳ ፫ ሌምም ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፤ የካህናትንም ፡ ፬ አለቆች ፡ የሕዝቡንም ፡ ፡ ፍች ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቦ ፡ ክርስቶስ ፡ ወዴት ፡ እንዲወለድ ፡ ጠየቃቸው ። ፭ እነርሱም ፡ ፦

፮ አንቺ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ የይሁዳ ፡ ምድር ፡ ከይሁዳ ፡ ገዦዎች ፡ ከቶ ፡ አታንሽም ፤ ሕዝ ቤን ፡ እስራኤልን ፡ የሚጠብቅ ፡ መስፍን ፡ ከአንቺ ፡ ይወጣልና ፡

ተብሎ ፡ በነቢይ ፡ እንዲህ ፡ ተጽፎአልና ፡ በይ ሁዳ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ አሉት ።

፯ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሄሮድስ ፡ ሰብአ ፡ ሰገልን ፡ በስ

፩ ፩—፲፯ ፤ ሉቃ. ፫ ÷ ፳፫—፴፰ ። ፪ ፤ ዘፍጥ. ፳፭ ÷ ፫ ፤ ፳፭ ÷ ፳፯ ፤ ፳፱ ÷ ፴፩ ። ፲፪—፲፮ ፤ ዘፍጥ. ፴፯ ÷ ፳፱ ፤ ፴፯ ። ፲፰—፳፭ ፤ ኢያ. ፮ ÷ ፳፫ ፤ ሩት ፤ ፪ ÷ ፲፯ ። ፮ ፤ ፪ ሳሙ. ፯፤፪ ÷ ፳፬ ። ፯—፲ ፤ ፪ ዜና ፤ ፫ ÷ ፲—፯፤፪ ። ፲፩ ÷ ፳፬ ፤ ፳፪ ÷ ፶ ። ፲፪ ፤ ዕዝ. ፫ ÷ ፪ ። ፲፫ ፤ ሉቃ. ፭ ÷ ፳፯ ፤ ፴፩ ። ፲፭ ÷ ፲፱ ። ፲፮ ፤ ሉቃ. ፭ ÷ ፴፩ ፤ ፪ ÷ ፲፭ ፤ ፳፭ ። ፲፰ ፤ ሉቃ. ፪ ÷ ፯ ።

፪ ፤ ፩ ፤ ሉቃ. ፪ ÷ ፩—፯ ። ፪ ፤ ዘኍል. ፳፬ ÷ ፲፯ ፤ ኤር. ፳፫ ÷ ፳ ። ፮ ፤ ሚክ. ፭ ÷ ፪ ።

፩ ፤ ፲፰ ፤ « ጌታችን » ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በግሪኩ ፡ ሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ አይገኝም ።

ውር ፡ ጠርቶ ፡ ከከቡ ፡ የታየበትን ፡ ዘመን ፡
፯ ከእነርሱ ፡ በጥንቃቄ ፡ ተረዳ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡
ልሔምም ፡ እነርሱን ፡ ሰድዶ ፡— ሂዱ ፡ ስለ ፡
ሕፃኑ ፡ በጥንቃቄ ፡ መርምሩ ፡ ባገኛችሁትም ፡
ጊዜ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ መጥቼ ፡ እንድሰግድለት ፡
፱ ንገሩኝ ፡ አላቸው ። እነርሱም ፡ ንጉሡን ፡ ሰም
ተው ፡ ሄዱ ። እነሆም ፡ በምሥራቅ ፡ ያዩት ፡
ከከብ ፡ ሕፃኑ ፡ በለበት ፡ ላይ ፡ መጥቶ ፡ እስኪ
፲ ቆም ፡ ድረስ ፡ ይመራቸው ፡ ነበር ። ከከቡንም ፡
ባዩ ፡ ጊዜ ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አላ
፲፩ ቸው ። ወደ ፡ ቤትም ፡ ገብተው ፡ ሕፃኑን ፡ ከእ
ናቱ ፡ ከማርያም ፡ ጋር ፡ አዩት ፡ ወድቀውም ፡
ሰገዱለት ፡ ሣጥኖቻቸውንም ፡ ከፍተው ፡ እጅ ፡
መንሻ ፡ ወርቅና ፡ ዕጣን ፡ ከርቤም ፡ አቀረቡለት ።
፲፪ ወደ ፡ ሄሮድስም ፡ እንዳይመለሱ ፡ በሕልም ፡ ተረ
ድተው ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ሄዱ ።
፲፫ እነርሱም ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ እነሆ ፡ የጌታ ፡ መል
አክ ፡ በሕልም ፡ ለዮሴፍ ፡— ሄሮድስ ፡ ሕፃ
ኑን ፡ ሊገድለው ፡ ይፈልገዋልና ፡ ተነሣ ፡ ሕፃኑ
ንና ፡ እናቱንም ፡ ይዘህ ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ሽሽ ፡
እስክነግርህም ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ።
፲፬፡፲፭ እርሱም ፡ ተነሥቶ ፡ ሕፃኑንና ፡ እናቱን ፡ በሌ
ሊት ፡ ያዘና ፡ ከጌታ ፡ ዘንድ ፡ በነቢይ ፡— ልጄን ፡
ከግብፅ ፡ ጠራሁት ፡ የተባለው ፡ እንዲፈጸም ፡
ወደ ፡ ግብፅ ፡ ሄደ ። ሄሮድስም ፡ እስኪሞት ፡
ድረስ ፡ በዚያ ፡ ኖረ ።
፲፮ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሄሮድስ ፡ ሰብአ ፡ ሰገል ፡ እንደ
ተሣለቁበት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተቈጣና ፡
ልከ ፡ ከሰብአ ፡ ሰገል ፡ እንደ ፡ ተረዳው ፡ ዘመን ፡
በዓተ ፡ ልሔምና ፡ በአውራጃዋ ፡ የነበሩትን ፡
ሁለት ፡ ዓመት ፡ የሆናቸውን ፡ ከዚያም ፡ የሚያ
፲፯፡፲፰ ንሱትን ፡ ሕፃናትን ፡ ሁሉ ፡ አስገደለ ። ያን ፡ ጊዜ ፡
በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፡—

ድምፅ ፡ በራማ ፡ ተሰማ ፡ ልቅሶና ፡ ብዙ ፡
ዋይታ ፤ ራሔል ፡ ስለ ፡ ልጆችዋ ፡ አለቀሰች ፡
መጽናናትም ፡ አልወደደችም ፡ የሉምና ፡

የተባለው ፡ ተፈጸመ ።
፲፱ ሄሮድስም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እነሆ ፡ የጌታ ፡ መል
አክ ፡ በግብፅ ፡ ለዮሴፍ ፡ በሕልም ፡ ታይቶ ፡—
፳ የሕፃኑን ፡ ነፍስ ፡ የፈለጉት ፡ ሞተዋልና ፡ ተነሣ ፡
ሕፃኑን ፡ እናቱንም ፡ ይዘህ ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡
፳፩ አገር ፡ ሂድ ፡ አለ ። እርሱም ፡ ተነሥቶ ፡ ሕፃኑ
ንና ፡ እናቱን ፡ ያዘና ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ አገር ፡
፳፪ ገባ ። በአባቱም ፡ በሄሮድስ ፡ ፈንታ ፡ አርኬላ
ዎስ ፡ በይሁዳ ፡ እንደ ፡ ነገሠ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደ
ዚያ ፡ መሄድን ፡ ፈራ ። በሕልምም ፡ ተረድቶ ፡
፳፫ ወደ ፡ ገሊላ ፡ አገር ፡ ሄደ ፤ በነቢያት ፡— ናዝራዊ ፡
ይባላል ፡ የተባለው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ናዝ
ሬት ፡ ወደምትባል ፡ ከተማ ፡ መጥቶ ፡ ኖረ ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

በዚያም ፡ ወራት ፡ መጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፡— ፩፡፪
መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ቀርባለችና ፡ ንስሐ ፡ ግቡ ፡
ብሎ ፡ በይሁዳ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ እየሰበከ ፡ መጣ ።
፫ በነቢዩ ፡ በኢሳይያስ ፡— ፫
የጌታን ፡ መንገድ ፡ አዘጋጁ ፡ ጥርጊያው
ንም ፡ አትኑ ፡ እያለ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የሚ
ጮህ ፡ ሰው ፡ ድምፅ ፡

የተባለለት ፡ ይህ ፡ ነውና ። ራሱም ፡ ዮሐንስ ፡ ፬
የግመል ፡ ጠጕር ፡ ልብስ ፡ ነበረው ፡ በወገቡም ፡
ጠፍር ፡ ይታጠቅ ፡ ነበር ፤ ምግቡም ፡ አንበጣና ፡
የበረሀ ፡ ማር ፡ ነበረ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ፭
ይሁዳም ፡ ሁሉ ፡ በዮርዳኖስም ፡ ዙሪያ ፡ ያለ ፡
አገር ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ይወጡ ፡ ነበር ፤ ኃጢ ፮
አታቸውንም ፡ እየተናዘዙ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ወንዝ ፡
ከእርሱ ፡ ይጠመቁ ፡ ነበር ።
ዳሩ ፡ ግን ፡ ከፈሪሳውያንና ፡ ከሰዱቃውያን ፡ ፯
ብዙዎች ፡ ወደ ፡ ጥምቀቱ ፡ ሲመጡ ፡ ባየ ፡
ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡— እናንተ ፡ የእፉኝት ፡
ልጆች ፡ ከሚመጣው ፡ ቍጣ ፡ እንድትሸሹ ፡
ማን ፡ አመለከታችሁ ? እንግዲህ ፡ ለንስሐ ፡ የሚ ፰
ገባ ፡ ፍሬ ፡ አድርጉ ፡ በልባችሁም ፡— አብርሃም ፡ ፱
አባት ፡ አለን ፡ እንደምትሉ ፡ አይምሰላችሁ ፤
እላችኋለሁና ፡ ከነዚህ ፡ ድንጋዮች ፡ ለአብርሃም ፡
ልጆች ፡ ሊያስነሣለት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይች
ላል ። አሁንስ ፡ ምሰር ፡ በዛፎች ፡ ሥር ፡ ተቀም ፲
ጦአል ፤ እንግዲህ ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ የማያደርግ ፡
ዛፍ ፡ ሁሉ ፡ ይቈረጣል ፡ ወደ ፡ እሳትም ፡ ይጣላል ።
እኔስ ፡ ለንስሐ ፡ በውኃ ፡ አጠምቃችኋለሁ ፤ ፲፩
ጫማውን ፡ እሸከም ፡ ዘንድ ፡ ከማይገባኝ ፡
ከእኔ ፡ በኋላ ፡ የሚመጣው ፡ ግን ፡ ከእኔ ፡ ይልቅ ፡
ይበረታል ፤ እርሱ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በእሳ
ትም ፡ ያጠምቃችኋል ፤ መንሹም ፡ በእጁ ፡ ነው ፡ ፲፪
አውድማውንም ፡ ፈጽሞ ፡ ያጠራል ፡ ስንዴውን ፡
በጎተራው ፡ ይከታል ፡ ገለባውን ፡ ግን ፡
በማይጠፋ ፡ እሳት ፡ ያቃጥለዋል ።
ያን ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ በዮሐንስ ፡ ሊጠመቅ ፡ ከገ ፲፫
ሊላ ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ መጣ ። ዮሐንስ ፡ ግን ፡— ፲፬
እኔ ፡ በእጅህ ፡ ልጠመቅ ፡ ያስፈልገኛል ፡ አንተም ፡
ወደ ፡ እኔ ፡ ትመጣለህን ? ብሎ ፡ ይከለክለው ፡
ነበር ። ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡— አሁንስ ፡ ፍቀድ ፲፭
ልኝ ፤ እንዲህ ፡ ጽድቅን ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ ይገ
ባናልና ፡ አለው ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ፈቀደለት ።
ኢየሱስም ፡ ከተጠመቀ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ ፲፮
ከውኃ ፡ ወጣ ፤ እነሆም ፡ ሰማያት ፡ ተከፈቱ ፡ የእ
ግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ እንደ ፡ርግብ ፡ ሲወ
ርድ ፡ በእርሱ ፡ ላይም ፡ ሲመጣ ፡ አየ ፤ እነሆም ፡ ፲፯
ድምፅ ፡ ከሰማያት ፡ መጥቶ ፡— በእርሱ ፡ ደስ ፡
የሚለኝ ፡ የምወደው ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለ ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ኢየሱስ ፡ ከዲያብሎስ ፡ ይፈ ፩
ተን ፡ ዘንድ ፡ በመንፈስ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡
ተወሰደ ። አርባ ፡ ቀንና ፡ አርባ ፡ ሌሊትም ፡ ጦሙ ፪
በኋላ ፡ ተራበ ። ፫ ፈታኝም ፡ ቀርቦ ፡— የእግዚአ
ብሔር ፡ ልጅ ፡ ከሆንህ ፡ እነዚህ ፡ ድንጋዮች ፡
እንጀራ ፡ እንዲሆኑ ፡ በል ፡ አለው ። እርሱም ፡ ፬
መልሶ ፡— ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ በሚ
ወጣ ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ እንጂ ፡ በእንጀራ ፡ ብቻ ፡
አይኖርም ፡ ተብሎ ፡ ተጽፎአል ፡ አለው ። ከዚህ ፡ ፭
በኋላ ፡ ዲያብሎስ ፡ ወደ ፡ ቅድስት ፡ ከተማ ፡ ወሰ
ደና ፡ እርሱን ፡ በመቅደስ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ አቁሞ ፡—
መላእክቱን ፡ ስለ ፡ እንተ ፡ ያዝልሃል ፡ እግ ፮
ርህንም ፡ በድንጋይ ፡ ከቶ ፡ እንዳትሰናከል ፡
በእጃቸው ፡ ያሥሉሃል ፡
ተብሎ ፡ ተጽፎአልና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅስ ፡
ከሆንህ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ራስህን ፡ ወርውር ፡ አለው ።
ኢየሱስም ፡— ጌታን ፡ አምላክህን ፡ አትፈታተ ፯
ነው ፡ ተብሎ ፡ ደግሞ ፡ ተጽፎአል ፡ አለው ።
ዲያብሎስ ፡ እጅግ ፡ ረጅም ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ ፰
ተራራ ፡ ወሰደው ፡ የዓለምንም ፡ መንግሥታት ፡
ሁሉ ፡ ክብራቸውንም ፡ አሳይቶ ፡— ወድቀህ ፡ ፱
ብትሰግድልኝ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እሰጥሃለሁ ፡ አለው ።
ያን ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡— ሂድ ፡ አንተ ፡ ሰይጣን ፤ ፲
ለጌታህ ፡ ለአምላክህ ፡ ስገድ ፡ እርሱንም ፡ ብቻ ፡
አምልክ ፡ ተብሎ ፡ ተጽፎአልና ፡ አለው ። ያን ፡
ጊዜ ፡ ዲያብሎስ ፡ ተወው ፡ እነሆም ፡ መላእክት ፡
ቀርበው ፡ ያገለግሉት ፡ ነበር ።
ኢየሱስም ፡ ዮሐንስ ፡ አልፎ ፡ እንደ ፡ ተሰጠ ፡ ፲፪
በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ፈቀቅ ፡ ብሎ ፡ ሄደ ።
ናዝሬትንም ፡ ትቶ ፡ በዛብሎንና ፡ በንፍታሌም ፡ ፲፫
አገር ፡ በባሕር ፡ አጠገብ ፡ ወደ ፡ አለችው ፡ ወደ ፡
ቅፍርናሆም ፡ መጥቶ ፡ ኖረ ። በነቢዩም ፡ በኢ ፲፬፡፲፮
ሳይያስ ፡—

የዛብሎን ፡ ምድርና ፡ የንፍታሌም ፡ ምድር ፡
የባሕር ፡ መንገድ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ የአ
ሕዛብ ፡ ገሊላ ፤ በጨለማ ፡ የተቀመጠው ፡
ሕዝብ ፡ ታላቅ ፡ ብርሃን ፡ አየ ፡ በሞት ፡ አገ
ርና ፡ ጥላ ፡ ለተቀመጡትም ፡ ብርሃን ፡ ወጣ
ላቸው ።
የተባለው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ሆነ ። ከዚያ ፡ ፲፯
ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ኢየሱስ ፡— መንግሥተ ፡ ሰማ
ያት ፡ ቀርባለችና ፡ ንስሐ ፡ ግቡ ፡ እያለ ፡ ይሰ
በክ ፡ ጀመር ።
በገሊላ ፡ ባሕር ፡ አጠገብ ፡ ሲመላለስም ፡ ሁለት ፡ ፲፰
ወንድማማች ፡ ጴጥሮስ ፡ የሚሉትን ፡ ስምዖንን ፡
ወንድሙንም ፡ እንድርያስን ፡ መረባቸውን ፡
ወደ ፡ ባሕር ፡ ሲጥሉ ፡ አየ ፡ አሣ ፡ አጥማጆች ፡

ነበሩና ። እርሱም ፡— በኋላዬ ፡ ኑና ፡ ሰዎችን ፡ ፲፱
አጥማጆች ፡ እንድትሆኑ ፡ አደርጋችኋለሁ ፡ አላ
ቸው ። ወዲያውም ፡ መረባቸውን ፡ ትተው ፡ ፳
ተከተሉት ። ከዚያም ፡ አልፍ ፡ ብሎ ፡ ሌሎችን ፡ ፳፩
ሁለት ፡ ወንድማማች ፡ የዘብዴዎስን ፡ ልጅ ፡ ያዕ
ቆብን ፡ ወንድሙንም ፡ ዮሐንስን ፡ ከአባታቸው ፡
ከዘብዴዎስ ፡ ጋር ፡ በታንኳ ፡ መረባቸውን ፡ ሲያ
በጁ ፡ አየ ፤ ጠራቸውም ። እነርሱም ፡ ወዲያው ፡ ፳፪
ታንኳይቱንና ፡ አባታቸውን ፡ ትተው ፡ ተከተ
ሉት ።
ኢየሱስም ፡ በምኵራቦቻቸው ፡ እያስተማረ ፡ ፳፫
የመንግሥትንም ፡ ወንጌል ፡ እየሰበከ ፡ በሕዝ
ብም ፡ ያለውን ፡ ደዌና ፡ ሕማም ፡ ሁሉ ፡ እየፈ
ወሰ ፡ በገሊላ ፡ ሁሉ ፡ ይዞር ፡ ነበር ። ዝናውም ፡ ፳፬
ወደ ፡ ሶርያ ፡ ሁሉ ፡ ወጣ ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ደዌና ፡
ሥቃይም ፡ ተይዘው ፡ የታመሙትን ፡ ሁሉ ፡
አጋንንትም ፡ ያደሩባቸውን ፡ በጨረቃም ፡ የሚ
ነሣባቸውን ፡ ሽባዎችንም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አመጡ ፡
ፈወሳቸውም ። ከገሊላም ፡ አሥር ፡ ከተማም ፡ ፳፭
ከሚባል ፡ አገር ፡ ከኢየሩሳሌምም ፡ ከይሁዳም ፡
ከዮርዳኖስም ፡ ማዶ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተከተሉት ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

ሕዝቡንም ፡ አይቶ ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ወጣ ፤ ፩
በተቀመጠም ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ወደ ፡
እርሱ ፡ ቀረቡ ፤ አፉንም ፡ ከፍቶ ፡ አስተማራ ፪
ቸው ፡ እንዲህም ፡ አለ ፡—
በመንፈስ ፡ ድሆች ፡ የሆኑ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ ፫
መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የእነርሱ ፡ ናትና ።
የሚያዝኑ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ መጽናናትን ፡ ፬
ያገኛሉና ።
የዋሆች ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ ምድርን ፡ ይወርሳ ፭
ሉና ።
ጽድቅን ፡ የሚራቡና ፡ የሚጠሙ ፡ ብፁዓን ፡ ፮
ናቸው ፡ ይጠግባሉና ።
የሚምሩ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ ይማራሉና ። ፯
ልበ ፡ ንጹሐት ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ እግዚአብ ፰
ሔርን ፡ ያዩታልና ።
የሚያስተራርቁ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ የእግዚአ ፱
ብሔር ፡ ልጆች ፡ ይባላሉና ።
ስለ ፡ ጽድቅ ፡ የሚሰደዱ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ ፲
መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የእነርሱ ፡ ናትና ።
ሲነቅፉአችሁና ፡ ሲያሳድዱአችሁ ፡ በእኔም ፡ ፲፩
ምክንያት ፡ ክፉውን ፡ ሁሉ ፡ በውሸት ፡ ሲናገሩባ
ችሁ ፡ ብፁዓን ፡ ናችሁ ። ዋጋችሁ ፡ በሰማያት ፡ ፲፪
ታላቅ ፡ ነውና ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡ ሐሤትም ፡ አድ
ርጉ ፤ ከእናንተ ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡ ነቢያትን ፡
እንዲሁ ፡ አሳደዋቸዋልና ።

፪ ፡ ፩—፲፩ ፤ ማር. ፩ ÷ ፲፪ ፤ ፲፫ ፡ ሉቃ. ፬ ÷ ፩ ። ፫ ፡ ዘዳግ. ፰÷፫ ። ፬ ፡ መዝ. ፺÷ ፲፩ ፤ ፲፪ ። ፮ ፡ ዘዳግ. ፮÷ ፲፮ ። ፯ ፡ ዘዳግ. ፮÷ ፲፫ ። ፰ ፡ ሉቃ. ፬÷ ፭ ። ፱ ፡ ፲፪ ። ፲ ፡ ሉቃ. ፭÷ ፲፪ ። ፲፩ ፡ ም. ፫ ÷ ፪ ። ፲፪—፳፪ ፤ ማር. ፩÷ ፲፯—፳ ፤ ሉቃ. ፭ ÷ ፩—፲፩ ። ፲፫ ፡ ማር. ፩÷ ፵፭ ። ፲፬ ፡ ሉቃ. ፭÷ ፵፬ ። ፲፭ ፡ ማር. ፩÷ ፵፭ ። ፲፮ ፡ ሉቃ. ፭ ÷ ፲፮ ።

፫ ፡ ፩—፲፪ ፤ ሉቃ. ፮÷ ፳—፳፫ ፤ ኢሳ. ፶፯÷ ፲፭ ። ፩ ፤ ኢሳ. ፵፩÷ ፩ ። ፫ ፤ መዝ. ፴፯÷ ፲፭ ። ፮ ፤ ኢሳ. ፶፩÷ ፭ ። ፱ ፤ ም·ሳ. ፳፭÷ ፳፭ ። ፲ ፡ ሉቃ. ፮÷ ፳፪ ። ፲፩ ፡ ሉቃ. ፮÷ ፳፮ ። ፲፪ ፡ ሉቃ. ፮÷ ፳፫ ። ፲፫ ፡ ሉቃ. ፲፬÷ ፴፬ ። ፲፮ ፡ ሉቃ. ፰÷ ፲፮ ።

* በግዕዝ ፣ « ስለ ፡ ጽድቅ ፡ የሚራቡና ፡ የሚጠሙ » ይላል ።

፲፫ እናንተ ፡ የምድር ፡ ጨው ፡ ናችሁ ፤ ጨው ፡
አልጫ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ በምን ፡ ይጣፍጣል ?
ወደ ፡ ውጭ ፡ ተጥሎ ፡ በሰው ፡ ከመረገጥ ፡ በቀር ፡
ወደ ፡ ፊት ፡ ለምንም ፡ አይጠቅምም ።
፲፬ እናንተ ፡ የዓለም ፡ ብርሃን ፡ ናችሁ ። በተራራ ፡
ላይ ፡ ያለች ፡ ከተማ ፡ ልትሰወር ፡ አይቻላትም ።
፲፭ መብራትንም ፡ አብርተው ፡ በዕንቅብ ፡ በታች ፡
አይደለም ፡ እንጂ ፡ በመቅረዙ ፡ ላይ ፡ ያኖሩታል ፡
፲፮ በቤት ፡ ላሉት ፡ ሁሉም ፡ ያበራል ። መልካ
ሙን ፡ ሥራችሁን ፡ አይተው ፡ በሰማያት ፡ ያለ
ውን ፡ አባታችሁን ፡ እንዲያከብሩ ፡ ብርሃናችሁ ፡
እንዲሁ ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ይብራ ።
፲፯ እኔ ፡ ሕግንና ፡ ነቢያትን ፡ ለመሻር ፡ የመጣሁ ፡
አይምሰላችሁ ፤ ልፈጽም ፡ እንጂ ፡ ለመሻር ፡ አል
፲፰ መጣሁም ። እውነት ፡ እላችኋለሁ ፥ ሰማይና ፡
ምድር ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፥ ከሕግ ፡ አንዲት ፡
የውጣ ፡ ወይም ፡ አንዲት ፡ ነጥብ ፡ ከቶ ፡ አታል
፲፱ ፍም ፥ ሁሉ ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ። እንግዲህ ፡
ከነዚህ ፡ ከሁሉ ፡ ካነሱት ፡ ትእዛዛት ፡ አንዲቱን ፡
የሚሽር ፡ ለሰውም ፡ እንዲሁ ፡ የሚያስተምር ፡
ማንም ፡ ሰው ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ከሁሉ ፡
ታናሽ ፡ ይባላል ፤ የሚያደርግ ፡ ግን ፡ የሚያስ
ተምርም ፡ ማንም ፡ ቢሆን ፡ እርሱ ፡ በመንግሥተ ፡
፳ ሰማያት ፡ ታላቅ ፡ ይባላል ። እላችኋለሁና ፡—
ጽድቃችሁ ፡ ከጻፎችና ፡ ከፈሪሳውያን ፡ ጽድቅ ፡
ካልበለጠ ፥ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ከቶ ፡
አትገቡም ።
፳፩ ለቀደሙት ፡— አትግደል ፡ እንደ ፡ ተባለ ፡ ሰም
ታችኋል ፤ የገደለም ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ይገባዋል ።
፳፪ እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ፥ በወንድሙ ፡ ላይ ፡ የሚ
ቈጣ ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ይገባዋል ፤ ወንድሙንም ፡
ጨርቃም ፡ የሚለው ፡ ሁሉ ፡ የሸንጎ ፡ ፍርድ ፡
ይገባዋል ፤ ደንቆሮ ፡ የሚለውም ፡ ሁሉ ፡ የገሃነመ ፡
፳፫ እሳት ፡ ፍርድ ፡ ይገባዋል ። እንግዲህ ፡ መባህን ፡
በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ብታቀርብ ፥ በዚያም ፡ ወን
ድምህ ፡ አንዳች ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ እንዳለው ፡
፳፬ ብታስብ ፥ በዚያ ፡ በመሠዊያው ፡ ፊት ፡ መባህን ፡
ትተህ ፡ ሂድ ፥ አስቀድመህም ፡ ከወንድምህ ፡
ጋር ፡ ታረቅ ፥ በኋላም ፡ መጥተህ ፡ መባህን ፡
፳፭ አቅርብ ። አብረኸው ፡ በመንገድ ፡ሳለህ ፡ ከባለ
ጋራህ ፡ ጋር ፡ ፈጥነህ ፡ ተስማማ ፤ ባለጋራ ፡ ለዳኛ ፡
እንዳይሰጥህ ፡ ዳኛም ፡ ለሎሌው ፥ ወደ ፡ ወህ
፳፮ ኒም ፡ ትጣላለህ ፤ እውነት ፡ እልሃለሁ ፥ የመጨ
ረሻዋን ፡ ሳንቲም ፡ እስክትከፍል ፡ ድረስ ፡ ከቶ ፡
ከዚያ ፡ አትወጣም ።
፳፯ አታመንዝር ፡ እንደ ፡ ተባለ ፡ ሰምታችኋል ።

እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ፥ ወደ ፡ ሴት ፡ ያየ ፡ ሁሉ ፡ ፳፰
የተመኛትም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በልቡ ፡ ከእርስዋ ፡
ጋር ፡ አመንዝሮአል ። ቀኝ ፡ ዓይንህም ፡ ብታሰ ፳፱
ናክልህ ፡ አውጥተህ ፡ ከአንተ ፡ ጣላት ፡ ሙሉ ፡
ሰውነትህ ፡ በገሃነም ፡ ከሚጣል ፡ ይልቅ ፡ ከአካላ
ትህ ፡ አንድ ፡ ቢጠፋ ፡ ይሻልሃልና ። ቀኝ ፡ እጅ ፴
ህም ፡ ብታሰናክልህ ፡ ቈርጠህ ፡ ከአንተ ፡ ጣላት ፡
ሙሉ ፡ ሰውነትህ ፡ በገሃነም ፡ ከሚጣል ፡ ይልቅ ፡
ከአካላትህ ፡ አንድ ፡ ቢጠፋ ፡ ይሻላልና ።
ሚስቱን ፡ የሚፈታት ፡ ሁሉ ፡ የፍችዋን ፡ ፴፩
ጽሕፈት ፡ ይስጣት ፡ ተባለ ። እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋ ፴፪
ለሁ ፥ ያለ ፡ ዝሙት ፡ ምክንያት ፡ ሚስቱን ፡ የሚ
ፈታ ፡ ሁሉ ፡ አመንዝራ ፡ ያደርጋታል ፥ የተፈ
ታችውንም ፡ የሚያገባ ፡ ሁሉ ፡ ያመነዝራል ።
ደግሞ ፡ ለቀደሙት ፡— በውሸት ፡ አትማል ፡ ፴፫
ነገር ፡ ግን ፡ መሐላዎችህን ፡ ለጌታ ፡ ስጥ ፡ እንደ ፡
ተባለ ፡ ሰምታችኋል ። እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ፡ ፴፬
ከቶ ፡ አትማሉ ፤ በሰማይ ፡ አይሆንም ፡ የእግዚ
አብሔር ፡ ዙፋን ፡ ነውና ፡ በምድርም ፡ አይሆ ፴፭
ንም ፡ የእግሩ ፡ መረገጫ ፡ ናትና ፡ በኢየሩሳ
ሌምም ፡ አይሆንም ፡ የታላቁ ፡ ንጉሥ ፡ ከተማ ፡
ናትና ፤ በራስህም ፡ አትማል ፡ አንዲቱን ፡ ጠጕር ፡ ፴፮
ነጭ ፡ ወይም ፡ ጥቁር ፡ ልታደርግ ፡ አትችል
ምና ። ነገር ፡ ግን ፡ ቃላችሁ ፡ አዎን ፡ አዎን ፡ ፴፯
ወይም ፡ አይደለም ፡ አይደለም ፡ ይሁን ፡ ከነዚ
ህም ፡ የወጣ ፡ ከክፉው ፡ ነው ።
ዓይን ፡ ስለ ፡ ዓይን ፡ ጥርስም ፡ ስለ ፡ ጥርስ ፡ ፴፰
እንደ ፡ ተባለ ፡ ሰምታችኋል ። እኔ ፡ ግን ፡ እላች ፴፱
ኋለሁ ፥ ክፉውን ፡ አትቃወሙ ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ቀኝ ፡
ጕንጭህን ፡ በጥፊ ፡ ለሚመታህ ፡ ሁሉ ፡ ሁለተኛ
ውን ፡ ደግሞ ፡ አዙርለት ፡ እንዲከስህም ፡ እጀ ፡ ፵
ጠባብህንም ፡ እንዲወስድ ፡ ለሚወድ ፡ መጐናጸ
ፊያህን ፡ ደግሞ ፡ ተውለት ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ፵፩
ምዕራፍ ፡ ትሄድ ፡ ዘንድ ፡ ቢያስገድድህ ፡ ሁለ
ተኛውን ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ሂድ ። ለሚለምንህ ፡ ፵፪
ስጥ ፡ ከአንተም ፡ ይበደር ፡ ዘንድ ፡ ከሚወደው ፡
ፊቀቅ ፡ አትበል ።
ባልንጀራህን ፡ ውደድ ፡ ጠላትህንም ፡ ጥላ ፡ ፵፫
እንደ ፡ ተባለ ፡ ሰምታችኋል ። እኔ ፡ ግን ፡ እላች ፵፬:፵፭
ኋለሁ ፡ በሰማያት ፡ ላለ ፡ አባታችሁ ፡ ልጆች ፡
ትሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ጠላቶቻችሁን ፡ ውደዱ ፡ የሚ
ረግሙአችሁንም ፡ መርቁ ፥ ለሚጠሉአችሁም ፡
መልካም ፡ አድርጉ ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ፡
ጸልዩ ፤ እርሱ ፡ በክፉዎችና ፡ በበጎዎች ፡ ላይ ፡
ፀሐይን ፡ ያወጣልና ፡ በጻድቃንና ፡ በኃጢአተ
ኞችም ፡ ላይ ፡ ዝናቡን ፡ ያዘንባልና ። የሚወዱ ፵፮

አችሁን ፡ ብትወዱ ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ አላችሁ ? ቀራ
፵፯ ጮችስ ፡ ያንኑ ፡ ያደርጉ ፡ የለምን ? ወንድሞቻ
ችሁንም ፡ ብቻ ፡ እጅ ፡ ብትነሡ ፡ ምን ፡ ብልጫ ፡
ታደርጋላችሁ አሕዛብስ ፡ ያንኑ ፡ ያደርጉ ፡ የለ
፵፰ ምን ? እንግዲህ ፡ የሰማዩ ፡ አባታችሁ ፡ ፍጹም ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ እናንተ ፡ ፍጹማን ፡ ሁኑ ።

ምዕራፍ ፡ ፮ ።

፩ ለሰዎች ፡ ትታዩ ፡ ዘንድ ፡ ምጽዋታችሁን ፡
በፊታቸው ፡ እንዳታደርጉ ፡ ተጠንቀቁ ፤ ያለዚያ ፡
በሰማያት ፡ ባለው ፡ አባታችሁ ፡ ዘንድ ፡ ዋጋ ፡
የላችሁም ።
፪ እንግዲህ ፡ ምጽዋት ፡ ስታደርግ ፥ ግብዞች ፡
በሰው ፡ ዘንድ ፡ ሊከበሩ ፡ በምኵራብ ፡ በመንገ
ድም ፡ እንደሚያደርጉ ፡ በፊትህ ፡ መለከት ፡ አታ
ስነፋ ፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፥ ዋጋቸውን ፡ ተቀ
፫:፬ ብለዋል ። አንተ ፡ ግን ፡ ምጽዋት ፡ ስታደርግ ፡
ምጽዋትህ ፡ በስውር ፡ እንዲሆን ፡ ቀኝህ ፡ የም
ትሠራውን ፡ ግራህ ፡ አትወቅ ፡ በስውር ፡ የሚ
ያይ ፡ አባትህም ፡ በግልጥ ፡ ያስረክብሃል ።
፭ ስትጸልዩም ፡ እንደ ፡ ግብዞች ፡ አትሁኑ ፡
ለሰው ፡ ይታዩ ፡ ዘንድ ፡ በምኵራብና ፡ በመን
ገድ ፡ ማዕዘን ፡ ቆመው ፡ መጸለይን ፡ ይወዳሉና ፡
እውነት ፡ እላችኋለሁ ፥ ዋጋቸውን ፡ ተቀበለዋል ።
፮ አንተ ፡ ግን ፡ ስትጸልይ ፥ ወደ ፡ እልፍኝህ ፡ ግባ ፡
መዝጊያህንም ፡ ዘግተህ ፡ በስውር ፡ ላለው ፡ አባ
ትህ ፡ ጸልይ ፡ በስውር ፡ የሚያይ ፡ አባትህም ፡
በግልጥ ፡ ያስረክብሃል ።
፯ አሕዛብም ፡ በመናገራቸው ፡ ብዛት ፡ እንዲሰሙ ፡
ይመስላቸዋልና ፡ ስትጸልዩ ፡ እንደ ፡ እነርሱ ፡
፰ በከንቱ ፡ አትድገሙ ። ስለዚህ ፡ አትምሰሉአ
ቸው ፡ ሳትለምኑት ፡ አባታችሁ ፡ የሚያስፈልጋ
፱ ችሁን ፡ ያውቃልና ። እንግዲህ ፡ እናንተስ ፡ እን
ዲህ ፡ ጸልዩ ፡— በሰማያት ፡ የምትኖር ፡ አባታ
፲ ችን ፡ ሆይ ፥ ስምህ ፡ ይቀደስ ፤ መንግሥትህ ፡ ት
ምጣ ፤ ፈቃድህ ፡ በሰማይ ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ እንዲሁ ፡
፲፩ በምድር ፡ ትሁን ፤ የዕለት ፡ እንጀራችንን ፡ ዛሬ ፡
፲፪ ስጠን ፤ እኛም ፡ ደግሞ ፡ የበደሉንን ፡ ይቅር ፡
፲፫ እንደምንል ፡ በደላችንን ፡ ይቅር ፡ በለን ፤ ከክ
ፉም ፡ አድነን ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ፈተና ፡ አታግባን ፤
መንግሥት ፡ ያንተ ፡ ነውና ፡ ኃይልም ፡ ክብርም ፡
፲፬ ለዘለዓለሙ ፤ አሜን ። ለሰዎች ፡ ኃጢአታቸ
ውን ፡ ይቅር ፡ ብትሉ ፥ የሰማዩ ፤ አባታችሁ ፡ እና
፲፭ ንተን ፡ ደግሞ ፡ ይቅር ፡ ይላችኋልና ፤ ለሰዎች ፡
ግን ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ይቅር ፡ ባትሉ ፥ አባታ
ችሁም ፡ ኃጢአታችሁን ፡ ይቅር ፡ አይላችሁም ።
፲፮ ስትጦሙም ፥ እንደ ፡ ግብዞች ፡ አትጠውልጉ ፤
ለሰዎች ፡ እንደ ፡ ጦመኛ ፡ ሊታዩ ፡ ፊታቸውን ፡
ያጠፋሉና ፤ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፥ ዋጋቸውን ፡
፲፯:፲፰ ተቀብለዋል ። አንተ ፡ ግን ፡ ስትጦም ፥ በስውር ፡

ላለው ፡ አባትህ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ጦመኛ ፡ ለሰ
ዎች ፡ እንዳትታይ ፡ ራስህን ፡ ተቀባ ፡ ፊትህንም ፡
ታጠብ ፤ በስውር ፡ የሚያይ ፡ አባትህም ፡ በግልጥ ፡
ያስረክብሃል ።
ብልና ፡ ዝገት ፡ በሚያጠፉት ፡ ሌቦችም ፡ ቈፍ ፲፱
ረው ፡ በሚሠርቁት ፡ ዘንድ ፡ ለእናንተ ፡ በምድር ፡
ላይ ፡ መዝገብ ፡ አትሰብስቡ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ብልም ፡ ፳
ዝገትም ፡ በማያጠፉት ፡ ሌቦችም ፡ ቈፍረው ፡
በማይሠርቁት ፡ ዘንድ ፡ ለእናንተ ፡ በሰማይ ፡ መዝ
ገብ ፡ ሰብስቡ ፤ መዝገብህ ፡ ባለበት ፡ ልብህ ፡ ፳፩
ደግሞ ፡ በዚያ ፡ ይሆናልና ።
የሰውነት ፡ መብራት ፡ ዓይን ፡ ናት ። ዓይንህ ፡ ፳፪
እንግዲህ ፡ ጤናማ ፡ ብትሆን ፥ ሰውነትህ ፡ ሁሉ ፡
ብሩህ ፡ ይሆናል ፤ ዓይንህ ፡ ግን ፡ ታማሚ ፡ ብት ፳፫
ሆን ፥ ሰውነትህ ፡ ሁሉ ፡ የጨለመ ፡ ይሆናል ።
እንግዲህ ፡ በአንተ ፡ ያለው ፡ ብርሃን ፡ ጨለማ ፡
ከሆነ ፥ ጨለማውስ ፡ እንዴት ፡ ይበረታ !
ለሁለት ፡ ጌቶች ፡ መገዛት ፡ የሚቻለው ፡ ማንም ፡ ፳፬
የለም ፤ ወይም ፡ አንዱን ፡ ይጠላል ፡ ሁለተኛው
ንም ፡ ይወዳል ፤ ወይም ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ይጠ
ጋል ፡ ሁለተኛውንም ፡ ይንቃል ፤ ለእግዚአብ
ሔርና ፡ ለገንዘብ ፡ መገዛት ፡ አትችሉም ።
ስለዚህ ፡ እላችኋለሁ ፥ ስለ ፡ ነፍሳችሁ ፡ በምት ፳፭
በሉትና ፡ በምትጠጡት ፥ ወይም ፡ ስለ ፡ ሰው
ነታችሁ ፡ በምትለብሱት ፡ አትጨነቁ ፤ ነፍስ ፡
ከመብል ፡ ሰውነትም ፡ ከልብስ ፡ አይበልጥምን ?
ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወፎች ፡ ተመልከቱ ፤ አይዘሩም ፡ ፳፮
አያጭዱምም ፡ በጎተራም ፡ አይከቱም ፥ የሰማዩ ፡
አባታችሁም ፡ ይመግባቸዋል ፤ እናንተ ፡ ከእነ
ርሱ ፡ እጅግ ፡ አትበልጡምን ? ከእናንተ ፡ ተጨ ፳፯
ንቆ ፡ በቁመቱ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ መጨመር ፡
የሚችል ፡ ማን ፡ ነው ? ስለ ፡ ልብስስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ፳፰
ትጨነቃላችሁ ? የሜዳ ፡ አበቦች ፡ እንዴት ፡ እን
ዲያድጉ ፡ ልብ ፡ አድርጋችሁ ፡ ተመልከቱ ፤
አይደክሙም ፡ አይፈትሉምም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ፳፱
እላችኋለሁ ፥ ሰሎሞንስ ፡ እንኳ ፡ በክብሩ ፡ ሁሉ ፡
ከነዚህ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ አልለበሰም ። እግዚአብ ፴
ሔር ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ ያለውን ፡ ነገም ፡ ወደ ፡ እቶን ፡
የሚጣለውን ፡ የሜዳን ፡ ሣር ፡ እንዲህ ፡ የሚያ
ለብሰው ፡ ከሆነ ፥ እናንተ ፡ እምነት ፡ የጐደላችሁ ፡
እናንተንማ ፡ ይልቁን ፡ እንዴት ? እንግዲህ ፡— ፴፩
ምን ፡ እንበላለን ? ምንስ ፡ እንጠጣለን ? ምንስ ፡
እንለብሳለን ? ብላችሁ ፡ አትጨነቁ ፤ ይህንስ ፡ ፴፪
ሁሉ ፡ አሕዛብ ፡ ይፈልጋሉ ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ እንዲ
ያስፈልጋችሁ ፡ የሰማዩ ፡ አባታችሁ ፡ ያውቃ
ልና ። ነገር ፡ ግን ፡ አስቀድማችሁ ፡ የእግዚአብ ፴፫
ሔርን ፡ መንግሥት ፡ ጽድቁንም ፡ ፈልጉ ፥
ይህም ፡ ሁሉ ፡ ይጨመርላችኋል ።
ነገ ፡ ለራሱ ፡ ይጨነቃልና ፡ ለነገ ፡ አትጨነቁ ፤ ፴፬
ለቀኑ ፡ ክፋቱ ፡ ይበቃዋል ።

ምዕራፍ ፡ ፮ ።

፩ እንዳይፈረድባችሁ ፡ አትፍረዱ ። በምትፈ
ርዱበት ፡ ፍርድ ፡ ይፈረድባችኋልና ፡ በምት
ሰፍሩበትም ፡ መስፈሪያ ፡ ይሰፈርባችኋል ።
፫ በወንድምህም ፡ ዓይን ፡ ያለውን ፡ ጕድፍ ፡ ስለ
፬ ምን ፡ ታያለህ ፡ በዓይንህ ፡ ግን ፡ ያለውን ፡ ምሰሶ
ስለ ፡ ምን ፡ አትመለከትም ? ወይም ፡ ወንድም
ህን ፡— ከዓይንህ ፡ ጕድፍ ፡ ላውጣ ፡ ፍቀድልኝ ፡
እንዴትስ ፡ ትለዋለህ ? እነሆም ፡ በዓይንህ ፡
፭ ምሰሶ ፡ አለ ። አንተ ፡ ግብዝ ፡ አስቀድመህ ፡
ከዓይንህ ፡ ምሰሶውን ፡ አውጣ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡
ከወንድምህ ፡ ዓይን ፡ ጕድፉን ፡ ታወጣ ፡ ዘንድ ፡
አጥርተህ ፡ ታያለህ ።
፮ በእግራቸው ፡ እንዳይረግጡት ፡ ተመልሰ
ውም ፡ እንዳይነክሱአችሁ ፡ የተቀደሰውን ፡
ለውሾች ፡ አትስጡ ፡ ዕንቁቾችሁንም ፡ በእሪ
ያዎች ፡ ፊት ፡ አትጣሉ ።
፯ ለምኑ ፡ ይሰጣችሁማል ፤ ፈልጉ ፡ ታገኙማ
ላችሁ ፤ መዝጊያ ፡ እንኳኩ ፡ ይከፈትላችሁ
፰ ማል ። የሚለምነው ፡ ሁሉ ፡ ይቀበላልና ፡ የሚ
ፈልገውም ፡ ያገኛል ፡ መዝጊያንም ፡ ለሚያ
፱ ንኳኳ ፡ ይከፈትለታል ። ወይስ ፡ ከእናንተ ፡
ልጁ ፡ እንጀራ ፡ ቢለምነው ፡ ድንጋይ ፡ የሚሰ
፲ ጠው ፡ ከእናንተ ፡ ማን ፡ ሰው ፡ ነው ? ዓሣስ ፡
፲፩ ቢለምነው ፡ እባብን ፡ ይሰጠዋልን ? እንኪያስ ፡
እናንተ ፡ ክፉዎች ፡ ስትሆኑ ፡ ለልጆቻችሁ ፡
መልካም ፡ ስጦታ ፡ መስጠትን ፡ ከወዳቸችሁ ፡
በሰማያት ፡ ያለው ፡ አባታችሁ ፡ ለሚለምኑት ፡
እንዴት ፡ አብልጦ ፡ መልካም ፡ ነገርን ፡ ይሰ
፲፪ ጣቸው ? እንግዲህ ፡ ሰዎች ፡ ሊያደርጉላችሁ ፡
የምትወዱትን ፡ ሁሉ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እን
ዲሁ ፡ አድርጉላቸው ፤ ሕግም ፡ ነቢያትም ፡
ይህ ፡ ነውና ።
፲፫ በጠበበው ፡ ደጅ ፡ ግቡ ፤ ወደ ፡ ጥፋት ፡ የሚወ
ስደው ፡ ደጁ ፡ ሰፊ ፡ መንገዱም ፡ ትልቅ ፡ ነውና ፡
ወደ ፡ እርሱም ፡ የሚገቡ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ፤
፲፬ ወደ ፡ ሕይወት ፡ የሚወስደው ፡ ደጁ ፡ የጠበበ ፡
መንገዱም ፡ የቀጠነ ፡ ነውና ፡ የሚያገኙትም ፡
ጥቂቶች ፡ ናቸው ።
፲፭ የበግ ፡ ለምድ ፡ ለብሰው ፡ ከሚመጡባችሁ ፡
በውሥጣቸው ፡ ግን ፡ ነጣቂዎች ፡ ተኵላዎች ፡
፲፮ ከሆኑ ፡ ከሐሰተኞች ፡ ነቢያት ፡ ተጠንቀቁ ። ከፍ
ሪያቸው ፡ ታውቁቸዋላችሁ ። ከእሾህ ፡ ወይን ፡
፲፯ ከኩርንችትስ ፡ በለስ ፡ ይለቀማልን ? እንዲሁ ፡
መልካም ፡ ዛፍ ፡ ሁሉ ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ ያደር
ጋል ፡ ክፋም ፡ ዛፍ ፡ ክፉ ፡ ፍሬ ፡ ያደርጋል ።
፲፰ መልክም ፡ ዛፍ ፡ ክፉ ፡ ፍሬ ፡ ማፍራት ፡ ወይም
ክፉ ፡ ዛፍ ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ ማፍራት ፡ አይቻ
፲፱ ለውም ። መልካም ፡ ፍሬ ፡ የማያደርግ ፡ ዛፍ ፡
ሁሉ ፡ ይቈረጣል ፡ ወደ ፡ እሳትም ፡ ይጣላል ።
፳ ስለዚህም ፡ ከፍሬያቸው ፡ ታውቋቸዋላችሁ ።
፳፩ በሰማያት ፡ ያለውን ፡ የአባቴን ፡ ፈቃድ ፡ የሚ
ያደርግ ፡ እንጂ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ የሚ
ለኝ ፡ ሁሉ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚገባ ፡ አይ
፳፪ ደለም ። በዚያ ፡ ቀን ፡ ብዙዎች ፡— ጌታ ፡ ሆይ ፡
ጌታ ፡ ሆይ ፡ በስምህ ፡ ትንቢት ፡ አልተናገርን
ምን ፡ በስምህስ ፡ አጋንንትን ፡ አላወጣንምን ፡
በስምህስ ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ አላደረግንምን ?
፳፫ ይሉኛል ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡— ከቶ ፡ አላወቅኋ
ችሁም ፤ እናንተ ፡ ዓመፀኞች ፡ ከእኔ ፡ ራቁ ፡ ብዬ ፡
እመሰክርባቸዋለሁ ።
፳፬ ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ቃሌን ፡ ሰምቶ ፡ የሚያደር
ገው ፡ ሁሉ ፡ ቤቱን ፡ በዓለት ፡ ላይ ፡ የሠራ ፡
ልበም ፡ ሰውን ፡ ይመስላል ። ዝናብም ፡ ወረደ ፡
፳፭ ጐርፍም ፡ መጣ ፡ ነፋሱም ፡ ነፈሰ ፡ ያንም ፡ ቤት ፡
ገፋው ፡ በዓለት ፡ ላይም ፡ ስለ ፡ ተመሠረተ ፡ አል
ወደቀም ። ይህንም ፡ ቃሌን ፡ ሰምቶ ፡ የማያደር
ገው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ቤቱን ፡ በአሸዋ ፡ ላይ ፡ የሠራ ፡
፳፮ ሰነፍ ፡ ሰውን ፡ ይመስላል ። ዝናብም ፡ ወረደ ፡
ጐርፍም ፡ መጣ ፡ ነፋሱም ፡ ነፈሰ ፡ ያንም ፡ ቤት ፡
መታው ፡ ወደቀም ፡ አወዳደቁም ፡ ታላቅ ፡ ሆነ ።
፳፯ ኢየሱስም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በጨረሰ ፡ ጊዜ ፡
ሕዝቡ ፡ በትምህርቱ ፡ ተገረሙ ። እንደ ፡ ጸሮቻ
ቸው ፡ ሳይሆን ፡ እንደ ፡ ባለ ፡ ሥልጣን ፡ ያስተ
፳፰ ምራቸው ፡ ነበርና ።

ምዕራፍ ፡ ፰ ።

፩ ከተራራም ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተከ
፪ ተሉት ። እነሆም ፡ ለምጻም ፡ ቀርቦ ፡— ጌታ ፡
ሆይ ፡ ብትወድስ ፡ ልታነጻኝ ፡ ትችላለህ ፡ እያለ ፡
፫ ሰገደለት ። እጁንም ፡ ዘርግቶ ፡ ዳሰሰውና ፡— እወ
ዳለሁ ፡ ንጻ ፡ አለው ። ወዲያውም ፡ ለምጹ ፡ ነጻ ።
፬ ኢየሱስም ፡— ለማንም ፡ እንዳትናገር ፡ ተጠን
ቀቅ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሄደህ ፡ ራስህን ፡ ለካህን ፡ አሳይ ፡
ለእነርሱም ፡ ምስክር ፡ እንዲሆን ፡ ሙሴ ፡ ያዘዘ
፭ ውን ፡ መባ ፡ አቅርብ ፡ አለው ።
፮ ወደ ፡ ቅፍርናሆምም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ የመቶ ፡
፯ አለቃ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀርቦ ፡— ጌታ ፡ ሆይ ፡ ብላ
፰ ቴናዬ ፡ ሽባ ፡ ሆኖ ፡ እጅግ ፡ እየተሣቀየ ፡ በቤት ፡
ተኝቶአል ፡ ብሎ ፡ ለመነው ። ኢየሱስም ፡— እኔ ፡
፱ መጥቼ ፡ እፈውሰዋለሁ ፡ አለው ። የመቶ ፡ አለ
ቃውም ፡ መልሶ ፡— ጌታ ፡ ሆይ ፡ በቤቴ ፡ ጣሪ ፡
በታች ፡ ልትገባ ፡ አይገባኝም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ቃል ፡
፲ ብቻ ፡ ተናገር ፡ ብላቴናዬም ፡ ይፈወሳል ። እኔ ፡
ደግሞ ፡ ለሌሎች ፡ ተገዢ ፡ ነኝና ፡ ከእኔም ፡ በታች ፡
ጭፍራ ፡ አለኝ ፤ አንዱንም ፡— ሂድ ፡ ብለው ፡ ይሄ
ዳል ፡ ሌላውንም ፡— ና ፡ ብለው ፡ ይመጣል ፡ ባሪ
ያዬንም ፡— ይህን ፡ አድርግ ፡ ብለው ፡ ያደርጋል ፡
፲፩ አለው ። ኢየሱስም ፡ ሰምቶ ፡ ተደነቀና ፡ ለተከ
ተሉት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— እውነት ፡ አላችኋለሁ ፡
በእስራኤል ፡ እንኳ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ትልቅ ፡ እም
፲፪ ነት ፡ አላገኘሁም ። እላችኋለሁም ፡ ብዙዎች ፡
ከምሥራቅና ፡ ከምዕራብ ፡ ይመጣሉ ፡ ከአብርሃ
ምና ፡ ከይስሐቅ ፡ ከያዕቆብም ፡ ጋር ፡ በመንግ
ሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይቀመጣሉ ፡ የመንግሥት ፡
ልጆች ፡ ግን ፡ በውጭ ፡ ወደ ፡ አለው ፡ ጨለማ ፡
፲፫ ይጣላሉ ፤ በዚያ ፡ ልቅሶና ፡ ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡
ይሆናል ። ኢየሱስም ፡ ለመቶ ፡ አለቃ ፡— ሂድና ፡
እንዳመንህ ፡ ይሁንልህ ፡ አለው ። ብላቴናውም ፡
በዚያች ፡ ሰዓት ፡ ተፈወሰ ።
፲፬ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ አማ
፲፭ ቱን ፡ በንዳድ ፡ ታማ ፡ ተኝታ ፡ አያት ፡ እጅዋንም ፡
ዳሰሰ ፡ ንዳዱም ፡ ለቀቃት ፡ ተነሥታም ፡ አገለገ
፲፮፡፲፯ ለቻቸው ። በመሸም ፡ ጊዜ ፡ አጋንንት ፡ ያደረባቸ
ውን ፡ ብዙዎችን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አመጡ ፤ በነቢዩ ፡
በኢሳይያስ ፡— እርሱ ፡ ድካማችንን ፡ ተቀበለ ፡
ደዌያችንንም ፡ ተሸከመ ፡ የተባለው ፡ ይፈጸም ፡
፲፰ ዘንድ ፡ መናፍስትን ፡ በቃሉ ፡ አወጣ ፡ የታመ
ሙትንም ፡ ሁሉ ፡ ፈወሰ ።
፲፱ ኢየሱስም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሲከቡት ፡ አይቶ ፡
፳ ወደ ፡ ማዶ ፡ እንዲሻገሩ ፡ አዘዘ ። አንድ ፡ ጸሐፊም ፡
ቀርቦ ፡— መምህር ፡ ሆይ ፡ ወደምትሄድበት ፡
፳፩ ሁሉ ፡ እከተልሃለሁ ፡ አለው ። ኢየሱስም ፡— ለቀበሮዎች ፡ ጕድጓድ ፡ ለሰማይም ፡ ወፎች ፡
መሰፈሪያ ፡ አላቸው ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ግን ፡
፳፪ ራሱን ፡ የሚያስጠጋበት ፡ የለውም ፡ አለው ።
፳፫ ከደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ሌላው ፡— ጌታ ፡ ሆይ ፡
አስቀድሜ ፡ ልሂድና ፡ አባቴን ፡ እቀብር ፡ ዘንድ ፡
፳፬ ፍቀድልኝ ፡ አለው ። ኢየሱስም ፡— ተከተለኝ ፡
ሙታናቸውንም ፡ እንዲቀብሩ ፡ ሙታንን ፡ ተዋ
ቸው ፡ አለው ።
፳፭ ወደ ፡ ታንኳም ፡ ሲገባ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ተከ
፳፮ ተሉት ። እነሆም ፡ ማዕበሉ ፡ ታንኳይቱን ፡ እስ
ኪደፍናት ፡ ድረስ ፡ በባሕር ፡ ታላቅ ፡ መናወጥ ፡
፳፯ ሆነ ፤ እርሱ ፡ ግን ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ። ደቀ ፡ መዛሙ
ርቱም ፡ ቀርበው ፡— ጌታ ፡ ሆይ ፡ አድነን ፡ ጠፋን ፡
፳፰ እያሉ ፡ አስነሡት ። እርሱም ፡— እናንተ ፡ እም
ነት ፡ የጐደላችሁ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትፈራላችሁ ፡ ?
አላቸው ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተነሥቶ ፡ ነፋሱንና ፡
፳፱ ባሕሩን ፡ ገሠጸ ፡ ታላቅ ፡ ጸጥታም ፡ ሆነ ። ሰዎ
ቹም ፡— ነፋሱስና ፡ ባሕርስ ፡ ስንኳ ፡ ስለሚታዘዙ
ለት ፡ ይህ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ነው ? እያሉ ፡
ተደነቁ ።
፴ ወደ ፡ ማዶም ፡ ወደ ፡ ጌርጌሴኖን ፡ አገር ፡
፴፩ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ አጋንንት ፡ ያደሩባቸው ፡ ሁለት ፡
ሰዎች ፡ ከመቃብር ፡ ወጥተው ፡ ተገናኙት ፤ እነ
ርሱም ፡ ሰው ፡ በዚያ ፡ መንገድ ፡ ማለፍ ፡ አስከ
፴፪ ሳነው ፡ ድረስ ፡ እጅግ ፡ ክፉዎች ፡ ነበሩ ። እነ
ሆም ፡— ኢየሱስ ፡ ሆይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡
ከእንተ ፡ ጋር ፡ ምን ፡ አለን ? ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡
ልትሣቀየን ፡ ወደዚህ ፡ መጣህን ? እያሉ ፡ ጮሁ ።
፴፫ ከእነርሱም ፡ ርቆ ፡ የብዙ ፡ እሪያ ፡ መንጋ ፡ ይሰ
፴፬ ማራ ፡ ነበር ። አጋንንቱም ፡— ታወጣንስ ፡ እንደ
ሆንህ ፡ ወደ ፡ እሪያው ፡ መንጋ ፡ ስደደን ፡ ብለው ፡
ለመኑት ። ሂዱ ፡ አላቸው ። እነርሱም ፡ ወጥ
፴፱ ተው ፡ ወደ ፡ እሪያዎቹ ፡ ሄዱና ፡ ገቡ ፤ እነሆም ፡
የእሪያዎቹ ፡ መንጋ ፡ ሁሉ ፡ ከአፋፉ ፡ ወደ ፡
ባሕር ፡ እየተሣደፉ ፡ ሮጡ ፡ በውኃም ፡ ውስጥ ፡
ሞቱ ። እረኞችም ፡ ሸሹ ፡ ወደ ፡ ከተማይቱም ፡
ሄደው ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ አጋንንትም ፡ በእደሩባ
ቸው ፡ የሆኑትን ፡ አወሩ ። እነሆም ፡ ከተማው ፡
፴፬ ሁሉ ፡ ኢየሱስን ፡ ሊገናኝ ፡ ወጣ ፡ በዩትም ፡
ጊዜ ፡ ከአገራቸው ፡ እንዲሄድላቸው ፡ ለመኑት ።

ምዕራፍ ፡ ፱ ።

፩ በታንኳም ፡ ገብቶ ፡ ተሻገረና ፡ ወደ ፡ ገዛ ፡ ከተ
፪ ማው ፡ መጣ ። እነሆም ፡ በአልጋ ፡ የተኛ ፡ ሽባ ፡
ወደ ፡ እርሱ ፡ አመጡ ። ኢየሱስም ፡ እምነታቸ
ውን ፡ አይቶ ፡ ሽባውን ፡— አንተ ፡ ልጅ ፡ አይዞህ ፡
ኃጢአትህ ፡ ተሰረየችልህ ፡ አለው ። እነሆም ፡
፫ ከጸሮቹ ፡ አንዳንዱ ፡ በልባቸው ፡— ይህስ ፡ ይሳደ
፬ ባል ፡ አሉ ። ኢየሱስም ፡ አሳባቸውን ፡ አውቆ ፡ እን
፭ ዲህ ፡ አለ ፡— ስለ ፡ ምን ፡ በልባችሁ ፡ ክፉ ፡ ታስባላ
ችሁ ? ኃጢአትህ ፡ ተሰረየችልህ ፡ ከማለት ፡
፮ ወይስ ፡— ተነሣና ፡ ሂድ ፡ ከማለት ፡ ማናቸው ፡ ይቀ
ላል ? ነገር ፡ ግን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ኃጢአትን ፡
፯ ያስተሰርይ ፡ ዘንድ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ሥልጣን ፡
እንዳለው ፡ እንድታውቁ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሽባ
፰ ውን ፡— ተነሣ ፤ አልጋህን ፡ ተሸክመህ ፡ ወደ ፡
ቤትህ ፡ ሂድ ፡ አለው ። ተነሥቶም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡
፱ ሄደ ። ሕዝቡም ፡ አይተው ፡ ተደነቁ ፡ ለሰውም ፡
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ የሰጠ ፡ እግዚአብሔ
ርን ፡ አከበሩ ።
፲ ኢየሱስም ፡ ከዚያ ፡ አልፎ ፡ በመቅረጫው ፡
ተቀምጦ ፡ የነበረ ፡ ማቴዎስ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡
ሰው ፡ አየና ፡— ተከተለኝ ፡ አለው ። ተነሥ
ቶም ፡ ተከተለው ።

፲፤ በቤቱም ፡ በማዕድ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ÷ እነሆ ÷
ብዙ ፡ ቀራጮችና ፡ ኃጢአተኞች ፡ መጥተው ፡
ከኢየሱስና ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋር ፡ አብረው ፡
፲፩፤ ተቀመጡ ። ፈሪሳውያንም ፡ አይተው ፡ ደቀ ፡
መዛሙርቱን ፡— መምህራችሁ ፡ ከቀራጮችና ፡
ከኃጢአተኞች ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይበ
፲፪፤ ላል ? አሉአቸው ። ኢየሱስም ፡ ሰምቶ ፡— ሕመ
ምተኞች ፡ እንጂ ፡ ባለ ፡ ጤናዎች ፡ ባለ ፡ መድኃ
፲፫፤ ኒት ፡ አያስፈልጋቸውም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሄዳችሁ ፡—
ምሕረትን ፡ እወዳለሁ ፡ መሥዋዕትንም ፡ አይደ
ለም ፡ ያለው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተማሩ ፤ ኃጢ
አተኞችን ፡ ወደ ፡ ንስሐ ፡ እንጂ ፡ ጻድቃንን ፡
ልጠራ ፡ አልመጣሁምና ፡ አላቸው ።
፲፬፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የዮሐንስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡
ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀርበው ፡— እኛና ፡ ፈሪሳውያን ÷
ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የምንጦመው ÷ ደቀ ፡ መዛሙርትህ ፡
ግን ፡ የማይጦሙት ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ? አሉት ።
፲፭፤ ኢየሱስም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡— ሚዜዎች ፡
ሙሽራው ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ሳለ ፡ ሊያዝኑ ፡ ይች
ላሉን ? ነገር ፡ ግን ፡ ሙሽራው ፡ ከእነርሱ ፡ የሚ
ወሰድበት ፡ ወራት ፡ ይመጣል ÷ በዚያ ፡ ጊዜም ፡
፲፮፤ ይጦማሉ ። በአረጀ ፡ ልብስ ፡ አዲስ ፡ እራፊ ፡ የሚ
ያኖር ፡ የለም ፤ መጣፊያው ፡ ልብሱን ፡ ይቦጭቀ
፲፯፤ ዋልና ÷ መቀደዱም ፡ የባሰ ፡ ይሆናል ። በአረጀ ፡
አቁማዳ ፡ አዲስ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ የሚያኖር ፡
የለም ፤ ቢደረግ ፡ ግን ÷ አቁማዳው ፡ ይፈነዳል ÷
የወይን ፡ ጠጁም ፡ ይፈሳል ፡ አቁማዳውም ፡ ይጠ
ፋል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አዲሱን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ በአ
ዲስ ፡ አቁማዳ ፡ ያኖረዋል ÷ ሁለቱም ፡ ይጠባበ
ቃሉ ።
፲፰፤ ይህንም ፡ ሲነግራቸው ÷ አንድ ፡ መኰንን ፡
መጥቶ ፡— ልጄ ፡ አሁን ፡ ሞተች ፤ ነገር ፡ ግን ፡
መጥተህ ፡ እጅህን ፡ ጫንባት ÷ በሕይወትም ፡ ትኖ
፲፱፤ ራለች ፡ እያለ ፡ ሰገደለት ። ኢየሱስም ፡ ተነሥቶ ፡
፳፤ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋር ፡ ተከተለው ። እነሆም ÷
ከአሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ደም ፡ የሚ
ፈስሳት ፡ ሴት ፡ በኋላው ፡ ቀርባ ፡ የልብሱን ፡
፳፩፤ ጫፍ ፡ ዳሰሰች ፤ በልብዋ ፡— ልብሱን ፡ ብቻ ፡
የዳሰስሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ÷ እድናለሁ ፡ ትል ፡
፳፪፤ ነበረችና ። ኢየሱስም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ አያ
ትና ፡— ልጄ ፡ ሆይ ÷ አይዞሽ ፤ እምነትሽ ፡ አድኖ
ሻል ፡ አላት ። ሴቲቱም ፡ ከዚያች ፡ ሰዓት ፡
፳፫፤ ጀምራ ፡ ዳነች ። ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ መኰ
ንኑ ፡ ቤት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ÷ እምቢልተኞች
ንና ፡ የሚንጫጫውን ፡ ሕዝብ ፡ አይቶ ፡—
፳፬፤ ብላቴናይቱ ፡ ተኝታለች ፡ እንጂ ፡ አልሞተ
ችምና ፡ ፈቀቅ ፡ በሉ ፡ አላቸው ። በጣምም ፡
፳፭፤ ሳቁበት ። ሕዝቡን ፡ ግን ፡ ካስወጡ ፡ በኋላ ፡
ገብቶ ፡ እጅዋን ፡ ያዘት ÷ ብላቴናይቱም ፡ ተነሣች ።

ያም ፡ ዝና ፡ ወደዚያ ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ወጣ ። ፳፮፤
ኢየሱስም ፡ ከዚያ ፡ ሲያልፍ ፡ ሁለት ፡ ዕው ፳፯፤
ሮች ፡— የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ ማረን ፡ ብለው ፡
እየጮሁ ፡ ተከተሉት ። ወደ ፡ ቤትም ፡ በገባ ፡ ፳፰፤
ጊዜ ፡ ዕውሮቹ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀረቡ ÷ ኢየሱ
ስም ፡— ይህን ፡ ማድረግ ፡ እንድችል ፡ ታምናላ
ችሁን ? አላቸው ። አዎን ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ አሉት ።
በዚያን ፡ ጊዜ ፡— እንደ ፡ እምነታችሁ ፡ ይሁንላ ፳፱፤
ችሁ ፡ ብሎ ፡ ዓይኖቻቸውን ፡ ዳሰሰ ። ዓይኖቻቸ ፴፤
ውም ፡ ተከፈቱ ። ኢየሱስም ፡— ማንም ፡ እንዳ
ያውቅ ፡ ተጠንቀቁ ፡ ብሎ ፡ በብርቱ ፡ አዘዛቸው ።
እነርሱ ፡ ግን ፡ ወጥተው ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ፴፩፤
ስለ ፡ እርሱ ፡ አወሩ ።
እነርሱም ፡ ሲወጡ ፡ እነሆ ፡ ጋኔን ፡ ያደረበ ፴፪፤
ትን ፡ ዲዳ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አመጡ ። ጋኔ ፴፫፤
ኑንም ፡ ካወጣው ፡ በኋላ ፡ ዲዳው ፡ ተናገረ ።
ሕዝቡም ፡— እንዲህ ፡ ያለ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡
ከቶ ፡ አልታየም ፡ እያሉ ፡ ተደነቁ ። ፈሪሳውያን ፡ ፴፬፤
ግን ፡— በአጋንንት ፡ አለቃ ፡ አጋንንትን ፡ ያወ
ጣል ፡ አሉ ።
ኢየሱስም ፡ በምኵራቦቻቸው ፡ እያስተማረ ÷ ፴፭፤
የመንግሥትንም ፡ ወንጌል ፡ እየሰበከ ÷ በሕዝ
ብም ፡ ያለውን ፡ ደዌና ፡ ሕማም ፡ ሁሉ ፡ እየፈወሰ ÷
በከተማዎችና ፡ በመንደሮች ፡ ሁሉ ፡ ይዞር ፡ ነበር ።
ብዙ ፡ ሕዝብም ፡ ባየ ፡ ጊዜ ÷ እረኛ ፡ እንደ ፡ ሌላ ፴፮፤
ቸው ፡ በጎች ፡ ተጨንቀው ፡ ተጥለውም ፡ ነበ
ርና ፡ አዘነላቸው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛ ፴፯፤
ሙርቱን ፡— መከሩስ ፡ ብዙ ፡ ነው ÷ ሠራተኞች ፡
ግን ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ፤ እንግዲህ ፡ የመከሩን ፡ ፴፰፤
ጌታ ፡ ወደ ፡ መከሩ ፡ ሠራተኞች ፡ እንዲልክ ፡ ለም
ኑት ፡ አላቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፲ ።

አሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ወደ ፡ ፩፤
እርሱ ፡ ጠርቶ ÷ እንዲያወጡአቸው ፡ በርኵሳን ፡
መናፍስት ፡ ላይ ፡ ደዌንና ፡ ሕማምንም ፡ ሁሉ ፡
እንዲፈውሱ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጣቸው ። የአሥራ ፡ ፪፤
ሁለቱም ፡ ሐዋርያት ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ መጀ
መሪያው ፡ ጴጥሮስ ፡ የተባለው ፡ ስምዖን ፡ ወን
ድሙ ፡ እንድርያስም ÷ የዘብዴዎስ ፡ ልጅ ፡ ያዕ
ቆብም ፡ ወንድሙ ፡ ዮሐንስም ÷ ፊልጶስም ፡ በር ፫፤
ተሎሜዎስም ÷ ቶማስም ፡ ቀራጩ ፡ ማቴዎስም ÷
የእልፍዮስ ፡ ልጅ ፡ ያዕቆብም ፡ ታዴዎስም ፡
የተባለው ፡ ልብድዮስ ÷ ቀነናዊውም ፡ ስምዖን ፡ ፬፤
ደግሞም ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠው ፡ የአስቆሮቱ ፡
ይሁዳ ።
እነዚህን ፡ አሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ኢየሱስ ፡ ላካ ፭፤
ቸው ÷ አዘዛቸውም ÷ እንዲህም ፡ አለ ፡— በአሕ
ዛብ ፡ መንገድ ፡ አትሂዱ ÷ ወደ ፡ ሳምራውያንም ፡

፱፤ ፲፫ ፤ ሆሴ. ፮÷፮ ፤ ማቴ. ፲፪÷፯ ፤ ፲፰÷፲፩ ። ፲፰—፳፮ ፤ ማር. ፭÷፳፪—፵፫ ፤ ሉቃ. ፰÷፵፩÷፶፮ ። ፳ ፤ ዘሌ. ፲፭÷፳፭ ፤ ማር. ፫÷፲ ። ፳፪ ፤ ቍ. ፲፭ ። ፳፱ ፤ ምዕ. ፲፭÷፳፰ ። ፴ ፤ ምዕ. ፳÷፴ ። ፴፬ ፤ ምዕ. ፲፪÷፳፬ ፤ ማር. ፫÷፳፪ ፤ ሉቃ. ፲፩÷፲፭ ። ፴፭ ፤ ምዕ. ፬÷፳፫ ። ፴፮ ፤ ማር. ፮÷፴፬ ፤ ሕዝ. ፴፬÷፭ ። ፴፯ ፤ ሉቃ. ፲÷፪ ፤ ዮሐ. ፬÷፴፭ ።

፲፤ ፩ ፤ ማር. ፫÷፲፬ ፤ ፲፭ ፤ ሉቃ. ፱÷፩ ፤ ፪ ። ፪—፬ ፤ ምዕ. ፬÷፲፰ ፤ ፳፩ ፤ ፲፯÷፲፰ ፤ ዮሐ. ፩÷፵፫ ፤ ማር. ፫÷፲፯—፲፱ ፤ ሉቃ. ፮÷፲፬—፲፮ ፤ የሐዋ. ፩÷፲፫ ። ፭ ፤ ማር. ፮÷፯ ፤ ሉቃ. ፱÷፪ ።

፮፤ ከተማ ፡ አትግቡ ፤ ይልቅስ ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡
ወደሚሆኑ ፡ ወደ ፡ ጠፉት ፡ በጎች ፡ ሂዱ ፡ እንጂ ።
፯፤ ሄዳችሁም ፡— መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ቀርባለች ፡
፰፤ ብላችሁ ፡ ስበኩ ። ድውዮችን ፡ ፈውሱ ፡ ሙታ
ንን ፡ አስነሡ ፤ ለምጻሞችን ፡ አንጹ ፡ አጋንን
ትን ፡ አውጡ ፤ በከንቱ ፡ ተቀብላችሁ ÷ በከንቱ ፡
፱፤ ስጡ ። ወርቅ ፡ ወይም ፡ ብር ፡ ወይም ፡ ናስ ፡ በመ
፲፤ ቀነታችሁ ፡ ወይም ፡ ለመንገድ ፡ ከረጢት ፡
ወይም ፡ ሁለት ፡ እጀ ፡ ጠባብ ፡ ወይም ፡ ጫማ ፡
ወይም ፡ በትር ፡ አታግኙ ፤ ለሠራተኛ ፡ ምግቡ ፡
፲፩፤ ይገባዋልና ። በምትገቡባትም ፡ በማናቸይቱም ፡
ከተማ ፡ ወይም ፡ መንደር ፡ በዚያ ፡ የሚገባው ፡
ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በጥንቃቄ ፡ መርምሩ ፡ እስክት
፲፪፤ ወጡም ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ተቀመጡ ። ወደ ፡
፲፫፤ ቤትም ፡ ስትገቡ ፡ ሰላምታ ፡ ስጡ ፡ ቤቱም ፡ የሚ
ገባው ፡ ቢሆን ፡ ሰላማችሁ ፡ ይድረስለት ፡ ባይገ
፲፬፤ ባው ፡ ግን ፡ ሰላማችሁ ፡ ይመለስላችሁ ። ከማይ
ቀበላችሁም ፡ ቃላችሁንም ፡ ከማይሰሙ ፡ ሁሉ ÷
ከዚያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ከዚያች ፡ ከተማ ፡ ስት
፲፭፤ ወጡ ፡ የእግራችሁን ፡ ትቢያ ፡ አራግፉ ። እው
ነት ፡ እላችኋለሁ ÷ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ከዚያች ፡
ከተማ ፡ ይልቅ ፡ ለሰዶምና ፡ ለገሞራ ፡ አገር ፡ ይቀ
ልላቸዋል ።
፲፮፤ እነሆ ÷ እኔ ፡ እንደ ፡ በጎች ፡ በተኵላዎች ፡
መካከል ፡ እልካችኋለሁ ፤ ስለዚህ ፡ እንደ ፡ እባብ ፡
ልባሞች ፡ እንደ ፡ ርግብም ፡ የዋሆች ፡ ሁኑ ።
፲፯፤ ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሸንጎ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡአ
ችኋል ÷ በምኵራቦቻቸውም ፡ ይገርፉአችኋልና ፡
፲፰፤ ከሰዎች ፡ ተጠበቁ ፤ ለእነርሱና ፡ ለአሕዛብም ፡
ምስክር ፡ እንዲሆን ÷ ስለ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ገዢዎች ፡
፲፱፤ ወደ ፡ ነገሥታትም ፡ ትወሰዳላችሁ ። አሳልፈ
ውም ፡ ሲሰጡአችሁ ÷ የምትናገሩት ፡ በዚያች ፡
ሰዓት ፡ ይሰጣችኋልና ፡ እንዴት ፡ ወይስ ፡ ምን ፡
፳፤ እንድትናገሩ ፡ አትጨነቁ ፤ በእናንተ ፡ የሚናገር ፡
የአባታችሁ ፡ መንፈስ ፡ ነው ፡ እንጂ ÷ የምትና
፳፩፤ ገሩ ፡ እናንተ ፡ አይደላችሁምና ። ወንድምም ፡
ወንድሙን ፡ አባትም ፡ ልጁን ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡
ይሰጣል ÷ ልጆችም ፡ በወላጆቻቸው ፡ ላይ ፡ ይነ
፳፪፤ ሣሉ ፡ ይገድሉአቸውማል ። በሁሉም ፡ ስለ ፡ ስሜ ፡
የተጠላችሁ ፡ ትሆናላችሁ ፤ እስከ ፡ መጨረሻ ፡
፳፫፤ የሚጸና ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ ይድናል ። በአንዲቱ ፡
ከተማም ፡ መከራ ፡ ቢያሳዩአችሁ ፡ ወደ ፡ ሌላ
ይቱ ፡ ሽሹ ፤ እውነት ፡ እላችኋለሁና ÷ የሰው ፡
ልጅ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ የእስራኤልን ፡ ከተ
ማዎች ፡ አትዘልቁም ።
፳፬፤ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ከመምህሩ ÷ ባሪያም ፡ ከጌ
፳፭፤ ታው ፡ አይበልጥም ። ደቀ ፡ መዝሙር ፡ እንደ ፡

መምህሩ ፡ ባሪያም ፡ እንደ ፡ ጌታው ፡ መሆኑ ፡ ይበ
ቃዋል ። ባለቤቱን ፡ ብዔል ፡ ዜቡል ፡ ካሉት ፡ ቤተ ፡
ሰዎቹንማ ፡ እንዴት ፡ አብዝተው ፡ አይሉአቸው !
እንግዲህ ፡ አትፍሩአቸው ፡ የማይገለጥ ፡ የተ ፳፮፤
ከደነ ፡ የማይታወቅም ፡ የተሰወረ ፡ ምንም ፡ የለ
ምና ። በጨለማ ፡ የምነግራችሁን ፡ በብርሃን ፡ ፳፯፤
ተናገሩ ፤ በጆሮም ፡ የምትሰሙትን ፡ በሰገነት ፡
ላይ ፡ ስበኩ ። ሥጋንም ፡ የሚገድሉትን ፡ ነፍስን ፡ ፳፰፤
ግን ፡ መግደል ፡ የማይቻላቸውን ፡ አትፍሩ ፤ ይል
ቅስ ፡ ነፍስንም ፡ ሥጋንም ፡ በገሃነም ፡ ሊያጠፋ ፡
የሚቻለውን ፡ ፍሩ ። ሁለት ፡ ድንቢጦች ፡ በአ ፳፱፤
ምስት ፡ ሳንቲም ፡ ይሸጡ ፡ የለምን ? ከእነርሱም ፡
አንዲቱ ፡ ያለ ፡ አባታችሁ ፡ ፈቃድ ፡ በምድር ፡
ላይ ፡ አትወድቅም ። የእናንተስ ፡ የራሳችሁ ፡ ፴፤
ጠጕር ፡ ሁሉ ፡ እንኳ ፡ ተቈጥሮአል ። እንግዲህ ፡ ፴፩፤
አትፍሩ ፡ ከብዙ ፡ ድንቢጦች ፡ እናንተ ፡ ትበል
ጣላችሁ ። ስለዚህ ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ለሚመሰክር ፴፪፤
ልኝ ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በሰማያት ፡ ባለው ፡
በአባቴ ፡ ፊት ፡ እመሰክርለታለሁ ፤ በሰው ፡ ፴፫፤
ፊትም ፡ የሚክደኝን ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በሰ
ማያት ፡ ባለው ፡ በአባቴ ፡ ፊት ፡ እክደዋለሁ ።
በምድር ፡ ላይ ፡ ሰላምን ፡ ለማምጣት ፡ የመ ፴፬፤
ጣሁ ፡ አይምሰላችሁ ፤ ሰይፍን ፡ እንጂ ፡ ሰላምን ፡
ለማምጣት ፡ አልመጣሁም ። ሰውን ፡ ከአባቱ ÷ ፴፭፤
ሴት ፡ ልጅንም ፡ ከእናትዋ ÷ ምራትንም ፡ ከአማ
ትዋ ፡ እለያይ ፡ ዘንድ ፡ መጥቻለሁና ፤ ለሰውም ፡ ፴፮፤
ቤተ ፡ ሰዎቹ ፡ ጠላቶች ፡ ይሆኑበታል ። ከእኔ ፡ ፴፯፤
ይልቅ ፡ አባቱን ፡ ወይም ፡ እናቱን ፡ የሚወድ ፡
ለእኔ ፡ ሊሆን ፡ አይገባውም ፤ ከእኔ ፡ ይልቅም ፡
ወንድ ፡ ልጁን ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ የሚወድ ፡
ለእኔ ፡ ሊሆን ፡ አይገባውም ፤ መስቀሉንም ፡ የማ ፴፰፤
ይዝ ፡ በኋላዬም ፡ የማይከተለኝ ፡ ለእኔ ፡ ሊሆን ፡
አይገባውም ። ነፍሱን ፡ የሚያገኝ ፡ ያጠፋታል ÷ ፴፱፤
ነፍሱንም ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ የሚያጠፋ ፡ ያገኛታል ።
እናንተን ፡ የሚቀበል ፡ እኔን ፡ ይቀበላል ÷ እኔ ፵፤
ንም ፡ የሚቀበል ፡ የላከኝን ፡ ይቀበላል ። ነቢ ፵፩፤
ይን ፡ በነቢይ ፡ ስም ፡ የሚቀበል ፡ የነቢይን ፡ ዋጋ ፡
ይወስዳል ÷ ጻድቅንም ፡ በጻድቅ ፡ ስም ፡ የሚቀ
በል ፡ የጻድቁን ፡ ዋጋ ፡ ይወስዳል ። ማንም ፡ ከእነ ፵፪፤
ዚህ ፡ ከታናናሾቹ ፡ ለአንዱ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ጽዋ ፡ ውኃ ፡
ብቻ ፡ በደቀ ፡ መዝሙር ፡ ስም ፡ የሚያጠጣ ÷ እው
ነት ፡ እላችኋለሁ ÷ ዋጋው ፡ አይጠፋበትም ።

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

ኢየሱስም ፡ አሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ደቀ ፡ መዛሙር ፩፤
ቱን ፡ ማዘዝ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ በከተሞቻቸው ፡
ሊያስተምርና ፡ ሊሰብክ ፡ ከዚያ ፡ አለፈ ።

፲ ። ፯ ፤ ምዕ. ፫÷፪ ። ፱—፲፭ ፤ ማር. ፮÷፰—፲፩ ፤ ሉቃ. ፱÷፫—፭ ፤ ፲÷፬—፲፪ ። ፲፭ ፤ ምዕ. ፲፩÷፳፬ ። ፲፮ ፤ ሉቃ. ፲÷፫ ። ፲፯—፳፪ ፤ ማር. ፲፫÷፱—፲፫ ፤ ሉቃ. ፲፪÷፲፩ ፤ ፲፪ ፤ ፳፩÷፲፪—፲፱ ። ፳፪ ፤ ምዕ. ፳፬÷፱ ፤ ፲፫ ። ፳፬ ፤ ሉቃ. ፮÷፵ ፤ ዮሐ. ፲፫÷፲፮ ፤ ፲፭÷፳ ። ፳፭ ፤ ማር. ፫÷፳፪ ። ፳፮—፴፫ ፤ ማር. ፬÷፳፪ ፤ ሉቃ. ፰÷፲፯ ፤ ፲፪÷፪—፱ ። ፴፩ ፤ ምዕ. ፮÷፳፮ ። ፴፫ ፤ ሉቃ. ፬÷፳፮ ። ፴፬ ፤ ፴፭ ፤ ሉቃ. ፲፪÷፶፩ ፤ ፶፫ ። ፴፮ ፤ ሚክ. ፯÷፮ ። ፴፯ ፤ ሉቃ. ፲፬÷፳፮ ። ፴፰ ፤ ምዕ. ፲፮÷፳፬ ፤ ማር. ፰÷፴፬ ፤ ሉቃ. ፱÷፳፫ ፤ ፲፬÷፳፯ ። ፴፱ ፤ ምዕ. ፲፮÷፳፭ ፤ ማር. ፰÷፴፭ ፤ ሉቃ. ፱÷፳፬ ፤ ዮሐ. ፲፪÷፳፭ ። ፵ ፤ ምዕ. ፲፰÷፭ ፤ ማር. ፱÷፴፯ ፤ ሉቃ. ፱÷፵፰ ፤ ፲÷፲፮ ፤ ዮሐ. ፲፫÷፳ ። ፵፪ ፤ ምዕ. ፳፭÷፵ ፤ ማር. ፱÷፵፩ ።

፱ ዮሐንስም ፡ በወህኒ ፡ ሳለ ፡ የክርስቶስን ፡ ሥራ ፡ ሰምቶ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሁለት ፡ ላከና ፡— ፲ የሚመጣው ፡ አንተ ፡ ነህን ፡ ወይስ ፡ ሌላ ፡ እንጠብቅ ? አለው ። ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡— ሄዳችሁ ፡ ያያችሁትን ፡ የሰማችሁትንም ፡ ለዮሐንስ ፡ አውሩለት ፡ ፡ ፫ ዕውሮች ፡ ያያሉ ፡ አንካሶችም ፡ ይሄዳሉ ፡ ለምጻሞችም ፡ ይነጻሉ ፡ ደንቆሮችም ፡ ይሰማሉ ፡ ሙታንም ፡ ይነሣሉ ፡ ለድሆችም ፡ ወንጌል ፡ ይሰበክል ፣ ፭ በእኔም ፡ የማ ይሰናከለው ፡ ሁሉ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ።

፯ እነዚያም ፡ ሲሄዱ ፡ ኢየሱስ ፡ ለሕዝቡ ፡ ስለ ፡ ዮሐንስ ፡ ሊናገር ፡ ጀመረ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፡— ምን ፡ ልታዩ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወጣችሁ ? ፰ ነፋስ ፡ የሚወዘውዘውን ፡ ሸምበቆን ? ወይስ ፡ ምን ፡ ልታዩ ፡ ወጣችሁ ? ቀጭን ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ ሰውን ? እነሆ ፡ ቀጭን ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡ በንጉሥ ፡ ቤት ፡ አሉ ። ፱ ወይስ ፡ ምን ፡ ልታዩ ፡ ወጣችሁ ? ነቢይን ? አዎን ፡ እላችኋለሁ ፡ ከነቢይም ፡ የሚበልጠውን ።

፲ እነሆ ፡ መንገድህን ፡ በፊትህ ፡ የሚጠርግ ፡ መልክተኛዬን ፡ በፊትህ ፡ እልክለሁ ፡ ተብሎ ፡ የተጻፈለት ፡ ይህ ፡ ነውና ። ፲፩ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ ከሴቶች ፡ ከተወለዱት ፡ መካከል ፡ ከመጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፡ የሚበልጥ ፡ አልተነሣም ፤ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ግን ፡ ከሁሉ ፡ የሚያንሰው ፡ ይበልጠዋል ። ፲፪ ከመጥምቁም ፡ ከዮሐንስ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ትገፋለች ፡ ግፈኞችም ፡ ይናጠቋታል ። ፲፫ ነቢያት ፡ ሁሉና ፡ ሕጉ ፡ እስከ ፡ ዮሐንስ ፡ ድረስ ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ፤ ፲፬ ልትቀበሉትስ ፡ ብትወዱ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ኤልያስ ፡ ይህ ፡ ነው ። ፲፭ የሚሰማ ፡ ጆሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ።

፲፮ ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ትውልድ ፡ በምን ፡ እመስለዋለሁ ? በገበያ ፡ የሚቀመጡትን ፡ ልጆች ፡ ይመስላሉ ፡ እንርሱም ፡ ባልንጀሮቻቸውን ፡ እየጠሩ ፡— ፲፯ እንቢልታ ፡ ነፋንላችሁ ፡ ዘፈንም ፡ አልዘፈናችሁም ፤ ሙሾ ፡ አወጣንላችሁ ፡ ዋይ ፡ ዋይም ፡ አላላችሁም ፡ ይሉአቸዋል ። ፲፰ ዮሐንስ ፡ ሳይበላና ፡ ሳይጠጣ ፡ መጣ ፡ እንርሱም ፡— ጋኔን ፡ አለበት ፡ አሉት ። ፲፱ የሰው ፡ ልጅ ፡ እየበላና ፡ እየጠጣ ፡ መጣ ፡ እንርሱም ፡— እነሆ ፡ በላተኛና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጠጭ ፡ የቀራጮችና ፡ የኃጢአተኞች ፡ ወዳጅ ፡ ይሉታል ። ፲ ጥበብም ፡ በልጆችዋ ፡ ጸደቀች ።

፳ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሚበዙ ፡ ተአምራት ፡ የተደረገባቸውን ፡ ከተማዎች ፡ ንስሐ ፡ ስላልገቡ ፡ ሊነቅፋቸው ፡ ጀመረ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፡— ፳፩ ወዮልሽ ፡ ኮራዚ ፡ ወዮልሽ ፡ ቤተ ፡ ሰይዳ ፡ በእናንተ ፡ የተደረገው ፡ ተአምራት ፡ በጢሮስና ፡ በሲዶና ፡ ተደርጎ ፡ ቢሆን ፡ ማቅ ፡ ለብሰው ፡ አመድም ፡ ነስንሰው ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ንስሐ ፡ በገቡ ፡ ነበርና ። ፳፪ ነገር ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ከእናንተ ፡ ይልቅ ፡ ለጢሮስና ፡ ለሲዶና ፡ ይቀልላቸዋል ። ፳፫ አንቺም ፡ ቅፍርናሆም ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ከፍ ፡ አልሽን ? ወደ ፡ ሲኦል ፡ ትወርጃለሽ ፤ በአንቺ ፡ የተደረገው ፡ ተአምራት ፡ በሰዶም ፡ ተደርጎ ፡ ቢሆን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በኖረች ፡ ነበርና ። ፳፬ ነገር ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ከእንቺ ፡ ይልቅ ፡ ለሰዶም ፡ አገር ፡ ይቀልላታል ።

፳፭ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— አባት ፡ ሆይ ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ጌታ ፡ ይህን ፡ ከጥበበኞችና ፡ ከአስተዋዮች ፡ ሰውረህ ፡ ለሕፃናት ፡ ስለ ፡ ገለጥህላቸው ፡ አመሰግንሃለሁ ፡ ፳፮ አዎን ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ ፈቃድህ ፡ በፊትህ ፡ እንዲህ ፡ ሆኖአልና ። ፳፯ ሁሉ ፡ ከአባቴ ፡ ዘንድ ፡ ተሰጥቶኛል ፤ ከአብ ፡ በቀር ፡ ወልድን ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ፡ ከወልድም ፡ በቀር ፡ ወልድም ፡ ሊገለጥለት ፡ ከሚፈቅድ ፡ በቀር ፡ አብን ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ። ፳፰ እናንተ ፡ ደክሞች ፡ ሸክማችሁ ፡ የከበደ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ኑ ፡ እኔም ፡ አሳርፋችኋለሁ ። ፳፱ ቀንበሬን ፡ በላያችሁ ፡ ተሸከሙ ፡ ከእኔም ፡ ተማሩ ፡ እኔ ፡ የዋህ ፡ በልቤም ፡ ትሑት ፡ ነኝና ፡ ለነፍሳችሁም ፡ ዕረፍት ፡ ታገኛላችሁ ፡ ፴ ቀንበሬ ፡ ልዝብ ፡ ሸክሜም ፡ ቀሊል ፡ ነውና ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

፩ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ በእርሻ ፡ መካከል ፡ አለፈ ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ተራቡና ፡ እሸት ፡ ይቅጥፉ ፡ ይበሉም ፡ ጀመር ። ፪ ፈሪሳውያንም ፡ አይተው ፡— እነሆ ፡ ደቀ ፡ መዘሙርትህ ፡ በሰንበት ፡ ማድረግ ፡ ያልተፈቀደውን ፡ ያደርጋሉ ፡ አሉት ። ፫ እርሱ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡— ዳዊትና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡ በተራቡ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ ያደረገውን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ካህናትም ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ እርሱና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡ ሊበሉት ፡ ያልተፈቀደውን ፡ የመሥዋዕቱን ፡ ኅብስት ፡ እንደ ፡ በላ ፡ አላነበባችሁምን ? ፬ ካህናትም ፡ በሰንበት ፡ በመቅደስ ፡ ሰንበትን ፡ እንዲያረክሱ ፡ ኃጢአትም ፡ እንዳይሆንባቸው ፡ በሕጉ ፡ አላነበባችሁምን ? ፭ ነገር ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ፡ ከመቅደስ ፡ የሚበልጥ ፡ ከዚህ ፡ አለ ። ፮ ምሕረትን ፡ እወዳለሁ ፡ መሥዋዕትንም ፡ አይደለም ፡ ያለው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብታውቁስ ፡ ኃጢአት ፡ የሌለባቸውን ፡ ባለ ፡ ኩነኔ ፡ ባላደረጋችሁ ፡ ነበር ። ፰ የሰው ፡ ልጅ ፡ የሰንበት ፡ ጌታ ፡ ነውና ።

፱ ከዚያም ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ ምኵራባቸው ፡ ገባ ። ፲ እነሆም ፡ እጁ ፡ የሰለለት ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ይከሱትም ፡ ዘንድ ፡— ዘሰንበት ፡ መፈወስ ፡ ተፈቅዶአልን ? ብለው ፡ ጠየቁት ። ፲፩ እርሱ ፡ ግን ፡— ከእናንተ ፡ አንድ ፡ በግ ፡ ያለው ፡ በሰንበት ፡ በጉድጓድ ፡ ቢወድቅበት ፡ ይህ ፡ የማያወጣው ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነው ? ፲፪ እንግዲህ ፡ ሰው ፡ ከበግ ፡ ይልቅ ፡ እንደምን ፡ አይበልጥም ! ስለዚህ ፡ በሰንበት ፡ መልካም ፡ መሥራት ፡ ተፈቅዶአል ፡ አላቸው ። ፲፫ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ሰውየውን ፡— እጅህን ፡ ዘርጋ ፡ አለው ። ዘረጋትም ፡ እንደ ፡ ሁለተኛይቱም ፡ ደህና ፡ ሆነች ። ፲፬ ፈሪሳውያን ፡ ግን ፡ ወጥተው ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ እንዲያጠፉት ፡ ተማከሩ ፡ በት ።

፲፭ ኢየሱስም ፡ አውቆ ፡ ከዚያ ፡ ፈቀቅ ፡ አለ ። ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ተከተሉት ፡ ሁሉንም ፡ ፈወሰ ፡ ፲፮፡፲፯ ቸው ፡ እንዳይገልጡትም ፡ አዘዛቸው ፡ በነቢዩ ፡ በኢሳይያስ ፡ የተባለው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡—

፲፰ እነሆ ፡ የመረጥሁት ፡ ብላቴናዬ ፡ ነፍሴ ፡ ደስ ፡ የተሰኘችበት ፡ ወዳጄ ፡ መንፈሴን ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ አኖራለሁ ፡ ፍርድንም ፡ ለአሕዛብ ፡ ያወራል ። ፲፱ አይከራከርም ፡ አይጮህም ፡ አይሰሙም ፡ ድምፁንም ፡ በአደባባይ ፡ የሚሰማ ፡ የለም ። ፳ ፍርድን ፡ ድል ፡ ለመንሣት ፡ እስኪ ፡ ያወጣ ፡ የተቀጠቀጠን ፡ ሸምበቆ ፡ አይሰብርም ፡ የሚጤስን ፡ የጥዋፍ ፡ ክርም ፡ አያጠፋም ። ፳፩ አሕዛብም ፡ በስሙ ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋሉ ።

፳፪ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጋኔን ፡ ያደረበትን ፡ ዕውር ፡ ዲዳም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አመጡ ፡ ዕውሩም ፡ ዲዳውም ፡ እስኪያይና ፡ እስኪናገር ፡ ድረስ ፡ ፈወሰው ። ፳፫ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ተገረመና ፡— እንጂ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ይሆንን ? አሉ ። ፳፬ ፈሪሳውያን ፡ ግን ፡ ሰምተው ፡— ይህ ፡ በብዔል ፡ ዜቡል ፡ በአጋንንት ፡ አለቃ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አጋንንትን ፡ አያወጣም ፡ አሉ ። ፳፭ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ አሳባቸውን ፡ አውቆ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡— እርስ ፡ በርስዋ ፡ የምትለያይ ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ ትጠፋለች ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ የሚለያይ ፡ ከተማም ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ ቤት ፡ አይቆምም ። ፳፮ ሰይጣንም ፡ ሰይጣንን ፡ የሚያወጣ ፡ ከሆነ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ተለያየ ፡ እንግዲህ ፡ መንግሥቱ ፡ እንዴት ፡ ትቆማለች ? እኔስ ፡ በብዔል ፡ ዜቡል ፡ አጋንንትን ፡ የማወጣ ፡ ከሆንሁ ፡ ልጆቻችሁ ፡ በማን ፡ ያወጡአቸዋል ? ስለዚህ ፡ እነርሱ ፡ ፈራጆች ፡ ይሆኑባችሁ ። ፳፰ እኔ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ አጋንንትን ፡ የማወጣ ፡ ከሆንሁ ፡ እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ወደ ፡ እናንት ፡ ደርሳለች ። ፳፱ ወይስ ፡ ሰው ፡ እስቀድሞ ፡ ኃይለኛውን ፡ ሳያስር ፡ ወደ ፡ ኃይለኛው ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ እቃውን ፡ ሊነጥቀው ፡ እንዴት ፡ ይችላል ? ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ቤቱን ፡ ይበዘብዛል ። ፴ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ያልሆነ ፡ ይቃወመኛል ፤ ከእኔ ፡ ጋርም ፡ የማያከማች ፡ ይበትናል ። ፴፩ ስለዚህ ፡ እላችኋለሁ ፡ ኃጢአትና ፡ ስድብ ፡ ሁሉ ፡ ለሰዎች ፡ ይሰረይላቸዋል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ለሰደበ ፡ አይሰረይለትም ። ፴፪ በሰው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ቃል ፡ የሚናገር ፡ ሁሉ ፡ ይሰረይለታል ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ የማናገር ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በሚመጣው ፡ አይሰረይለትም ።

፴፫ ዛፉ ፡ ከፍሬዋ ፡ ትታወቃለችና ፡ ዛፉዋን ፡ መልካም ፡ ፍሬዋንም ፡ መልካም ፡ አድርጉ ፡ ወይም ፡ ዛፉዋን ፡ ክፉ ፡ ፍሬዋንም ፡ ክፉ ፡ አድርጉ ። እናንተ ፡ የእፉኝት ፡ ልጆች ፡ ክፉዎች ፡ ስትሆኑ ፡ መልካም ፡ ለመናገር ፡ እንዴት ፡ ትችላላችሁ ? በልብ ፡ ሞልቶ ፡ ከተረፈው ፡ አፍ ፡ ይናገራልና ። ፴፬ መልካም ፡ ሰው ፡ ከልቡ ፡ መልካም ፡ መዝገብ ፡ ያወጣል ፤ ክፉ ፡ ሰውም ፡ ከክፉ ፡ መዝገብ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ያወጣል ። ፴፭ እኔ ፡ እላችኋለሁ ፡ ሰዎች ፡ ስለሚናገሩት ፡ ስለ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ መልስ ፡ ይሰጡበታል ፤ ፴፮ ከቃልህ ፡ የተነሣ ፡ ትጸድቃለህና ፡ ከቃልህም ፡ የተነሣ ፡ ትኰነናለህ ።

፴፯ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከጸሮችና ፡ ከፈሪሳውያን ፡ አንዳንዶቹ ፡ መለሱና ፡— መምህር ፡ ሆይ ፡ ከአንተ ፡ ምልክት ፡ እንድናይ ፡ እንወዳለን ፡ አሉ ። ፴፰ እርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡— ክፋና ፡ አመንዝራ ፡ ትውልድ ፡ ምልክት ፡ ይሻል ፡ ከነቢዩም ፡ ዘካርያስ ፡ ምልክት ፡ በቀር ፡ ምልክት ፡ አይሰጠውም ። ፴፱ ዮናስ ፡ በዓሣ ፡ አንባሪ ፡ ሆድ ፡ ሦስት ፡ ቀንና ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንዲሁ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በምድር ፡ ልብ ፡ ሦስት ፡ ቀንና ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ ይኖራል ። ፵ የነነዌ ፡ ሰዎች ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ ትውልድ ፡ ጋር ፡ ተነሥተው ፡ ይፈርዱበታል ፤ በዮናስ ፡ ስብከት ፡ ንስሐ ፡ ገብተዋልና ፡ እነሆም ፡ ከዮናስ ፡ የሚበልጥ ፡ ከዚህ ፡ አለ ። ፵፩ ንግሥተ ፡ ዓዜብ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ ትውልድ ፡ ጋር ፡ ተነሥታ ፡ ትፈርድበታለች ፤ የሰሎሞንን ፡ ጥበብ ፡ ለመስማት ፡ ከምድር ፡ ዳር ፡ መጥታለችና ፡ እነሆም ፡ ከሰሎሞን ፡ የሚበልጥ ፡ ከዚህ ፡ አለ ።

፵፪ ርኩስ ፡ መንፈስ ፡ ግን ፡ ከሰው ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ዕረፍት ፡ እየፈለገ ፡ ውኃ ፡ በሌለበት ፡ ቦታ ፡ ያልፋል ፡ አያገኝምም ። ፵፫ በዚያን ፡ ጊዜም ፡— ወደ ፡ ኋላ ። እኔ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ አጋንንትን ፡ የማወጣ ፡ ከሆንሁ ፡ እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ወደ ፡ እናንት ፡ ደርሳለች ። ፳፰ ወይስ ፡ ሰው ፡ እስቀድሞ ፡ ኃይለኛውን ፡ ሳያስር ፡ ወደ ፡ ኃይለኛው ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ እቃውን ፡ ሊነጥቀው ፡ እንዴት ፡ ይችላል ? ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ቤቱን ፡ ይበዘብዛል ። ፳፱ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ያልሆነ ፡ ይቃወመኛል ፤ ከእኔ ፡ ጋርም ፡ የማያከማች ፡ ይበትናል ። ፴ ስለዚህ ፡ እላችኋለሁ ፡ ኃጢአትና ፡ ስድብ ፡ ሁሉ ፡ ለሰዎች ፡ ይሰረይላቸዋል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ለሰደበ ፡ አይሰረይለትም ። ፴፩ በሰው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ቃል ፡ የሚናገር ፡ ሁሉ ፡ ይሰረይለታል ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ የማናገር ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በሚመጣው ፡ አይሰረይለትም ።

፴፫ ዛፉ ፡ ከፍሬዋ ፡ ትታወቃለችና ፡ ዛፉዋን ፡ መልካም ፡ ፍሬዋንም ፡ መልካም ፡ አድርጉ ፡ ወይም ፡ ዛፉዋን ፡ ክፉ ፡ ፍሬዋንም ፡ ክፉ ፡ አድርጉ ። እናንተ ፡ የእፉኝት ፡ ልጆች ፡ ክፉዎች ፡ ስትሆኑ ፡ መልካም ፡ ለመናገር ፡ እንዴት ፡ ትችላላችሁ ? በልብ ፡ ሞልቶ ፡ ከተረፈው ፡ አፍ ፡ ይናገራልና ። ፴፬ መልካም ፡ ሰው ፡ ከልቡ ፡ መልካም ፡ መዝገብ ፡ ያወጣል ፤ ክፉ ፡ ሰውም ፡ ከክፉ ፡ መዝገብ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ያወጣል ። ፴፭ እኔ ፡ እላችኋለሁ ፡ ሰዎች ፡ ስለሚናገሩት ፡ ስለ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ መልስ ፡ ይሰጡበታል ፤ ፴፮ ከቃልህ ፡ የተነሣ ፡ ትጸድቃለህና ፡ ከቃልህም ፡ የተነሣ ፡ ትኰነናለህ ።

፴፯ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከጸሮችና ፡ ከፈሪሳውያን ፡ አንዳንዶቹ ፡ መለሱና ፡— መምህር ፡ ሆይ ፡ ከአንተ ፡ ምልክት ፡ እንድናይ ፡ እንወዳለን ፡ አሉ ። ፴፰ እርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡— ክፋና ፡ አመንዝራ ፡ ትውልድ ፡ ምልክት ፡ ይሻል ፡ ከነቢዩም ፡ ዘካርያስ ፡ ምልክት ፡ በቀር ፡ ምልክት ፡ አይሰጠውም ። ፴፱ ዮናስ ፡ በዓሣ ፡ አንባሪ ፡ ሆድ ፡ ሦስት ፡ ቀንና ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንዲሁ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በምድር ፡ ልብ ፡ ሦስት ፡ ቀንና ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ ይኖራል ። ፵ የነነዌ ፡ ሰዎች ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ ትውልድ ፡ ጋር ፡ ተነሥተው ፡ ይፈርዱበታል ፤ በዮናስ ፡ ስብከት ፡ ንስሐ ፡ ገብተዋልና ፡ እነሆም ፡ ከዮናስ ፡ የሚበልጥ ፡ ከዚህ ፡ አለ ። ፵፩ ንግሥተ ፡ ዓዜብ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ ትውልድ ፡ ጋር ፡ ተነሥታ ፡ ትፈርድበታለች ፤ የሰሎሞንን ፡ ጥበብ ፡ ለመስማት ፡ ከምድር ፡ ዳር ፡ መጥታለችና ፡ እነሆም ፡ ከሰሎሞን ፡ የሚበልጥ ፡ ከዚህ ፡ አለ ።

ወጣሁበት ፡ ቤቴ ፡ እመለሳለሁ ፡ ይላል ፡ ዘመ
ጣም ፡ ብዶ ፡ ሆኖ ፡ ተጠርጎና ፡ አጊጦ ፡ ያገኘ
ዋል ። ከዘያ ፡ ወዲያ ፡ ይሄይና ፡ ከእርሱ ፡ የከፉ
ትን ፡ ሰባት ፡ ሌሎችን ፡ እጋንንት ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡
ይወስዳል ፡ ገብተውም ፡ በዚያ ፡ ይኖራሉ ፡ ለዚ
ያም ፡ ሰው ፡ ከፊተኛው ፡ ይልቅ ፡ የኋለኛው ፡
ይብስበታል ። ለዚህ ፡ ክፉ ፡ ትውልድ ፡ ደግሞ ፡
እንዲሁ ፡ ይሆንበታል ።

ገና ፡ ለሕዝቡ ፡ ሲናገር ፡ እነሆ ፡ እናቱና ፡
ወንድሞቹ ፡ ሊነጋገሩት ፡ ፈልገው ፡ በውጭ ፡
ቆመው ፡ ነበር ። አንዱም ፦— እነሆ ፡ እናትህና ፡
ወንድሞችህ ፡ ሊነጋገሩህ ፡ ፈልገው ፡ በውጭ ፡
ቆመዋል ፡ አለው ። እርሱ ፡ ግን ፡ ለነገረው ፡
መልሶ ፦— እናቴ ፡ ማን ፡ ናት ? ወንድሞቼስ ፡ እነ፡
ማን ፡ ናቸው ? አለው ። እጁንም ፡ ወደ ፡ ደቀ ፡
መዛሙርቱ ፡ ዘርግቶ ፦—እነሆ ፡ እናቴና ፡ ወንድ
ሞቼ ፡ በሰማያት ፡ ያለውን ፡ የአባቴን ፡ ፈቃድ ፡
የሚያደርግ ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ ወንድሜ ፡ እኅቴም ፡
እናቴም ፡ ነውና ፡ አለ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

በዚያን ፡ ቀን ፡ ኢየሱስ ፡ ከቤት ፡ ወጥቶ ፡ በባ
ሕር ፡ አጠገብ ፡ ተቀመጠ ። እርሱም ፡ በታንኳ ፡
ገብቶ ፡ እስኪቀመጥ ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወደ
እርሱ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ በወደቡ ፡
ቆመው ፡ ነበር ። በምሳሌም ፡ ብዙ ፡ ነገራቸው ፡
እንዲህም ፡ አላቸው ፡—እነሆ ፡ ዘሪ ፡ ሊዘራ ፡ ወጣ ።
እርሱም ፡ ሲዘራ ፡ አንዳንዱ ፡ በመንገድ ፡ ዳር ፡
ወደቀ ፥ ወፎችም ፡ መጥተው ፡ በሉት ። ሌላ
ውም ፡ ብዙ ፡ መሬት ፡ በሌለበት ፡ በጭንጫ ፡
ላይ ፡ ወደቀ ፡ ጥልቅ ፡ መሬትም ፡ ስላልነበረው ፡
ወዲያው ፡ በቀለ ፡ ፀሐይ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡
ጠወለገ ፥ ሥርም ፡ ስላልነበረው ፡ ደረቀ ። ሌላ
ውም ፡ በእሾህ ፡ መካከል ፡ ወደቀ ፡ እሾህም ፡
ወጣና ፡ አነቀው ። ሌላውም ፡ በመልካም ፡
መሬት ፡ ወደቀ ፡ አንዱም ፡ መቶ ፡ አንዱም ፡
ዅሳ ፡ አንዱም ፡ ሠላሳ ፡ ፍሬ ፡ ሰጠ ። የሚሰማ ፡
ጆሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ።

ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ቀርበው ፡ ፦ ስለ ፡ ምን ፡
በምሳሌ ፡ ትነግራቸዋለህ ? አሉት ። እርሱም ፡
መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦— ለእናንተ ፡ የመን
ግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ምሥጢር ፡ ማወቅ ፡ ተሰጥ
ቶአችኋል ፥ ለእነርሱ ፡ ግን ፡ አልተሰጣቸውም ።
ላለው ፡ ይሰጠዋልና ፡ ይበዛለትማል ፡ ከሌለው ፡
ግን ፡ ያው ፡ ያለው ፡ እንኳ ፡ ይወሰድበታል ።
ስለዚህ ፡ እያዩ ፡ ስለማያዩ ፡ እየሰሙም ፡ ስለማ
ይሰሙ ፡ ስለማያስተውሉም ፡ በምሳሌ ፡ እነግራ
ቸዋለሁ ።

መስማት ፡ ትሰማላችሁና ፡ አታስተውሉም ፡
ማየትም ፡ ታያላችሁና ፡ አትመለከቱም ።
በዓይናቸው ፡ እንዳያዩ ፡ በጆሮአቸውም ፡
እንዳይሰሙ ፥ በልባቸውም ፡ እንዳያስተ
ውሉ ፡ ተመልሰውም ፡ እንዳልፈውሳቸው ፡
የዘህ ፡ ሕዝብ ፡ ልብ ፡ ደንድኖአልና ፡ ጆሮ
አቸውም ፡ ደንቁሮአል ፡ ዓይናቸውንም ፡
ጨፍነዋል ፡
የሚል ፡ የኢሳይያስ ፡ ትንቢት ፡ በእነርሱ ፡ ይፈጸ
ማል ። የእናንተ ፡ ግን ፡ ዓይኖቻችሁ ፡ ስለማያዩ ፡
ጆሮቻችሁም ፡ ስለሚሰሙ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ።
እውነት ፡ አላችኋለሁ ፥ ብዙዎች ፡ ነቢያትና ፡ ጻድ
ቃን ፡ የምታዩትን ፡ ሊያዩ ፡ ተመኝተው ፡ አላ
ዩም ፥ የምትሰሙትንም ፡ ሊሰሙ ፡ ተመኝተው ፡
አልሰሙም ።

እንግዲህ ፡ እናንተ ፡ የዘሪውን ፡ ምሳሌ ፡ ስሙ ።
የመንግሥትን ፡ ቃል ፡ ሰምቶ ፡ በማያስተውል ፡
ሁሉ ፡ ክፉው ፡ ይመጣል ፡ በልቡ ፡ የተዘራው
ንም ፡ ይነዋቃል ፡ በመንገድ ፡ ዳር ፡ የተዘራው ፡
ይህ ፡ ነው ። በጭንጫ ፡ ላይ ፡ የተዘራውም ፡ ይህ ፡
ቃሉን ፡ ሰምቶ ፡ ወዲያው ፡ በደስታ ፡ የሚቀበ
ለው ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለጊዜው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
በእርሱ ፡ ሥር ፡ የለውም ፡ በቃሉ ፡ ምክንያትም ፡
መከራ ፡ ወይም ፡ ስደት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ወዲያው ፡
ይሰናከላል ። በእሾህ ፡ መካከል ፡ የተዘራውም ፡
ይህ ፡ ቃሉን ፡ የሚሰማ ፡ ነው ፥ የዚህም ፡ ዓለም ፡
አሳብና ፡ የባለጠግነት ፡ መታለል ፡ ቃሉን ፡ ያን
ቃል ፥ የማያፈራም ፡ ይሆናል ። በመልካም ፡
መሬት ፡ የተዘራውም ፡ ይህ ፡ ቃሉን ፡ ሰምቶ ፡
የሚያስተውል ፡ ነው ፡ እርሱም ፡ ፍሬ ፡ ያፈራል ፡
አንዱም ፡ መቶ ፡ አንዱም ፡ ስድሳ ፡ አንዱም ፡
ሠላሳ ፡ ያፈርያል ።

ሌላ ፡ ምሳሌ ፡ አቀረበላቸው ፡ እንዲህም ፡
አለ ፦— መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ በእርሻው ፡ መል
ካም ፡ ዘርን ፡ የዘራን ፡ ሰው ፡ ትመስላለች ። ሰዎቹ ፡
ሲተኙ ፡ ግን ፡ ጠላቱ ፡ መጣና ፡ በስንዴው ፡ መካ
ከል ፡ እንክርዳድ ፡ ዘርቶ ፡ ሄደ ። ስንዴውም ፡
በበቀለና ፡ በአፈራ ፡ ጊዜ ፡ እንክርዳዱ ፡ ደግሞ ፡
ያን ፡ ጊዜ ፡ ታየ ። የበለጌቱም ፡ ባሮች ፡ ቀር
በው ፡—ጌታ ፡ ሆይ ፥ መልካምን ፡ ዘር ፡ በእርሻህ ፡
ዘርተህ ፡ አልነበርህምን ? እንክርዳዱንስ ፡ ከወ
ዴት ፡ አገኘ ? አሉት ። እርሱም ፡— ጠላት ፡
ይህን ፡ አደረገ ፡ አላቸው ። በሮቹም ፡ ፡— እንግ
ዲህ ፡ ሄደን ፡ ብንለቅመው ፡ ትወዳለህን ? አሉት ።
እርሱ ፡ ግን ፡— እንክርዳዱን ፡ ስትለቅሙ ፡ ስን
ዴውን ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ እንዳትነቅሉት ፡ አይሆ
ንም ። ተዉአቸው ፡ እስከ ፡ መከር ፡ ጊዜ ፡ አብ
ረው ፡ ይደጉ ፡ በመከር ፡ ጊዜም ፡ አጫጆችን ፡—
እንክርዳዱን ፡ አስቀድማችሁ ፡ ልቀሙ ፡ በእሳ
ትም ፡ ለማቃጠል ፡ በየነዶው ፡ እሰሩ ፥ ስንዴ
ውን ፡ ግን ፡ በጎተራዬ ፡ ክተቱ ፡ እላለሁ ፡ አለ ።

ሌላ ፡ ምሳሌ ፡ አቀረበላቸው ፡ እንዲህም ፡
አለ ፦— መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ሰው ፡ መስዶ ፡ በእ
ርሻው ፡ የዘራትን ፡ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ትመ
ስላለች ። እርስዋም ፡ ከዘር ፡ ሁሉ ፡ ታንሳለች ፥
በእደጎች ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ከአታክልቶች ፡ ትበል
ጣለች ፡ የሰማይም ፡ ወፎች ፡ መጥተው ፡ በቅርን
ጫፎችዋ ፡ እስኪሰፍሩ ፡ ድረስ ፡ ባሳና ፡ ትባሳናለች ።

ሌላ ፡ ምሳሌ ፡ ነገራቸው ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦—
መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ሰው ፡ እስኪበ ፡ ድረስ ፡
ሴት ፡ መስዳ ፡ በሦስት ፡ መስፈሪያ ፡ ዱቄት ፡ የሸ
ሸገችውን ፡ እርሾ ፡ ትመስላለች ።

ኢየሱስም ፡ ለሕዝቡ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ በምሳሌ ፡
ተናገረ ፤ በነቢዩም ፡—

በምሳሌ ፡ አፌን ፡ እከፍታለሁ ፡ ዓለም ፡ ከተ
ፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ የተሰወረውንም ፡ እናገራ
ለሁ ፡

የተባለው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ያለ ፡ ምሳሌ ፡ አል
ተናገራቸውም ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡
ገባ ። ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀር
በው ፡— የእርሻውን ፡ እንክርዳድ ፡ ምሳሌ ፡ ተር
ጉምልን ፡ አሉት ። እርሱም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡
አላቸው ፡—መልካምን ፡ ዘር ፡ የዘራው ፡ የሰው ፡
ልጅ ፡ ነው ፤ እርሻውም ፡ ዓለም ፡ ነው ፡ መልካ
ሙም ፡ ዘር ፡ የመንግሥት ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፡
እንክርዳዱም ፡ የክፉው ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፥ የዘራ
ውም ፡ ጠላት ፡ ዲያብሎስ ፡ ነው ፡ መከሩም ፡ የዓ
ለም ፡ መጨረሻ ፡ ነው ፥ አጫጆችም ፡ መላእክት ፡
ናቸው ። እንግዲህ ፡ እንክርዳድ ፡ ተለቅሞ ፡ በእ
ሳት ፡ እንደሚቃጠል ፥ በዓለም ፡ መጨረሻ ፡ እን
ዲሁ ፡ ይሆናል ። የሰው ፡ ልጅ ፡ መላእክቱን ፡
ይልክል ፥ ከመንግሥቱም ፡ እንቅፋትን ፡ ሁሉ ፡
ዓመፃንም ፡ የሚያደርጉትን ፡ ይለቅማሉ ፥ ወደ ፡
እቶን ፡ እሳትም ፡ ይጥሉአቸዋል ። በዚያ ፡ ልቅ
ሶና ፡ ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ይሆናል ። በዚያን ፡
ጊዜ ፡ ጻድቃን ፡ በአባታቸው ፡ መንግሥት ፡
እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ይበራሉ ። የሚሰማ ፡ ጆሮ ፡
ያለው ፡ ይስማ ።

ደግሞ ፡ መንግሥት ፡ ሰማያት ፡ በእርሻ ፡
ውስጥ ፡ የተሰወረን ፡ መዝገብ ፡ ትመስላለች ፥
ሰው ፡ አግኝቶ ፡ ሰወረው ፥ ከደስታውም ፡ የተ
ነሣ ፡ ሄዶ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ሸጠና ፡ ያን ፡ እርሻ ፡
ገዛ ።

ደግሞ ፡ መንግሥት ፡ ሰማያት ፡ መልካምን ፡
ዕንቁ ፡ የሚሻ ፡ ነጋዴን ፡ ትመስላለች ፤ ዋጋውም ፡
እጅግ ፡ የበዛ ፡ አንዲት ፡ ዕንቁ ፡ በአገኘ ፡ ጊዜ ፡
ሄዶ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ሸጠና ፡ ገዛት ።

ደግሞ ፡ መንግሥት ፡ ሰማያት ፡ ወደ ፡ በሕር ፡ የተ
ጣለች ፡ ከሁሉም ፡ ዓይነት ፡ የሰበሰበች ፡ መረብን ፡
አለ ፡—መንግሥት ፡ ሰማያት ፡ ሰው ፡ መስዶ ፡ በእ
ርሻው ፡ የዘራትን ፡ የስናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ትመ
ስላለች ። እርስዋም ፡ ከዘር ፡ ሁሉ ፡ ታንሳለች ፥
በእደጎች ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ከአታክልቶች ፡ ትበል
ጣለች ፡ የሰማይም ፡ ወፎች ፡ መጥተው ፡ በቅርን
ጫፎችዋ ፡ እስኪሰፍሩ ፡ ድረስ ፡ ባሳና ፡ ትባሳናለች ።

ሌላ ፡ ምሳሌ ፡ ነገራቸው ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦—
መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ሰው ፡ እስኪበ ፡ ድረስ ፡
ሴት ፡ መስዳ ፡ በሦስት ፡ መስፈሪያ ፡ ዱቄት ፡ የሸ
ሸገችውን ፡ እርሾ ፡ ትመስላለች ።

ኢየሱስም ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ለሕዝቡ ፡ በምሳሌ ፡
ተናገረ ፤ ምሳሌም ፡ ሳይነግራቸው ፡ አልተና
ገራቸውም ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡
ገባ ። ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀር
በው ፡— የእርሻውን ፡ እንክርዳድ ፡ ምሳሌ ፡ ተር
ጉምልን ፡ አሉት ። እርሱም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡
አላቸው ፡—መልካምን ፡ ዘር ፡ የዘራው ፡ የሰው ፡
ልጅ ፡ ነው ፤ እርሻውም ፡ ዓለም ፡ ነው ፡ መልካ
ሙም ፡ ዘር ፡ የመንግሥት ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፡
እንክርዳዱም ፡ የክፉው ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፥ የዘራ
ውም ፡ ጠላት ፡ ዲያብሎስ ፡ ነው ፡ መከሩም ፡ የዓ
ለም ፡ መጨረሻ ፡ ነው ፥ አጫጆችም ፡ መላእክት ፡
ናቸው ። እንግዲህ ፡ እንክርዳድ ፡ ተለቅሞ ፡ በእ
ሳት ፡ እንደሚቃጠል ፥ በዓለም ፡ መጨረሻ ፡ እን
ዲሁ ፡ ይሆናል ። የሰው ፡ ልጅ ፡ መላእክቱን ፡
ይልክል ፥ ከመንግሥቱም ፡ እንቅፋትን ፡ ሁሉ ፡
ዓመፃንም ፡ የሚያደርጉትን ፡ ይለቅማሉ ፥ ወደ ፡
እቶን ፡ እሳትም ፡ ይጥሉአቸዋል ። በዚያ ፡ ልቅ
ሶና ፡ ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ይሆናል ። በዚያን ፡
ጊዜ ፡ ጻድቃን ፡ በአባታቸው ፡ መንግሥት ፡
እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ይበራሉ ። የሚሰማ ፡ ጆሮ ፡
ያለው ፡ ይስማ ።

ትመስላለች ። በሞላችም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ወደቡ ፡
አወጡአት ፡ ተቀምጠውም ፡ መልካሙን ፡ ለቅ
መው ፡ በየቃዎች ፡ ውስጥ ፡ አከማቹ ፡ ክፉውን ፡
ግን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ጣሉት ። በዓለም ፡ መጨረሻ ፡
እንዲሁ ፡ ይሆናል ፤ መላእክት ፡ መጥተው ፡ ኃጢ
አተኞችን ፡ ከጻድቃን ፡ መካከል ፡ ይለዩአቸዋል ፥
ወደ ፡ እቶን ፡ እሳትም ፡ ይጥሉአቸዋል ፡ በዚያ ፡
ልቅሶና ፡ ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ይሆናል ።

ኢየሱስም ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አስተዋላችሁን ፡
አላቸው ፡ አሙን ፡ አሉት ። እርሱም ፡— ስለዚህ ፡
የመንግሥት ፡ ሰማያት ፡ ደቂ ፡ መገዛሙር ፡ የሆነ ፡
ጻፊ ፡ ሁሉ ፡ ከመዝገቡ ፡ አዲሱንና ፡ አሮጌውን ፡
የሚያወጣ ፡ ባለቤትን ፡ ይመስላል ፡ አላቸው ።

ኢየሱስም ፡ እነዚህን ፡ ምሳሌዎች ፡ ከጨረሰ ፡
በኋላ ፡ ከዘያ ፡ ሄደ ። ወደ ፡ ገዘ ፡ አገሩም ፡ መጥቶ ፡
እስኪገረሙ ፡ ድረስ ፡ በምኵራባቸው ፡ ያስተም
ራቸው ፡ ነበር ፤ እንዲህም ፡ አሉ ፡— ይህን ፡ ጥበ
በና ፡ ተአምራት ፡ ይህ ፡ ከወዴት ፡ አገኘው ፡ ?
ይህ ፡ የአራቢ ፡ ልጅ ፡ አይደለምን ? እናቱስ ፡
ማርያም ፡ ትባል ፡ የለምን ? ወንድሞቹስ ፡ ያዕቆ
ብና ፡ ዮሳ ፡ ስምዖንም ፡ ይሁዳም ፡ አይደሉምን ?
እኅቶቹስ ፡ ሁሉ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ያሉ ፡ አይደሉ
ምን ? እንኪያስ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ከወዴት ፡ አገ
ኘው ? ተሰናከሉበትም ። ኢየሱስ ፡ ግን ፡ -ነቢይ ፡
ከገዛ ፡ አገሩና ፡ ከገዛ ፡ ቤቱ ፡ በቀር ፡ ሳይከበር ፡
አይቀርም ፡ አላቸው ። በአለማመናቸውም ፡ ምክ
ንያት ፡ በዘያ ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ አላደረገም ።

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

በዘያ ፡ ዘመን ፡ የአራተኛው ፡ ክፍል ፡ ገዢ ፡
ሄሮድስ ፡ የኢየሱስን ፡ ገና ፡ ሰማ ። ለሎሌዎ
ቹም ፡— ይህ ፡ መጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ነው ፡ እርሱ ፡
ከሙታን ፡ ተነሥቶአል ፡ ስለዚህም ፡ ኃይል ፡
በእርሱ ፡ ይደረጋል ፡ አለ ። ሄሮድስ ፡ በወን
ድሙ ፡ በፊልጶስ ፡ ሚስት ፡ በሄሮድያዳ ፡ ምክን
ያት ፡ ዮሐንስን ፡ አሰረው ። አሰስሮት ፡ በወህኒ ፡
አኖሮት ፡ ነበርና ፤ ዮሐንስ ፡—እርስዋ ፡ ለእንተ ፡
ትሆን ፡ ዘንድ ፡ አልተፈቀደም ፡ ይለው ፡ ነበርና ።
ሊገድለውም ፡ ወዶ ፡ ሰለ ፡ ሕዝቡ ፡ እንደ ፡ ነቢይ ፡
ስለ ፡ አዩት ፡ ፈራቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሄሮድስ ፡
የተወለደበት ፡ ቀን ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የሄሮድያዳ ፡
ልጅ ፡ በመካከላቸው ፡ ዘፈነች ፡ ሄሮድስንም ፡
ደስ ፡ አሰኘችው ፡ ስለዚህም ፡ የምትለምነውን ፡
ሁሉ ፡ እንዲሰጣት ፡ በመሐላ ፡ ተስፋ ፡ አደረገ
ላት ። እርስዋም ፡ በእናትዋ ፡ ተመክራ ፡—የመ
ጥምቁን ፡ የዮሐንስን ፡ ራስ ፡ በዚህ ፡ በመጭት ፡
ስጠኝ ፡ አለችው ። ንጉሡም ፡ አዘነ ፡ ነገር ፡
ግን ፡ ስለ ፡ መሐላው ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ተቀም

ፍ = ፴፫ ፡ ሉቃ. ፲፫÷፳፭ = ፴፱ ፡ ማር. ፬÷፲፭ = ፵፩ ፡ ሉቃ. ፲፫÷፳፰ = ፵፫ ፡ ዘፍ. ፩÷፩ = ፵፮ ፡ ዳን. ፲፪÷፫ = ፵፯—፵፱ ፡ ማር. ፮÷፭—፯ ፡ ሉቃ. ፭÷፲፯—፲፱ = ፶፱ ፡ ም. ፭÷፳፰ = ፷፩ ፡ ም. ፲፰÷፮ = ፷፯ ፡ ሉሐ. ፮÷፲፭ = ፷፰ ፡ ም. ፲፭÷፮ ፡ ሉሐ. ፱÷፵፱ =

ፍ = ፩ ፡ ማር. ፮÷፲፪—፲፯ ፡ ሉቃ. ፫÷፭፣፲፱÷፭ ፡ ፱÷፯ = ፱ ፡ ዘሌዋ. ፲፯÷፲፩ = ፲፫ ፡ ም. ፳፭÷፳፯ ፡ ማር. ፯÷፲፱ ፡ ፯ ÷ ፯—፲፱ ፡ ማር. ፯÷፳፭—፳፱ ።

ጠው ፡ ስላሉት ፡ ሰዎች ፡ እንዲሰጡአት ፡ አዘዘ ፡
፲፩ ልክም ፡ የዮሐንስን ፡ ራስ ፡ በወገረ ፡ አስቀረ
፲፪ ጠው ። ራሱንም ፡ በወሰዱት ፡ አምጥተው ፡ ለብ
ላቴናይቱ ፡ ሰጡአት ፡ ወደ ፡ እናትዋም ፡ መለ
፲፫ ደችው ። ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ቀርበው ፡ በድ
ኑን ፡ ወሰዱና ፡ ቀበሩት ፡ መጥተውም ፡ ለኢየ
ሱስ ፡ አወሩለት ።
፲፬ ኢየሱስም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከዚያ ፡ ብቻውን ፡
ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በታንኳ ፡ ፈቀቅ ፡ አለ ፡ ሕዝ
ቡም ፡ ሰምተው ፡ ከከተማዎቹ ፡ በእግር ፡ ተከተ
፲፭ ሉት ። ወጥቶም ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ አየና ፡ እዘነላ
፲፮ ቸው ፡ ድውዮቻቸውንም ፡ ፈወሰ ። በመሸም ፡
ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀርበው ፡ —
በታው ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ነው ፡ አሁንም ፡ ሰዓቱ ፡
አልፎአል ፡ ወደ ፡ መንደሮች ፡ ሄደው ፡ ለራሳ
ቸው ፡ ምግብ ፡ እንዲገዙ ፡ ሕዝቡን ፡ አሰናብት ፡
፲፯ አሉት ። ኢየሱስም ፡ — እናንተ ፡ የሚበሉትን ፡
ስጡአቸው ፡ እንጂ ፡ ሊሄዱ ፡ አያስፈልግም ፡
፲፰ አላቸው ። እነርሱም ፡ — ከአምስት ፡ እንጀራና ፡
ከሁለት ፡ ዓሣ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ የለንም ፡ አሉት ።
፲፱ እርሱም ፡ — እነዚያን ፡ ወደዚህ ፡ አምጡልኝ ፡
አላቸው ። ሕዝቡም ፡ በሣር ፡ ላይ ፡ እንዲቀ
መጡ ፡ አዘዘ ፡ አምስቱንም ፡ እንጀራና ፡ ሁለ
ቱን ፡ ዓሣ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አሸቅበ ፡ አየና ፡
ባረከ ፡ እንጀራውንም ፡ ቆርሶ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙ
ርቱ ፡ ሰጠ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ለሕዝቡ ።
፳ ሁሉም ፡ በልተው ፡ ጠገቡ ፡ የተረፈውንም ፡
ቀርጫራ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ መሶብ ፡ ሙሉ ፡
፳፩ አነሡ ። ከሴቶችና ፡ ከልጆችም ፡ በቀር ፡ የበ
ሉት ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ወንዶች ፡ ያህሉ ፡ ነበር ።
፳፪ ወዲያውም ፡ ሕዝቡን ፡ ሲያሰናብት ፡ ሳለ ፡
ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ በታንኳይቱ ፡ ገብተው ፡ ወደ ፡
፳፫ ማዶ ፡ እንዲቀድሙት ፡ ግድ ፡ አላቸው ። ሕዝ
ብንም ፡ አሰናብቶ ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ ብቻውን ፡
ወደ ፡ ተራራ ፡ ወጣ ። በመሸም ፡ ጊዜ ፡ ብቻ
፳፬ ውን ፡ በዚያ ፡ ነበረ ። ታንኳይቱም ፡ አሁን ፡ በባ
ሕር ፡ መካከል ፡ ሳለች ፡ ነፋስ ፡ ከወደ ፡ ፊት ፡ ነበ
፳፭ ርና ፡ በማዕበል ፡ ትጨነቅ ፡ ነበር ። ከሌሊቱም ፡
በአራተኛው ፡ ክፍል ፡ ኢየሱስ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡
፳፮ እየሄደ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ መጣ ። ደቀ ፡ መዛሙ
ርቱም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ሲሄድ ፡ በዩት ፡ ጊዜ ፡ —
ምትሐት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ታወኩ ፡ በፍርሃትም ፡
፳፯ ጮሁ ። ወዲያውም ፡ ኢየሱስ ፡ ተናገራቸውና ፡ —
አይዞአችሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ አትፍሩ ፡ አላቸው ።
፳፰ ጴጥሮስም ፡ መልሶ ፡ — ጌታ ፡ ሆይ ፡ አንተስ ፡
ከሆንህ ፡ በውኃው ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ እንድ
፳፱ መጣ ፡ እዘዘኝ ፡ አለው ። እርሱም ፡ — ና ፡ አለው ።
ጴጥሮስም ፡ ከታንኳይቱ ፡ ወርዶ ፡ ወደ ፡ ኢየ
ሱስ ፡ ሊደርስ ፡ በውኃው ፡ ላይ ፡ ሄደ ። ነገር ፡ ግን ፡
የነፋሱን ፡ ኃይል ፡ አይቶ ፡ ፈራ ፡ ሊሰጥምም ፡
በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ — ጌታ ፡ ሆይ ፡ አድነኝ ፡ ብሎ ፡
ጮኸ ። ወዲያውም ፡ ኢየሱስ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡
ያዘውና ፡ — አንተ ፡ እምነት ፡ የጐደለህ ፡ ስለ ፡
ምን ፡ ተጠራጠርህ ? አለው ። ወደ ፡ ታንኳይ
ቱም ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ነፋሱ ፡ ተወ ። በታንኳይ
ቱም ፡ የነበሩት ፡ — በእውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡
ልጅ ፡ ነህ ፡ ብለው ፡ ሰገዱለት ።
ተሻግረውም ፡ ወደ ፡ ጌንሴሬጥ ፡ ምድር ፡ መጡ ።
የዚያ ፡ በታ ፡ ሰዎችም ፡ በወቁት ፡ ጊዜ ፡ በዙር
ያው ፡ ወዳለ ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ላኩ ፡ ሕመምተኞ
ችንም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አመጡ ፡ የልብሱ
ንም ፡ ጫፍ ፡ ብቻ ፡ ሊዳስሱ ፡ ይለምኑት ፡ ነበር ፡
የዳሰሱትም ፡ ሁሉ ፡ ዳኑ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጻፎችና ፡ ፈሪሳውያን ፡ ከኢየ
ሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ ቀረቡና ፡ — ደቀ ፡ መዛ
ሙርትህ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ የሽማግሌዎችን ፡ ወግ ፡
ይተላለፋሉ ? እንጀራ ፡ ሲበሉ ፡ እጃቸውን ፡
አይታጠቡምና ፡ አሉት ። እርሱም ፡ መልሶ ፡ እን
ዲህ ፡ አላቸው ፡ — እናንተስ ፡ ስለ ፡ ወጋችሁ ፡ የእ
ግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተተላለፋሳ
ችሁ ? እግዚአብሔር ፡ — አባትህንና ፡ እናትህን ፡
አክብር ፡ ደግሞ ፡ — አባቱን ፡ ወይም ፡ እናቱን ፡
የሰደበ ፡ ፈጽሞ ፡ ይሙት ፡ ብሎአልና ፡ እናንተ ፡
ግን ፡ — አባቱን ፡ ወይም ፡ እናቱን ፡ — ከእኔ ፡ የምት
ጠቀምበት ፡ መባ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ሁሉ ፡ አባቱን ፡
ወይም ፡ እናቱን ፡ እያከብርም ፡ ትላላችሁ ፡ ስለ ፡
ወጋችሁም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ሻራችሁ ።
እናንተ ፡ ግብዞች ፡ ኢሳይያስ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ —
ይህ ፡ ሕዝብ ፡ በከንፈሩ ፡ ያከብረኛል ፡ ልቡ ፡
ግን ፡ ከእኔ ፡ በጣም ፡ የራቀ ፡ ነው ፤ የሰውም ፡
ሥርዓት ፡ የሆነ ፡ ትምህርት ፡ እያስተማሩ ፡
በከንቱ ፡ ያመልኩኛል ፡
ብሎ ፡ በእውነት ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ።
ሕዝቡንም ፡ ጠርቶ ፡ — ስሙ ፡ አስተውሉም ፡
ሰውን ፡ የሚያረክሰው ፡ ወደ ፡ አፍ ፡ የሚገባ ፡
አይደለም ፡ ከአፍ ፡ የሚወጣው ፡ ግን ፡ ሰውን ፡
የሚያረክሰው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አላቸው ። በዚያን ፡
ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ቀርበው ፡ — ፈሪሳው
ያን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ሰምተው ፡ እንደ ፡ ተሰናከሉ ፡
አወቅህን ? አሉት ። እርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፡ — የሰ
ማዩ ፡ አባቴ ፡ ያልተከለው ፡ ተክል ፡ ሁሉ ፡ ይነ
ቀላል ። ተዉአቸው ፡ ሰውሮችን ፡ የሚመሩ ፡
ሰውሮች ፡ ናቸው ፡ ሰውርም ፡ ሰውርን ፡ ቢመ
ራው ፡ ሁለቱም ፡ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ ይወድቃሉ ፡

ነጽ። ፲፫—፳፭ ፡ ማር. ፮ ÷ ፴፪—፶፱ ፡ ሉቃ. ፱ ÷ ፯—፲፮ ። ፲፬ ፡ ሮሜ. ፲፩ ÷ ፳፭—፴፪ ። ፲፮ ፡ ፩ኛ ነገሥ. ፱ ÷ ፶፱—፷፱ ። ፳፩—፳፪ ። ማር. ፮ ÷ ፵፭—፶፩ ። ሉቃ. ፱ ÷ ፲፯—፳፩ ። ፳፫ ፡ ማር. ፩ ÷ ፴፭ ፡ ሉቃ. ፭ ÷ ፲፮ ። ፳፮ ፡ ሉቃ. ፳፬ ÷ ፴፯ ። ፳፰ ፡ ፩ኛ ነገሥ. ፲፰ ÷ ፴፰ ። ፳፱ ፡ ም. ፹ ÷ ፵፱ ። ፴፩—፴፪ ፡ ማር. ፮ ÷ ፶፫—፶፮ ። ፴፭ ፡ ም. ፹ ÷ ፵፱ ።

ነጽ። ፩—፭ ፡ ማር. ፯ ÷ ፩—፱ ። ፭ ፡ ሉቃ. ፲፩ ÷ ፵፭ ። ፮ ፡ ዘዳኦ. ፮ ÷ ፲፫ ፡ ፲፰ ÷ ፲፯ ። ፰ ፡ ዘፍ. ፲፰ ÷ ፳፫ ። ፲፩ ፡ ም. ፵፫ ÷ ፲፯ ፡ ሉቃ. ፮ ÷ ፵፩ ።

፲፭ አለ ። ጴጥሮስም ፡ መልሶ ፡ — ምሳሌውን ፡ ተርጕ
፲፮ ምልን ፡ አለው ። ኢየሱስም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ —
እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እስካሁን ፡ የማታስተውሉ ፡
፲፯ ናችሁን ? ወደ ፡ አፍ ፡ የሚገባ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡
ሆድ ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ አዳሪ ፡ እንዲጣል ፡ አትመ
ለከቱምን ? ከአፍ ፡ የሚወጣ ፡ ግን ፡ ከልብ ፡
ይወጣል ፡ ሰውንም ፡ የሚያረክሰው ፡ ያ ፡ ነው ።
፲፱ ከልብ ፡ ክፉ ፡ አሳብ ፡ መግደል ፡ ምንዝርነት ፡
ዝሙት ፡ መስረቅ ፡ በውሸት ፡ መመስከር ፡ ስድብ ፡
፳ ይወጣልና ። ሰውን ፡ የሚያረክሰው ፡ ይህ ፡ ነው ፡
እንጂ ፡ ባልታጠበ ፡ እጅ ፡ መብላትስ ፡ ሰውን ፡
አያረክሰውም ።
፳፩ ኢየሱስም ፡ ከዚያ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ጢሮስና ፡
፳፪ ወደ ፡ ሲዶና ፡ አገር ፡ ሄደ ። እነሆም ፡ ከነናዊት ፡
ሴት ፡ ከዚያ ፡ አገር ፡ ወጥታ ፡ — ጌታ ፡ ሆይ ፡ የዳ
ዊት ፡ ልጅ ፡ ማረኝ ፡ ልጂን ፡ ጋኔን ፡ ክፉኛ ፡ ይዞ
፳፫ አታል ፡ ብላ ፡ ጮኸች ። እርሱ ፡ ግን ፡ አንዳች ፡
አልመለሰላትም ። ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ቀር
በው ፡ — በኋላችን ፡ ትጮኻለችና ፡ አሰናብታት ፡
፳፬ እያሉ ፡ ለመኑት ። እርሱም ፡ መልሶ ፡ — ከእስራ
ኤል ፡ ቤት ፡ ለጠፉት ፡ በጎች ፡ በቀር ፡ አልተላክ
፳፭ ሁም ፡ አለ ። እርስዋ ፡ ግን ፡ መጥታ ፡ — ጌታ ፡
፳፮ ሆይ ፡ እርዳኝ ፡ እያለች ፡ ሰገደችለት ። እርሱ ፡
ግን ፡ መልሶ ፡ — የልጆችን ፡ እንጀራ ፡ ይዞ ፡ ለቡ
፳፯ ችሎች ፡ መጣል ፡ አይገባም ፡ አለ ። እርስዋም ፡ —
አዎን ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ ቡችሎችም ፡ እኮ ፡ ከጌቶቻ
ቸው ፡ ማዕድ ፡ የወደቀውን ፡ ፍርፋሪ ፡ ይበላሉ ፡
፳፰ አለች ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ መልሶ ፡ —
አንቺ ፡ ሴት ፡ እምነትሽ ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡ እንደ ፡
ወደድሽ ፡ ይሁንልሽ ፡ አላት ። ልጅዋም ፡ ከዚ
፳፱ ያች ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ ዳነች ።
ኢየሱስም ፡ ከዚያ ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡
ባሕር ፡ አጠገብ ፡ መጣ ፡ ወደ ፡ ተራራም ፡ ወጥቶ ፡
፴ በዚያ ፡ ተቀመጠ ። ብዙ ፡ ሕዝብም ፡ አንካሰ
ችን ፡ ዕውሮችንም ፡ ዲዳዎችንም ፡ ጉንጮች
ንም ፡ ሌሎችንም ፡ ብዙ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡
ቀረቡ ፡ በኢየሱስም ፡ እግር ፡ አጠገብ ፡ ጣሉአ
፴፩ ቸው ፡ ፈወሳቸውም ። ስለዚህም ፡ ሕዝቡ ፡ ዲዳ
ዎች ፡ ሲናገሩ ፡ ጉንጮች ፡ ሲድኑ ፡ አንካሰ
ችም ፡ ሲሄዱ ፡ ዕውሮችም ፡ ሲያዩ ፡ አይተው ፡
ተደነቁ ፡ የእስራኤልንም ፡ አምላክ ፡ አከበሩ ።
፴፪ ኢየሱስም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ጠርቶ ፡ —
ሕዝቡ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ እስከሁን ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡
ውሎዋልና ፡ የሚበሉት ፡ ስለ ፡ ሌላቸው ፡ እዝ
ንላቸዋለሁ ፡ በመንገድም ፡ እንዳይዝሉ ፡ ጠማ
ቸውን ፡ ላሰናብታቸው ፡ አልወድም ፡ አላቸው ።
፴፫ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ — ይህን ፡ ያህል ፡ ሕዝብ ፡
የሚያጠግብ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ እንጀራ ፡ በምድረ ፡
፴፬ በዳ ፡ ከወዴት ፡ እናገኛለን ? አሉት ። ኢየሱ

ነጽ። ፲፭—፳፭ ፡ ማር. ፯ ÷ ፳፬—፴ ። ፳፪ ፡ ም. ፯ ÷ ፳ ፡ ፯ ። ፳፫ ፡ ም. ፯ ÷ ፲፫ ። ፳፮—፳፯ ፡ ማር. ፯ ÷ ፳፰—፳፱ ። ፴፩—፴፪ ፡ ም. ፲፭ ÷ ፲፬—፳፭ ፡ ማር. ፰ ÷ ፩—፯ ።

ነጽ። ፩—፲፪ ፡ ም. ፲፮ ÷ ፴፭ ፡ ማር. ፰ ÷ ፲፩—፳፭ ። ፪ ፡ ፫ ፡ ሉቃ. ፲፪ ÷ ፶፱ ። ፬ ፡ ም. ፲፪ ÷ ፴፱ ። ፯ ፡ ሉቃ. ፲፪ ÷ ፭ ። ፰ ፡ ም. ፲፮ ÷ ፲፭ — ፳፭ ። ፲፫ ፡ ም. ፲፮ ÷ ፲፯ — ፳፰ ። ፲፮ ፡ ማር. ፰ ÷ ፳፱ ፡ ሉቃ. ፱ ÷ ፲፰ ። ፲፯ ፡ ም. ፲፯ ÷ ፩ ፡ ፭ ። ፲፰ ፡ ዮሐ. ፩ ÷ ፵፪ — ፵፫ ። ፲፱ ፡ ሉቃ. ፱ ÷ ፵፩ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

፩ ፈሪሳውያንና ፡ ሰዱቃውያንም ፡ ቀርበው ፡
ሲፈትኑት ፡ ከሰማይ ፡ ምልክት ፡ እንዲያሳያቸው ፡
፪ ለመኑት ። እርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላ
ቸው ፡ — በመሸ ፡ ጊዜ ፡ — ሰማዩ ፡ ቀልቶአልና ፡
፫ ብራ ፡ ይሆናል ፡ ትላላችሁ ፡ ማለዳም ፡ — ሰማዩ ፡
ደምኖ ፡ ቀልቶአልና ፡ ዛሬ ፡ ይዘንባል ፡ ትላላ
፬ ችሁ ። የሰማዩን ፡ ፊትማ ፡ መለየት ፡ ታውቃላ
ችሁ ፡ የዘመኑንስ ፡ ምልክት ፡ መለየት ፡ አትች
ሉምን ? ክፉና ፡ አመንዝራ ፡ ትውልድ ፡ ምልክት ፡
፭ ይሻል ፡ ከነቢይም ፡ ከዮናስ ፡ ምልክት ፡ በቀር ፡
ምልክት ፡ አይሰጠውም ። ትቶአቸውም ፡ ሄደ ።
፮ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ወደ ፡ ማዶ ፡ በመጡ ፡
ጊዜ ፡ እንጀራ ፡ መያዝን ፡ ረሱ ። ኢየሱስም ፡ —
፯ ከፈሪሳውያንና ፡ ከሰዱቃውያን ፡ እርሾ ፡ ተጠን
፰ ቀቁና ፡ ተጠበቁ ፡ አላቸው ። እነርሱም ፡ — እን
፱ ጀራ ፡ ባንይዝ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡
፲ ተነጋገሩ ። ኢየሱስም ፡ ዐውቆ ፡ እንዲህ ፡ አላ
ቸው ፡ — እናንተ ፡ እምነት ፡ የጐደላችሁ ፡ እን
፲፩ ጀራ ፡ ስለ ፡ ሌላችሁ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡
ትነጋገራላችሁ ? ገና ፡ አታስተውሉምን ? ለአ
፲፪ ምስቱ ፡ ሺህ ፡ አምስቱ ፡ እንጀራ ፡ ስንት ፡ መሶ
ብም ፡ እንዳነሣችሁ ፡ ትዝ ፡ አይላችሁምን ?
ወይስ ፡ ለአራቱ ፡ ሺህ ፡ ሰባቱ ፡ እንጀራ ፡ ስንት ፡
፲፫ ቅርጫትም ፡ እንዳነሣችሁ ፡ ትዝ ፡ አይላችሁ
ምን ? ከፈሪሳውያንና ፡ ከሰዱቃውያን ፡ እርሾ ፡
፲፬ እንድትጠበቁ ፡ ብዬ ፡ ስለ ፡ እንጀራ ፡ እንዳልተ
ናገርኋችሁ ፡ እንዴት ፡ አታስተውሉምን ? እነር
፲፭ ሱም ፡ ከፈሪሳውያንና ፡ ከሰዱቃውያን ፡ ትምህ
ርት ፡ እንጂ ፡ ከእንጀራ ፡ እርሾ ፡ እንዲጠበቁ ፡
እንዳላላቸው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አስተዋሉ ።
፲፮ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ፊልጶስ ፡ ቂሣርያ ፡ አገር ፡
በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ — ሰዎች ፡
የሰውን ፡ ልጅ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይሉታል ?
፲፯ ብሎ ፡ ጠየቀ ። እነርሱም ፡ — አንዳንዱ ፡ መጥ
ምቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ሌሎችም ፡ ኤልያስ ፡ ሌሎችም ፡
ኤርምያስ ፡ ወይም ፡ ከነቢያት ፡ አንዱ ፡ ነው ፡

፲፫ ይላሉ ፡ አሉት ። እርሱም ፡— እናንተስ ፡ እኔን ፡
፲፮ ማን ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ትላላችሁ ፡ አላቸው ። ስም
ዖን ፡ ጴጥሮስም ፡ መልሶ ፡— አንተ ፡ ክርስቶስ ፡
የሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነህ ፡ አለ ።
፲፯ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡— የዮናስ ፡
ልጅ ፡ ስምዖን ፡ ሆይ ፡ በሰማያት ፡ ያለው ፡ አባቴ ፡
እንጂ ፡ ሥጋና ፡ ደም ፡ ይህን ፡ አልገለጠልህምና ፡
፲፰ ብውዕ ፡ ነህ ። እኔም ፡ እልሃለሁ ፡ አንተ ፡ ጴጥ
ሮስ ፡ ነህ ፡ በዚችም ፡ ዓለት ፡ ላይ ፡ ቤተ ፡ ክርስ
ቲያኔን ፡ እሠራለሁ ፡ የገሃነም ፡ ደጆችም ፡ አይ
፲፱ ችሉአትም ። የመንግሥተ ፡ ሰማያትንም ፡ መክ
ፈቻዎች ፡ እሰጥሃለሁ ፡ በምድር ፡ የምታስረው ፡
ሁሉ ፡ በሰማያት ፡ የታሰረ ፡ ይሆናል ፡ በምድ
ርም ፡ የምትፈታው ፡ ሁሉ ፡ በሰማያት ፡ የተ
፳ ፈታ ፡ ይሆናል ። ያን ፡ ጊዜም ፡ እርሱ ፡ ክርስቶስ ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማንም ፡ እንዳይነግሩ ፡ ደቀ ፡ መዘ
ሙርቱን ፡ አዘዘቸው ።

፳፩ ከዚያን ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ኢየሱስ ፡ ወደ ፡ ኢየሩ
ሳሌም ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ ከሽማግሌችና ፡ ከክህ
ናት ፡ አለቆች ፡ ከጻፎችም ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ይቀ
በልና ፡ ይገደል ፡ ዘንድ ፡ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡
ይነሣ ፡ ዘንድ ፡ እንዲገባው ፡ ለደቀ ፡ መዘሙ
፳፪ ርቱ ፡ ይገልጥላቸው ፡ ጀመር ። ጴጥሮስም ፡ ወደ ፡
እርሱ ፡ ወስዶ ፡ — አይሁንብህ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡
ይህ ፡ ከቶ ፡ አይደርስብህም ፡ ብሎ ፡ ሊገሥጸው ፡
፳፫ ጀመረ ። እርሱ ፡ ግን ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ጴጥሮ
ስን ፡— ወደ ፡ ኋላዬ ፡ ሂድ ፡ አንተ ፡ ሰይጣን ፡ የሰ
ውን ፡ እንጂ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ አታስብምና ፡
ዕንቅፋት ፡ ሆነህብኛል ፡ አለው ።

፳፬ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ ለደቀ ፡ መዘሙርቱ ፡
እንዲህ ፡ አለ ፡— እኔን ፡ መከተል ፡ የሚወድ ፡
ቢኖር ፡ ራሱን ፡ ይክድ ፡ መስቀሉንም ፡ ተሸክሞ ፡
፳፭ ይከተለኝ ። ነፍሱን ፡ ሊያድን ፡ የሚወድ ፡ ሁሉ ፡
ያጠፋታል ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ነፍሱን ፡ የሚያ
፳፮ ጠፋ ፡ ሁሉ ፡ ያገኛታል ። ሰው ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡
ቢያተርፍና ፡ ነፍሱንም ፡ ቢያጎድል ፡ ምን ፡ ይጠ
ቅመዋል ? ወይስ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ነፍሱ ፡ ቤዛ ፡
፳፯ ምን ፡ ይሰጣል ? የሰው ፡ ልጅ ፡ ከመላእክቱ ፡
ጋር ፡ በአባቱ ፡ ክብር ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ አለውና ፡
ያን ፡ ጊዜም ፡ ለሁሉ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ያስረክ
፳፰ በዋል ። እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡
በመንግሥቱ ፡ ሲመጣ ፡ እስኪያዩ ፡ ድረስ ፡ እዚህ ፡
ከሚቆሙት ፡ ሞትን ፡ የማይቀምሱ ፡ አንዳንድ ፡
አሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

፩ ከስድስት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ ጴጥሮ
ስንና ፡ ያዕቆብን ፡ ወንድሙንም ፡ ዮሐንስን ፡
ይዞ ፡ መደ ፡ ረጅም ፡ ተራራ ፡ ብቻቸውን ፡ አወጣ
፪ ቸው ። በፊታቸውም ፡ ተለወጠ ፡ ፊቱም ፡ እንደ ፡
ፀሐይ ፡ በራ ፡ ልብሱም ፡ እንደ ፡ ብርሃን ፡ ነጭ
፫ ሆነ ። እነሆም ፡ ሙሴና ፡ ኤልያስ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡
ሲነጋገሩ ፡ ታዩአቸው ። ጴጥሮስም ፡ መልሶ ፡
፬ ኢየሱስን ፡— ጌታ ፡ ሆይ ፡ በዚህ ፡ መሆን ፡ ለእኛ ፡
መልካም ፡ ነው ፡ ብትወድስ ፡ በዚህ ፡ ሦስት ፡
ዳስ ፡ እንሥራ ፡ ለአንተ ፡ እንዱንም ፡ ለሙሴ ፡
እንዱንም ፡ ለኤልያስ ፡ እንሥራ ፡ አለ ። እርሱም ፡
፭ ገና ፡ ሲናገር ፡ እነሆ ፡ ብሩህ ፡ ደመና ፡ ጋረዳ
ቸው ፡ እንሆም ፡ ከደመናው ፡ — በእርሱ ፡ ደስ ፡
የሚለኝ ፡ የምወደው ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እርሱን ፡
ስሙት ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ መጣ ። ደቀ ፡ መዘሙ
፮ ርቱም ፡ ሰምተው ፡ በፊታቸው ፡ ወደቁ ፡ እጅ
፯ ግም ፡ ፈርተው ፡ ነበር ። ኢየሱስም ፡ ቀርቦ ፡
ዳሰሰቸውና ፡— ተነሡ ፡ አትፍሩም ፡ አላቸው ።
፰ ዓይናቸውንም ፡ አቅንተው ፡ ሲያዩ ፡ ከኢየሱስ ፡
ብቻ ፡ በቀር ፡ ማንንም ፡ አላዩም ።

፱ ከተራራውም ፡ በወረዱ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ — ፡
የሰው ፡ ልጅ ፡ ከሙታን ፡ እስኪነሣ ፡ ድረስ ፡
ያያችሁትን ፡ ለማንም ፡ አትንገሩ ፡ ብሎ ፡ አዘ
፲ ዛቸው ። ደቀ ፡ መዘሙርቱም ፡— እንግዲህ ፡
ጻፎች ፡—ኤልያስ ፡ አስቀድሞ ፡ ሊመጣ ፡ ይገባ
፲፩ ዋል ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይላሉ ፡ ? ብለው ፡ ጠየቁት ።
፲፪ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡— ኤልያስማ ፡ አስቀድሞ ፡
ይመጣል ፡ ሁሉንም ፡ ያቀናል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እላች
ኋለሁ ፡ ኤልያስ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ መጣ ፡ የወደ
ዱትንም ፡ ሁሉ ፡ እደረጉበት ፡ እንጂ ፡ አላወቁ
ትም ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ከእ
ነርሱ ፡ መከራ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ አለው ። አላ
፲፫ ቸው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዘሙርቱ ፡ ስለ ፡
መጥምቁ ፡ ስለ ፡ ዮሐንስ ፡ እንደ ፡ ነገራቸው ፡
አስተዋሉ ።

፲፬ ወደ ፡ ሕዝቡም ፡ ሲደርሱ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡
፲፭ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀረበና ፡ ተንበርክከ ፡ — ጌታ ፡
ሆይ ፡ ልጄን ፡ ማረልኝ ፡ በጨረቃ ፡ እየተነሣበት ፡
ክፉኛ ፡ ይሣቀያልና ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በእሳት ፡ ብዙ ፡
፲፮ ጊዜም ፡ በውኃ ፡ ይወድቃልና ። ወደ ፡ ደቀ ፡
መዘሙርትህም ፡ አመጣሁት ፡ ሊፈውሱትም ፡
አቃታቸው ፡ አለው ። ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡—
የማታምኑ ፡ ጠማማ ፡ ትውልድ ፡ ሆይ ፡ እስከ ፡
መቼ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ እኖራለሁ ፡ ? እስከ ፡
መቼስ ፡ እታገሣችኋለሁ ፡ ? ወደዚህ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡
፲፯ አምጡት ፡ አለ ። ኢየሱስም ፡ ገሠጸው ፡ ጋኔ
ንም ፡ ከእርሱ ፡ ወጣ ፡ ብላቴናውም ፡ ከዚያች ፡
ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ ተፈወሰ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደቀ ፡
፲፰ መዘሙርቱ ፡ ብቻቸውን ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ ቀረ
ቡና ፡— እኛ ፡ ልናወጣው ፡ ያልቻልን ፡ ስለ ፡

፳ ምን ፡ ነው ? አሉት ። ኢየሱስም ፡— ስለ ፡ እምነ
ታችሁ ፡ ማነስ ፡ ነው ፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ የሰ
ናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ የሚያህል ፡ እምነት ፡ ቢኖራ
ችሁ ፡ ይህን ፡ ተራራ ፡— ከዚህ ፡ ወደዚያ ፡ እለፍ ፡
ብትሉት ፡ ያልፋል ፤ የሚሳናችሁም ፡ ነገር ፡
፳፩ የለም ። ይህ ፡ ዓይነት ፡ ግን ፡ ከጸሎትና ፡ ከጦም ፡
በቀር ፡ አይወጣም ፡ አላቸው ።

፳፪ በገሊላም ፡ ሲመላለሱ ፡ ኢየሱስ ፡— የሰው ፡
ልጅ ፡ በሰዎች ፡ እጅ ፡ አልፎ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡
፳፫ አለው ፡ ይገድሉትማል ፡ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡
ይነሣል ፡ አላቸው ። እጅግም ፡ አዘኑ ።

፳፬ ወደ ፡ ቅፍርናሆምም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ግብር ፡
የሚቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቀረቡና ፡—
መምህራችሁ ፡ ሁለቱን ፡ ዲናር ፡ (1) ይከፍላ
፳፭ ልን ? አሉት ። አዎን ፡ ይገብራል ፡ አለ ። ወደ ፡
ቤትም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ አስቀድሞ ፡—
ስምዖን ፡ ሆይ ፡ ምን ፡ ይመስልሃል ? የምድር ፡
ነገሥታት ፡ ቀረጥና ፡ ግብር ፡ ከማን ፡ ይቀበላሉ ?
ከልጆቻቸውን ፡ ወይስ ፡ ከእንግዶች ? አለው ።
፳፮ ጴጥሮስም ፡— ከእንግዶች ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ኢየ
ሱስ ፡— እንኪያስ ፡ ልጆቻቸው ፡ ነጻ ፡ ናቸው ።
፳፯ ነገር ፡ ግን ፡ እንዳናሰናክላቸው ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡
ሂድና ፡ መቃጥን ፡ ጣል ፡ መጀመሪያም ፡ የሚ
ወጣውን ፡ ዓሣ ፡ ውሰድና ፡ አፉን ፡ ስትከፍት ፡
እስታቴር ፡ (2) ታገኛለህ ፤ ያን ፡ ወስደህ ፡ ስለ ፡
እኔና ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ስጣቸው ፡ አለው ።

(1) አንድ ፡ ዲናር ፡ አምሳ ፡ የኢት ፡ ብር ፡ ሳንቲም ፡ ያህል ፡ ነው ።
(2) እስታቴር ፡ ሁለት ፡ ብር ፡ ያህል ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

፩ በዚያች ፡ ሰዓት ፡ ደቀ ፡ መዘሙርቱ ፡ ወደ ፡
ኢየሱስ ፡ ቀርበው ፡— በመንግሥት ፡ ሰማያት ፡
ከሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ማን ፡ ይሆን ? አሉት ።
፪ ሕፃንም ፡ ጠርቶ ፡ በመካከላቸው ፡ አቆመ ፡
፫ እንዲህም ፡ አለ ፡— እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ ካል
ተመለሳችሁ ፡ እንደ ፡ ሕፃናትም ፡ ከልሆናችሁ ፡
ወደ ፡ መንግሥት ፡ ሰማያት ፡ ከቶ ፡ አትገቡም ።
፬ እንግዲህ ፡ እንደዚህ ፡ ሕፃን ፡ ራሱን ፡ የሚያዋ
ርድ ፡ ሁሉ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚበልጥ ፡
እርሱ ፡ ነው ።
፭ እንደዚህም ፡ ያለውን ፡ አንድ ፡ ሕፃን ፡ በስሜ ፡
፮ የሚቀበል ፡ ሁሉ ፡ እኔን ፡ ይቀበላል ፤ በእኔም ፡
ከሚያምኑ ፡ ከነዚህ ፡ ከታናናሾቹ ፡ አንዱን ፡
የሚያሰናክል ፡ ሁሉ ፡ የወፍጮ ፡ ድንጋይ ፡ በአ
ንገቱ ፡ ታስሮ ፡ ወደ ፡ ጥልቅ ፡ ባሕር ፡ መስጠም ፡
ይሻለው ፡ ነበር ።
፯ ወዮ ፡ ለዓለም ፡ ስለ ፡ ማሰናከያ ፤ ማሰናከያ ፡ ሳይ
መጣ ፡ አይቀርምና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በእርሱ ፡ ጠንቅ ፡
ማሰናከያ ፡ ለሚመጣበት ፡ ለዚያ ፡ ሰው ፡ ወዮ

፮ አመጡ ። የሚከፍለውም ፡ ቢያጣ ÷ እርሱና ፡ ሚስቱ ፡ ልጆቹም ፡ ያለውም ፡ ሁሉ ፡ እንዲሸ
፯ ጥና ፡ ዕዳው ፡ እንዲከፈል ፡ ጌታው ፡ አዘዘ ። ስለ ዚህ ፡ ባሪያው ፡ ወድቆ ፡ ሰገደለትና ፡— ጌታ ፡ ሆይ ÷ ታገሠኝ ÷ ሁሉንም ፡ እከፍልሃለሁ ፡ አለው ።
፰ የዚያም ፡ ባሪያ ፡ ጌታ ፡ አዘነለትና ፡ ለቀቀው ÷ ዕዳ
፱ ውንም ፡ ተወለት ። ነገር ፡ ግን ፡ ያ ፡ ባሪያ ፡ ወጥቶ ፡ ከባልንጀሮቹ ፡ ከባሮቹ ፡ መቶ ፡ ዲናር ፡ ዕዳ ፡ ያለ
በትን ፡ አንዱን ፡ አገኘና ፡— ዕዳህን ፡ ክፈለኝ ፡
፳ ብሎ ፡ ያዘና ፡ አነቀው ። ስለዚህ ፡ ባልንጀራው ፡ ባሪያ ፡ ወድቆ ፡— ታገሠኝ ÷ ሁሉንም ፡ እከፍልሃ
፳፩ ለሁ ፡ ብሎ ፡ ለመነው ። እርሱም ፡ አልወደደም ÷ ግን ፡ ሄዶ ፡ ዕዳውን ፡ እስኪከፍል ፡ ድረስ ፡ በወ
፳፪ ኅኒ ፡ አኖረው ። ባልንጀሮቹ ፡ የሆኑ ፡ በሮችም ፡ ያደረገውን ፡ አይተው ፡ እጅግ ፡ አዘኑ ÷ መጥተ
ውም ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ለጌታቸው ፡ ገለጡ ።
፳፫ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ጌታው ፡ ጠርቶ ፡— አንተ ፡ ክፉ ፡ ባሪያ ÷ ስለ ፡ ለመንኸኝ ፡ ያን ፡ ዕዳ ፡ ሁሉ ፡ ተው
፳፬ ሁልህ ፤ እኔ ፡ እንደ ፡ ማርሁህ ፡ ባልንጀራህ ፡ የሆነውን ፡ ያን ፡ ባሪያ ፡ ልትምረው ፡ ለአንተስ ፡
፳፭ አይገባህምን ? አለው ። ጌታውም ፡ ተቈጣና ፡ ዕዳውን ፡ ሁሉ ፡ እስኪከፍለው ፡ ድረስ ፡ ለሚሣ
፳፮ ቅዩት ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠው ። ከእናንተ ፡ እያንዳ
ንዱ ፡ ወንድሙን ፡ ከልቡ ፡ ይቅር ፡ ካላለ ፡ እን
ዲሁ ፡ ደግሞ ፡ የሰማዩ ፡ አባቴ ፡ ያደርግባችኋል ።

ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

፩ ኢየሱስም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ÷ ከገሊላ ፡ ሄዶ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ አውራጃ ፡ ወደ ፡
፪ ዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ መጣ ። ብዙ ፡ ሕዝብም ፡ ተከ
ተሉት ÷ በዚያም ፡ ፈወሳቸው ።
፫ ፈሪሳውያንም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀረቡና ፡ ሲፈት
ኑት ፡— ሰው ፡ በሆነው ፡ ምክንያት ፡ ሁሉ ፡ ሚስ
ቱን ፡ ሊፈታ ፡ ተፈቅዶለታልን ? አሉት ።
፬ እርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— ፈጣሪ ፡
በመጀመሪያ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አደረጋቸው ÷
፭ አለም ፡— ስለዚህ ፡ ሰው ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡
ይተዋል ÷ ከሚስቱም ፡ ጋር ፡ ይተበበራል ÷ ሁለ
ቱም ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ይሆናሉ ፡ የሚሉውን ፡
፮ ቃል ፡ አላነበባችሁምን ? ስለዚህ ፡ አንድ ፡
ሥጋ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሁለት ፡ አይ
ደሉም ። እግዚአብሔር ፡ ያጣመረውን ፡ እንግ
፯ ዲህ ፡ ሰው ፡ አይለየው ። እነርሱም ፡— እንኪ
ያስ ፡ ሙሴ ፡ የፍቾዋን ፡ ጽሕፈት ፡ ሰጥተው ፡ እን
፰ ዲፈቱአት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አዘዘ ? አሉት ። እር
ሱም ፡— ሙሴስ ፡ ስለ ፡ ልባችሁ ፡ ጥንካሬ ፡ ሚስ
ቶቻችሁን ፡ ትፈቱ ፡ ዘንድ ፡ ፈቀደላችሁ ፤ ከጥ
፱ ንት ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አልነበረም ። እኔ ፡ ግን ፡
አላችኋለሁ ÷ ያለ ፡ ዝሙት ፡ ምክንያት ፡ ሚስ
ቱን ፡ ፈትቶ ፡ ሌላዪቱን ፡ የሚያገባ ፡ ሁሉ ፡ ያመ
ነዝራል ÷ የተፈታችውንም ፡ የሚያገባ ፡ ያመነ
ዝራል ፡ አላቸው ።
፲ ደቀ ፡ መዘሙርቱም ፡— የባልና ፡ የሚስት ፡
፲፩ ሥርዓት ፡ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ መጋባት ፡ አይጠቅ
ምም ፡ አሉት ። እርሱ ፡ ግን ፡— ይህ ፡ ነገር ፡ ለተ
፲፪ ሰጣቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለሁሉ ፡ አይደለም ፤ በእ
ናት ፡ ማኅፀን ፡ ጃንደረቦች ፡ ሆነው ፡ የተወለዱ ፡
አሉ ÷ ሰውም ፡ የሰለባቸው ፡ ጃንደረቦች ፡ አሉ ÷
ስለ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ ራሳቸውን ፡ የሰ
ለቡ ፡ ጃንደረቦች ፡ አሉ ። ሊቀበለው ፡ የሚችል ፡
ይቀበለው ፡ አላቸው ።
፲፫ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እጁን ፡ እንዲጭንባቸውና ፡ እን
ዲጸልይ ፡ ሕፃናትን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አመጡ ፤ ደቀ ፡
መዘሙርቱም ፡ ገሠጹአቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ኢየ
፲፬ ሱስ ፡— ሕፃናትን ፡ ተዉአቸው ÷ ወደ ፡ እኔም ፡
ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ አትክልክሉአቸው ፤ መንግ
ሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንደነዚህ ፡ ላሉ ፡ ናትና ፡ አለ ፡
እጁንም ፡ ጫነባቸውና ፡ ከዚያ ፡ ሄደ ።
፲፭ እነሆም ÷ አንድ ፡ ሰው ፡ ቀርቦ ፡— መምህር ፡
ሆይ ÷ የዘላለምን ፡ ሕይወት ፡ እንዳገኝ ፡ ምን ፡
መልካም ፡ ነገር ፡ ላድርግ ? አለው ። እርሱም ፡—
፲፮ ስለ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ ትጠይቀኛለህ ?
መልካም ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ወደ ፡ ሕይወት ፡
መግባት ፡ ብትወድ ፡ ግን ፡ ትእዛዛትን ፡ ጠብቅ ፡
አለው ። እርሱም ፡— የትኞቹን ? አለው ። ኢየ
፲፯ ሱስም ፡— አትግደል ÷ አታመንዝር ÷ አትስ
፲፰ ረቅ ÷ በሐሰት ፡ አትመስክር ÷ አባትህንና ፡ እና
፲፱ ትህን ፡ አክብር ÷ ባልንጀራህንም ፡ እንደ ፡ ራስህ ፡
ውደድ ፡ አለው ። ጕበዙም ፡— ይህንማ ፡ ሁሉ ፡ ከ
፳ ከአያንቱ ፡ ጀምሬ ፡ ጠብቅአለሁ ÷ ደግሞስ ፡
የሚጐድለኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ? አለው ። ኢየሱ
፳፩ ስም ፡— ፍጹም ፡ ልትሆን ፡ ብትወድ ÷ ሂድና ፡
ያለህን ፡ ሽጠህ ፡ ለድሆች ፡ ስጥ ÷ መዝገብም ፡
በሰማያት ፡ ታገኛለህ ÷ መጥተህም ፡ ተከተ
፳፪ ለኝ ፡ አለው ። ጕበዙም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡
በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ንብረት ፡ ነበረውና ፡ እያ
ዘነ ፡ ሄደ ።
፳፫ ኢየሱስም ፡ ለደቀ ፡ መዘሙርቱ ፡— እውነት ፡
አላችኋለሁ ÷ ለባለጠጋ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማ
፳፬ ያት ፡ መግባት ፡ ጭንቅ ፡ ነው ። ዳግመኛም ፡ እላ
ችኋለሁ ÷ በሰለጠጋ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግ
ሥት ፡ ከሚገባ ፡ ግመል ፡ በመርፌ ፡ ቀዳዳ ፡ ቢገባ ፡
፳፭ ይቀላል ፡ አለ ። ደቀ ፡ መዘሙርቱም ፡ ሰም
ተው ፡ እጅግ ፡ ተገረሙና ፡— እንኪያስ ፡ ማን ፡
ሊድን ፡ ይችላል ? አሉ ። ኢየሱስም ፡ አነርሱን ፡
፳፮ ተመልክቶ ፡— ይህ ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ አይቻልም ፡
በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ሁሉ ፡ ይቻላል ፡
አላቸው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጴጥሮስ ፡ መልሶ ፡—
፳፯ እነሆ ÷ እኛ ፡ ሁሉን ፡ ትተን ፡ ተከተልንህ ፤ እን

፳፰ ኪያስ ፡ ምን ፡ እናገኝ ፡ ይሆን ? አለው ። ኢየ
ሱስም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ እውነት ፡ እላች
ኋለሁ ፡ እናንተስ ፡ የተከተላችሁኝ ፡ በዳግመኛ ፡
ልደት ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በክብሩ ፡ ዙፋን ፡ በሚቀ
መዋበት ፡ ጊዜ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ በአሥራ ፡
ሁለቱ ፡ የእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ስትፈርዱ ፡ በአ
፳፱ ሥራ ፡ ሁለት ፡ ዙፋን ፡ ትቀመጣላችሁ ። ስለ ፡
ስሜም ፡ ቤቶችን ፡ ወይም ፡ ወንድሞችን ፡ ወይም ፡
እኅቶችን ፡ ወይም ፡ አባትን ፡ ወይም ፡ እናትን ፡
ወይም ፡ ሚስትን ፡ ወይም ፡ ልጆችን ፡ ወይም ፡
እርሻን ፡ የተው ፡ ሁሉ ፡ መቶ ፡ እጥፍ ፡ ይቀበላል ፡
፴ የዘላለምንም ፡ ሕይወት ፡ ይወርሳል ። ነገር ፡
ግን ፡ ብዙዎቹ ፡ ፊተኞች ፡ ኋለኞች ፡ ኋለኞችም ፡
ፊተኞች ፡ ይሆናሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፳ ።

፩ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ለወይኑ ፡ አትክልት ፡
ሠራተኞችን ፡ ሊቀጥር ፡ ማልዶ ፡ የወጣ ፡ በለ
፪ ቤት ፡ ሰውን ፡ ትመስላለችና ። ሠራተኞችንም ፡
በቀን ፡ አንድ ፡ ዲናር ፡ ተስማምቶ ፡ ወደ ፡ ወይኑ ፡
፫ አትክልት ፡ ሰደዳቸው ። በሦስት ፡ ሰዓትም ፡
ወጥቶ ፡ ሥራ ፡ የፈቱ ፡ ሌሎችን ፡ በአደባባይ ፡
፬ ቆመው ፡ አየ ÷ እነዚያንም ፡— እናንተ ፡ ደግሞ ፡
ወደ ፡ ወይኔ ፡ አትክልት ፡ ሂዱ ፡ የሚገባውንም ፡
እሰጣችኋለሁ ፡ አላቸው ። እነርሱም ፡ ሄዱ ።
፭ ደግሞም ፡ በስድስትና ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ወጥቶ ፡
እንዲሁ ፡ አደረገ ። በአሥራ ፡ አንደኛውም ፡
፮ ሰዓት ፡ ወጥቶ ፡ ሌሎችን ፡ ቆመው ፡ አገኘና ፡—
ሥራ ፡ ፈትታችሁ ፡ ቀኑን ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ስለ
፯ ምን ፡ ትቆማላችሁ ? አላቸው ። የሚቀጥረን ፡
ስለ ፡ አጣን ፡ ነው ፡ አሉት ። እርሱም ፡— እናንተ ፡
ደግሞ ፡ ወደ ፡ ወይኔ ፡ አትክልት ፡ ሂዱ ፡ የሚገ
፰ ባውንም ፡ ትቀበላላችሁ ፡ አላቸው ። በመሸም ፡
ጊዜ ፡ የወይኑ ፡ አትክልት ፡ ጌታ ፡ አዘዘኝ ፡ ፡ ሠራ
ተኞችን ፡ ዋራኒ ፡ ከኋለኞች ፡ ጀምረህ ፡ እስከ ፡
ፊተኞች ፡ ድረስ ፡ ደመወዝ ፡ ስጣቸው ፡ አለው ።
፱ በአሥራ ፡ አንደኛው ፡ ሰዓትም ፡ የገቡ ፡ መጥ
ተው ፡ እያንዳንዳቸው ፡ አንድ ፡ ዲናር ፡ ተቀ
፲ በሉ ። ፊተኞችም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ አብዝተው ፡
የሚቀበሉ ፡ መስሎአቸው ፡ ነበር ፤ እነርሱም ፡
ደግሞ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ አንድ ፡ ዲናር ፡ ተቀ
፲፩ በሉ ። ተቀብለውም ፡— እነዚህ ፡ ኋለኞች ፡ አንድ ፡
ሰዓት ፡ ሠሩ ÷ የቀኑንም ፡ ድካምና ፡ ትኵሳት ፡
ከተሸከምን ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ አስተካከልሃቸው ፡
፲፪ ብለው ፡ በባለቤቱ ፡ ላይ ፡ አንሾራጩሩ ።ኢርሱ ፡
ግን ፡ መልሶ ፡ ከአነርሱ ፡ ለአንዱ ፡ እንዲህ ፡
አለው ፡— ወዳጄ ፡ ሆይ ÷ አልበደልሁህም ፤ በአ
፲፫ ንድ ፡ ዲናር ፡ አልተስማማኸኝምን ? ድርሻህን ፡
ውሰድና ፡ ሂድ ፤ እኔ ፡ ለዚህ ፡ ለኋለኛው ፡ እንደ ፡
፲፬ አንተ ፡ ልሰጠው ፡ እወዳለው ፡ በገንዘቤ ፡ የወደ
፲፭ ድሁትን ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡ መብት ፡ የለኝምን ?
ወይስ ፡ እኔ ፡ መልካም ፡ ስለ ፡ ሆንሁ ፡ ዓይንህ ፡
ምቀኛ ፡ ናትን ? እንዲሁ ፡ ኋለኞች ፡ ፊተኞች ፡
፲፮ ፊተኞችም ፡ ኋለኞች ፡ ይሆናሉ ፤ የተጠሩ ፡
ብዙዎች ፡ የተመረጡ ፡ ግን ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸውና ።
፲፯ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሊወጣ ፡
ሳለ ÷ በመንገድ ፡ አሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ደቀ ፡ መዘ
ሙርት ፡ ብቻቸውን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አቅርቦ ፡—
፲፰ እነሆ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንወጣለን ÷ የሰው ፡
ልጅም ፡ ለካህናት ፡ አለቆችና ፡ ለጻፎች ፡ ይሰ
ጣል ፤ የሞት ፡ ፍርድም ፡ ይፈርዱበታል ÷
፲፱ ሊዘበቱበትም ፡ ሊገርፉትም ፡ ሊሰቅሉትም ፡
ለአሕዛብ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡታል ÷ በሦስተኛ
ውም ፡ ቀን ፡ ይነሣል ፡ አላቸው ።
፳ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የዘብዴዎስ ፡ ልጆች ፡ እናት ፡
ከልጆችዋ ፡ ጋር ፡ እየሰገደችና ፡ አንድ ፡ ነገር ፡
፳፩ እየለመነች ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀረበች ። እርሱም ፡— ም
ን ፡ ትፈልጊያለሽ ? አላት ። እርስዋም ፡— እነ
ዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ልጆቼ ፡ አንዱ ፡ በቀኝህ ፡ አንዱም ፡
በግራህ ፡ በመንግሥትህ ፡ እንዲቀመጡ ፡ አዘዝ ፡
፳፪ አሉአቸው ። ኢየሱስ ፡ ግን ፡ መልሶ ፡— የምትለም
ኑትን ፡ አታውቁም ። እኔ ፡ ልጠጣው ፡ ያለውን ፡
ጽዋ ፡ ልትጠጡ ፡ እኔም ፡ የምጠመቀውን ፡ ጥም
ቀት ፡ ልትጠመቁ ፡ ትችላላችሁን ? አለ ። እነች
ላለን ፡ አሉት ። እርሱም ፡— ጽዋዬንስ ፡ ትጠ
፳፫ ጣላችሁ ፤ በቀኜና ፡ በግራ ፡ መቀመጥ ፡ ግን ፡ ከእ
ኔ ፡ ዘንድ ፡ ለተዘጋጀላቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡
የምሰጥ ፡ አይደለሁም ፡ አላቸው ። አሥሩም ፡
፳፬ ሰምተው ፡ በሁለቱ ፡ ወንድማማች ፡ ተቈጡ ።
፳፭ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡
አላቸው ፡— የአሕዛብ ፡ አለቆች ፡ እንዲገዙአ
ቸው ፡ ታላላቆቹም ፡ በላያቸው ፡ እንዲሠለጥኑ ፡
ታውቃላችሁ ። በእናንተስ ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፡
፳፮ ነገር ፡ ግን ፡ ማንም ፡ ከእናንተ ፡ ታላቅ ፡ ሊሆን ፡
የሚወድ ፡ የእናንተ ፡ አገልጋይ ፡ ይሁን ÷ ከእ
፳፯ ናንተም ፡ ማንም ፡ ፊተኛ ፡ ሊሆን ፡ የሚወድ ፡
የእናንተ ፡ ባሪያ ፡ ይሁን ፤ እንዲሁም ፡ የሰው ፡
፳፰ ልጅ ፡ ሊያገለግል ፡ ነፍሱንም ፡ ለብዙዎች ፡ ቤዛ ፡
ሊሰጥ ፡ እንጂ ፡ እንዲያገለግሉት ፡ አልመጣም ።
፳፱ ከኢያሪኮም ፡ ሲወጡ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተከተ
ሉት ። እነሆም ፡ ሁለት ፡ ዕውሮች ፡ በመንገድ ፡
፴ ዳር ፡ ተቀምጠው ÷ ኢየሱስ ፡ እንዲያልፍ ፡
በሰሙ ፡ ጊዜ ፡— ጌታ ፡ ሆይ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ÷
ማረን ፡ ብለው ፡ ጮኹ ። ሕዝቡም ፡ ዝም ፡ እን
፴፩ ዲሉ ፡ ገሠጹአቸው ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡— ጌታ ፡ ሆይ ÷
የዳዊት ፡ ልጅ ÷ ማረን ፡ እያሉ ፡ አብዝተው ፡
ጮኹ ። ኢየሱስም ፡ ቆሞ ፡ ጠራቸውና ፡— ምን ፡
፴፪ ላደርግላችሁ ፡ ትወዳላችሁ ? አለ ። ጌታ ፡ ሆይ ÷
፴፫ ዓይኖቻችን ፡ ይከፈቱ ፡ ዘንድ ፡ አሉት ። ኢየሱ

ስም ፡ አዘነላቸውና ፡ ዓይኖቻቸውን ፡ ዳሰሰ ÷ ወዲያውም ፡ አዩና ፡ ተከተሉት ።

ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

፩ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ቀርበው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ፋጌ ፡ ሲደርሱ ÷ ያንጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ ከደቀ ፡ መዘሙርቱ ፡ ሁለት ፡ ላከ ÷ እንዲህም ፡ አላቸው ፡ — በፊታችሁ ፡ ወዳለችው ፡ መንደር ፡ ሂዱ ÷ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ የታሰረችን ፡ አህያ ፡ ውርንጫም ፡ ከእርስዋ ፡ ጋር ፡ ታገኛላችሁ ፤ ፈትታችሁ ፡ አምጡልኝ ። ፫ ማንም ፡ አንዳች ፡ ቢላችሁ ፡ — ለጌታ ፡ ያስፈልጉታል ፡ በሉ ፤ ወዲያውም ፡ ይሰዳቸዋል ።

፬ ፭ ለጽዮን ፡ ልጅ ፡ — እነሆ ÷ ንጉሥሽ ፡ የዋህ ፡ ሆኖ ፡ በአህያ ፡ ላይና ፡ በአህያይቱ ፡ ግልገል ፡ በውርንጫይቱ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ይመጣል ፡ በሉአት ፡

ተብሎ ፡ በነቢይ ፡ የተነገረው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ሆነ ። ፮ ደቀ ፡ መዘሙርቱም ፡ ሄደው ፡ ኢየሱስ ፡ እንዳዘዛቸው ፡ አደረጉ ÷ ፯ አህያይቱንና ፡ ውርንጫዋንም ፡ አመጡለት ÷ ልብሳቸውንም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ጫኑ ÷ ተቀመጠባቸውም ። ፰ ከሕዝቡም ፡ እጅግ ፡ ብዙዎች ፡ ልብሳቸውን ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ አነጠፉ ÷ ሌሎችም ፡ ከዛፍ ፡ ጫፍ ፡ ጫፉን ፡ እየቈረጡ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ያነጥፉ ፡ ነበር ። ፱ የሚቀድሙትም ፡ ሕዝብ ፡ የሚከተሉትም ፡ — ሆሣዕና ፡ ለዳዊት ፡ ልጅ ፤ በጌታ ፡ ስም ፡ የሚመጣ ፡ የተባረከ ፡ ነው ፤ ሆሣዕና ፡ በአርያም ፡ አያሉ ፡ ይጮኹ ፡ ነበር ። ፲ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ መላው ፡ ከተማ ፡ — ይህ ፡ ማን ፡ ነው ? ብሎ ፡ ተናወጠ ። ፲፩ ሕዝቡም ፡ — ይህ ፡ ከገሊላ ፡ ናዝሬት ፡ የመጣ ፡ ነቢይ ፡ ኢየሱስ ፡ ነው ፡ አሉ ።

፲፪ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ገባና ፡ በመቅደስ ፡ የሚሸጡትንና ፡ የሚገዙትን ፡ ሁሉ ፡ አወጣ ÷ የገንዘብ ፡ ለዋጮችንም ፡ ገበታዎች ፡ የርግብ ፡ ሻጮችንም ፡ ወንበሮች ፡ገለበጠና ፡ — ፲፫ ቤቴ ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ትባላለች ፡ ተብሎ ፡ ተጽፎአል ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ የወንበዶች ፡ ዋሻ ፡ አደረጋችኋት ፡ አላቸው ።

፲፬ በመቅደስም ፡ ዕውሮችና ፡ አንካሶች ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀረቡና ፡ ፈወሳቸው ። ፲፭ ነገር ፡ ግን ፡ የካህናት ፡ አለቆችና ፡ ጻፎች ፡ ያደረገውን ፡ ድንቃድንቅ ፡ በመቅደስም ፡ — ሆሣዕና ፡ ለዳዊት ፡ ልጅ ፡ እያሉ ፡ የሚጮኹትን ፡ ልጆች ፡ በዩ ፡ ጊዜ ÷ ተቈጥተው ፡ — ፲፮ እነዚህ ፡ የሚሉትን ፡ አትሰማምን ? አሉት ። ኢየሱስም ፡ — አሰማለሁ ፤ ከሕፃናትና ፡ ከሚጠቡት ፡ አፍ ፡ ምስጋናን ፡ ለራስህ ፡ አዘጋጀህ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ከቶ ፡ አላነበባችሁምን ? ፲፯ አላቸው ። ትቶአቸውም ፡ ከከተማ ፡ ወደ ፡ ቢታንያ ፡ ወጣ ፡ በዚያም ፡ አደረ ።

፲፰ በማለዳም ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ሲመለስ ፡ ተራበ ። ፲፱ በመንገድም ፡ አጠገብ ፡ በለስ ፡ አይቶ ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡ መጣ ፤ ከቅጠልም ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አላገኘባትምና ፡ — ለዘላለሙ ፡ ፍሬ ፡ አይገኝብሽ ፡ አሳት ። በለሲቱም ፡ ያንጊዜውን ፡ ደረቀች ። ፳ ደቀ ፡ መዘሙርቱም ፡ ይህን ፡ አይተው ፡ — በለሲቲቱ ፡ ያንጊዜውን ፡ እንዴት ፡ ደረቀች ? ብለው ፡ ተደነቁ ። ፳፩ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ — እውነት ፡ እላችኋለሁ ÷ እምነት ፡ ቢኖራችሁ ፡ በትጠራጠሩም ÷ በበለሲቱ ፡ እንደ ፡ ሆነባት ፡ ብቻ ፡ አታደርጉም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ተራራ ፡ እንኳ ፡ — ተነቅለህ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ተወርወር ፡ ብትሉት ፡ ይሆናል ። ፳፪ አምናችሁም ፡ በጸሎት ፡ የምትለምኑትን ፡ ሁሉ ፡ ትቀበላላችሁ ፡ አላቸው ።

፳፫ ወደ ፡ መቅደስም ፡ ገብቶ ፡ ሲያስተምር ፡ የካህናት ፡ አለቆችና ፡ የሕዝብ ፡ ሽማግሌች ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀረቡና ፡ — በምን ፡ ሥልጣን ፡ እነዚህን ፡ ታደርጋለህ ? ይህንስ ፡ ሥልጣን ፡ ማን ፡ ሰጠህ ? አሉት ። ፳፬ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ — እኔ ፡ ደግሞ ፡ አንዲት ፡ ነገር ፡ እጠይቃችኋለሁ ፤ እናንተም ፡ ያችን ፡ ብትነግሩኝ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እነዚህን ፡ በምን ፡ ሥልጣን ፡ እንዳደርግ ፡ እነግራችኋለሁ ፤ ፳፭ የዮሐንስ ፡ ጥምቀት ፡ ከወዴት ፡ ነበረች ፡ ከሰማይን ፡ ወይስ ፡ ከሰው ? አላቸው ። እነርሱም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲነጋገሩ ፡ — ከሰማይ ፡ ብንል ፡ — እንኪያስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አላመናችሁበትም ? ይለናል ፤ ፳፮ ከሰው ፡ ግን ፡ ብንል ÷ ዮሐንስን ፡ ሁሉም ፡ እንደ ፡ ነቢይ ፡ ያዩታልና ፡ ሕዝቡን ፡ እንፈራለን ፤ አሉ ። ፳፯ ለኢየሱስም ፡ መልሰው ፡ — እናውቅም ፡ አሉት ። እርሱም ፡ ደግሞ ፡ — እኔም ፡ በምን ፡ ሥልጣን ፡ እነዚህን ፡ እንዳደርግ ፡ አልነግራችሁም ፡ አላቸው ።

፳፰ ነገር ፡ ግን ፡ ምን ፡ ይመስላችኋል ? አንድ ፡ ሰው ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፤ ወደ ፡ አንደኛው ፡ ቀርቦ ፡ — ልጄ ፡ ሆይ ፡ ዛሬ ፡ ሂድና ፡ በወይኔ ፡ አትክልት ፡ ሥራ ፡ አለው ። ፳፱ እርሱም ፡ መልሶ ፡ — አልወድም ፡ አለ ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ ተጸጸተና ፡ ሄደ ። ፴ ወደ ፡ ሁለተኛውም ፡ ቀርቦ ፡ እንዲሁ ፡ አለው ፡ እርሱም ፡ መልሶ ፡ — እሺ ፡ ጌታዬ ፡ አለ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አልሄደም ። ፴፩ ከሁለቱ ፡ የአባቱን ፡ ፈቃድ ፡ ያደረገ ፡ ማን ፡ ነው ? ፈተኖው ፡ አሉት ። ኢየሱስ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ — እውነት ፡ እላችኋለሁ ÷ ቀራጮችና ፡ ጋለሞቶች ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ በመግባት ፡ ይቀድሙአችኋል ። ፴፪ ዮሐንስ ፡ በጽድቅ ፡ መንገድ ፡ መጥቶላችሁ ፡ ነበርና ÷ አላመናችሁበትም ፤ ቀራጮችና ፡ ጋለሞቶች ፡ ግን ፡ አመኑበት ፤ እናንተም ፡ ይህን ፡ አይታችሁ ፡ ታምኑበት ፡ ዘንድ ፡ በኋላ ፡ ንስሐ ፡ አልገባችሁም ።

፴፫ ሌላ ፡ ምሳሌ ፡ ስሙ ። የወይን ፡ አትክልት ፡ የተከለ ፡ ባለቤት ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ቅጥርም ፡ ቀጠረለት ÷ መጥመቂያም ፡ ማሰለት ÷ ግንብም ፡ ሠራ ፡ ለገበሬዎች ፡ አከራይቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ሄደ ። ፴፬ የሚያፈራበትም ፡ ጊዜ ፡ ሲቀርብ ÷ ፍሬውን ፡ ሊቀበሉ ፡ ባሮቹን ፡ ወደ ፡ ገበሬዎች ፡ ላከ ። ፴፭ ገበሬዎችም ፡ ባሮቹን ፡ ይዘው ፡ አንዱን ፡ ደበደቡት ፡ አንዱንም ፡ ገደሉት ፡ ሌላውንም ፡ ወገሩት ። ፴፮ ደግሞ ፡ ከፊተኞች ፡ የሚበዙ ፡ ሌሎች ፡ ባሮች ፡ ላከ ÷ እንዲሁም ፡ አደረጉባቸው ። ፴፯ በኋላ ፡ ግን ፡ — ልጄንስ ፡ ያፍሩታል ፡ ብሎ ፡ ልጁን ፡ ላከባቸው ። ፴፰ ገበሬዎቹ ፡ ግን ፡ ልጁን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ — ወራሹ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እንግደለውና ፡ ርስቱን ፡ እናግኝ ፡ ተባባሉ ። ፴፱ ይዘውም ፡ ከወይኑ ፡ አትክልት ፡ አወጡና ፡ ገደሉት ። እንግዲህ ፡ የወይኑ ፡ አትክልት ፡ ጌታ ፡ በሚመጣ ፡ ጊዜ ፡ በእነዚህ ፡ ገበሬዎች ፡ ምን ፡ ያደርግባቸዋል ? እነርሱም ፡ — ክፋዎችን ፡ በክፉ ፡ ያጠፋቸዋል ÷ የወይኑንም ፡ አትክልት ፡ ፍሬውን ፡ በየጊዜው ፡ ለሚያስረክቡ ፡ ለሌሎች ፡ ገበሬዎች ፡ ይሰጠዋል ፡ አሉት ።

፵፪ ኢየሱስ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ —

ግንበኞች ፡ የናቁ ፡ ድንጋይ ÷ እርሱ ፡ የማዕዘን ፡ ራስ ፡ ሆነ ፤ ይህም ፡ ከጌታ ፡ ዘንድ ፡ ሆነ ÷ ለዓይኖቻችንም ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡

የሚሉውን ፡ ከቶ ፡ በመጽሐፍ ፡ አላነበባችሁምን ?

፵፫ ስለዚህ ፡ እላችኋለሁ ÷ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ከእናንተ ፡ ትወሰዳለች ፡ ፍሬዋንም ፡ ለሚያደርግ ፡ ሕዝብ ፡ ትሰጣለች ። ፵፬ በዚህም ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ የሚወድቅ ፡ ይቀጠቀጣል ፤ ድንጋዩ ፡ ግን ፡ የሚወድቅበትን ፡ ሁሉ ፡ ይፈጨዋል ።

፵፭ የካህናት ፡ አለቆችና ፡ ፈሪሳውያንም ፡ ምሳሌዎቹን ፡ ሰምተው ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ አስተዋሉ ፤ ፵፮ ሊይዙትም ፡ ሲፈልጉት ፡ ሰዎ ፡ ሕዝቡ ፡ እንደ ፡ ነቢይ ፡ ስላዩት ፡ ፈሩአቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

፩ ኢየሱስም ፡ መለሰ ፡ ደግሞም ፡ በምሳሌ ፡ ነገራቸው ፡ እንዲህም ፡ አለ ፡ — ፪ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ለልጁ ፡ ሰርግ ፡ ያደረገ ፡ ንጉሥን ፡ ትመስላለች ። ፫ የታደሙትንም ፡ ወደ ፡ ሰርጉ ፡ ይጠሩ ፡ ዘንድ ፡ ባሮቹን ፡ ላከ ፡ ሊመጡም ፡ አልወደዱም ። ፬ ደግሞ ፡ ሌሎችን ፡ ባሮች ፡ ልከ ፡ — የታደሙትን ፡ — እነሆ ፡ ድግሴን ፡ አዘጋጀሁ ÷ ከርማም ፡ ቄና ፡ የሰቡት ፡ ከብቶቼ ፡ ታርደዋል ÷ ሁሉም ፡ ተዘጋጅቶአል ፤ ወደ ፡ ሰርጉ ፡ ኑ ፡ በሉአቸው ። ፭ አለ ። እነርሱ ፡ ግን ፡ ቸል ፡ ብለው ፡ አንዱ ፡ ወደ ፡ እርሻው ÷ ሌላውም ፡ ወደ ፡ ንግዱ ፡ ሄደ ፤ ፮ የቀሩትም ፡ ባሮቹን ፡ ይዘው ፡ አንገላቱአቸው ፡ ገደሉአቸውም ። ፯ ንጉሡም ፡ ተቈጣ ÷ ጭፍሮቹንም ፡ ልከ ፡ እነዚያን ፡ ገዳዮች ፡ አጠፋ ፤ ከተማቸውንም ፡ አቃጠለ ። ፰ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ባሮቹን ፡ — ሰርጉ ፡ ተዘጋጅቶአል ÷ ነገር ፡ ግን ፡ የታደሙት ፡ የማይገባቸው ፡ ሆኑ ፤ ፱ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ መንገድ ፡ መተላለፊያ ፡ ሄዳችሁ ፡ ያገኛቸሁትን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ሰርጉ ፡ ጥሩ ፡ አለ ። ፲ እነዚያም ፡ ባሮች ፡ ወደ ፡ መንገድ ፡ ወጥተው ፡ ያገኙትን ፡ ሁሉ ፡ ክፉዎችንም ፡ በጎዎችንም ፡ ሰበሰቡ ፤ የሰርጉንም ፡ ቤት ፡ ተቀማጮች ፡ ሞሉት ።

፲፩ ንጉሡም ፡ የተቀመጡትን ፡ ለማየት ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ የሰርግ ፡ ልብስ ፡ ያለበሰ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አየና ፡ — ወዳጄ ፡ ሆይ ÷ የሰርግ ፡ ልብስ ፡ ሳትለብስ ፡ እንዴት ፡ ወደዚህ ፡ ገባህ ? አለው ፤ ፲፪ እርሱም ፡ ዝም ፡ አለ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ አገልጋዮቹን ፡ — እጁንና ፡ እግሩን ፡ አስራችሁ ፡ በውጭ ፡ ወዳለው ፡ ጨለማ ፡ አውጡት ፤ በዚያ ፡ ልቅሶና ፡ ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ይሆናል ፡ አለ ። ፲፫ የተጠሩ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ፡ የተመረጡ ፡ ግን ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸውና ።

፲፬ ስለዚህ ፡ ፈሪሳውያን ፡ ሄዱና ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ በነገር ፡ እንዲያጠምዱት ፡ ተማከሩ ። ፲፭ ደቀ ፡ መዘሙርታቸውንም ፡ ከሄሮድስ ፡ ወገን ፡ ጋር ፡ ላኩበት ÷ እነርሱም ፡ — መምህር ፡ ሆይ ÷ እውነተኛ ፡ እንደ ፡ ሆንህ ፡ በእውነትም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንገድ ፡ እንድታስተምር ፡ እናውቃለን ÷ ለማንምም ፡ አታደላም ÷ የሰውን ፡ ፊት ፡ አትመለከትምና ፤ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ይመስልሃል ? ንገረን ፤ ለቄሣር ፡ ግብር ፡ መስጠት ፡ ተፈቅዶአልን ፡ ወይስ ፡ አልተፈቀደም ? አሉት ። ፲፮ ኢየሱስም ፡ ክፋታቸውን ፡ አውቆ ፡ — እናንተ ፡ ግብዞች ÷ ስለ ፡ ምን ፡ ትፈትኑኛላችሁ ? የግብሩን ፡ ብር ፡ አሳዩኝ ፡ አለ ። እነርሱም ፡ ዲናር ፡ አመጡለት ። ፲፯ እርሱም ፡ — ይህች ፡ መልክ ፡ ጽሕፈቷስ ፡ የማን ፡ ናት ? አላቸው ። የቄሣር ፡ ነው ፡ አሉት ። ፲፰ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ — እንኪያስ ፡ የቄሣርን ፡ ለቄሣር ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አስረክቡ ፡ አላቸው ። ፲፱ ይህንም ፡ ሰምተው ፡ ተደነቁ ፡ ትተውትም ፡ ሄዱ ።

፳ በዚያን ፡ ቀን ፡ — ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ የለም ፡ የሚሉ ፡ ሰዱቃውያን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀረቡ ÷ ፳፩ እንዲህም ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ፡ — መምህር ፡ ሙሴ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ሳይወልድ ፡ ሲሞት ፡ ወንድሙ ፡ ሚስቱን ፡ አግብቶ ፡ ለወንድሙ ፡ ዘር ፡ ይተካ ፡ አለ ። ፳፪ ሰባት ፡ ወንድማማች ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ነበሩ ፤ ፈተኛውም ፡ ሚስት ፡ አግብቶ ፡ ሞተ ÷ ዘርም ፡ ስለሌለው ፡ ሚስቱን ፡ ለወንድሙ ፡ ተወለት ፤ ፳፫ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ ሁለተኛው ፡ ሦስተኛውም ፡ እስከ ፡ ሰባተኛው ፡ ድረስ ። ፳፬ ከሁሉም ፡ በኋላ ፡ ሴቲቱ ፡ ሞተች ። ፳፭ ሁሉ ፡ አግብተዋልና ፡ በትንሣኤ ፡ ቀንስ ፡ ከሰባቱ ፡ ለማናቸው ፡ ሚስት ፡ ትሆናለች ?

፳፮ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ — መጻሕፍትንና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ኃይል ፡ አታ

፴፥ ውቱምና ፡ ትስታላችሁ ። በትንሣኤስ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መላእክት ፡ በሰማይ ፡ ይሆናሉ
፴፩-፴፪ እንጂ ፡ አያገቡም ፡ አይጋቡምም ። ስለ ፡ ትን ሣኤ ፡ ሙታን ፡ ግን ፡—እኔ ፡ የአብርሃም ፡ አም ላክ ፡ የይስሐቅም ፡ አምላክ ፡ የያዕቆብም ፡ አም ላክ ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ የተባለውን ፡ አላነበባችሁምን ? የሕያዋን ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሙታን ፡
፴፫ አይደለም ። ሕዝቡም ፡ ይህን ፡ ሰምተው ፡ በት ምህርቱ ፡ ተገረሙ ።
፴፬፡ ፈሪሳውያንም ፡ ሰዱቃውያንን ፡ ዝም ፡ እንዳ ሰኛቸው ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ አብረው ፡ ተሰበሰቡ ።
፴፭፡ ከእነርሱም ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ አዋቂ ፡ ሊፈትነው ፡—
፴፮፡ መምህር ፡ ሆይ ፡ ከሕግ ፡ ማናቸይቱ ፡ ትእዛዝ ፡
፴፯፡ ታላቅ ፡ ናት ? ብሎ ፡ ጠየቀው ። ኢየሱስም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡— ጌታ ፡ አምላክህን ፡ በፍ ጹም ፡ ልብህ ፡ በፍጹም ፡ ነፍስህም ፡ በፍጹም ፡
፴፰፡ አሳብህም ፡ ውደድ ። ታላቂቱና ፡ ፈተኖያቱ ፡
፴፱፡ ትእዛዝ ፡ ይህች ፡ ናት ። ሁለተኛይቱም ፡ ይህ ችን ፡ ትመስላለች ፡ እርስዋም ፡—ባልንጀራህን ፡
፵፡ እንደ ፡ ነፍስህ ፡ ውደድ ፡ የምትለው ፡ ናት ። አሪስና ፡ ነቢያት ፡ በእነዚህ ፡ በሁለቱ ፡ ትእዛዛት ፡ ጸኑ ።
፵፩-፵፪ ፈሪሳውያንም ፡ ተሰብስበው ፡ ሳሉ ፡ ኢየ ሱስ ፡— ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ምን ፡ ይመስላችኋል ፡ የማን ፡ ልጅ ፡ ነው ? ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። የዳ
፵፫-፵፬ ዊት ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ አሉት ። እርሱም ፡— እንኪ ያስ ፡ ዳዊት ፡—
ጌታ ፡ ጌታዬን ፡—ጠላቶችህን ፡ የእግርህ ፡ መረገጫ ፡ እስክደርግልህ ፡ ድረስ ፡ በቀኜ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ፡
ሲል ፡ እንዴት ፡ በመንፈስ ፡ ጌታ ፡ ብሎ ፡ ይጠ
፵፭፡ ራዋል ? ዳዊትስ ፡ ጌታ ፡ ብሎ ፡ ከጠራው ፡ እን
፵፮፡ ዴት ፡ ልጁ ፡ ይሆናል ? አላቸው ። አንድም ፡ ቃል ፡ ስንኳ ፡ ይመልስለት ፡ ዘንድ ፡ የተቻለው ፡ የለም ፡ ከዚያ ፡ ቀንም ፡ ጀምሮ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ማንም ፡ ሊጠይቀው ፡ አልደፈረም ።

ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

፩፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ ለሕዝቡና ፡ ለደቀ
፪፡ መዛሙርቱ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገራቸው ፡— ጻፎ ችና ፡ ፈሪሳውያን ፡ በሙሴ ፡ ወንበር ፡ ተቀምጠ
፫፡ ዋል ። ስለዚህ ፡ ያዘዙአችሁን ፡ ሁሉ ፡ አድርጉ ፡ ጠብቁትም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እየተናገሩ ፡ እያደር
፬፡ ጉትምና ፡ እንደ ፡ ሥራቸው ፡ አታድርጉ ። ከባ ድንና ፡ አስቸጋሪ ፡ ሸክም ፡ ተጠቅለው ፡ በሰው ፡ ትከሻ ፡ ይጭናሉ ፡ እነርሱ ፡ ግን ፡ በጣታቸው ፡
፭፡ ስንኳ ፡ ሊነኩት ፡ አይወዱም ። ለሰውም ፡ እንዲ ታዩ ፡ ሥራቸውን ፡ ሁሉ ፡ ያደርጋሉ ። ስለዚህ ፡
፮፡ አሸንኩታባቸውን ፡ ያሰፋሉ ። ዘርፉንም ፡ ያስረ ዝማሉ ። በምሳም ፡ የከበሬታ ፡ ስፍራ ፡ በሃይኩ ፡
፯፡ ራብም ፡ የነበረታ ፡ ወንበር ፡ በገበያም ፡ ሰላም
፰፡ ታኖ ፡— መምህር ፡ ሆይ ፡ መምህር ፡ ሆይ ፡ ተብ ለው ፡ እንዲጠሩ ፡ ይወዳሉ ። እናንት ፡ ግን ፡—
፱፡ መምህር ፡ ተብላችሁ ፡ አትጠሩ ፡ መምህራችሁ ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እናንተም ፡ ሁላችሁ ፡ ወንድ ማማች ፡ ናችሁ ። አባታችሁ ፡ አንዱ ፡ እርሱም ፡
፲፡ የሰማዩ ፡ ነውና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ማንንም ፡— አባት ፡ ብላችሁ ፡ አትጥሩ ። ሊቃችሁ ፡ አንድ ፡ እርሱም ፡ ክርስቶስ ፡ ነውና ፡— ሊቃውንት ፡ ተብላችሁ ፡ አትጠሩ ። ከእናንተም ፡ የሚበል
፲፩፡ ጠው ፡ አገልጋያችሁ ፡ ይሆናል ። ራሱን ፡ ከፍ
፲፪፡ የሚያደርግ ፡ ሁሉ ፡ ይዋረዳል ፡ ራሱንም ፡ የሚ ያዋርድ ፡ ሁሉ ፡ ከፍ ፡ ይላል ።
፲፫፡ እናንት ፡ ግብዞች ፡ ጻፎችና ፡ ፈሪሳውያን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ስለምት ዘጉ ፡ ወዮላችሁ ። እናንት ፡ አትገቡም ፡ የሚገ
፲፬፡ ቡትንም ፡ እንዳይገቡ ፡ ተከለክላላችሁ ። እና ንት ፡ ግብዞች ፡ ጻፎችና ፡ ፈሪሳውያን ፡ በጸሎት ፡ ርዝመት ፡ እያመካኛችሁ ፡ የመበለቶችን ፡ ቤት ፡ ስለምትበሉ ፡ ወዮላችሁ ፡ ስለዚህ ፡ የባሰ ፡ ፍርድ ፡ ትቀበላላችሁ ። እናንት ፡ ግብዞች ፡ ጻፎችና ፡
፲፭፡ ፈሪሳውያን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ልታሳምኑ ፡ በባሕ ርና ፡ በደረቅ ፡ ስለምትዞሩ ፡ በሆነም ፡ ጊዜ ፡ ከእ ናንተ ፡ ይልቅ ፡ ሁለት ፡ እጥፍ ፡ የበሰ ፡ የገሃንም ፡ ልጅ ፡ ስለምታደርጉት ፡ ወዮላችሁ ።
፲፮፡ እናንት ፡— ማንም ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ የሚ ምል ፡ ምንም ፡ የለበትም ፤ ማንም ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወርቅ ፡ የሚምል ፡ ግን ፡ በመሐላው ፡ ይያዛል ፡ የምትሉ ፡ ዕውሮች ፡ መሪዎች ፡ ወዮ
፲፯፡ ላችሁ ። እናንት ፡ ደንቆሮዎችና ፡ ዕውሮች ፡ ማናቸው ፡ ይበልጣል ? ወርቁ ፡ ነውን ? ወይስ ፡ ወርቁን ፡ የቀደሰው ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ? ያልማች
፲፰፡ ሁም ፡— ማንም ፡ በመሠዊያው ፡ የሚምል ፡ ምንም ፡ የለበትም ፤ ማንም ፡ በላዩ ፡ በሰው ፡ መባ ፡ የሚምል ፡ ግን ፡ በመሐላው ፡ ይያዛል ፡ ትላላ
፲፱፡ ችሁ ። እናንተ ፡ ደንቆሮዎችና ፡ ዕውሮች ፡ ማና ቸው ፡ ይበልጣል ? መባው ፡ ነውን ? ወይስ ፡ መባውን ፡ የሚቀድሰው ፡ መሠዊያው ? እንግ
፳፡ ዲህ ፡ በመሠዊያው ፡ የሚምለው ፡ በእርሱና ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ሁሉ ፡ ይምላል ፡ በቤተ ፡ መቅደስም ፡ የሚምለው ፡ በእርሱና ፡ በእርሱ ፡
፳፪፡ በሚኖረው ፡ ይምላል ። በሰማይም ፡ የሚምለው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዙፋንና ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ በተ ቀመጠው ፡ ይምላል ።
፳፫፡ እናንተ ፡ ግብዞች ፡ ጻፎችና ፡ ፈሪሳውያን ፡ ከአ

ሮቁ ። ፴፪ ፤ ዘዳኢ. ፮÷፭ ። ፴፭—፴፱ ፤ ማር. ፲፪÷ሮቁ—፴፩፡ ሉቃ. ፲÷ሮ፭ ። ፴፮ ፤ ዘዳግ. ፮÷፭ ። ፴፱ ፤ ዘሌዋ. ፲፱÷፲፰ ። ፵፩—፵፭ ፤ ማር. ፲፪÷ሮ፭—ሮ፮፡ ሉቃ. ፳÷፵፩—፵፬ ። ፵፱ ፤ መዝ. ፻፱÷፩ ።

ሮቃ ። ፩ ፤ ሉቃ. ፳÷፵፯ ። ፪ ፤ ሉቃ. ፲፩÷፵፭ ። ፫ ፤ ም. ፭÷፭ ፤ ዘዕኡ. ፲፫÷፩ ። ፭ ፤ ዘኁል. ፲፭÷ሮ፭ ። ፮ ፤ ፯ ፤ ማር. ፲፪÷ ሮ፭ ፤ ሮ፱ ፤ ሉቃ. ፲፩÷፵፫ ፤ ፲፱÷፯ ፤ ፳÷፵፯ ። ፰ ፤ ም. ፭÷፭ ፤ ዘዕኡ. ፲፱÷፲፰ ። ፲፩ ፤ ም. ፻፳÷፮ ፤ ፻፵፭ ። ፲፪ ፤ ም. ፱÷፪ ፤ ፭÷፲፭ ። ፲፫ ፤ ም. ፻፳÷፮፻፭ ። ፲፬ ፤ ም. ፻፳÷፲፪ ። ፲፭ ፤ ሉቃ. ፲፩÷፵፫ ። ፲፮ ፤ ሉቃ. ፲፩÷፵፬ ። ፲፯ ፤ ማር. ፲፪÷ሮ፱ ፤ ሉቃ. ፳÷፵፯ ። ፲፰ ፤ ም. ፲፭÷፲፱ ። ፲፱ ፤ ዘዕኡ. ፳፱÷ሮ፭ ። ፳፪ ፤ ዘሌዋ. ፳፯÷፲፪ ። ፳፫ ፤ ሉቃ. ፲፩÷፵፪ ።

ዝሙድና ፡ ከእንስላል ፡ ከከሙንም ፡ አሥራት ፡ ስለምታወጡ ፡ ፍርድንና ፡ ምሕረትን ፡ ታማኝ ነትንም ፡ በሕግ ፡ ያለውን ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ስለምት ተዉ ፡ ወዮላችሁ ፤ ሴላውን ፡ ሳትተዉ ፡ ይህን ፡
፳፬፡ ልታደርጉ ፡ ይገባችሁ ፡ ነበር ። እናንተ ፡ ዕው ሮች ፡ መሪዎች ፡ ትንኝን ፡ የምታጠሩ ፡ ግመል ንም ፡ የምትውጡ ።
፳፭፡ እናንተ ፡ ግብዞች ፡ ጻፎችና ፡ ፈሪሳውያን ፡ ሆ በስጡ ፡ ቅሚያና ፡ ስስት ፡ ሞልቶ ፡ ሳለ ፡ የጽ ዋውንና ፡ የወጭቱን ፡ ውጭ ፡ ስለምታጠሩ ፡
፳፮፡ ወዮላችሁ ። እንተ ፡ ዕውር ፡ ፈሪሳዊ ፡ ውጭው ፡ ደግሞ ፡ ጥሩ ፡ እንዲሆን ፡ አስቀድመህ ፡ የጽዋ ውንና ፡ የወጭቱን ፡ ውስጡን ፡ አጥራ ።
፳፯፡ እናንተ ፡ ግብዞች ፡ ጻፎችና ፡ ፈሪሳውያን ፡ ሆ በውጭ ፡ አምረው ፡ የሚታዩ ፡ በውስጥ ፡ ግን ፡ የሙታን ፡ አጥንት ፡ ርኩሰትም ፡ ሁሉ ፡ የተሞሉ ፡ በኖራ ፡ የተለሰኑ ፡ መቃብሮችን ፡ ስለምትመ
፳፰፡ ስሉ ፡ ወዮላችሁ ። እንዲሁ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ በውጭ ፡ ለሰው ፡ እንደ ፡ ጻድቃን ፡ ትታያላችሁ ፡ በውስጣችሁ ፡ ግን ፡ ግብዝነትና ፡ ዓመፀኝነት ፡ ሞልቶባችኋል ።
፳፱፡ እናንተ ፡ ግብዞች ፡ ጻፎችና ፡ ፈሪሳውያን ፡ የነ ቢያትን ፡ መቃብር ፡ ስለምትሠሩ ፡ የጻድቃንንም ፡
፴፡ መቃብር ፡ ስለምታስጌጡና ፡— በእባቶቻችን ፡ ዘመን ፡ ኖረን ፡ በሆነስ ፡ በነቢያት ፡ ደም ፡ በእልተ ባበርናቸውም ፡ ነበር ፡ ስለምትሉ ፡ ወዮላችሁ ።
፴፩፡ እንግዲያስ ፡ የነቢያት ፡ ገዳዮች ፡ ልጆች ፡ እንደ ሆናችሁ ፡ በራሳችሁ ፡ ላይ ፡ ትመሰክራላችሁ ።
፴፪፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ የአባቶቻችሁን ፡ መስፈሪያ
፴፫፡ ሙሉ ። እናንተ ፡ እባቦች ፡ የእፉኝት ፡ ልጆች ፡ ከገሃነም ፡ ፍርድ ፡ እንዴት ፡ ታመልጣላችሁ ?
፴፬፡ ስለዚህ ፡ እነሆ ፡ ነቢያትንና ፡ ጥበበኞችን ፡ ጻፎ ችንም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እልካለሁ ፤ ከእነርሱም ፡ ትገድላላችሁ ፡ ትሰቅሉማላችሁ ፡ ከእነርሱም ፡ በምኵራባችሁ ፡ ትገርፋላችሁ ፡ ከከተማም ፡
፴፭፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ታሳድዳላችሁ ፤ ከጻድቁ ፡ ከአቤል ፡ ደም ፡ ጀምሮ ፡ በቤተ ፡ መቅደስና ፡ በመሠዊያው ፡ መካከል ፡ እስከ ፡ ገደላችሁት ፡ እስከ ፡ በራክዩ ፡ ልጅ ፡ እስከ ፡ ዘካርያስ ፡ ደም ፡ ድረስ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የፈሰሰው ፡ የጻድቅ ፡ ደም ፡ ሁሉ ፡ ይደር
፴፮፡ ስባችሁ ፡ ዘንድ ። እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ትውልድ ፡ ላይ ፡ ይደርሳል ።
፴፯፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፡ ነቢያትን ፡ የምትገድል ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡ የተላኩትንም ፡ የምትወግር ፡ ዶሮ ፡ ጫጩቶችዋን ፡ ከክንፍ ችዋ ፡ በታች ፡ እንደምትሰበስብ ፡ ልጆችሽን ፡ እሰበስብ ፡ ዘንድ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ ወደድሁ ፤ አል
፴፰፡ ወደዳችሁምም ። እነሆ ፡ ቤታችሁ ፡ የተፈታ ፡
፴፱፡ ሆኖ ፡ ይቀርላችኋል ። እላችኋለሁና ፡ በጌታ ፡ ስም ፡ የሚመጣ ፡ የተባረከ ፡ ነው ፡ እስክትሉ ፡ ድረስ ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አታዩኝም ።

ምዕራፍ ፡ ፳፬ ።

፩፡ ኢየሱስም ፡ ከመቅደስ ፡ ወጥቶ ፡ ሄደ ፡ ደቀ መዛሙርቱም ፡ የመቅደሱን ፡ ግንቦች ፡ ሊያሳ
፪፡ የት ፡ ቀረቡ ። እርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፡— ይህን ፡ ሁሉ ፡ ታያላችሁን ? እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ ድን ጋይ ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ ሳይፈርስ ፡ በዚህ ፡ አይ
፫፡ ቀርም ፡ አላቸው ።
እርሱም ፡ በደብረ ፡ ዘይት ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ለብቻቸው ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀር በው ፡— ንገረን ፡ ይህ ፡ መቼ ፡ ይሆናል ? የመም ጣትህና ፡ የዓለም ፡ መጨረሻ ፡ ምልክቱስ ፡ ምን ድር ፡ ነው ? አሉት ። ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እን
፬፡ ዲህ ፡ አላቸው ፡— ማንም ፡ እንዳያስታችሁ ፡ ተጠንቀቁ ። ብዙዎች ፡— እኔ ፡ ክርስቶስ ፡ ነኝ ፡
፭፡ እያሉ ፡ በስሜ ፡ ይመጣሉና ፤ ብዙዎችንም ፡ ያስ ታሉ ። ጦርንም ፡ የጦርንም ፡ ወሬ ፡ ትሰሙ ፡
፮፡ ዘንድ ፡ አላችሁ ፤ ይህ ፡ ሊሆን ፡ ግድ ፡ ነውና ፡ ተጠበቁ ። አትደንግጡ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ መጨረ ሻው ፡ ገና ፡ ነው ። ሕዝብ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ መንግ
፯፡ ሥትም ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ይነሣልና ፡ ራብም ፡ ቸነፈርም ፡ የምድርም ፡ መናወጥ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ ይሆናል ፤ እነዚህም ፡ ሁሉ ፡ የምጥ ፡
፰፡ ጣር ፡ መጀመሪያ ፡ ናቸው ።
በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ለመከራ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡ
፱፡ አችኋል ፡ ይገድሉአችሁማል ። ስለ ፡ ስሜም ፡ በአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ የተጠላችሁ ፡ ትሆናላችሁ ።
፲፡ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ብዙዎች ፡ ይሰናከላሉ ፡ እርስ ፡ በርሳቸውም ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጣጣሉ ፡ እርስ ፡
፲፩፡ በርሳቸውም ፡ ይጣላሉ ፤ ብዙ ፡ ሐሰተኞች ፡ ነቢ
፲፪፡ ያትም ፡ ይነሣሉ ፡ ብዙዎችንም ፡ ያስታሉ ፤ ከኀ
፲፫፡ መፃም ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ የብዙ ፡ ሰዎች ፡ ፍቅር ፡ ትቀዘቅዛለች ። እስከ ፡ መጨረሻ ፡ የሚጸና ፡ ግን ፡
፲፬፡ እርሱ ፡ ይድናል ። ለአሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ ምስክር ፡ እንዲሆን ፡ ይህ ፡ የመንግሥት ፡ ወንጌል ፡ በዓ ለም ፡ ሁሉ ፡ ይሰበክል ፡ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ መጨ
፲፭፡ ረሻው ፡ ይመጣል ።
እንግዲህ ፡ በነቢዩ ፡ በዳንኤል ፡ የተባለውን ፡
፲፮፡ የጥፋትን ፡ ርኩሰት ፡ በተቀደሰች ፡ ስፍራ ፡ ቆሞ ፡ ስታዩ ፡ አንባቢው ፡ ያስተውል ፡ በዚ
፲፯፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በይሁዳ ፡ ያሉት ፡ ወደ ፡ ተራራዎች ፡
፲፰፡ ይሽሹ ፡ በሰገነትም ፡ ያለ ፡ በቤቱ ፡ ያለውን ፡ ሊወስድ ፡ አይውረድ ፡ በእርሻም ፡ ያለ ፡ ልብ
፲፱፡ ሱን ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ አይመ ለስ ። በዚያችም ፡ ወራት ፡ ለርጉዝችና ፡ ለሚ
፳፡ ያጠቡ ፡ ወዮላቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሽሽታችሁ ፡ በክረምት ፡ ወይም ፡ በሰንበት ፡ እንዳይሆን ፡

ሮቁ ። ፩ ፤ ሉቃ. ፲፭÷፵፱ ፤ ማር. ፮÷፩ ። ፪ ፤ ሉቃ. ፲፱÷ሮ፱ ። ፬—፭ ፤ ሉቃ. ፲፩÷ሮ፮—፲፩ ። ፮ ፤ ዘዳግ. ፲፫÷፫ ። ፱—፲ ፤ ሉቃ. ፲፩÷ሮ፯—፲፭ ። ፲፩ ፤ ፪ ዜና ሰ፮÷፲፯ ። ፲፭ ፤ ዘፍጥ. ፱÷፳፫ ፤ ፪ ዜና ሰ፮÷፲፫ ፤ ፲፯ ፤ ዘነኃ. ፭÷፭ ። ፲፰—፲፱ ፤ ሉቃ. ፲፩÷ሮ፯—፲፰ ። ፳፩ ፤ ኤር. ፲፭÷፭ ። ፲፱ ፤ መዝ. ፻፴፮÷፰ ። ፳፪ ፤ ዘፀአ. ፲፯÷፲፬ ። ፳፭ ፤ ሉቃ. ፳፩÷፳፫ ። ፳፰ ፤ ዘዳግ. ፳፰÷፵፱ ። ፳፱—፴፪ ፤ ሉቃ. ፳፩÷ሮ፭—፳፰ ። ፴፫ ፤ ሙሴ. ፫÷፲፭ ። ፴፬ ፤ ሉቃ. ፲፩÷፵፱ ። ፴፭ ፤ ዘፍጥ. ፬÷፰ ። ፴፮ ፤ ዘዳግ. ፴፪÷፭ ። ፴፰ ፤ ሉቃ. ፲፫÷፴፭ ። ፴፱ ፤ መዝ. ፻፲፰÷፳፮ ።

ሮቃ ። ፩ ፤ ሉቃ. ፳፩÷፭ ። ፫ ፤ ማር. ፲፫÷፫ ። ፬ ፤ ሉቃ. ፳፩÷ሮ፬ ። ፮ ፤ ዘዳግ. ፲፫÷፫ ። ፯ ፤ ኢሳ. ፲፱÷፪ ። ፰ ፤ ማቴ. ፳፬÷፰ ። ፱ ፤ ሉቃ. ፳፩÷ሮ፪ ። ፲ ፤ ሉቃ. ፳፩÷ሮ፫ ። ፲፩ ፤ ዘዳግ. ፲፫÷፭ ። ፲፪ ፤ ሉቃ. ፳፩÷ሮ፮ ። ፲፫ ፤ ማቴ. ፲፬÷፲፫ ። ፲፬ ፤ ሉቃ. ፳፬÷፵፯ ። ፲፭ ፤ ዳን. ፱፳÷፳፯ ። ፲፮ ፤ ሉቃ. ፳፩÷ሮ፩ ።

፳፩፤ ጸልዩ ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከዓለም ፡ መጀመሪያ ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያልሆነ ፡ እንግዲ
ህም ፡ ከቶ ፡ የማይሆን ፡ ታላቅ ፡ መከራ ፡ ይሆና
፳፪፤ ልና ። እነዚያ ፡ ቀኖችስ ፡ ባያጥሩ ፡ ሥጋ ፡ የለ
በሰ ፡ ሁሉ ፡ ባልዳነም ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እነ
ዚያ ፡ ቀኖች ፡ ስለ ፡ ተመረጡት ፡ ሰዎች ፡ ያጥ
፳፫፤ ራሉ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ማንም ፡— እነሆ ፥ ክርስ
ቶስ ፡ ከዚህ ፡ አለ ፡ ወይም ፡— ከዚያ ፡ አለ ፡ ቢላ
፳፬፤ ችሁ ፡ አትመኑ ፤ ሐሰተኞች ፡ ክርስቶሶችና ፡
ሐሰተኞች ፡ ነቢያት ፡ ይነሣሉና ፥ ቢቻላቸውስ ፡
የተመረጡትን ፡ እንኳ ፡ እስኪያስቱ ፡ ድረስ ፡
፳፭፤ ታላላቅ ፡ ምልክትና ፡ ድንቅ ፡ ያሳያሉ ። እነሆ ፥
፳፮፤ አስቀድሜ ፡ ነገርኋችሁ ። እንግዲህ ፡— እነሆ ፥
በበረሀ ፡ ነው ፡ ቢሉአችሁ ፥ አትውጡ ፤ እነሆ ፥
፳፯፤ በእልፍኝ ፡ ነው ፡ ቢሉአችሁ ፥ አትመኑ ፤ መብ
ረቅ ፡ ከምሥራቅ ፡ ወጥቶ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ እን
ደሚታይ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ መምጣት ፡ እንዲሁ ፡
፳፰፤ ይሆናልና ፤ በድን ፡ ወዳለበት ፡ በዚያ ፡ አሞራ
ዎች ፡ ይሰበሰባሉ ።
፳፱፤ ከዚያች ፡ ወራትም ፡ መከራ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡
ፀሐይ ፡ ይጨልማል ፥ ጨረቃም ፡ ብርሃንዋን ፡
አትሰጥም ፥ ከዋክብትም ፡ ከሰማይ ፡ ይወድቃሉ ፥
፴፤ የሰማያትም ፡ ኃይላት ፡ ይናወጣሉ ። በዚያን ፡
ጊዜም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ምልክት ፡ በሰማይ ፡ ይታ
ያል ፥ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ የምድር ፡ ወገኖች ፡
ሁሉ ፡ ዋይ ፡ ዋይ ፡ ይላሉ ፥ የሰው ፡ ልጅንም ፡
በኃይልና ፡ በብዙ ፡ ክብር ፡ በሰማይ ፡ ደመና ፡
፴፩፤ ሲመጣ ፡ ያዩታል ፤ መላእክቱንም ፡ ከታላቅ ፡
መለከት ፡ ድምፅ ፡ ጋር ፡ ይልካቸዋል ፥ ከሰማያ
ትም ፡ ዳርቻ ፡ እስከ ፡ ዳርቻው ፡ ከአራቱ ፡ ነፋ
ሳት ፡ ለእርሱ ፡ የተመረጡትን ፡ ይሰበስባሉ ።
፴፪፤ ምሳሌውንም ፡ ከበለስ ፡ ተማሩ ፤ ጫፍዋ ፡ ሲለ
ሰልስ ፡ ቅጠልዋም ፡ ሲያቈጠቍጥ ፥ ያን ፡ ጊዜ ፡
፴፫፤ በጋ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ ታውቃላችሁ ፤ እንዲሁ ፡
እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ስታዩ ፡ በደጅ ፡
፴፬፤ እንደ ፡ ቀረበ ፡ እወቁ ። እውነት ፡ እላችኋለሁ ፥
ይህ ፡ ሁሉ ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ ትውልድ ፡
፴፭፤ አያልፍም ። ሰማይና ፡ ምድር ፡ ያልፋሉ ፥ ቃሌ ፡
ግን ፡ አያልፍም ።
፴፮፤ ስለዚያች ፡ ቀንና ፡ ስለዚያች ፡ ሰዓት ፡ ግን ፡
ከአብ ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ የሰማይ ፡ መላእክትም ፡
ቢሆኑ ፡ ልጅም ፡ ቢሆን ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ።
፴፯፤ የኖኅ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መም
፴፰፤ ጣት ፡ እንዲሁ ፡ ይሆናልና ። በዚያች ፡ ወራት ፡
ከጥፋት ፡ ውኃ ፡ በፊት ፥ ኖኅ ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡
እስከገባበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፥ ሲበሉና ፡ ሲጠጡ ፡
፴፱፤ ሲያገቡና ፡ ሲጋቡም ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፥ የጥፋት ፡
ውኃም ፡ መጥቶ ፡ ሁሉን ፡ እስከ ፡ ወሰደ ፡ ድረስ ፡
እንዳላወቁ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ መምጣት ፡ ደግሞ ፡
፵፤ እንዲሁ ፡ ይሆናል ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡
በእርሻ ፡ ይሆናሉ ፤ አንዱ ፡ ይወሰዳል ፡ አንዱም ፡
ይቀራል ፤ ሁለት ፡ ሴቶች ፡ በወፍጮ ፡ ይፈጫሉ ፤ ፵፩፤
አንዲቱ ፡ ትወሰዳለች ፡ አንዲቱም ፡ ትቀራለች ።
ጌታችሁ ፡ በምን ፡ ሰዓት ፡ እንዲመጣ ፡ አታው ፵፪፤
ቁምና ፡ እንግዲህ ፡ ንቁ ።
ያን ፡ ግን ፡ እወቁ ፤ ባለቤት ፡ ከሌሊቱ ፡ በየት ፵፫፤
ኛው ፡ ክፍል ፡ ሌባ ፡ እንዲመጣ ፡ ቢያውቅ ፡
ኖሮ ፥ በነቃ ፡ ቤቱም ፡ ሊቈፈር ፡ ባልተወም ፡
ነበር ። ስለዚህ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ተዘጋጅታ ፵፬፤
ችሁ ፡ ኑሩ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ በማታስቡበት ፡ ሰዓት ፡
ይመጣልና ።
እንኪያስ ፡ ምግባቸውን ፡ በጊዜው ፡ ይሰጣ ፵፭፤
ቸው ፡ ዘንድ ፡ ጌታው ፡ በቤት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡
የሾመው ፡ ታማኝና ፡ ልባም ፡ ባሪያ ፡ ማን ፡ ነው ?
ጌታው ፡ መጥቶ ፡ እንዲህ ፡ ሲያደርግ ፡ የሚያገ ፵፮፤
ኘው ፡ ያ ፡ ባሪያ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ፤ እውነት ፡ እላች ፵፯፤
ኋለሁ ፥ ባለው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይሾመዋል ። ያ ፡ ፵፰፤
ክፉ ፡ ባሪያ ፡ ግን ፡— ጌታዬ ፡ እስኪመጣ ፡ ይዘገ
ያል ፡ ብሎ ፡ በልቡ ፡ ቢያስብ ፥ ባልንጀሮቹን ፡ ፵፱፤
ባሮች ፡ ሊመታ ፡ ቢጀምር ፡ ከሰካሮችም ፡ ጋር ፡
ቢበላና ፡ ቢጠጣ ፥ የዚያ ፡ ባሪያ ፡ ጌታ ፡ ባልጠ ፶፤
በቃት ፡ ቀን ፡ ባላወቃትም ፡ ሰዓት ፡ ይመጣል ፥
ከሁለትም ፡ ይሰነጥቀዋል ፥ እድሉንም ፡ ከግብ ፶፩፤
ዞች ፡ ጋር ፡ ያደርግበታል ፤ በዚያ ፡ ልቅሶና ፡
ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ይሆናል ።

ምዕራፍ ፡ ፳፭ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መብ ፩፡
ራታቸውን ፡ ይዘው ፡ ሙሽራውን ፡ ሊቀበሉ ፡
የወጡ ፡ አሥር ፡ ቈነጃጅትን ፡ ትመስላለች ።
ከእነርሱም ፡ አምስቱ ፡ ሰነፎች ፡ አምስቱም ፡ ልባ ፪፡
ሞች ፡ ነበሩ ። ሰነፎቹ ፡ መብራታቸውን ፡ ይዘው ፡ ፫፡
ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ዘይት ፡ አልያዙምና ፤ ልባሞቹ ፡ ፬፡
ግን ፡ ከመብራታቸው ፡ ጋር ፡ በማሰሮአቸው ፡
ዘይት ፡ ያዙ ። ሙሽራውም ፡ በዘገየ ፡ ጊዜ ፡ ፭፡
ሁሉ ፡ እንቅልፍ ፡ እንቅልፍ ፡ አላቸውና ፡ ተኙ ።
እኩል ፡ ሌሊትም ፡ ሲሆን ፡— እነሆ ፡ ሙሽራው ፡ ፮፡
ይመጣል ፥ ትቀበሉት ፡ ዘንድ ፡ ወጡ ፡ የሚል ፡
ውካታ ፡ ሆነ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ ቈነጃ ፯፡
ጆች ፡ ሁሉ ፡ ተነሡና ፡ መብራታቸውን ፡ አዘጋጁ ።
ሰነፎቹም ፡ ልባሞቹን ፡— መብራታችን ፡ ሊጠ ፰፡
ፋብን ፡ ነው ፤ ከዘይታችሁ ፡ ስጡን ፡ አሉአቸው ።
ልባሞቹ ፡ ግን ፡ መልሰው ፡— ምናልባት ፡ ለእ ፱፡
ኛና ፡ ለእናንተ ፡ ባይበቃስ ፤ ይልቅስ ፡ ወደሚሸ
ጡት ፡ ሄዳችሁ ፡ ለራሳችሁ ፡ ግዙ ፡ አሉአቸው ።
ሊገዙም ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ ሙሽራው ፡ መጣ ፥ ተዘጋ ፲፡
ጅተው ፡ የነበሩትም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ሰርግ ፡
ገቡ ፥ ደጁም ፡ ተዘጋ ። በኋላም ፡ ደግሞ ፡ የቀሩቱ ፡ ፲፩፡
ቈነጃጅት ፡ መጡና ፡— ጌታ ፡ ሆይ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥
ክፈትልን ፡ አሉ ። እርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፡— እው ፲፪፡

፲፫፤ ነት ፡ እላችኋለሁ ፥ አላውቃችሁም ፡ አለ ። ቀኒቱ
ንና ፡ ሰዓቲቱን ፡ አታውቁምና ፡ እንግዲህ ፡ ንቁ ።
፲፬፤ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ የሚሄድ ፡ ሰው ፡ ባሮቹን ፡
ጠርቶ ፡ ያለውን ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ሰጣቸው ፡ እን
፲፭፤ ዲሁ ፡ ይሆናልና ፤ ለእያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ዓቅሙ ፥
ለአንዱ ፡ አምስት ፡ መክሊት ፡ ለአንዱ ፡ ሁለት ፡
ለአንዱም ፡ አንድ ፡ ሰጠና ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡
፲፮፤ ወዲያው ፡ ሄደ ። አምስት ፡ መክሊትም ፡ የተቀበ
ለው ፡ ሄዶ ፡ ነገደበት ፡ ሌላም ፡ አምስት ፡ አተ
፲፯፤ ረፈ ፤ እንዲሁም ፡ ሁለት ፡ የተቀበለው ፡ ሌላ ፡
፲፰፤ ሁለት ፡ አተረፈ ። አንድ ፡ የተቀበለው ፡ ግን ፡
ሄዶ ፡ ምድርን ፡ ቈፈረና ፡ የጌታውን ፡ ገንዘብ ፡
፲፱፤ ቀበረ ። ከብዙ ፡ ዘመንም ፡ በኋላ ፡ የእነዚያ ፡ ባሮች ፡
፳፤ ጌታ ፡ መጣና ፡ ተቈጣጠራቸው ። አምስት ፡ መክ
ሊት ፡ የተቀበለውም ፡ ቀረበና ፡ ሌላ ፡ አምስት ፡
መክሊት ፡ አስረክቦ ፡— ጌታ ፡ ሆይ ፥ አምስት ፡
መክሊት ፡ ሰጥተኸኝ ፡ ነበር ፤ እነሆ ፥ ሌላ ፡ አም
፳፩፤ ስት ፡ መክሊት ፡ አተረፍሁበት ፡ አለ ። ጌታ
ውም ፡— መልካም ፥ አንተ ፡ በጎ ፡ ታማኝም ፡
ባሪያ ፤ በጥቂቱ ፡ ታመንሃል ፥ በብዙ ፡ እሾምሃ
፳፪፤ ለሁ ፤ ወደ ፡ ጌታህ ፡ ደስታ ፡ ግባ ፡ አለው ። ሁለት ፡
መክሊትም ፡ የተቀበለው ፡ ደግሞ ፡ ቀርቦ ፡—
ጌታ ፡ ሆይ ፥ ሁለት ፡ መክሊት ፡ ሰጥተኸኝ ፡
ነበር ፤ እነሆ ፥ ሌላ ፡ ሁለት ፡ መክሊት ፡ አተረፍ
፳፫፤ ሁበት ፡ አለ ። ጌታውም ፡— መልካም ፥ አንተ ፡
በጎ ፡ ታማኝም ፡ ባሪያ ፤ በጥቂቱ ፡ ታመንሃል ፥
በብዙ ፡ እሾምሃለሁ ፥ ወደ ፡ ጌታህ ፡ ደስታ ፡ ግባ ፡
፳፬፤ አለው ። አንድ ፡ መክሊትም ፡ የተቀበለው ፡
ደግሞ ፡ ቀርቦ ፡— ጌታ ፡ ሆይ ፥ ካልዘራህበት ፡
የምታጭድ ፡ ካልበተንህበትም ፡ የምትሰበስብ ፡
፳፭፤ ጨካኝ ፡ ሰው ፡ መሆንህን ፡ አውቃለሁ ፡ ፈራ
ሁም ፡ ሄጄም ፡ መክሊትህን ፡ በምድር ፡ ቀበር
፳፮፤ ሁት ፤ እነሆ ፥ መክሊትህ ፡ አለህ ፡ አለ ። ጌታ
ውም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡— አንተ ፡ ክፉና ፡
ሃኬተኛ ፡ ባሪያ ፥ ካልዘራሁበት ፡ እንዳጭድ ፡
ካልበተንሁበትም ፡ እንድሰበስብ ፡ ታውቃለህን ?
፳፯ ስለዚህ ፡ ገንዘቤን ፡ ለለዋጮች ፡ አደራ ፡ ልትሰ
ጠው ፡ በተገባህ ፡ ነበር ፥ እኔም ፡ መጥቼ ፡ ያለ
፳፰፤ ኝን ፡ ከትርፉ ፡ ጋር ፡ እወስደው ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡
መክሊቱን ፡ ውሰዱበት ፡ አሥር ፡ መክሊትም ፡
፳፱፤ ላለው ፡ ስጡት ፤ ላለው ፡ ሁሉ ፡ ይሰጠዋልና ፡
ይበዛለትማል ፤ ከሌለው ፡ ግን ፡ ያው ፡ ያለው ፡
፴፤ እንኳ ፡ ይወሰድበታል ። የማይጠቅመውንም ፡
ባሪያ ፡ በውጭ ፡ ወዳለው ፡ ጨለማ ፡ አውጡት ፤
በዚያ ፡ ልቅሶና ፡ ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ይሆናል ።
፴፩፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ በክብሩ ፡ በሚመጣበት ፡ ጊዜ ፡
ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ቅዱሳን ፡ መላእክቱ ፡ ሁሉ ፥
በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በክብሩ ፡ ዙፋን ፡ ይቀመጣል ፤
፴፪፤ አሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ በፊቱ ፡ ይሰበሰባሉ ፤ እረኛም ፡
በጎቹን ፡ ከፍየሎች ፡ እንደሚለይ ፡ እርስ ፡ በር
ሳቸው ፡ ይለያቸዋል ፥ በጎችን ፡ በቀኙ ፡ ፍየሎ ፴፫፤
ችንም ፡ በግራው ፡ ያቆማቸዋል ። ንጉሡም ፡ ፴፬፤
በቀኙ ፡ ያሉትን ፡ እንዲህ ፡ ይላቸዋል ፡— እናንተ ፡
የአባቴ ፡ ቡሩካን ፥ ኑ ፤ ዓለም ፡ ከተፈጠረበት ፡
ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የተዘጋጀላችሁን ፡ መንግሥት ፡
ውረሱ ። ተርቤ ፡ አብልታችሁኛልና ፥ ተጠ ፴፭፤
ምቼ ፡ አጠጥታችሁኛልና ፥ እንግዳ ፡ ሆኜ ፡ ተቀ
ብላችሁኛልና ፥ ታርዤ ፡ አልብሳችሁኛልና ፥ ፴፮፤
ታምሜ ፡ ጠይቃችሁኛልና ፥ ታስሬ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡
መጥታችኋልና ። ጻድቃንም ፡ መልሰው ፡ ይሉ ፴፯፤
ታል ፡— ጌታ ፡ ሆይ ፥ ተርበህ ፡ አይተን ፡ መቼ ፡
አበላንህስ ? ወይስ ፡ ተጠምተህ ፡ አይተን ፡ መቼ ፡
አጠጣንህ ? እንግዳ ፡ ሆነህስ ፡ አይተን ፡ መቼ ፡ ፴፰፤
ተቀበልንህ ? ወይስ ፡ ታርዘህ ፡ አይተን ፡ መቼ ፡
አለበስንህ ? ወይስ ፡ ታመህ ፡ ወይስ ፡ ታስረህ ፡ ፴፱፤
አይተን ፡ መቼ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ መጣን ? ንጉሡም ፡ ፵፤
መልሶ ፡— እውነት ፡ እላችኋለሁ ፥ ከሁሉ ፡ ከሚያ
ንሱ ፡ ከእነዚህ ፡ ወንድሞቼ ፡ ለአንዱ ፡ እንኳ ፡ ስላ
ደረጋችሁት ፡ ለእኔ ፡ አደረጋችሁት ፡ ይላቸዋል ።
በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በግራው ፡ ያሉትን ፡ ደግሞ ፡ ፵፩፤
ይላቸዋል ፡— እናንተ ፡ ርጉማን ፥ ለሰይጣንና ፡
ለመላእክቱ ፡ ወደ ፡ ተዘጋጀ ፡ ወደ ፡ ዘላለም ፡
እሳት ፡ ከእኔ ፡ ሂዱ ። ተርቤ ፡ አላበላችሁኝምና ፥ ፵፪፤
ተጠምቼ ፡ አላጠጣችሁኝምና ፥ እንግዳ ፡ ሆኜ ፡ ፵፫፤
አልተቀበላችሁኝምና ፥ ታርዤ ፡ አላለበሳችሁ
ኝምና ፥ ታምሜ ፡ ታስሬም ፡ አልጠየቃችሁኝ
ምና ። እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ይመልሱና ፡— ጌታ ፡ ፵፬፤
ሆይ ፥ ተርበህ ፡ ወይስ ፡ ተጠምተህ ፡ ወይስ ፡
እንግዳ ፡ ሆነህ ፡ ወይስ ፡ ታርዘህ ፡ ወይስ ፡ ታመህ ፡
ወይስ ፡ ታስረህ ፡ መቼ ፡ አይተን ፡ አላገለገልን
ህም ? ይሉታል ። ያን ፡ ጊዜ ፡— እውነት ፡ እላች ፵፭፤
ኋለሁ ፥ ከሁሉ ፡ ከሚያንሱ ፡ ከእነዚህ ፡ ለአንዱ ፡
ስላላደረጋችሁት ፡ ለእኔ ፡ ደግሞ ፡ አላደረጋችሁ
ትም ፡ ብሎ ፡ ይመልስላቸዋል ። እነዚያም ፡ ወደ ፡ ፵፮፤
ዘላለም ፡ ቅጣት ፥ ጻድቃን ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ዘላለም ፡
ሕይወት ፡ ይሄዳሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፮ ።

ኢየሱስም ፡ እነዚህን ፡ ቃሎች ፡ ሁሉ ፡ በፈ ፩፤
ጸመ ፡ ጊዜ ፥ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡— ከሁለት ፡ ፪፤
ቀን ፡ በኋላ ፡ ፋሲካ ፡ እንዲሆን ፡ ታውቃላችሁ ፥
የሰው ፡ ልጅም ፡ ሊሰቀል ፡ አልፎ ፡ ይሰጣል ፡
አለ ።
በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ የሕዝብም ፡ ፫፤
ሽማግሎች ፡ ቀያፋ ፡ በሚባለው ፡ በሊቀ ፡ ካህ
ናቱ ፡ ግቢ ፡ ተሰበሰቡ ፥ ኢየሱስንም ፡ በተንኰል ፡ ፬፤
ሊያስይዙት ፡ ሊገድሉትም ፡ ተማከሩ ፤ ነገር ፡ ፭፤
ግን ፡— በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ ሁከት ፡ እንዳይነሣ ፡
በበዓል ፡ አይሁን ፡ አሉ ።
ኢየሱስም ፡ በቢታንያ ፡ በለምጻሙ ፡ በስም ፮፤

፭፤ አግዶን? አንተው ፡ ተጠንቀቅ ፡ አሉ ። ብሩንም ፡
በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ጥሎ ፡ ሄደና ፡ ታንቆ ፡ ሞተ ።
፮፤ የካህናት ፡ አለቆችም ፡ ብሩን ፡ አንሥተው ፡—
የደም ፡ ዋጋ ፡ ነውና ፡ ወደ ፡ መባ ፡ ልንጨም
፯፤ ረው ፡ አልተፈቀደም ፡ አሉ ። ተማክረውም ፡
የሸክላ ፡ ሠሪ ፡ መሬት ፡ ለእንግዶች ፡ መቃብር ፡
፰፤ ገዙበት ። ስለዚህ ፡ ያ ፡ መሬት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡
፱፤ ድረስ ፡ የደም ፡ መሬት ፡ ተባለ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡
በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፡ የተባለው ፡—

ከእስራኤል ፡ ልጆችም ፡ አንዳንዶቹ ፡ የገመ
ቱትን ÷ የተገመተውን ፡ ዋጋ ፡ ሠላሳ ፡ ብር ፡
፲፤ ያዙ ÷ ጌታም ፡ እንዳዘዘኝ ፡ ስለ ፡ ሸክላ ፡ ሠሪ ፡
መሬት ፡ ሰጡት ፡

የሚል ፡ ተፈጸመ ።
፲፩፤ ኢየሱስም ፡ በገዢው ፡ ፊት ፡ ቆመ ፤ ገዢ
ውም ፡— የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ አንተ ፡ ነህን?
ብሎ ፡ ጠየቀው ፤ ኢየሱስም ፡— አንተ ፡ አልህ ፡
፲፪፤ አለው ። የካህናት ፡ አለቆችም ፡ ሽማግሎችም ፡
፲፫፤ ሲከሱት ፡ ምንም ፡ አልመለሰም ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡
ጲላጦስ ፡— ስንት ፡ ያህል ፡ እንዲመሰክሩብህ ፡
፲፬፤ አትሰማምን? አለው ። ገዢውም ፡ እጅግ ፡ እስ
ኪደነቅ ፡ ድረስ ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ ስንኳ ፡ አል
መለሰለትም ።
፲፭፤ በዚያም ፡ በዓል ፡ ሕዝቡ ፡ የወደዱትን ፡ አንድ ፡
እስረኛ ፡ ሊፈታላቸው ፡ ለገዢው ፡ ልማድ ፡ ነበ
፲፮፤ ረው ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ በርባን ፡ የሚባል ፡
፲፯፤ በጣም ፡ የታወቀ ፡ እስረኛ ፡ ነበራቸው ። እንግ
ዲህ ፡ እነርሱ ፡ ተሰብስበው ፡ ሳሉ ፡ ጲላጦስ ፡—
በርባንን ፡ ወይስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተባለውን ፡ ኢየ
ሱስን ፡ ማንኛውን ፡ ልፈታላችሁ ፡ ትወዳላችሁ?
፲፰፤ አላቸው ፤ በቅንዓት ፡ አሳልፈው ፡ እንደ ፡ ሰጡት ፡
፲፱፤ ያውቅ ፡ ነበርና ። እርሱም ፡ በፍርድ ፡ ወንበር ፡
ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ሚስቱ ፡— ስለ ፡ እርሱ ፡ ዛሬ ፡
በሕልም ፡ እጅግ ፡ መከራ ፡ ተቀብያለሁና ፡ በዚያ ፡
ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ አታድርግ ፡ ብላ ፡ ላከች
፳፤ በት ። የካህናት ፡ አለቆችና ፡ ሽማግሎች ፡ ግን ፡
በርባንን ፡ እንዲለምኑ ፡ ኢየሱስን ፡ ግን ፡ እንዲያ
፳፩፤ ጠፉ ፡ ሕዝቡን ፡ አባበሉ ። ገዢውም ፡ መልሶ ፡—
ከሁለቱ ፡ ማንኛውን ፡ ልፈታላችሁ ፡ ትወዳላ
ችሁ? አላቸው ፤ እነርሱም ፡— በርባንን ፡ አሉ ።
፳፪፤ ጲላጦስ ፡— ክርስቶስ ፡ የተባለውን ፡ ኢየሱስን ፡
እንግዲህ ፡ ምን ፡ ላድርገው? አላቸው ፤ ሁሉም ፡—
፳፫፤ ይሰቀል ፡ አሉ ። ገዢውም ፡— ምን ፡ ነው? ያደ
ረገው ፡ ክፋት ፡ ምንድር ፡ ነው? አለ ፤ እነርሱ ፡
ግን ፡— ይሰቀል ፡ እያሉ ፡ ጮኹ ፡ አበዙ ።
፳፬፤ ጲላጦስም ፡ ሁከት ፡ እንዲጀመር ፡ እንጂ ፡ አን
ዳች ፡ እንዳይረባ ፡ በየ ፡ ጊዜ ÷ ውኃ ፡ አንሥቶ ፡—
እኔ ፡ ከዚህ ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ደም ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፤
እናንተ ፡ ተጠንቀቁ ፡ ሲል ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡
እጁን ፡ ታጠበ ። ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ መልሰው ፡— ፳፭፤
ደሙ ፡ በእኛና ፡ በልጆቻችን ፡ ላይ ፡ ይሁን ፡ አሉ ።
በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በርባንን ፡ ፈታላቸው ÷ ኢየሱ ፳፮፤
ስን ፡ ግን ፡ ገርፎ ፡ ሊሰቀል ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ።
በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የገዢው ፡ ወታደሮች ፡ ኢየ ፳፯፤
ሱስን ፡ ወደ ፡ ገዢው ፡ ግቢ ፡ ውሥጥ ፡ ወሰዱት ፡
ጭፍራውንም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አከማቹ ።
ልብሱንም ፡ ገፈው ፡ ቀይ ፡ ልብስ ፡ አለበሱት ÷ ፳፰፤
ከእሾህም ፡ አክሊል ፡ ጐንጕነው ፡ በራሱ ፡ ላይ ÷ ፳፱፤
በቀኝ ፡ እጁም ፡ መቃ ፡ አኖሩ ÷ በፊቱም ፡ ተን
በርክከው ፡— የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ÷ ሰላም ፡
ለአንተ ፡ ይሁን ፡ እያሉ ፡ ዘበቱበት ፤ ተፉበትም ፡ ፴፤
መቃውንም ፡ ይዘው ፡ ራሱን ፡ መቱት ። ከዘበቱ ፴፩፤
በትም ፡ በኋላ ፡ ቀዩን ፡ ልብስ ፡ ገፈፉት ÷ ልብሱ
ንም ፡ አለበሱት ፡ ሊሰቅሉትም ፡ ወሰዱት ።
ሲወጡም ፡ ስምዖን ፡ የተባለ ፡ የቀሬናን ፡ ሰው ፡ ፴፪፤
አገኙ ፤ እርሱንም ፡ መስቀሉን ፡ ይሸከም ፡ ዘንድ ፡
አስገደዱት ። ትርጓሜው ፡ የራስ ፡ ቅል ፡ ስፍራ ፡ ፴፫፤
ወደሚሆን ፡ ጎልጎታ ፡ ወደሚባለው ፡ ስፍራ ፡
በደረሱ ፡ ጊዜም ÷ በሐሞት ፡ የተደባለቀ ፡ የወ ፴፬፤
ይን ፡ ጠጅ ፡ ሊጠጣ ፡ አቀረቡለት ፤ ቀምሶም ፡
ሊጠጣው ፡ አልወደደም ። ከሰቀሉትም ፡ በኋላ ፡ ፴፭፤
ልብሱን ፡ ዕጣ ፡ ጥለው ፡ ተካፈሉ ÷ በዚያም ፡ ተቀ ፴፮፤
ምጠው ፡ ይጠብቁት ፡ ነበር ። ይህ ፡ ኢየሱስ ፡ ፴፯፤
የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ የክሱን ፡ ጽሕ
ፈት ፡ ከራሱ ፡ በላይ ፡ አኖሩ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፴፰፤
ሁለት ፡ ወንበዶች ፡ አንዱ ፡ በቀኝ ፡ አንዱም ፡
በግራ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ተሰቀሉ ። የሚያልፉ ፴፱፤
ትም ፡ ራሳቸውን ፡ እየነቀነቁ ፡ ይሰድቡት ፡ ነበ
ርና ፡— ቤተ ፡ መቅደስን ፡ የምታፈርስ ፡ በሦስት ፡ ፵፤
ቀንም ፡ የምትሠራው ÷ ራስህን ፡ አድን ፤ የእግዚ
አብሔር ፡ ልጅስ ፡ ከሆንህ ፡ ከመስቀል ፡ ውረድ ፡
አሉት ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የካህናት ፡ አለ ፵፩፤
ቆች ፡ ከጻፎችና ፡ ከሽማግሎች ፡ ጋር ፡ እየዘበቱ
በት ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፡— ሌሎችን ፡ አዳነ ÷ ራሱን ፡ ፵፪፤
ሊያድን ፡ አይችልም ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡
ከሆነ ÷ አሁን ፡ ከመስቀል ፡ ይውረድ ፡ እኛም ፡
እናምንበታለን ። በእግዚአብሔር ፡ ታምኖአል ፤ ፵፫፤
የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ብሎአልና ፡ ከወደ
ደውስ ፡ አሁን ፡ ያድነው ። ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የተ ፵፬፤
ሰቀሉት ፡ ወንበዶች ፡ ደግሞ ፡ ያንኑ ፡ እያሉ ፡
ይነቅፉት ፡ ነበር ።
ከስድስት ፡ ሰዓትም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ፵፭፤
ሰዓት ፡ ድረስ ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ጨለማ ፡
ሆነ ። በዘጠኝ ፡ ሰዓትም ፡ ኢየሱስ ፡— ኤሎሄ ፡ ፵፮፤
ኤሎሄ ፡ ላማ ፡ ሰበቅታኒ? ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡
ጮኸ ። ይህም ፡— አምላኬ ፡ አምላኬ ÷ ስለ ፡ ምን ፡

፳፯ ። ፩ ፤ የሐዋ· ፩÷፲፰ ። ፰ ፤ የሐዋ· ፩÷፲፱ ። ፱ ፡ ፲ ፤ ዘካ· ፲፩÷፲፫ ። ፲፩ - ፲፬ ፤ ማር· ፲፭÷፪—፭ ፤ ሉቃ· ፳፫÷፪ ፡ ፫ ፤ ዮሐ· ፲፰÷፳፱—፴፰ ። ፲፪ ፤ ኢሳ· ፶፫÷፯ ። ፲፭—፳፮ ፤ ማር· ፲፭÷፮—፲፭ ፤ ሉቃ· ፳፫÷፲፰—፳፭ ፤ ዮሐ· ፲፰ ÷ ፴፱ ፡ ፵ ፤ ፲፱÷፲፫ ፡ ፲፮ ። ፳፬ ፤ ዘዳግ· ፳፩÷፮—፰ ። ፳፮ ፤ ኢሳ· ፶ ÷ ፮ ፤ ፶፫÷፭ ፤ ዮሐ· ፲፱ ÷ ፩ ። ፳፯—፴፩ ፤ ማር· ፲፭ ÷ ፲፮—፳ ፤ ዮሐ· ፲፱ ÷ ፪ ፡ ፫ ። ፴ ፤ ም· ፳፮ ÷ ፷፯ ። ፴፪ ፤ ማር· ፲፭ ÷ ፳፩ ፤ ሉቃ· ፳፫ ÷ ፳፮ ። ፴፫—፵፩ ፤ ማር· ፲፭ ÷ ፳፪—፴፰ ፤ ሉቃ· ፳፫÷፴፪—፴፰ ፡ ፵፬—፵፱ ፤ ዮሐ· ፲፱ ÷ ፲፯—፲፱ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬ ፡ ፳፰—፴ ። ፴፬ ፤ መዝ· ፷፰÷፳፩ ። ፴፭ ፤ መዝ· ፳፩÷፲፰ ፡ ፲፰ ። ፴፱ ፤ መዝ· ፳፩÷፯ ። ፵ ፤ ም· ፳፮ ÷ ፷፩ ። ፵፫ ፤ መዝ· ፳፩÷፰ ። ፵፬ ፤ ሉቃ· ፳፫÷፴፱—፵፫ ። ፵፮ ፤ መዝ· ፳፩÷፩ ።

፵፯፤ ተውኸኝ? ማለት ፡ ነው ። በዚያም ፡ ከቆሙት ፡
ሰዎች ፡ ሰምተው ፡— ይህስ ፡ ኤልያስን ፡ ይጠ
፵፰፤ ራል ፡ አሉ ። ወዲያውም ፡ ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡
ሮጠ ፤ ሰፍነግም ፡ ይዞ ፡ ሆምጣጤ ፡ ሞላበት ÷
፵፱፤ በመቃም ፡ አድርጎ ፡ አጠጣው ። ሌሎቹ ፡ ግን ፡—
ተው ÷ ኤልያስ ፡ መጥቶ ፡ ያድነው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
፶፤ እንይ ፡ አሉ ። ኢየሱስም ፡ ሁለተኛ ፡ በታላቅ ፡
ድምፅ ፡ ጮኾ ፡ ነፍሱን ፡ ተወ ።
፶፩፤ እነሆም ÷ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ መጋረጃ ፡ ከላይ ፡
እስከ ፡ ታች ፡ ከሁለት ፡ ተቀደደ ÷ ምድርም ፡
፶፪፤ ተናወጠች ÷ ዓለቶችም ፡ ተሰነጠቁ ፤ መቃብሮ
ችም ፡ ተከፈቱ ÷ ተኝተው ፡ ከነበሩትም ፡ ከቅዱ
፶፫፤ ሳን ፡ ብዙ ፡ ሥጋዎች ፡ ተነሡ ፤ ከትንሣኤውም ፡
በኋላ ፡ ከመቃብሮች ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ቅድስት ፡
፶፬፤ ከተማ ፡ ገቡና ፡ ለብዙዎች ፡ ታዩ ። የመቶ ፡ አለ
ቃም ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ኢየሱስን ፡ የሚጠብቁ ፡
መናወጡንና ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ አይተው ፡—
ይህ ፡ በእውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፡
ብለው ፡ እጅግ ፡ ፈሩ ።
፶፭፤ ኢየሱስን ፡ እያገለገሉ ፡ ከገሊላ ፡ የተከተሉት ፡
ብዙ ፡ ሴቶች ፡ በሩቅ ፡ ሆነው ፡ ሲመለከቱ ፡ በዚያ ፡
፶፮፤ ነበሩ ፤ ከእነርሱም ፡ መግደላዊት ፡ ማርያምና ፡
የያዕቆብና ፡ የዮሳ ፡ እናት ፡ ማርያም ፡ የዘብዴዎ
ስም ፡ የልጆቹ ፡ እናት ፡ ነበሩ ።
፶፯፤ በመሸም ፡ ጊዜ ፡ ዮሴፍ ፡ የተባለው ፡ ባለ ፡ ጠጋ ፡
ሰው ፡ ከአርማትያስ ፡ መጣ ÷ እርሱም ፡ ደግሞ ፡
፶፰፤ የኢየሱስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ነበረ ፤ ይኸውም ፡
ወደ ፡ ጲላጦስ ፡ ቀርቦ ፡ የኢየሱስን ፡ ሥጋ ፡ ለመ
፶፱፤ ነው ። ጲላጦስም ፡ እንዲሰጡት ፡ አዘዘ ። ዮሴ
ፍም ፡ ሥጋውን ፡ ይዞ ፡ በንጹሕ ፡ በፍታ ፡ ከፈ
፷፤ ነው ÷ ከዓለት ፡ በወቀረው ፡ በአዲሱ ፡ መቃብ
ርም ፡ አኖረው ÷ በመቃብሩም ፡ ደጃፍ ፡ ታላቅ ፡
፷፩፤ ድንጋይ ፡ አንከባሎ ፡ ሄደ ። መግደላዊት ፡ ማር
ያምም ፡ ሁለተኛይቱም ፡ ማርያም ፡ በመቃብሩ ፡
አንጻር ፡ ተቀምጠው ፡ በዚያ ፡ ነበሩ ።
፷፪፤ በማግሥቱም ፡ ከመዘጋጀት ፡ በኋላ ፡ በሚሆ
ነው ፡ ቀን ÷ የካህናት ፡ አለቆችና ፡ ፈሪሳውያን ፡
፷፫፤ ወደ ፡ ጲላጦስ ፡ ተሰበሰቡና ፡— ጌታ ፡ ሆይ ÷ ያ ፡
አሳች ፡ በሕይወቱ ፡ ገና ፡ ሳለ ፡— ከሦስት ፡ ቀን ፡
፷፬፤ በኋላ ፡ እነሣለሁ ፡ እንዳለ ፡ ትዝ ፡ አለን ። እንግ
ዲህ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ መጥተው ፡ በሌሊት ፡
እንዳይሰርቁት ፡ ለሕዝቡም ፡— ከሙታን ፡ ተነሣ ፡
እንዳይሉ ÷ የኋለኛይቱ ፡ ስሕተት ፡ ከፊተኛይቱ ፡
ይልቅ ፡ የከፋች ፡ ትሆናለችና ፡ መቃብሩ ፡ እስከ ፡
ሦስተኛ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ እንዲጠበቅ ፡ እዘዝ ፡
፷፭፤ አሉት ። ጲላጦስም ፡— ጠባቆች ፡ አሉአችሁ ፤
ሄዳችሁ ፡ እንዳወቃችሁ ፡ አስጠብቁ ፡ አላቸው ።
፷፮፤ እነርሱም ፡ ሄደው ፡ ከጠባቆች ፡ ጋር ፡ ድንጋዩን ፡
አትመው ፡ መቃብሩን ፡ አስጠበቁ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፰ ።

በሰንበትም ፡ መጨረሻ ፡ መጀመሪያው ፡ ቀን ፡ ፩፤
ሲነጋ ፡ መግደላዊት ፡ ማርያምና ፡ ሁለተኛይቱ ፡
ማርያም ፡ መቃብሩን ፡ ሊያዩ ፡ መጡ ። እነሆም ÷ ፪፤
የጌታ ፡ መልአክ ፡ ከሰማይ ፡ ስለ ፡ ወረደ ፡ ታላቅ ፡
የምድር ፡ መናወጥ ፡ ሆነ ፤ ቀርቦም ፡ ድንጋዩን ፡
አንከባሎ ፡ በላዩ ፡ ተቀመጠ ። መልኩም ፡ እንደ ፡ ፫፤
መብረቅ ፡ ልብሱም ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ ነጭ ፡ ነበረ ።
ጠባቆቹም ፡ እርሱን ፡ ከመፍራት ፡ የተነሣ ፡ ተና ፬፤
ወጡ ፡ እንደ ፡ ሞቱም ፡ ሆኑ ። መልአኩም ፡ ፭፤
መልሶ ፡ ሴቶቹን ፡ አላቸው ፡— እናንተስ ፡ አት
ፍሩ ፤ የተሰቀለውን ፡ ኢየሱስን ፡ እንድትሹ ፡
አውቃለሁና ፤ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ተነሥቶአልና ፡ ፮፤
በዚህ ፡ የለም ፤ የተኛበትን ፡ ስፍራ ፡ ኑና ፡ እዩ ።
ፈጥናችሁም ፡ ሂዱና ፡— ከሙታን ፡ ተነሣ ÷ እነ ፯፤
ሆም ÷ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ይቀድማችኋል ፡ በዚያም ፡
ታዩታላችሁ ፡ ብላችሁ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡
ንገሩአቸው ። እነሆም ÷ ነገርኋችሁ ። በፍርሃ ፰፤
ትና ፡ በታላቅ ፡ ደስታም ፡ ፈጥነው ፡ ከመቃብር ፡
ሄዱ ÷ ለደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ሊያወሩ ፡ ሮጡ ።
እነሆም ÷ ኢየሱስ ፡ አገኛቸውና ፡— ደስ ፡ ይበላ ፱፤
ችሁ ፡ አላቸው ። እነርሱም ፡ ቀርበው ፡ እግሩን ፡
ይዘው ፡ ሰገዱለት ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡— ፲፤
አትፍሩ ፤ ሄዳችሁ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ እንዲሄዱ ፡ ለወ
ንድሞቼ ፡ ተናገሩ ÷ በዚያም ፡ ያዩኛል ፡ አላቸው ።
ሲሄዱም ፡ ሳሉ ፡ እነሆ ÷ ከጠባቆቹ ፡ አንዳንድ ፡ ፲፩፤
ወደ ፡ ከተማ ፡ መጥተው ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ለካ
ህናት ፡ አለቆች ፡ አወሩ ። ከሽማግሎች ፡ ጋርም ፡ ፲፪፤
ተሰብስበው ፡ ተማከሩና ፡ ለጭፍሮች ፡ ብዙ ፡ ገን
ዘብ ፡ ሰጥተዋቸው ፡— እኛ ፡ ተኝተን ፡ ሳለን ፡ ደቀ ፡ ፲፫፤
መዛሙርቱ ፡ በሌሊት ፡ መጥተው ፡ ሰረቁት ፡ በሉ ።
ይህም ፡ በገዢው ፡ ዘንድ ፡ የተሰማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ÷ ፲፬፤
እኛ ፡ እናስረዳዋለን ፡ እናንተም ፡ ያለ ፡ ሥጋት ፡
እንድትሆኑ ፡ እናደርጋለን ፡ አሉአቸው ። እነር ፲፭፤
ሱም ፡ ገንዘቡን ፡ ተቀብለው ፡ እንደ ፡ አስተማሩ
አቸው ፡ አደረጉ ። ይህም ፡ ነገር ፡ በአይሁድ ፡
ዘንድ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሲወራ ፡ ይኖራል ።
አሥራ ፡ አንዱ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ግን ፡ ኢየ ፲፮፤
ሱስ ፡ ወዳዘዛቸው ፡ ተራራ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ሄዱ ÷
በዩትም ፡ ጊዜ ፡ ሰገዱለት ፤ የተጠራጠሩ ፡ ግን ፡ ፲፯፤
ነበሩ ። ኢየሱስም ፡ ቀረበና ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ፲፰፤
ተናገራቸው ፡— ሥልጣን ፡ ሁሉ ፡ በሰማይና ፡
በምድር ፡ ተሰጠኝ ። እንግዲህ ፡ ሂዱና ፡ አሕ ፲፱፡፳፤
ዛብን ፡ ሁሉ ፡ በአብ ፡ በወልድና ፡ በመንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ስም ፡ እያጠመቃችኋቸው ÷ ያዘዝኋች
ሁንም ፡ ሁሉ ፡ እንዲጠብቁ ፡ እያስተማራችኋ
ቸው ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ አድርጓቸው ፤ እነ
ሆም ፡ እኔ ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ ሁል
ጊዜ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ነኝ ።

፵፮ ፤ መዝ· ፷፰÷፳፩ ። ፶፩ ፤ ዘፀአ· ፳፮÷፴፩—፴፫ ። ፶፩—፶፮ ፤ ማር· ፲፭÷፴፱—፵፩ ፤ ሉቃ· ፳፫÷፵፯ ፡ ፵፱ ። ፶፱ ፤ ም· ፳ ÷ ፪ ፡ ፫ ። ፶፭ ፡ ፶፮ ፤ ሉቃ· ፰ ÷ ፪ ፡ ፫ ። ፶፯—፷፩ ፤ ማር· ፲፭÷፵፪—፵፯ ፤ ሉቃ ፳፫÷፶—፶፮ ፤ ዮሐ· ፲፱ ÷ ፴፰—፵፪ ፤ ኢሳ· ፶፫÷፱ ። ፷፫ ፤ ም· ፲፮÷፳፩ ።

፳፰ ። ፩—፰ ፤ ማር· ፲፮ ÷ ፩—፰ ፤ ሉቃ· ፳፬ ÷ ፩—፲ ፤ ዮሐ· ፳ ÷ ፩ ። ፫ ፤ ም· ፲፯ ÷ ፪ ። ፯ ፤ ም· ፳፮ ÷ ፴፫ ። ፯ ፤ ም· ፳፮ ÷ ፴፪ ። ፲ ፤ ዮሐ· ፳ ÷ ፲፯ ። ፲፰ ፤ ም· ፲፩ ÷ ፳፯ ፤ ዮሐ· ፫ ÷ ፴፭ ፤ ፲፫ ÷ ፫ ። ፲፱ ፤ ማር· ፲፮÷፲፭ ፡ ፲፮ ። ፳ ፤ ም· ፲፰÷፳ ።

የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡

ቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ እንደ ፡ ጻፈው ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ መጀመሪያ ።

፪ ፡ ፫ እነሆ ፡ መንገድህን ፡ የሚጠርግ ፡ መልክተኛዬን ፡ በፊትህ ፡ እልክለሁ ፡ የጌታን ፡ መንገድ ፡ አዘጋጁ ፡ ጥርጊያውንም ፡ አትኑ ፡ እያለ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የሚጮኽ ፡ ሰው ፡ ድምፅ ፡

፬ ፡ ፮ ተብሎ ፡ በነቢዩ ፡ በኢሳይያስ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ዮሐንስ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እያጠመቀ ፡ የንስሐንም ፡ ጥምቀት ፡ ለኃጢአት ፡ ስርየት ፡ እየሰበከ ፡ መጣ ። የይሁዳም ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ የኢየሩሳሌምም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ይወጡ ፡ ነበር ፡ ኃጢአታቸውንም ፡ እየተናዘዙ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ወንዝ ፡ ከእርሱ ፡ ያጠመቁ ፡ ነበር ። ዮሐንስም ፡ የግመል ፡ ጠጕር ፡ ለብሶ ፡ በወገቡ ፡ ጠፍር ፡ ይታጠቅ ፡ አንበጣና ፡ የበረሀ ፡ ማርም ፡ ይበላ ፡ ነበር ። ፰ ፡ ፲ ትኩንብሽ ፡ የሚሻውን ፡ ጠፍር ፡ መፍታት ፡ የማይገባኝ ፡ ከእኔ ፡ የሚበረታ ፡ በኋላዬ ፡ ይመጣል ። እኔ ፡ በውኃ ፡ አጠመቅኋችሁ ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያጠምቃችኋል ፡ እያለ ፡ ይሰብክ ፡ ነበር ።

፱ ፡ ፲፩ በዚያ ፡ ወራትም ፡ ኢየሱስ ፡ ከገሊላ ፡ ናዝሬት ፡ መጥቶ ፡ ከዮሐንስ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ወንዝ ፡ ተጠመቀ ። ወዲያውም ፡ ከውኃው ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ሰማያት ፡ ሲቀደዱ ፡ መንፈስም ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ ሲወርድበት ፡ አየና ፡ ። ፡ የምወድህ ፡ ልጄ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ በአንተ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ከሰማያት ፡ መጣ ።

፲፪ ፡ ፲፫ ወዲያውም ፡ መንፈስ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አወጣው ። በምድረ ፡ በዳም ፡ ከሰይጣን ፡ እየተፈተነ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ሰነበተ ፡ ከአራዊትም ፡ ጋር ፡ ነበረ ፡ መላእክቱም ፡ አገለገሉት ።

፲፬ ፡ ፲፭ ዮሐንስም ፡ አልፎ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ወንጌል ፡ እየሰበከና ፡ — ዘመኑ ፡ ተፈጸመ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መንግሥት ፡ ቀርቦለች ፡ ንስሐ ፡ ግቡ ፡ በወንጌልም ፡ እመኑ ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ መጣ ።

፲፮ ፡ ፳ በገሊላ ፡ ባሕርም ፡ አጠገብ ፡ ሲያልፍ ፡ ስምዖንን ፡ ወንድሙንም ፡ እንድርያስን ፡ መረባቸውን ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ሲጥሉ ፡ አየ ። ዓሣ ፡ አጥማጆች ፡ ነበሩና ። ፲ኢየሱስም ፡ — በኋላዬ ፡ ኑና ፡ ሰዎችን ፡ አጥማጆች ፡ እንድትሆኑ ፡ አደርጋችኋለሁ ፡ አላቸው ። ፲፰ ወዲያውም ፡ መረባቸውን ፡ ትተው ፡ ተከተሉት ። ፲፱ ከዚያም ፡ ጥቂት ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ የዘብዴዎስን ፡ ልጅ ፡ ያዕቆብን ፡ ወንድሙንም ፡ ዮሐንስን ፡ ደግሞ ፡ በታንኳ ፡ ላይ ፡ መረባቸውን ፡ ሲያበጁ ፡ አየ ። ፳ ወዲያውም ፡ ጠራቸው ፡ አባታቸው ፡ ዘብዴዎስን ፡ ከሞያተኞቹ ፡ ጋር ፡ በታንኳ ፡ ላይ ፡ ትተው ፡ ተከትለውት ፡ ሄዱ ።

፳፩ ፡ ፳፰ ወደ ፡ ቅፍርናሆምም ፡ ገቡ ፡ ወዲያውም ፡ በሰንበት ፡ ወደ ፡ ምኩራብ ፡ ገብቶ ፡ አስተማረ ። ፳፪ እንደ ፡ ባለ ፡ ሥልጣን ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ጸሮች ፡ አይደለምና ። ፳፫ ፡ ፳፬ በምኩራባቸው ፡ ርኩስ ፡ መንፈስ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ እርሱም ፡ — የናዝሬቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ሆይ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ምን ፡ አለን ? ልታጠፋን ፡ መጣህን ? ማን ፡ እንደ ፡ ሆንህ ፡ አውቅሃለሁ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቅዱሱ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ። ፳፭ ኢየሱስም ፡ — ዝም ፡ በል ፡ ከእርሱም ፡ ውጣ ፡ ብሎ ፡ ገሠጸው ። ፳፮ ርኩሱም ፡ መንፈስ ፡ እንፈራገጠውና ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኾ ፡ ከእርሱ ፡ ወጣ ። ፳፯ ሁሉም ፡ — ይህ ፡ ምን ፡ ድር ፡ ነው ? በሥልጣን ፡ ርዝሳን ፡ መናፍስትን ፡ ያዝዛል ፡ እነርሱም ፡ ይታዘዙለታልና ፡ ይህ ፡ አዲስ ፡ ትምህርት ፡ ምንድር ፡ ነው ? ብለው ፡ እስኪጠያየቁ ፡ ድረስ ፡ አደነቁ ። ፳፰ ዝናውም ፡ ወዲያው ፡ በየስፍራው ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ዙሪያ ፡ ሁሉ ፡ ወጣ ።

፳፱ ፡ ፴፩ ወዲያውም ፡ ከምኩራብ ፡ ወጥቶ ፡ ከያዕቆብና ፡ ከዮሐንስ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ስምዖንና ፡ ወደ ፡ እንድርያስ ፡ ቤት ፡ ገባ ። ፴ የስምዖንም ፡ አማት ፡ በንዳድ ፡ ታማ ፡ ተኝታ ፡ ነበር ። ስለ ፡ እርስዋም ፡ ወዲያው ፡ ነገሩት ። ፴፩ ቀርቦም ፡ እጅዋን ፡ ይዞ ፡ አስነሣት ። ንዳዱም ፡ ወዲያው ፡ ለቀቃትና ፡ አገለገለቻቸው ።

፴፪ ፡ ፴፬ ዐሥራም ፡ ገብቶ ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ የታመሙትንና ፡ አጋንንት ፡ ያደረባቸውን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አመጡ ፡ ከተማይቱም ፡ ሁላ ፡ በደጅ ፡ ተሰብስባ ፡ ነበር ። ፴፫ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ደዌም ፡ የታመሙትን ፡ ብዙዎችን ፡ ፈወሰ ፡ ብዙዎችንም ፡ አጋንንት ፡ አወጣ ። አጋንንትንም ፡ ክርስቶስ ፡ መሆኑን ፡ አውቀው ፡ ነበርና ፡ ሊናገሩ ፡ አልፈቀደላቸውም ።

፴፭ ፡ ፴፮ ማለዳም ፡ ተነሥቶ ፡ ገና ፡ ሌሊት ፡ ሳለ ፡ ወጣ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡ ሄዶ ፡ በዚያ ፡ ጸለየ ። ፴፯ ስምዖንና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የነበሩትም ፡ ተከተሉት ። ፴፰ ባገኙትም ፡ ጊዜ ፡ — ሁሉ ፡ ይፈልጉሃል ፡ አሉት ። እርሱም ፡ — በዚያ ፡ ደግሞ ፡ ልሰብክ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ በቅርብ ፡ ወዳሉ ፡ መንደሮች ፡ እንሂድ ፡ ስለዚህ ፡ ወጥቻለሁና ፡ አላቸው ። ፴፱ በምኩራቦቻቸውም ፡ እየሰበከ ፡ አጋንንትንም ፡ እያወጣ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ሁሉ ፡ መጣ ።

፵ ፡ ፵፭ ለምጻምም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ መጥቶ ፡ ተንበረከከና ፡ — ብትወድስ ፡ ልታነጻኝ ፡ ትችላለህ ፡ ብሎ ፡ ለመነው ። ፵፩ ኢየሱስም ፡ አዘነለት ፡ እጁንም ፡ ዘርግቶ ፡ ዳሰሰውና ፡ — እወድሃለሁ ፤ ንጻ ፡ አለው ። ፵፪ ፡ ፵፫ በተናገረም ፡ ጊዜ ፡ ለምጹ ፡ ወዲያው ፡ ለቀቀውና ፡ ነጻ ። ፵፬ በብርቱም ፡ ተናግሮ ፡ ወዲያው ፡ አወጣው ፤ ለማንም ፡ አንዳች ፡ እንዳትናገር ፡ ተጠንቀቅ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሄደህ ፡ ራስህን ፡ ለካህን ፡ አሳይ ፡ ለእነርሱም ፡ ምስክር ፡ እንዲሆን ፡ ስለ ፡ መንጻትህ ፡ ሙሴ ፡ ያዘዘውን ፡ አቅርብ ፡ አለው ። ፵፭ እርሱ ፡ ግን ፡ ሲወጣ ፡ ብዙ ፡ ሊሰብክና ፡ ነገሩን ፡ ሊያወራ ፡ ጀመረ ፡ ስለዚህም ፡ ኢየሱስ ፡ ተገልጦ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ መግባት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ተሳነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በውጭ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ይኖር ፡ ነበር ፤ ከየስፍራውም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ይመጡ ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ፡ ፪ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ቅፍርናሆም ፡ ደግሞ ፡ ገብቶ ፡ በቤት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተሰማ ። ፪ በደጅ ፡ ያለው ፡ ስፍራም ፡ እስኪጠባቸው ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተሰበሰቡ ፤ ቃሉንም ፡ ይነግራቸው ፡ ነበር ። ፫ አራት ፡ ሰዎችም ፡ የተሸከሙትን ፡ ሽባ ፡ አመጡለት ። ፬ ስለ ፡ ሕዝቡም ፡ ብዛት ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ማቅረብ ፡ ቢያቅታቸው ፡ እርሱ ፡ ያለበትን ፡ የቤቱን ፡ ጣሪ ፡ አነሡ ፥ ነድለውም ፡ ሽባው ፡ የተኛበትን ፡ አልጋ ፡ አወረዱ ። ፭ ኢየሱስም ፡ እምነታቸውን ፡ አይቶ ፡ ሽባውን ፡ — አንተ ፡ ልጅ ፡ ኃጢአትህ ፡ ተሰረየችልህ ፡ አለው ። ፮ ከጻፎችም ፡ አንዳንዶቹ ፡ በዚያ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፡ በልባቸውም ፡ — ይህ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ስድብ ፡ ይናገራል ? ከአንዱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ ኃጢአት ፡ ሊያስተሰርይ ፡ ማን ፡ ይችላል ? ብለው ፡ አሰቡ ። ፰ ወዲያውም ፡ ኢየሱስ ፡ በልባቸው ፡ እንዲህ ፡ እንዳሰቡ ፡ በመንፈሱ ፡ አውቆ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ — በልባችሁ ፡ ይህን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ታስባላችሁ ? ፱ ሽባውን ፡ — ኃጢአትህ ፡ ተሰረየችልህ ፡ ከማለት ፡ ወይስ ፡ — ተነሣ ፡ አልጋህንም ፡ ተሸክመና ፡ ሂድ ፡ ከማለት ፡ የቱ ፡ ይቀላል ? ነገር ፡ ግን ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ኃጢአትን ፡ ሊያስተሰርይ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ እንድታውቁ ፤ ፲ ሽባውን ፡ — አንተን ፡ እልሃለሁ ፡ ተነሣ ፡ አልጋህን ፡ ተሸክመና ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ ሂድ ፡ አለው ። ፲፩ ተነሥቶም ፡ ወዲያው ፡ አልጋውን ፡ ተሸክሞ ፡ በሁሉ ፡ ፊት ፡ ወጣ ፡ ስለዚህም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ተገረሙና ፡ — እንዲህ ፡ ያለ ፡ ከቶ ፡ አላየንም ፡ ብለው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አከበሩ ።

፲፫ ፡ ፲፯ ደግሞም ፡ በባሕር ፡ አጠገብ ፡ ወጣ ፤ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ መጡና ፡ አስተማራቸው ። ፲፬ ሲያልፍም ፡ በመቅረጫው ፡ ተቀምጦ ፡ የነበረውን ፡ የአልፍዮስን ፡ ልጅ ፡ ሌዊን ፡ አየና ፡ — ተከተለኝ ፡ አለው ። ተነሥቶም ፡ ተከተለው ።

፲፭ ፡ ፲፮ በቤቱም ፡ በማዕድ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ብዙ ፡ ቀራጮችና ፡ ኃጢአተኞች ፡ ከኢየሱስና ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፤ ጋር ፡ ተቀመጡ ፤ ብዙ ፡ ነበሩ ፡ ይከተሉትም ፡ ነበር ። ፲፮ ጸሮችና ፡ ፈሪሳውያንም ፡ ከቀራጮችና ፡ ከኃጢአተኞች ፡ ጋር ፡ ሲበላ ፡ አይተው ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ — ከቀራጮችና ፡ ከኃጢአተኞች ፡ ጋር ፡ የሚበላና ፡ የሚጠጣ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ? አሉ ። ፲፯ ኢየሱስም ፡ ሰምቶ ፡ — ሕመምተኞች ፡ እንጂ ፡ ብርቱዎች ፡ ባለ ፡ መድኃኒት ፡ አያስፈልጋቸውም ፤ ኃጢአተኞችን ፡ እንጂ ፡ ጻድቃንን ፡ ልጠራ ፡ አልመጣሁም ፡ አላቸው ።

፲፰ ፡ ፳ የዮሐንስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትና ፡ ፈሪሳውያን ፡ ይጦሙ ፡ ነበር ። መጥተውም ፡ — የዮሐንስና ፡ የፈሪሳውያን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ የሚጦሙት ፡ የአንተ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ግን ፡ የማይጦሙት ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ? አሉት ። ፲፱ ኢየሱስም ፡ አላቸው ፡ — ሙሽራው ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ሳለ ፡ ሚዜዎች ፡ ሊጦሙ ፡ ይችላሉን ? ሙሽራው ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ሳለ ፡ ሊጦሙ ፡ አይችሉም ። ፳ ነገር ፡ ግን ፡ ሙሽራው ፡ ከእነርሱ ፡ የሚወሰድበት ፡ ወራት ፡ ይመጣል ፡ በዚያ ፡ ወራትም ፡ ይጦማሉ ። ፳፩ በአረጀ ፡ ልብስ ፡ አዲስ ፡ እራፊ ፡ የሚጥፍ ፡ የለም ፤ ቢደረግ ፡ ግን ፡ አዲሱ ፡ መጣፊያ ፡ አሮጌውን ፡ ይበጭቀዋል ፡ መቀደዱም ፡ የበሰ ፡ ይሆናል ። ፳፪ በአረጀ ፡ አቁማዳም ፡ አዲስ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ የሚያኖር ፡ የለም ፤ ቢደረግ ፡ ግን ፡ የወይን ፡ ጠጁ ፡ አቁማዳውን ፡ ያፈነዳል ፡ የወይኑም ፡ ጠጅ ፡ ይፈሳል ፡ አቁማዳውም ፡ ይጠፋል ፡ አዲሱን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ግን ፡ በአዲስ ፡ አቁማዳ ፡ ያኖራሉ ።

፳፫ ፡ ፳፰ በሰንበትም ፡ በእርሻ ፡ መካከል ፡ ሲያልፍ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ እየሄዱ ፡ እሸት ፡ ይቀጥፉ ፡ ጀመር ። ፳፬ ፈሪሳውያንም ፡ — እነሆ ፡ በሰንበት ፡ ያልተፈቀደውን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ያደርጋሉ ? ፡ ሉት ። ፳፭ እርሱም ፡ — ዳዊት ፡ በሰፈልጎ ፡ ተቀምጦ ፡ የነበረውና ፡ ራቡ ፡ እርሱና ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡ ያደረጉትን ፡ ከቶ ፡ አላነበባችሁምን ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ተርቦ ፡ ተርቦም ፡ የነበሩት ፡ ከአብያታር ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ከካህናት ፡ በቀር ፡ መብላት ፡ ያልተፈቀደውን ፡ የመሥዋዕ

ትን፡ እንጀራ፡ እንደ፡ በላ÷ከእርሱም፡ ጋር፡ ለነበሩት፡ እንደ፡ ሰጣቸው፡ ከቶ፡ አላነበባችሁምን ፥
፳፭፡ አላቸው ። ደግሞ ፡— ሰንበት፡ ስለ፡ ሰው፡ ተፈጥሮአል ፡ እንጂ ፡ ሰው፡ ስለ፡ ሰንበት፡ አልተፈጠረም ፤ እንዲሁም ፡ የሰው፡ ልጅ፡ ለሰንበት፡ እንኳ፡ ጌታዋ ፡ ነው፡ አላቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩፡ ደግሞም ፡ ወደ ፡ ምኵራብ ፡ ገባ ። በዚያም ፡
፪፡ እጁ ፡ የሰለለች ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ሊከሱትም ÷ በሰንበት ፡ ይፈውሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይጠባበቁት ፡
፫፡ ነበር ። እጁ ፡ የሰለለችውንም ፡ ሰው ፡— ተነሥተህ፡ ወደ፡ መካከል ፡ ና ፡ አለው ። በሰንበት ፡ በጎ፡
፬፡ ማድረግ ፡ ተፈቅዶአልን ፡ ወይስ ፡ ክፉ ? ነፍስ ፡ ማዳንን ፡ ወይስ ፡ መግደል ? አላቸው ፡ እነርሱም ፡
፭፡ ዝም ፡ አሉ ። ስለ ፡ ልባቸውም ፡ ድንዝዝ ፡ አዝኖ ፡ ዙሪያውን ፡ እየ ፡ ተመለከተ ፡ በቍጣ ፡ እያየው-
ሰውየውንም ፡— እጅህን ፡ ዘርጋ ፡ አለው ። ዘረ ፡ ጋትም ፤ እጁም ፡ ዳነች ። ፌሪሳውያንም ፡ ወጥ፡
፮፡ ተው ፡ ወዲያው ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ እንዳያ ጠፉት ፡ ከሄሮድስ ፡ ወገን ፡ ጋር ፡ ተማከሩበት ።
፯፡ ኢየሱስም ፡ ከደቀ ፡ መዘሙርቱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ፈቀቅ ፡ አለ ፤ ከገሊላ ፡ የመጡም ፡ ብዙ ፡
፰፡ ሰዎች ፡ ተከተሉት ፤ እንዲት ፡ ትልቅ ፡ ነገርም ፡ እንዳደረገው ፡ ሰምተው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከይ-
ሁዳ ፡ ከኢየሩሳሌምም ፡ ከኤዶምያስም ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ማዶም ፡ ከጢሮስና ፡ ከሲዶና ፡ ምድርም ፡
፱፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ መጡ ። ሰዎቹም ፡ እንዳያጋፉት ፡ ታንኳን ፡ ያቶይለት ፡ ዘንድ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡
፲፡ አዘዘቸው ፤ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ አድኖ ፡ ነበርና ÷ ስለዚህም ፡ ሥቃይ ፡ ያልባቸው ፡ ሁሉ ፡ እንዲዳ-
፲፩፡ ስሱት ፡ ይወድቁበት ፡ ነበር ። ርኩሳን ፡ መናፍስትም ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ በፊቱ ፡ ተደፍተው ፡ ፡—
አንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነህ ፡ እያሉ ፡
፲፪፡ ጮኹ ። እንዳይገልጡትም ፡ በጣም ፡ አዘዘቸው ።
፲፫፡ ወደ ፡ ተራራም ፡ ወጣ ÷ ራሱም ፡ የወደዳቸውን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ጠራ ÷ ወደ ፡ እርሱም ፡ ሄዱ ።
፲፬፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ እንዲኖሩና ፡ ለመስበክ ፡ እን-
፲፭፡ ዲልካቸው ፡ ድውዮችንም ፡ ሊፈውሱ ፡ አጋንንትንም ፡ ሊያወጡ ፡ ሥልጣን ፡ ይሠጣቸው ፡
፲፮፡ ዘንድ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ አደረገ ፤ ስምዖንንም ፡
፲፯፡ ጴጥሮስ ፡ ብሎ ፡ ሰየመው ፤ የዘብዴዎስንም ፡ ልጅ ፡ ያዕቆብን ፡ የያዕቆብንም ፡ ወንድም ፡ ዮሐንስን ፡
በእኔርጌስ ፡ ብሎ ፡ ሰየማቸው ÷ የነጐድጓድ ፡
፲፰፡ ልጆች ፡ ማለት ፡ ነው ፤ እንድርያስንም ፡ ፊልጵስንም ፡ በርተሎሜዎስንም ፡ ማቴዎስንም ፡ ቶማስንም ፡ የአልፍዮስን ፡ ልጅ ፡ ያዕቆብንም ፡ ታዴዎስ-
ንም ፡ ቀንናዊውንም ፡ ስምዖንን ÷ አሳልፎ ፡ የሰጠውንም ፡ የአስቆሮቱን ፡ ይሁዳን ።
፲፱፡ ወደ ፡ ቤትም ፡ መጡ ፤ እንጀራም ፡ መብላት ፡
፳፡ ስንኳ ፡ እስኪ ፡ ሳናቸው ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ብዙ ፡
ሰዎች ፡ ተሰበሰቡ ። ዘመዶቹም ፡ ሰምተው ፡—
፳፩፡ አበደ ፡ ብለዋልና ፡ ሊያዙት ፡ ወጡ ። ከኢየሩሳ-
፳፪፡ ሌም ፡ የወረዱ ፡ ጻፎችም ፡— ብዔል ፡ ዘቡል ፡ አለበት ፡ ደግሞ ፡— በእጋንጉት ፡ አለቃ ፡ አጋንን-
ትን ፡ ያወጣል ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ። እነርሱንም ፡
፳፫፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ጠርቶ ፡ በምሳሌ ፡ አላቸው ፡— ሰይ-
ጣን ፡ ሰይጣንን ፡ ሊያወጣው ፡ እንዴት ፡ ይች-
ላል ፡ መንግሥትም ፡ እርስ ፡ በርስዋ ፡ ከተለያ-
፳፬፡ የች ፡ ያች ፡ መንግሥት ፡ ልትቆም ፡ አትችልም ፡
፳፭፡ ቤትም ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ከተለያየ ፡ ያ ፡ ቤት ፡
፳፮፡ ሊቆም ፡ አይችልም ። ሰይጣንም ፡ ራሱን ፡ ተቃ-
፳፯፡ ውሞ ፡ ከተለያየ ÷ መጨረሻ ፡ ይሆንበታል ፡ እንጂ ፡
ሊቆም ፡ አይችልም ። ነገር ፡ ግን ፡ አስቀድሞ ፡
፳፰፡ ኃይለኛውን ፡ ሳያስር ፡ ወደ ፡ ኃይለኛው ፡ ቤት ፡
ገብቶ ፡ ዕቃውን ፡ ሊበዘብዝ ፡ የሚችል ፡ የለም ÷
ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ቤቱን ፡ ይበዘብዛል ።
፳፱፡ እውነት ፡ አላችኋለሁ ÷ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ኀጢ-
፴፡ አት ፡ ሁሉ ፡ የሚሰደቡትም ፡ ስድብ ፡ ሁሉ ፡ ይሰረ-
ይላቸዋል ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ የሚሰደብ ፡
፴፩፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ የዘላለም ፡ ኃጢአት ፡ ዕዳ ፡ ይሆን-
በታል ፡ እንጂ ፡ ለዘላለም ፡ አይሰረይለትም ።
፴፪፡ ርኩስ ፡ መንፈስ ፡ አለበት ፡ ይሉ ፡ ነበርና ።
፴፫፡ እናቱና ፡ ወንድሞቹም ፡ መጡ ፡ በውጭም ፡
፴፬፡ ቆመው ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ልከው ፡ አስጠሩት ። ብዙ ፡
፴፭፡ ሰዎችም ፡ በዙሪያው ፡ ተቀምጠው ፡ ነበሩና ፡—
እነሆ ÷ እናትህ ፡ ወንድሞችህም ፡ በውጭ ፡
ቆመው ፡ ይፈልጉሃል ፡ አሉት ። መልሶም ፡—
፴፮፡ እናቴ ፡ ማን ፡ ናት ? ወንድሞቼስ ፡ እነ ፡ ማን ፡
ናቸው ? አላቸው ። በዙሪያው ፡ ተቀምጠው ፡
፴፯፡ ወደ ፡ ነበሩት ፡ ተመለከተና ፡— እነሆ ፡ እናቴ ፡
ወንድሞቼም ። የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡
፴፰፡ የሚያደርግ ፡ ሁሉ ÷ እርሱ ፡ ወንድሜ ፡ ነው ፡
እኅቴም ፡ እናቴም ፡ አለ ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩፡ ደግሞም ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ ሊያስተምር ፡ ጀመረ ።
እጅግ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ስለ ፡ ተሰ-
በሰቡ ፡ እርሱ ፡ በታንኳ ፡ ገብቶ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡
ተቀመጠ ፤ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ በም-
፪፡ ድር ፡ ላይ ፡ ነበሩ ። በምሳሌም ፡ ብዙ ፡ ያስተም-
ራቸው ፡ ነበር ÷ በትምህርቱም ፡ አላቸው ፡—
፫፡ ስሙ ። እነሆ ÷ ዘሪ ፡ ሊዘራ ፡ ወጣ ። ሲዘራም ፡
፬፡ አንዳንዱ ፡ በመንገድ ፡ ዳር ፡ ወደቀና ፡ ወፎች ፡

፳፱ ። ፳፭ ፡ ዘዳግ ፡ ፭÷፲፱ ።

፫ ። ፩—፭ ፡ ማቴ ፡ ፲፪ ÷ ፱—፲፬ ፡ ሉቃ ፡ ፮ ÷ ፯—፲፩ ። ፮ ፡ ማቴ ፡ ፳፪ ÷ ፲፯ ። ፯ ፡ ፳፫ ፡ ሉቃ ፡ ፮ ÷ ፲፯ ፡ ፲፰ ። ፰ ፡ ም ፡ ፭ ÷ ፳፭ ፡ ፯ ÷ ፲፭ ፡ ሉቃ ፡ ፮ ÷ ፲፱ ። ፲፩ ፡ ም ፡ ፭ ÷ ፳፱ ፤ ፭ ÷ ፯ ፤ ፲፭ ÷ ፴፱ ፤ ማቴ ፡ ፭ ÷ ፳፱ ፤ ሉቃ ፡ ፱ ÷ ፵፭ ፤ ዮሐ ፡ ፭ ÷ ፱ ። ፲፪ ፡ ማቴ ፡ ፲፫ ፡ ፲፭ ። ፲፫—፲፭ ፡ ማቴ ፡ ፲ ÷ ፩ ፤ ሉቃ ፡ ፮ ÷ ፲፪ ፤ ፻፫ ። ፲፮—፲፱ ፡ ማቴ ፡ ፲ ÷ ፪—፬ ፤ ሉቃ ፡ ፮ ÷ ፲፬—፲፮ ፤ የሐዋ ፡ ፩ ÷ ፲፫ ። ፲፯ ፡ ማቴ ፡ ፲፯ ÷ ፲፰ ፤ ዮሐ ፡ ፩ ÷ ፵፪ ። ፳፪ ፤ ማቴ ፡ ፱ ÷ ፴፬ ። ፳፫—፳፭ ፤ ማቴ ፡ ፲፪ ÷ ፳፭—፳፰ ፤ ሉቃ ፡ ፲፩ ÷ ፲፭—፲፰ ። ፳፮ ፡ ማቴ ፡ ፲፪ ÷ ፴፪ ። ፳፱ ፡ ማቴ ፡ ፲፪ ÷ ፴፩ ። ፴፩ ፡ ማቴ ፡ ፲፪ ÷ ፴፪ ። ፴፪ ፡ ማቴ ፡ ፲፪ ÷ ፵፮ ፤ ሉቃ ፡ ፰ ÷ ፲፱ ። ፴፫ ፡ ማቴ ፡ ፲፪ ÷ ፵፮—፵፱ ፤ ሉቃ ፡ ፰ ÷ ፲፱—፳፩ ። ፴፭ ፡ ማቴ ፡ ፲፪ ÷ ፵፮ ፤ ሉቃ ፡ ፰ ÷ ፲፱ ። ፴፮ ፡ ማቴ ፡ ፲፪ ÷ ፵፰ ፤ ሉቃ ፡ ፰ ÷ ፳ ። ፴፯ ፡ ማቴ ፡ ፲፪ ÷ ፵፱ ፤ ሉቃ ፡ ፰ ÷ ፳፩ ። ፴፰ ፡ ማቴ ፡ ፲፪ ÷ ፶ ፤ ሉቃ ፡ ፰ ÷ ፳፩ ።

፭፡ መጥተው ፡ በሉት ። ሌላውም ፡ ብዙ ፡ መሬት ፡
በሌለበት ፡ በጭንጫ ፡ ላይ ፡ ወደቀና ፡ ጥልቅ ፡
፮፡ መሬት ፡ ስላልነበረው ፡ ወዲያው ፡ በቀለ ፤ ፀሐ-
ይም ፡ ሲወጣ ፡ ጠወለገ ÷ ሥርም ፡ ስላልነበረው ፡
፯፡ ደረቀ ። ሌላውም ፡ በእሾህ ፡ መካከል ፡ ወደቀ ÷
እሾህም ፡ ወጣና ፡ አነቀው ÷ ፍሬም ፡ አልሰጠም ።
፰፡ ሌላውም ፡ በመልካም ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ወደቀና ፡
ወጥቶ ፡ አድጎ ፡ ፍሬ ፡ ሰጠ ÷ አንዱም ፡ ሠላሳ ፡ አን-
፱፡ ዱም ፡ ስድሳ ፡ አንዱም ፡ መቶ ፡ አፈራ ። የሚ-
ሰማ ፡ ጆሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ፡ አለ ።
፲፡ ብቻውንም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በዙሪያው ፡ የነበሩት ፡
ከአሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ምሳሌው ፡ ጠየ-
፲፩፡፲፪፡ ቁት ። እንዲህም ፡ አላቸው ፡— ለእናንተ ፡ የእግ
ዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ምሥጢር ፡ ማወቅ ፡
ተሰጥቶአችኋል ፡ በውጭ ፡ ላሉት ፡ ግን ÷
አይተው ፡ እንዳያዩ ፡ እንዳይመለከቱም ÷
ሰምተውም ፡ እንዳሰሙ ፡ እንዳያስተው-
ሉም ÷ እንዳይመለሱ ፡ ኃጢአታቸውም ፡
እንዳይሰረይላቸው ፡
፲፫፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በምሳሌ ፡ ይሆንባቸዋል ። አላቸ-
ውም ፡— ይህን ፡ ምሳሌ ፡ አታውቁምን ? እንዴ-
፲፬፡ ት ፡ ምሳሌዎቹን ፡ ሁሉ ፡ ታውቃላችሁ ? ዘሪው ፡
፲፭፡ ቃሉን ፡ ይዘራል ። ቃልም ፡ በተዘራበት ፡ በመ
ንገድ ፡ ዳር ፡ የሆኑት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ÷ በሰ
ሙት ፡ ጊዜም ፡ ሰይጣን ፡ ወዲያው ፡ መጥቶ ፡
በልባቸው ፡ የተዘራውን ፡ ቃል ፡ ይወስዳል ።
፲፮፡ እንዲሁም ፡ በጭንጫ ፡ ላይ ፡ የተዘሩት ፡ እነዚህ ፡
ናቸው ÷ ቃሉንም ፡ ሰምተው ፡ ወዲያው ፡ በደ
፲፯፡ ስታ ፡ ይቀበሉታል ÷ ለጊዜውም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
በእነርሱ ፡ ሥር ፡ የላቸውም ÷ ኃላም ፡ በቃሉ ፡
ምክንያት ፡ መከራ ፡ ወይም ፡ ስደት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡
፲፰፡ ወዲያው ፡ ይሰናከላሉ ። በእሾህም ፡ የተዘሩት ፡
ሌሎች ፡ ናቸው ÷ ቃሉን ፡ የሰሙት ፡ እነዚህ ፡
፲፱፡ ናቸው ÷ የዚህም ፡ ዓለም ፡ አሳብና ፡ የብለጠግነት ፡
ማታለል ፡ የሌላውም ፡ ነገር ፡ ምኞት ፡ ገብተው ፡
፳፡ ቃሉን ፡ ያንቃሉ ÷ የማያፈራም ፡ ይሆናል ። በመ
ልካም ፡ መሬት ፡ የተዘሩት ፡ ቃሉን ፡ ሰምተው ፡
የሚቀበሉት ፡ አንዱም ፡ ሠላሳ ፡ አንዱም ፡ ስድሳ ፡
አንዱም ፡ መቶ ፡ ፍሬ ፡ የሚያፈሩት ፡ እነዚህ ፡
ናቸው ።
፳፩፡ እንዲህም ፡ አላቸው ፡— መብራትን ፡ ከዕን
ቅብ ፡ ወይስ ፡ ከአልጋ ፡ በታች ፡ ሊያኖሩት ፡ ያመ
ጡታልን ? በመቅረዝ ፡ ላይ ፡ ሊያኖሩት ፡ እይ
፳፪፡ ደለምን ? እንዲገለጥ ፡ ባይሆን ፡ የተሰወረ ፡ የለ
ምና ፤ ወደ ፡ ግልጥ ፡ እንዲመጣ ፡ እንጂ ፡ የተሸ
፳፫፡ ሸገ ፡ የለም ። የሚሰማ ፡ ጆሮ ፡ ያለው ፡ ይሰማ ።
፳፬፡ ደስማ ። አላቸውም ፡— ምን ፡ እንድትሰሙ ፡
ተጠበቁ ። በምትሰፍሩበት ፡ መስፈሪያ ፡ ይሰፈ-
ርላችኋል ፡ ለእናንተም ፡ ይጨመርላችኋል ።
፳፭፡ ላለው ፡ ይሰጠዋልና ፤ ከሌለውም ፡ ያው ፡ ያለው ፡

እንኳ ፡ ይወሰድበታል ።
፳፮፡ እርሱም ፡ አለ ፡— በምድር ፡ ዘርን ፡ እንደሚ
ዘራ ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ እን
፳፯፡ ደዚህ ፡ ናት ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ ይተኛልም ፡ ይነ
ሣልም ÷ እርሱም ፡ እንዴት ፡ እንደሚሆን ፡ ሰያ
፳፰፡ ውቅ ፡ ዘሩ ፡ ይበቅላል ፡ ያድግማል ። ምድሪ
፳፱፡ ቱም ፡ አውቃ ፡ በመጀመሪያ ፡ ቡቃያ ፡ ኋላም ፡
ዛላ ፡ ኋላም ፡ በዛላው ፡ ፍጹም ፡ ሰብል ፡ ታፈራ-
ለች ። ፍሬ ፡ ግን ፡ ሲበስል ፡ መከር ፡ ደርሶአልና ፡
፴፡ ወዲያው ፡ ማጭድ ፡ ይልካል ።
፴፩፡ እርሱም ፡ አለ ፡— የእግዚአብሔርን ፡ መን
፴፪፡ ግሥት ፡ በምን ፡ እናስመስላታለን ? ወይስ ፡
በምን ፡ ምሳሌ ፡ እንመስላታለን ? እንደ ፡ ሰና
፴፫፡ ፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ናት ÷ እርስዋም ፡ በምድር ፡ በተ
ዘራች ፡ ጊዜ ፡ በምድር ፡ ካለ ፡ ዘር ፡ ሁሉ ፡ ታን
ሳለች ፡ በተዘራችም ፡ ጊዜ ፡ ትወጣለች ፡ ከአት
፴፬፡ ክልትም ፡ ሁሉ ፡ የምትበልጥ ፡ ትሆናለች ፡ የሰ
ማይ ፡ ወፎችም ፡ በጥላዋ ፡ ሊሰፍሩ ፡ እስኪችሉ ፡
ታላላቅ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ታደርጋለች ።
፴፭፡ መስማትም ፡ በሚችሉበት ፡ መጠን ፡ እነዚ
፴፮፡ ህን ፡ በሚመስል ፡ በብዙ ፡ ምሳሌ ፡ ቃሉን ፡ ይነ
ግራቸው ፡ ነበር ፤ ያለ ፡ ምሳሌ ፡ ግን ፡ አልነገራቸ
፴፯፡ ውም ÷ ለብቻቸውም ፡ ሲሆኑ ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡
ለገዝ ፡ ደቀ ፡ መዘሙርቱ ፡ ይፈታላቸው ፡ ነበር ።
፴፰፡ በዚያም ፡ ቀን ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡— ወደ ፡ ማዶ ፡
፴፱፡ እንሻገር ፡ አላቸው ። ሕዝቡንም ፡ ትተው ፡ በታ
ንኳ ፡ እንዳለው ፡ ወሰዱት ÷ ሌሎች ፡ ታንኳዎ
፵፡ ችም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ነበሩ ። ብርቱ ፡ ዐውሎ ፡
፵፩፡ ነፋስም ፡ ተነሣና ፡ ውኃ ፡ በታንኳይቱ ፡ እስኪሞላ ፡
ድረስ ፡ ማዕበሉ ፡ በታንኳይቱ ፡ ይገባ ፡ ነበር ።
እርሱም ፡ በስተኋላዋ ፡ ትራስ ፡ ተንተርሶ ፡ ተኝቶ ፡
ነበር ። አንቅተውም ፡— መምህር ፡ ሆይ ÷ ስን
ጠፋ ፡ አይገድህምን ? አሉት ። ነቅቶም ፡ ነፋ-
ስን ፡ ገሠጸው ፡ ባሕሩንም ፡— ዝም ፡ በል ÷ ፀጥ ፡
በል ፡ አለው ። ነፋሱም ፡ ተወ ፡ ታላቅ ፡ ፀጥ
ታም ፡ ሆነ ። እንዲህ ፡ የምትፈሩ ፡ ስለ ፡ ምን ፡
፵፩፡ ነው ? እንዴትስ ፡ እምነት ፡ የላችሁም ? አላ
ቸው ። እጅግም ፡ ፈሩና ፡— እንግዲህ ፡ ነፋስም ፡
ባሕርም ፡ የሚታዘዙለት ፡ ይህ ፡ ማን ፡ ነው ?
ተባባሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ማዶም ፡ ወደ ፡ ጌርጌሴኖን ፡ አገር ፡
፪፡ መጡ ። ከታንኳይቱም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ÷ ርኩስ ፡
፫፡ መንፈስ ፡ የያዘው ፡ ሰው ፡ ከመቃብር ፡ ወጥቶ ፡
ወዲያው ፡ ተገናኘው ። እርሱም ፡ በመቃብር ፡
፬፡ ይኖር ፡ ነበር ÷ በሰንሰለትም ፡ ስንኳ ፡ ማንም ፡
ሊያስረው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አይችልም ፡ ነበር ፤
፭፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በእግር ፡ ብረትና ፡ በሰንሰለት ፡ ይታ
ሰር ፡ ነበርና ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ሰንሰለቱን ፡ ይበጣ

፭ ። ፲፪ ፡ ኢሳ ፡ ፮ ÷ ፱ ፤ ፮ ። ፲፮—፳፩ ፡ ሉቃ ፡ ፰ ÷ ፲፮—፲፰ ፤ ማቴ ፡ ፭ ÷ ፲፭ ። ፲፯ ፡ ማቴ ፡ ፮ ÷ ፳፭ ። ፲፱ ፡ ማቴ ፡ ፮ ÷ ፳፫ ። ፳፩ ፡ ማቴ ፡ ፲፫ ÷ ፲፪ ። ፳፪ ፡ ሉቃ ፡ ፰ ÷ ፲፯ ። ፳፬ ፡ ማቴ ፡ ፲፫ ÷ ፲፪ ። ፳፭ ፡ ማቴ ፡ ፳፭ ÷ ፳፱ ። ፳፮—፳፱ ፡ ማቴ ፡ ፲፫ ÷ ፴፪—፴፫ ። ፴ ፡ ማቴ ፡ ፲፫ ÷ ፴፬ ። ፴፫—፴፬ ፡ ማቴ ፡ ፲፫ ÷ ፴፭ ፤ ሉቃ ፡ ፰ ÷ ፳፪ ። ፴፭ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፳፫ ። ፴፮ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፳፮ ። ፴፯ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፳፮ ። ፴፰ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፳፬ ። ፴፱ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፳፮ ። ፵ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፳፯ ። ፵፩ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፳፯ ።

፩ ። ፩—፭ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፳፰—፴፪ ፤ ሉቃ ፡ ፰ ÷ ፳፮—፴፱ ። ፭ ፡ ኢሳ ፡ ፷፭ ÷ ፩ ። ፮ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፳፱ ። ፯ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፩ ። ፰ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፪ ። ፱ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፫ ። ፲ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፬ ። ፲፩ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፭ ። ፲፪ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፭ ። ፲፫ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፲፬ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፲፭ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፲፮ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፲፯ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፲፰ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፲፱ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፳ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፳፩ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፳፪ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፳፫ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፳፬ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፳፭ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፳፮ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፳፯ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፳፰ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፳፱ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፴ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፴፩ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፴፪ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፴፫ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፴፬ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፴፭ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፴፮ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፴፯ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፴፰ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፴፱ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፵ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ። ፵፩ ፡ ማቴ ፡ ፰ ÷ ፴፮ ።

ጥስ ፡ እግር ፡ ብረቱንም ፡ ይሰባብር ፡ ነበር ÷ ሊያ
፭ ሸንፈውም ፡ የሚችል ፡ አልነበረም ። ሁልጊ
ዜም ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ በመቃብርና ፡ በተራራ ፡
ሆኖ ፡ ይጮኽ ፡ ነበር ፡ ሰውነቱንም ፡ በድንጋይ ፡
፮ ይቧጭር ፡ ነበር ። ኢየሱስንም ፡ ከሩቅ ፡ በየ
፯ ጊዜ ፡ ሮጦ ፡ ሰገደለት ÷ በታላቅ ፡ ድምፅም ፡ እየ
ጮኸ ፡ ፦ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ኢየ
ሱስ ፡ ሆይ ÷ ከእንተ ፡ ጋር ፡ ምን ፡ አለኝ ? እንዳ
ትሣቅየኝ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምልሃለሁ ፡ አለ ፤
፰ አንተ ፡ ርኩስ ፡ መንፈስ ÷ ከዚህ ፡ ሰው ፡ ውጣ ፡
፱ ብሎት ፡ ነበርና ። ስምህ ፡ ማን ፡ ነው ? ብሎ ፡
ጠየቀው ። ብዙዎች ፡ ነንና ፡ ስሜ ፡ ሌጌዎን ፡ (1)
፲ ነው ፡ አለው ፡ ከአገርም ፡ ውጭ ፡ እንዳይሰዳ
፲፩ ቸው ፡ አጥብቆ ፡ ለመነው ። በዚያም ፡ በተራራ ፡
ጥግ ፡ ብዙ ፡ የእሪያ ፡ መንጋ ፡ ይሰማራ ፡ ነበርና ፡ —
፲፪ ወደ ፡ እሪያዎቹ ፡ እንድንገባ ፡ ስደደን ፡ ብለው ፡
፲፫ ለመኑት ። ኢየሱስም ፡ ፈቀደላቸው ። ርኩሳን ፡
መናፍስቱም ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ እሪያዎቹ ፡ ገቡ ÷
ሁለት ፡ ሺህም ፡ የሚያህል ፡ መንጋ ፡ ከአፋፉ ፡
ወደ ፡ ባሕር ፡ ተሣደፉና ፡ በባሕር ፡ ሰጠሙ ።

፲፬ እረኞቹም ፡ ሸሽተው ፡ በከተማውና ፡ በአገሩ ፡
አወሩ ፤ ነገሩም ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማየት ፡
፲፭ መጡ ። ወደ ፡ ኢየሱስም ፡ መጡ ÷ አጋንንትም ፡
ያደራበትን ፡ ሌጌዎንም ፡ የነበረበትን ፡ ሰው ፡
ተቀምጦ ፡ ለብሶም ፡ ልቡም ፡ ተመልሶ ፡ አዩና ፡
፲፮ ፈሩ ። ያዩት ፡ ሰዎችም ፡ አጋንንት ፡ ላደራበት ፡
ሰው ፡ የሆነውንና ፡ ስለ ፡ እሪያዎቹ ፡ ተረከላቸው ።
፲፯ ከአገራቸውም ፡ እንዲሄድላቸው ፡ ይለምኑት ፡
፲፰ ጀመር ። ወደ ፡ ታንኳይቱም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ አጋ
ንንት ፡ አድረውበት ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ከእርሱ ፡
፲፱ ጋር ፡ እንዲኖር ፡ ለመነው ። ኢየሱስም ፡ አልፈ
ቀደለትም ÷ ነገር ፡ ግን ፡ — ወደ ፡ ቤትህ ፡ በቤተ ፡
ሰዎችህ ፡ ዘንድ ፡ ሄደህ ፡ ጌታ ፡ እንዲት ፡ ያለ ፡
ታላቅ ፡ ነገር ፡ እንዳደረገልህ ፡ እንዲነግራቸው ፡ እንደ ፡
፳ ማረህ ፡ አውራላቸው ፡ አለው ። ሄዶም ፡ ኢየ
ሱስ ፡ እንዲት ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ እንዳደረገ
ለት ፡ አሥር ፡ ከተማ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ ይሰብክ ፡
ጀመር ÷ ሁሉም ፡ ተደነቁ ።

፳፩ ኢየሱስም ፡ ደግሞ ፡ በታንኳይቱ ፡ ወደ ፡ ማዶ ፡
ከተሻገረ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡
፳፪ ተሰበሰቡ ÷ በባሕርም ፡ አጠገብ ፡ ነበር ። ኢያ
ኢሮስ ፡ የተባለ ፡ ከምኵራብ ፡ አለቆች ፡ አንዱ ፡
መጣ ፤ በየውም ፡ ጊዜ ፡ በእግሩ ፡ ላይ ፡ ወደቀና ፡ —
፳፫ ታናሽቱ ፡ ልጄ ፡ ልትሞት ፡ ቀርባለችና ፡ እንድ
ትድንና ፡ በሕይወት ፡ እንድትኖር ፡ መጥተህ ፡
እጅህን ፡ ጫንበት ፡ ብሎ ፡ አጥብቆ ፡ ለመነው ።
፳፬ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ሄደ ። ብዙ ፡ ሕዝብም ፡ ተከ
ተሉት ፡ አጋፋትም ።

፳፭ ከአሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመትም ፡ ጀምሮ ፡ ደም ፡
፳፮ የሚፈሰት ፡ ሴት ፡ ነበረች ÷ ከብዙ ፡ ባለ ፡ መድ
(1) ሌጌዎን ፡ ማለት ፡ ሠፍራ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ኃኒቶችም ፡ ብዙ ፡ ተጣቀየች ፤ ገንዘብዋንም ፡
ሁሉ ፡ ከስራ ፡ ባሰበት ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ አልተ
ጠቀመችም ፤ የኢየሱስንም ፡ ወሬ ፡ ሰምታ ፡ በስ
፳፯ ተኋላው ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ መጥታ ፡ ልብሱን ፡
ዳሰሰች ፦ ልብሱን ፡ ብቻ ፡ የዳሰስሁ ፡ እንደ
፳፰ ሆነ ፡ እድናለሁ ፡ ብላለችና ። ወዲያውም ፡ የደ
ምዋ ፡ ምንጭ ፡ ደረቀ ፡ ከሥቃይዋም ፡ እንደ ፡
ዳነች ። በሰውነትዋ ፡ አወቀች ። ወዲያውም ፡
፴ ኢየሱስ ፡ ከእርሱ ፡ ኃይል ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ በገዛ ፡
ራሱ ፡ አውቆ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ —
ልብሴን ፡ የዳሰሰ ፡ ማን ፡ ነው ? አለ ። ደቀ ፡ መዛ
፴፩ ሙርቱም ፡ — ሕዝቡ ፡ ሲያጋፉህ ፡ እያየህ ፡ — ማን ፡
ዳሰሰኝ ፡ ትላለህን ? አሉት ። ይህንም ፡ ያደረገች
፴፪ ውን ፡ ለማየት ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ይመለከት ፡ ነበር ።
፴፫ ሴቲቱ ፡ ግን ፡ የተደረገላትን ፡ ስላወቀች ÷ እየ
ፈራች ፡ እየተንቀጠቀጠችም ÷ መጥታ ፡ በፊቱ ፡
ተደፋች ፡ እውነቱንም ፡ ሁሉ ፡ ነገረችው ። እር
፴፬ ሱም ፡ — ልጄ ፡ ሆይ ÷ እምነትሽ ፡ አድኖሻል ፡
በሰላም ፡ ሂጂ ፡ ከሥቃይሽም ፡ ተፈወሽ ፡ አላት ።

፴፭ እርሱም ፡ ገና ፡ ሲናገር ፡ ከምኵራብ ፡ አለቃው ፡
ቤት ፡ ዘንድ ፡ የመጡት ፡ — ልጅህ ፡ ሞታለች ፤
ስለ ፡ ምን ፡ መምህሩን ፡ አሁን ፡ ታደክመዋለህ ?
አሉት ። ኢየሱስ ፡ ግን ፡ የተናገሩትን ፡ ቃል ፡
፴፮ አድምጦ ፡ ለምኵራቡ ፡ አለቃ ፡ — እመን ፡ ብቻ ፡
እንጂ ፡ አትፍራ ፡ አለው ። ከጴጥሮስም ፡ ከያዕቆ
፴፯ ብም ፡ ከያዕቆብም ፡ ወንድም ፡ ከዮሐንስ ፡ በቀር ፡
ማንም ፡ እንዲከተለው ፡ አልፈቀደም ። ወደ ፡
፴፰ ምኵራቡ ፡ አለቃ ፡ ቤትም ፡ መጥቶ ፡ ሰዎች ፡
ሲንጫጩና ፡ ሲያለቅሱ ፡ ዋይታም ፡ ሲያበዙ ፡
፴፱ አየ ፤ ገብቶም ፡ — ስለ ፡ ምን ፡ ትንጫጫላችሁ ፡
ታለቅሳላችሁም ? ብላቴናይቱ ፡ ተኝታለች ፡
እንጂ ፡ አልሞተችም ፡ አላቸው ። በጣምም ፡
፵ ሳቁበት ። እርሱ ፡ ግን ፡ ሁሉን ፡ አስወጥቶ ፡ የብ
ላቴናይቱን ፡ አባትና ፡ እናትም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡
የነበሩትንም ፡ ይዞ ፡ ብላቴናይቱ ፡ ወዳለችበት ፡
ገባ ። የብላቴናይቱንም ፡ እጅ ፡ ይዞ ፡ — ጣሊታ ፡
፵፩ ቁሚ ፡ አላት ፤ ፍችውም ፡ አንቺ ፡ ብላቴና ፡ ተነሽ ፡
አልሻለሁ ፡ ነው ። ብላቴናይቱም ፡ የአሥራ ፡
፵፪ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረችና ፡ ወዲያው ፡ ቆማ ፡
ተመላለሰች ። ወዲያውም ፡ ታላቅ ፡ መገረም ፡
፵፫ ተገረሙ ። ይህንም ፡ ማንም ፡ እንዳያውቅ ፡ አዋ
ጠቆ ። አዘአቸው ፡ — የምትበላውን ፡ ስጡአት ፡
አላቸው ።

ምዕራፍ ፮ ።

ከዚያም ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ገዛ ፡ አገሩ ፡ መጣ ፡ ፩
ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ተከተሉት ። ሰንበትም ፡ ፪
በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በምኵራብ ፡ ያስተምር ፡ ጀመር ፤
ብዙዎችም ፡ ሰምተው ፡ ተገረሙና ፡ — እነዚህን ፡
ነገሮች ፡ ይህ ፡ ከወዴት ፡ አገኛቸው ? ለዚህ ፡ የተ
ሰጠችው ፡ ጥበብ ፡ ምንድር ፡ ናት ? በእጁም ፡

የሚደረጉ ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉ ፡ ተአምራት ፡ ምን
፪ ድር ፡ ናቸው ? ይህስ ፡ ጸራቢው ፡ የማርያም ፡
ልጅ ፡ የያዕቆብም ፡ የዮሳም ፡ የይሁዳም ፡ የስምዖ
ንም ፡ ወንድም ፡ አይደለምን ? እኅቶቹስ ፡ በዚህ ፡
በእኛ ፡ ዘንድ ፡ አይደሉምን ? አሉ ። ይሰናከሉ
፬ በትም ፡ ነበር ። ኢየሱስም ፡ — ነቢይ ፡ ከገዛ ፡ አገ
ሩና ፡ ከገዛ ፡ ዘመዶቹ ፡ ከገዛ ፡ ቤቱም ፡ በቀር ፡
፭ ሳይከበር ፡ አይቀርም ፡ አላቸው ። በዚያም ፡ በጥ
ቂቶች ፡ ድውዮች ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ጭኖ ፡ ከመፈ
ወስ ፡ በቀር ÷ ተአምር ፡ ሊያደርግ ፡ ምንም ፡ አል
፮ ቻለም ። ስለ ፡ አለማመናቸውም ፡ ተደነቀ ።

በመንደሮችም ፡ እያስተማረ ፡ ይዘር ፡ ነበር ።
፯ አሥራ ፡ ሁለቱንም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ጠራ ፡ ሁለት ፡
ሁለቱንም ፡ ይልካቸው ፡ ጀመር ÷ በርኩሳን ፡
፰ መናፍስትም ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጣቸው ÷ ለመ
ንገድም ፡ ከበትር ፡ በቀር ፡ እንጀራም ፡ ቢሆን ፡
ከረጢትም ፡ ቢሆን ፡ መሐለቅም ፡ በመቀነታቸ
፱ ቸው ፡ ቢሆን ፡ እንዳይዙ ፡ አዘዛቸው ። በእግ
ራችሁ ፡ ጫማ ፡ አድርጉ ፡ እንጂ ፡ ሁለት ፡ እጀ
፲ ጠባብ ፡ አትልበሱ ፡ አለ ። በማናቸውም ፡ ስፍራ ፡
ወደ ፡ ቤት ፡ ብትገቡ ፡ ከዚያ ፡ እስክትወጡ ፡
፲፩ ድረስ ፡ በዚያው ፡ ተቀመጡ ። ከማይቀበሏአች
ሁና ፡ ከማይሰሙአችሁ ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ከዚያ ፡
ወጥታችሁ ፡ ምስክር ፡ ይሆንባቸው ፡ ዘንድ ፡ ከእ
ግራችሁ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ትቢያ ፡ አራግፉ ።
እውነት ፡ እላችኋለሁ ÷ ከዚያች ፡ ከተማ ፡ ይልቅ ፡
ለሰዶምና ፡ ለገሞራ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ይቀልላቸ
፲፪ ዋል ፡ አላቸው ። ወጥተውም ፡ ንስሐ ፡ እንዲገቡ ፡
፲፫ ሰበኩ ÷ ብዙ ፡ አጋንንትንም ፡ አወጡ ÷ ብዙ ፡
ድውዮችንም ፡ ዘይት ፡ እየቀቡ ፡ ፈወሱአቸው ።

፲፬ ስሙም ፡ ተገልጦአልና ፡ ንጉሡ ፡ ሄሮድስ ፡
በሰማ ፡ ጊዜ ፡ — መጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ከሙታን ፡
ተነሥቶአል ፡ ስለዚህም ፡ ኃይል ፡ በእርሱ ፡ ይደ
፲፭ ረጋል ፡ አለ ። ሌሎችም ፡ — ኤልያስ ፡ ነው ፡ አሉ ፡
ሌሎችም ፡ — ከነቢያት ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ነቢይ ፡
፲፮ ነው ፡ አሉ ። ሄሮድስ ፡ ግን ፡ ሰምቶ ፡ — እኔ ፡
ራሱን ፡ ያስቈረጥሁት ፡ ዮሐንስ ፡ ይህ ፡ ነው ፤
፲፯ እርሱ ፡ ከሙታን ፡ ተነሥቶአል ፡ አለ ። ሄሮድስ ፡
የወንድሙን ፡ የፊልጶስን ፡ ሚስት ፡ ሄሮድያዳን ፡
አግብቶ ፡ ነበርና ፡ በእርስዋ ፡ ምክንያት ፡ ራሱ ፡
ልከ ፡ ዮሐንስን ፡ አስይዞ ፡ በወኅኒ ፡ አሳስሮት ፡
፲፰ ነበር ። ዮሐንስ ፡ ሄሮድስን ፡ — የወንድምህ ፡
ሚስት ፡ ለአንተ ፡ ልትሆን ፡ አልተፈቀደም ፡
፲፱ ይለው ፡ ነበርና ። ሄሮድያዳ ፡ ግን ፡ ተቃውማው ፡
ልትገድለው ፡ ትፈልግ ፡ ነበር ፡ አልቻለችም ፤
፳ ሄሮድስ ፡ ዮሐንስ ፡ ጻድቅና ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ አውቆ ፡ ይፈራውና ፡ ይጠባበቀው ፡ ነበር ፤
አርስቱንም ፡ ሰምቶ ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ ያመነታ ፡ ነበር ፤
፳፩ በደስታም ፡ ይሰማው ፡ ነበር ። ሄሮድስም ፡ በተወ
ለደበት ፡ ቀን ፡ ለመኳንንቱና ፡ ለሻለቆቹ ፡ ለገሊ
ላም ፡ ሹማምንት ፡ ግብር ፡ በደረገ ፡ ጊዜ ፡ ምቹ ፡

ቀን ፡ ሆነላትና ፡ የሄሮድያዳ ፡ ልጅ ፡ ገብታ ፡ ስትዝ
፳፪ ፍን ፡ ሄሮድስንና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የተቀመጡትን ፡
ደስ ፡ አሰኘቻቸው ። ንጉሡም ፡ ብላቴናይቱን ፡ —
የምትወጂውን ፡ ሁሉ ፡ ለምኚኝ ፡ እሰጥሽማለሁ ፡
፳፫ አላት ፡ የመንግሥቴ ፡ እኩሌታ ፡ ስንኳ ፡ ቢሆን ፡
፳፬ የምትለምኚውን ፡ ሁሉ ፡ እሰጥሻለሁ ፡ ብሎ ፡ ማለ
፳፭ ላት ። ወዋታም ፡ ለእናትዋ ፡ — ምን ፡ ልለምነው ?
አለች ። እርስዋም ፡ — የመጥምቁን ፡ የዮሐን
ስን ፡ ራስ ፡ አለች ። ወዲያውም ፡ ፈጥና ፡ ወደ ፡
፳፮ ንጉሡ ፡ ገብታ ፡ — የመጥምቁን ፡ የዮሐንስን ፡
ራስ ፡ በወጭት ፡ አሁን ፡ ልትሰጠኝ ፡ እወዳለሁ ፡
ብላ ፡ ለመነችው ። ንጉሡም ፡ እጅግ ፡ አዘነ ፡
፳፯ ስለ ፡ መሐላው ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ተቀመ
ጡት ፡ ሊኀሣት ፡ አልወደደም ። ወዲያውም ፡
፳፰ ንጉሡ ፡ ባለ ፡ ወግ ፡ ልከ ፡ ራሱን ፡ እንዲያመጣ ፡
አዘዘው ። ሄዶም ፡ በወኅኒ ፡ ራሱን ፡ ቈረጠ ÷
፳፱ ራሱንም ፡ በወጭት ፡ አምጥቶ ፡ ለብላቴናይቱ ፡
ሰጣት ÷ ብላቴናይቱም ፡ ለእናትዋ ፡ ሰጠች ።
፴ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ሰምተው ፡ መጡ ፡ በድኑ ፡
፴፩ ንም ፡ ወስደው ፡ ቀበሩት ።

ሐዋርያትም ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ ተሰብስበው ፡ ፴
ያደረጉትንና ፡ ያስተማሩትን ፡ ሁሉ ፡ ነገሩት ።
፴፪ እናንት ፡ ራሳችሁ ፡ ብቻችሁን ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡
በዳ ፡ ኑና ፡ ዋቂት ፡ ዕረፉ ፡ አላቸው ፤ የሚመጡና ፡
የሚሄዱ ፡ ብዙዎች ፡ ነበሩና ÷ ለመብላት ፡ እንኳ ፡
፴፫ ጊዜ ፡ አጡ ። በታንኳም ፡ ብቻቸውን ፡ ወደ ፡
፴፬ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሄዱ ። ሰዎችም ፡ ሲሄዱ ፡ አዩአ
ቸው ፡ ብዙዎችም ፡ አወቁአቸውና ፡ ከከተሞች ፡
ሁሉ ፡ በእግር ፡ እየሮጡ ፡ ወዳያ ፡ ቀደሙአቸው ፡
ወደ ፡ እርሱም ፡ ተሰበሰቡ ። ኢየሱስም ፡ ወጥቶ ፡
፴፭ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ አየና ፡ አረኛ ፡ እንደሌላቸው ፡
በጎች ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ አዘነላቸው ÷ ብዙም ፡ ነገር ፡
ያስተምራቸው ፡ ጀምር ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ብዙ ፡
፴፮ ሰዓት ፡ ከለፈ ፡ በኋላ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ወደ ፡
እርሱ ፡ ቀርበው ፡ — በታው ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ነው ፡
አሁንም ፡ መሸቶአል ፤ የሚበሉት ፡ የላቸውምና ፡
፴፯ በዙሪያ ፡ ወዳሉ ፡ ገጠሮችና ፡ መንደሮች ፡ ሄደው ፡
እንጀራ ፡ ለራሳቸው ፡ እንዲገዙ ፡ አሰናብታቸው ፡
አሉት ። እርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፡ — እናንተ ፡ የሚበ
፴፰ ሉትን ፡ ስጡአቸው ፡ አላቸው ። ሄዶ ፡ እንጀራ ፡
በሁለት ፡ መቶ ፡ ዲናር ፡ እንግዛላቸውን ? እንዲ
በሉም ፡ እንስጣቸውን ? አሉት ። እርሱም ፡ —
፴፱ ስንት ፡ እንጀራ ፡ አላችሁ ? ሂዱና ፡ እዩ ፡ አላ
ቸው ። በወቁም ፡ ጊዜ ፡ — አምስት ÷ ሁለትም ፡
፵ ዓሣ ፡ አሉት ። ሁሉንም ፡ በየክፍሉ ፡ በለመለመ ፡
፵፩ ሣር ፡ ላይ ፡ እንዲያስቀምጡአቸው ፡ አዘዘቸው ።
፵፪ መቶ ፡ መቶውና ፡ አምሳ ፡ አምሳው ፡ እየሆኑ ፡
፵፫ በተራ ፡ በተራ ፡ ተቀመጡ ። አምስቱንም ፡ እን
፵፬ ጀራ ፡ ሁሉቱንም ፡ ዓሣ ፡ ይዘ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አሸ
ቅቦ ፡ አየና ፡ ባረከ ÷ እንጀራውንም ፡ ቈርሶ ፡ እን
ዲያቀርቡላቸው ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሰጠ ÷

፵፪፡ ሁለቱን ፡ ዓሣ ፡ ደግሞ ፡ ለሁሉ ፡ ከፈለ ። ሁሉም ፡
፵፫፡ በልተው ፡ ጠገቡ ፡ ከቍርስራሹም ፡ አሥራ ፡
ሁለት ፡ መሶብ ፡ የሞላ ፡ አነሡ ፡ ከዓሣውም ፡
፵፬፡ ደግሞ ። እንጀራውንም ፡ የበሉት ፡ ወንዶቹ ፡
አምስት ፡ ሺህ ፡ ነበሩ ።
፵፭፡ ወዲያውም ፡ ሕዝቡን ፡ ሲያሰናብት ፡ ሳለ ፡ ደቀ ፡
መዛሙርቱ ፡ በታንኳ ፡ ገብተው ፡ ወደ ፡ ማዶ ፡
ወደ ፡ ቤተ ፡ ሳይዳ ፡ እንዲቀድሙት ፡ግድ ፡ አላ
፵፮፡ ቸው ። ካሰናበታቸውም ፡ በኋላ ፡ ሊጸልይ ፡ ወደ ፡
፵፯፡ ተራራ ፡ ወጣ ። በመሸም ፡ ጊዜ ፡ ታንኳይቱ ፡ በባ
ሕር ፡ መካከል ፡ ሳለች ፡ እርሱ ፡ ብቻውን ፡ በም
፵፰፡ ድር ፡ ላይ ፡ ነበረ ። ነፋስ ፡ ከወደ ፡ ፊታቸው ፡ ነበ
ረና ፡ እየቀዘፉ ፡ ሲጨነቁ ፡ አይቶ ፤ ከሌሊቱ ፡ በአ
ራተኛው ፡ ክፍል ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ እየሄደ ፡ ወደ ፡
እነርሱ ፡ መጣ ፤ ሊያልፋቸውም ፡ ይወድ ፡ ነበር ።
፵፱፡ እነርሱ ፡ ግን ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ሲሄድ ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡
፶፡ ምትሀት ፡ መሰላቸውና ፡ ጮኹ ፤ ሁሉ ፡ አይተ
ውታልና ፤ ታወኩም ። ወዲያውም ፡ ተናገራቸ
ውና ፡— አይዞአችሁ ፤ እኔ ፡ ነኝ ፤ አትፍሩ ፡ አላ
፶፩፡ ቸው ። ወደ ፡ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ታንኳይቱ ፡ ገባ ፤
ነፋሱም ፡ ተወ ፤ በራሳቸውም ፡ ያለ ፡ መጠን ፡
፶፪፡ እጅግ ፡ ተገረሙ ፤ ስለ ፡ እንጀራው ፡ አላስተዋሉ
ምና ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ልባቸው ፡ ደንዝዞ ፡ ነበር ።
፶፫፡ ተሻግረውም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ ጌንሴሬጥ ፡
፶፬፡ ደረሱ ፡ ታንኳይቱንም ፡ አስጠጉ ። ከታንኳይ
፶፭፡ ቱም ፡ ሲወጡ ፡ ወዲያው ፡ አውቀውት ፡ በዚያች ፡
አገር ፡ ሁሉ ፡ ዞሪያ ፡ ሮጡና ፡ እርሱ ፡ እንዳለ ፡
ወደ ፡ ሰሙበት ፡ ስፍራ ፡ ሕመምተኞችን ፡ በአ
፶፮፡ ልጋ ፡ ላይ ፡ ያመጡ ፡ ጀመር ። በገባበትም ፡ ስፍራ ፡
ሁሉ ፤ መንደርም ፡ ከተማም ፡ ገጠርም ፡ ቢሆን ፤
በገበያ ፡ ድውዮችን ፡ ያኖሩ ፡ ነበር ፡ የልብሱንም ፡
ጫፍ ፡ እንኳ ፡ ሊዳስሱ ፡ ይለምኑት ፡ ነበር ፤ የዳ
ሰሱትም ፡ ሁሉ ፡ ዳኑ ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

፩፡ ፈሪሳውያንና ፡ ከጻፎች ፡ ወገን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡
፪፡ የመጡትም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ተሰበሰቡ ። ከደቀ ፡
መዛሙርቱም ፡ አንዳንድ ፡ በርኩስ ፡ ማለት ፡ ባል
፫፡ ታጠበ ፡ እጅ ፡ እንጀራ ፡ ሲበሉ ፡ አዩ ። ፈሪሳውያ
ንና ፡ አይሁድም ፡ ሁሉ ፡ የሽማግሌዎችን ፡ ወግ ፡
ሲጠብቁ ፡ እጃቸውን ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ ሳይ
፬፡ ታጠቡ ፡ አይበሉምና ፤ ከገበያም ፡ ተመልሰው ፡
ካልታጠቡ ፡ አይበሉም ፤ ጽዋንም ፡ ማድጋንም ፡
የናስ ፡ ዕቃንም ፡ አልጋንም ፡ እንደ ፡ ማጠብ ፡
ሌላ ፡ ነገር ፡ ሊጠብቁት ፡ የተቀበሉት ፡ ብዙ ፡
፭፡ አለ ። ፈሪሳውያንም ፡ ጻፎችም ፡— ደቀ ፡ መዛሙ
ርትህ ፡ እንደ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ወግ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አይ
ሄዱም ? ነገር ፡ ግን ፡ እጃቸውን ፡ ሳይታጠቡ ፡
፮፡ እንጀራ ፡ ይበላሉ ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ። እርሱ ፡
ግን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡— ኢሳይያስ ፡ ስለ ፡ እና
ንተ ፡ ስለ ፡ ግብዞች ፡—
ይህ ፡ ሕዝብ ፡ በከንፈሩ ፡ ያከብረኛል ፡ ልቡ ፡
ግን ፡ ከእኔ ፡ በጣም ፡ የራቀ ፡ ነው ፤ የሰውም ፡ ፯፡
ሥርዓት ፡ የሆነ ፡ ትምህርት ፡ እያስተማሩ ፡
በከንቱ ፡ ያመልኩኛል ፡
ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ በእውነት ፡ ትንቢት ፡
ተናገረ ። የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ትታችሁ ፡ ፰፡
ጽዋን ፡ ማድጋንም ፡ እንደ ፡ ማጠብ ፡ የሰውን ፡
ወግ ፡ ትጠብቃላችሁ ፤ ይህንም ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡
ሌላ ፡ ነገር ፡ ታደርጋላችሁ ።
እንዲህም ፡ አላቸው ፡— ወጋችሁን ፡ ትጠብቁ ፡ ፱፡
ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ እጅግ ፡ ንቃ
ችኋል ። ሙሴ ፡— አባትህንና ፡ እናትህን ፡ አክ ፲፡
ብር ፤ ደግሞ ፡— አባቱን ፡ ወይም ፡ እናቱን ፡ የሰ
ደበ ፡ ፈጽሞ ፡ ይሙት ፡ ብሎአልና ። እናንተ ፡ ፲፩፡
ግን ፡ ትላላችሁ ፡— ሰው ፡ አባቱን ፡ ወይም ፡ እና
ቱን ፡ — ከእኔ ፡ የምትጠቀምበት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
ቍርባን ፡ ማለት ፡ መባ ፡ ነው ፡ ቢል ፤ ለአባቱና ፡ ፲፪፡
ለእናቱ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ሊያደርግ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡
አትፈቅዱለትም ፤ ባስተላለፋችሁትም ፡ ወግ ፡ ፲፫፡
የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ትሽራላችሁ ፡ እንደ
ዚሁም ፡ ይህን ፡ የሚመስል ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ታደ
ርጋላችሁ ።
ደግሞም ፡ ሕዝቡን ፡ ጠርቶ ፡— ሁላችሁ ፡ እኔን ፡ ፲፬፡
ስሙ ፡ አስተውሉም ። ከሰው ፡ የሚወጡት ፡ ፲፭፡
ሰውን ፡ የሚያረክሱ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ከሰው ፡
ውጭ ፡ የሚገባውስ ፡ ሊያረክሰው ፡ የሚችል ፡
ምንም ፡ የለም ። የሚሰማ ፡ ጆሮ ፡ ያለው ፡ ቢኖር ፡ ፲፮፡
ይስማ ፡ አላቸው ። ከሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ፲፯፡
ከገባ ፡ በኋላ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ምሳሌውን ፡
ጠየቁት ። እርሱም ፡—እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፲፰፡
ዚህ ፡ የማታስተውሉ ፡ ናችሁን ? ከውጭ ፡ ወደ ፡
ሰው ፡ የሚገባ ፡ ሊያረክሰው ፡ ምንም ፡ እንዳይ
ችል ፡ አትመለከቱምን ? ወደ ፡ ሆድ ፡ ገብቶ ፡ ፲፱፡
ወደ ፡ እዳሪ ፡ ይወጣል ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ልብ ፡ አይ
ገባምና ፤ መብልን ፡ ሁሉ ፡ እያጠራ ፡ አላቸው ።
እርሱም ፡ አለ ፡— ከሰው ፡ የሚወጣው ፡ ሰውን ፡ ፳፡
የሚያረክስ ፡ ያ ፡ ነው ። ከውስጥ ፡ ከሰው ፡ ልብ ፡ ፳፩፡
የሚወጣ ፡ ክፉ ፡ አሳብ ፤ ዝሙት ፤ መስረቅ ፤ ፳፪፡
መግደል ፤ ምንዝርነት ፤ መጐምጀት ፤ ክፋት ፤
ተንኰል ፤ መዳራት ፤ ምቀኝነት ፤ ስድብ ፤ ትዕ
ቢት ፤ ስንፍና ፡ ናቸውና ፤ ይህ ፡ ክፉው ፡ ሁሉ ፡ ፳፫፡
ከውስጥ ፡ ይወጣል ፡ ሰውንም ፡ ያረክሰዋል ።
ከዚያም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ጢሮስና ፡ ወደ ፡ ፳፬፡
ሲዶና ፡ አገር ፡ ሄደ ። ወደ ፡ ቤትም ፡ ገብቶ ፡
ማንም ፡ እንዳያውቅበት ፡ ወደደ ፡ ሊሰወርም ፡
አልተቻለውም ፤ ወዲያው ፡ ግን ፡ ታናሺቱ ፡ ፳፭፡
ልጅዋ ፡ ርኩስ ፡ መንፈስ ፡ ያደረባት ፡ አንዲት ፡
ሴት ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ሰምታ ፡ መጣችና ፡ በእግሩ ፡
ላይ ፡ ተደፋች ፤ ሴቲቱም ፡ግሪክ ፤ ትውልድዋም ፡ ፳፮፡
ሲሮፊኒቃዊት ፡ ነበረች ፤ ከልጅዋ ፡ ጋኔን ፡ ያወ
ጣላት ፡ ዘንድ ፡ ለመነችው ። ኢየሱስ ፡ ግን ፡— ፳፯፡
ልጆቹ ፡ በፊት ፡ ይጠግቡ ፡ ዘንድ ፡ ተዪ ፤ የልጆ
ቹን ፡ እንጀራ ፡ ይዞ ፡ ለቡችሎች ፡ መጣል ፡ አይ

፳፰፡ ገባምና ፡ አላት ። እርስዋም ፡ መልሳ ፡— አዎን ፤
ጌታ ፡ ሆይ ፤ ቡችሎች ፡ እንኳ ፡ ከማዕድ ፡ በታች ፡
ሆነው ፡ የልጆችን ፡ ፍርፋሪ ፡ ይበላሉ ፡ አለችው ።
፳፱፡ እርሱም ፡— ስለዚህ ፡ ቃል ፡ ሂጂ ፤ ጋኔኑ ፡ ከል
፴፡ ጅሽ ፡ ወጥቶአል ፡ አላት ። ወደ ፡ ቤትዋም ፡ ሄዳ ፡
ጋኔኑ ፡ ወጥቶ ፡ ልጅዋም ፡ በአልጋ ፡ ላይ ፡ ተኝታ ፡
አገኘች ።
፴፩፡ ደግሞም ፡ ከጢሮስ ፡ አገር ፡ ወጥቶ ፡ በሲዶና ፡
አልፎ ፡ አሥር ፡ ከተማ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ መካ
፴፪፡ ከል ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ባሕር ፡ መጣ ። ደንቆሮና ፡
ኰልታፋም ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አመጡ ፤
፴፫፡ እጁንም ፡ ይጭንበት ፡ ዘንድ ፡ ለመኑት ። ከሕ
ዝቡም ፡ ለይቶ ፡ ለብቻው ፡ ወሰደው ፤ ጣቶቹ
ንም ፡ በጆሮቹ ፡ አገባ ፡ እንትፍም ፡ ብሎ ፡ መላ
፴፬፡ ሱን ፡ ዳሰሰ ፤ ወደ ፡ ሰማይም ፡ አሻቅቦ ፡ አይቶ ፡
ቃተተና ፡— ኤፍታህ ፡ አለው ፤ እርሱም ፡ ተከ
፴፭፡ ፈት ፡ ማለት ፡ ነው ። ወዲያውም ፡ ጆሮቹ ፡ ተከ
ፈቱ ፡ የመላሱም ፡ እስራት ፡ ተፈታ ፡ አጥርቶም ፡
፴፮፡ ተናገረ ። ለማንም ፡ አትንገሩ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ፤
እነርሱ ፡ ግን ፡ ባዘዛቸው ፡ መጠን ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡
፴፯፡ አወሩት ። ያለ ፡ መጠንም ፡ ተገረሙና ፡— ሁሉን ፡
ደኅና ፡ አድርጎአል ፤ ደንቆሮችም ፡ እንዲሰሙ ፡
ዲዳዎችም ፡ እንዲናገሩ ፡ ያደርጋል ፡ አሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፰ ።

፩፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ነበረ ፡
የሚበሉትም ፡ ስለሌላቸው ፡ ደቀ ፡ መዛሙር
፪፡ ቱን ፡ ጠርቶ ፡— ሕዝቡ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ እስከሁን ፡
ሦስት ፡ ቀን ፡ ውለዋልና ፡ የሚበሉት ፡ ስለሌ
፫፡ ላቸው ፡ አዝንላቸዋለሁ ፤ ከእነርሱም ፡ አንዳን
ዶቹ ፡ ከሩቅ ፡ መጥተዋልና ፡ ጦማቸውን ፡ ወደ ፡
ቤታቸው ፡ ባሰናብታቸው ፡ በመንገድ ፡ ይዝላሉ ፡
፬፡ አላቸው ። ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡— በዚህ ፡ በም
ድረ ፡ በዳ ፡ እንጀራ ፡ ከየት ፡ አግኝቶ ፡ ሰው ፡
እነዚህን ፡ ማጥገብ ፡ ይችላል ? ብለው ፡ መለሱ
፭፡ ለት ። እርሱም ፡—ስንት ፡ እንጀራ ፡ አላችሁ ?
ብሎ ፡ ጠየቃቸው ፤ እነርሱም ፡— ሰባት ፡ አሉት ።
፮፡ ሕዝቡም ፡ በምድር ፡ እንዲቀመጡ ፡ አዘዘ ።
ሰባቱንም ፡ እንጀራ ፡ ይዞ ፡ አመሰገነ ፤ ቈርሶም ፡
እንዲያቀርቡላቸው ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሰጠ ፤
፯፡ ለሕዝቡም ፡ አቀረቡ ። ጥቂትም ፡ ትንሽ ፡ ዓሣ ፡
ነበራቸው ፤ ባረከውም ፡ ይህንም ፡ ደግሞ ፡ እን
፰፡ ዲያቀርቡላቸው ፡ አዘዘ ። በሉም ፡ ጠገቡም ፤
የተረፈውንም ፡ ቍርስራሽ ፡ ሰባት ፡ ቅርጫት ፡
፱፡ አነሡ ። የበሉትም ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ ያህል ፡ ነበሩ ።
፲፡ አሰናበታቸውም ። ወዲያውም ፡ ከደቀ ፡ መዛ
ሙርቱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ታንኳይቱ ፡ ገብቶ ፡ ወደ ፡
ዳልማኑታ ፡ አገር ፡ መጣ ።
፲፩፡ ፈሪሳውያንም ፡ ወጡና ፡ ሊፈትኑት ፡ ከሰማይ ፡
ምልክት ፡ ከእርሱ ፡ ፈልገው ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡
ይከራከሩ ፡ ጀመር ። በመንፈሱም ፡ እጅግ ፡ ቃተ ፲፪፡
ተና ፡— ይህ ፡ ትውልድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ምልክት ፡
ይፈልጋል ? እውነት ፡ እላችኋለሁ ፤ ለዚህ ፡
ትውልድ ፡ ምልክት ፡ አይሰጠውም ፡ አለ ። ትቶ ፲፫፡
አቸውም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ታንኳይቱ ፡ ገብቶ ፡
ወደ ፡ ማዶ ፡ ሄደ ።
እንጀራ ፡ መያዝም ፡ ረሱ ፤ ለእነርሱም ፡ ከአ ፲፬፡
ንድ ፡ እንጀራ ፡ በቀር ፡ በታንኳይቱ ፡ አልነበረ
ቸውም ። እርሱም ፡— ተጠንቀቁ ፤ ከፈሪሳው ፲፭፡
ያንና ፡ ከሄሮድስ ፡ እርሾ ፡ ተጠበቁ ፡ ብሎ ፡ አዘ
ዛቸው ። እርስ ፡ በርሳቸውም ፡— እንጀራ ፡ ስለ ፲፮፡
ሌለን ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ ተነጋገሩ ። ኢየሱ ፲፯፡
ስም ፡ አውቆ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡— እንጀራ ፡
ስለሌላችሁ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትነጋገራላችሁ ? ገና ፡
አልተመለከታችሁምን ? አላስተዋላችሁምን ?
ልባችሁስ ፡ ደንዝዞአልን ? ዓይን ፡ ሳላችሁ ፡ ፲፰፡
አታዩምን ? ጆሮስ ፡ ሳላችሁ ፡ አትሰሙምን ?
ትዝስ ፡ አይላችሁምን ? አምስቱን ፡ እንጀራ ፡ ፲፱፡
ለአምስት ፡ ሺህ ፡ በቈረስሁ ፡ ጊዜ ፤ ቍርስራሹ ፡
የሞላ ፡ ስንት ፡ መሶብ ፡ አነሣችሁ ? እነርሱም ፡—
አሥራ ፡ ሁለት ፡ አሉት ። ሰባቱን ፡ እንጀራስ ፡ ፳፡
ለአራት ፡ ሺህ ፡ በቈረስሁ ፡ ጊዜ ፤ ቍርስራሹ ፡
የሞላ ፡ ስንት ፡ ቅርጫት ፡ አነሣችሁ ? እነር
ሱም ፡— ሰባት ፡ አሉት ። ገና ፡ አላስተዋላችሁ ፳፩፡
ምን ? አላቸው ።
ወደ ፡ ቤተ ፡ ሳይዳም ፡ መጡ ። ዕውርም ፡ ፳፪፡
አመጡለት ፤ እንዲዳስሰውም ፡ ለመኑት ። ዕው ፳፫፡
ሩንም ፡ እጁን ፡ ይዞ ፡ ከመንደር ፡ ውጭ ፡ አወ
ጣው ፤ በዓይኑም ፡ ተፍቶበት ፡ እጁንም ፡ ጭኖ
በት ፡— አንዳች ፡ ታያለህን ? ብሎ ፡ ጠየቀው ።
አሻቅቦም ፡— ሰዎች ፡ እንደ ፡ ዛፍ ፡ ሲመላለሱ ፡ ፳፬፡
አያለሁ ፡ አለ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ እጁን ፡ ፳፭፡
በዓይኑ ፡ ላይ ፡ ጫነበት ፤ አጥርቶም ፡ አየ ፡ ዳነም ፡
ከሩቅም ፡ ሳይቀር ፡ ሁሉን ፡ ተመለከተ ። ወደ ፡ ፳፮፡
ቤቱም ፡ ሰደደውና ፡— ወደ ፡ መንደሩ ፡ አትግባ ፡
በመንደሩም ፡ ለማንም ፡ አንዳች ፡ አትናገር ፡
አለው ።
ኢየሱስና ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ በፊልጶስ ፡ ፳፯፡
ቂሣርያ ፡ ወዳሉ ፡ መንደሮች ፡ ወጡ ፤ በመንገ
ድም ፡— ሰዎች ፡ እኔ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡
ይላሉ ? ብሎ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ጠየቃቸው ።
እነርሱም ፡— መጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፤ ሌሎችም ፡ ፳፰፡
ኤልያስ ፤ ሌሎችም ፡ ከነቢያት ፡ አንዱ ፡ ብለው ፡
ነገሩት ። እናንተስ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ፳፱፡
ትላላችሁ ? ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። ጴጥሮስም ፡—
አንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ነህ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ስለ ፡ ፴፡
እርሱም ፡ ለማንም ፡ እንዳይናገሩ ፡ አዘዛቸው ።
የሰው ፡ ልጅ ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ሊቀበል ፤ ከሽ ፴፩፡

ማግሥትም ፡ ከከዘናት ፡ አለቆችም ፡ ከጻፎችም ፡ ሊጣል ፡ ሊገደልም ፡ ከሥስት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ሊነሣ ፡ እንዲገባው ፡ ያስተምራቸው ፡ ጀመር ፤ ፴፪ ቃሉንም ፡ ገልጦ ፡ ይናገር ፡ ነበር ። ጴጥሮስም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ወስዶ ፡ ይገሥጸው ፡ ጀመር ። ፴፫ እርሱ ፡ ግን ፡ ዘወር ፡ አለ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱንም ፡ አይቶ ፡ ጴጥሮስን ፡ ገሠጸውና ፡— ወደ ፡ ኋላዬ ፡ ሂድ ፡ አንተ ፡ ሰይጣን ፡ የሰውን ፡ እንጂ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ አታስብምና ፡ አለው ።

፴፬ ሕዝቡንም ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋር ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡— በኋላዬ ፡ ሊመጣ ፡ የሚወድ ፡ ቢኖር ፡ ራሱን ፡ ይካድ ፡ መስቀሉንም ፡ ተሸክሞ ፡ ይከተለኝ ። ፴፭ ነፍሱን ፡ ሊያድን ፡ የሚወድ ፡ ሁሉ ፡ ያጠፋታልና ፡ ስለ ፡ እኔና ፡ ስለ ፡ ወንጌል ፡ ነፍሱን ፡ የሚያጠፋ ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ያድናታል ። ፴፮ ሰው ፡ ዓለምን ፡ ሁሉ ፡ ቢያተርፍ ፡ ነፍሱን ፡ ቢያጐድል ፡ ምን ፡ ይጠቅመዋል ? ፴፯ ሰውስ ፡ ስለ ፡ ነፍሱ ፡ ቤዛ ፡ ምን ፡ ይሰጣል ? ፴፰ በዚህም ፡ በዘማዊና ፡ በኃጢአተኛ ፡ ትውልድ ፡ መካከል ፡ በእኔና ፡ በቃሌ ፡ የሚያፍር ፡ ሁሉ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ደግሞ ፡ በአባቱ ፡ ክብር ፡ ከቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ ጋር ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በእርሱ ፡ ያፍርበታል ።

ምዕራፍ ፡ ፱ ።

፩ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ በዚህ ፡ ከቆሙት ፡ ሰዎች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ በኃይል ፡ ስተመጣ ፡ እስኪያዩ ፡ ድረስ ፡ ሞትን ፡ የማይቀምሱ ፡ አንዳንዶች ፡ አሉ ፡ አላቸው ።

፪ ከስድስት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ ጴጥሮስንና ፡ ያዕቆብን ፡ ዮሐንስንም ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ረጅም ፡ ተራራ ፡ ብቻቸውን ፡ አወጣቸው ። በፊታቸውም ፡ ተለወጠ ፡ ልብሱም ፡ እንጸባረቀ ፤ አጣቢም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደዚያ ፡ ሊያነጣው ፡ እስከማይችል ፡ በጣም ፡ ነጭ ፡ ሆነ ። ፬ ኤልያስና ፡ ሙሴም ፡ ታዩአቸው ፡ ከኢየሱስም ፡ ጋር ፡ ይነጋገሩ ፡ ነበር ። ፭ ጴጥሮስም ፡ መልሶ ፡ ኢየሱስን ፡— መምህር ፡ ሆይ ፡ በዚህ ፡ መሆን ፡ ለእኛ ፡ መልካም ፡ ነውና ፡ አንድ ፡ ለአንተ ፡ አንድም ፡ ለሙሴ ፡ አንድም ፡ ለኤልያስ ፡ ሦስት ፡ ዳሶች ፡ እንሥራ ፡ አለው ። እጅግ ፡ ስለ ፡ ፈሩ ፡ የሚለውን ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። ፮ ደመናም ፡ መጥቶ ፡ ጋረዳቸው ፡ ከደመናውም ፡— የምወደው ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እርሱን ፡ ስሙት ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ መጣ ። ፰ ድንገትም ፡ ዘረጋው ፡ ሲመለከቱ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ከኢየሱስ ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ማንንም ፡ አላዩም ።

፱ ከተራራውም ፡ ሲወርዱ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ከሙታን ፡ እስኪነሣ ፡ ድረስ ፡ ያዩትን ፡ ለማንም ፡ እንዳይነግሩ ፡ አዘዛቸው ። ፲ ቃሉንም ፡ ይዘው ፡— ከሙታን ፡ መነሣት ፡ ምንድር ፡ ነው ? እያሉ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተጠያየቁ ። ፲፩ እነርሱም ፡— ኤልያስ ፡ አስቀድሞ ፡ ሊመጣ ፡ እንዲገባው ፡ ጻፎች ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይላሉ ? ብለው ፡ ጠየቁት ። ፲፪ እርሱም ፡ መልሶ ፡— ኤልያስማ ፡ አስቀድሞ ፡ ይመጣል ፡ ሁሉንም ፡ ያቀናናል ፤ ስለ ፡ ሰው ፡ ልጅም ፡ እንዴት ፡ ተብሎ ፡ ተጽፎአል ? ብዙ ፡ መከራ ፡ እንዲቀበል ፡ እንዲናቅም ። ፲፫ ነገር ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ፡ ኤልያስ ፡ ደግሞ ፡ መጥቶአል ፡ ስለ ፡ እርሱም ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ የወደዱትን ፡ ሁሉ ፡ አደረጉበት ፡ አላቸው ።

፲፬ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ሲከበቡአቸው ፡ ጻፎችም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ሲከራከሩ ፡ አየ ። ፲፭ ወዲያውም ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ደነገጡ ፡ ወደ ፡ እርሱም ፡ ሮጠው ፡ እጅ ፡ ነሡት ። ፲፮ ጻፎችንም ፡— ስለ ፡ ምን ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ትከራከራላችሁ ? ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። ፲፯ ከሕዝቡ ፡ አንዱ ፡ መልሶ ፡— መምህር ፡ ሆይ ፡ ዲዳ ፡ መንፈስ ፡ ያደረበትን ፡ ልጄን ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ አምጥቼአለሁ ፤ ፲፰ በያዘውም ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ይጥለዋል ፡ አረፋም ፡ ይደፍቃል ፡ ጥርሱንም ፡ ያፋጫል ፡ ይደርቃልም ፡ እንዲያወጡለትም ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርትህ ፡ ነገርኋቸው ፡ አልቻሉምም ፡ አለው ። ፲፱ እርሱም ፡ መልሶ ፡— የማታምን ፡ ትውልድ ፡ ሆይ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ እኖራለሁ ? እስከ ፡ መቼስ ፡ እታገሣችኋለሁ ? ወደ ፡ እኔ ፡ አምጡት ፡ አላቸው ። ፳ ወደ ፡ እርሱም ፡ አመጡት ። እርሱንም ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ መንፈስ ፡ ወዲያው ፡ እንፈራገጠው ፡ ወደ ፡ ምድርም ፡ ወድቆ ፡ አረፋ ፡ እየደፈቀ ፡ ተንፈራፈረ ። ፳፩ አባቱንም ፡— ይህ ፡ ከያዘው ፡ ስንት ፡ ዘመን ፡ ነው ? ብሎ ፡ ጠየቀው ። እርሱም ፡— ከሕፃንነቱ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ፤ ፳፪ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ሊያጠፋው ፡ ወደ ፡ እሳትም ፡ ወደ ፡ ውኃም ፡ ጣለው ፡ ቢቻልህ ፡ ግን ፡ እዘንልን ፡ እርዳንም ፡ አለው ። ፳፫ ኢየሱስም ፡— ቢቻልህ ፡ ትላለህ ፤ ለሚያምን ፡ ሁሉ ፡ ይቻላል ፡ አለው ። ፳፬ ወዲያውም ፡ የብላቴናው ፡ አባት ፡ ጮኾ ፡— አምናለሁ ፡ ለማመኔን ፡ እርዳው ፡ አለ ። ፳፭ ኢየሱስም ፡ ሕዝቡ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሲራወጥ ፡ አይቶ ፡ ርኩሱን ፡ መንፈስ ፡ ገሠጸና ፡— አንተ ፡ ዲዳ ፡ ደንቆሮም ፡ መንፈስ ፡ እኔ ፡ አዝሃለሁ ፡ ከእርሱ ፡ ውጣ ፡ እንግዲህም ፡ አትግባበት ፡ አለው ። ጮኾም ፡ እጅግም ፡ አንፈራግጠት ፡ ወጣ ፤ ብዙዎችም ፡— ሞተ ፡ እስኪሉ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ሙት ፡ ሆነ ። ፳፮ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ እጁን ፡ ይዞ ፡ አስነሣው ፡ ቆመም ። ፳፯ ወደ ፡ ቤትም ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡— እኛ ፡ ልናወጣው ፡ ያልቻልን ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ? ብለው ፡ ብቻውን ፡ ጠየቁት ። ፳፰ ይህ ፡ ወገን ፡ በጸሎትና ፡ በጦም ፡ ካልሆነ ፡ በምንም ፡ ሊወጣ ፡ አይችልም ፡ አላቸው ።

፴፱፡፳፪ ከዚያም ፡ ወጥተው ፡ በገሊላ ፡ በኩል ፡ አለፉ ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱንም ፡ ያስተምር ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ማንም ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ አልወደደም ፤ ፴፩ እነርሱም ፡— የሰው ፡ ልጅ ፡ በሰዎች ፡ እጅ ፡ አልፎ ፡ ይሰጣል ፡ ይገድሉትማል ፡ ተገድሎም ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ይነሣል ፡ ይላቸው ፡ ነበር ። ፴፪ እነርሱም ፡ ነገሩን ፡ አላስተዋሉም ፡ እንዳይጠይቁትም ፡ ፈሩ ።

፴፫ ወደ ፡ ቅፍርናሆምም ፡ መጣ ። በቤትም ፡ ሆኖ ፡— በመንገድ ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ምን ፡ ተነጋገራችሁ ? ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። ፴፬ እነርሱ ፡ ግን ፡ በመንገድ ፡— ከሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ማን ፡ ይሆን ? ተባብለው ፡ ነበርና ፡ ዝም ፡ አሉ ። ፴፭ ተቀምጦም ፡ አሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ጠርቶ ፡— ሰው ፡ ፊተኛ ፡ ሊሆን ፡ ቢወድ ፡ ከሁሉ ፡ በኋላ ፡ የሁሉም ፡ አገልጋይ ፡ ይሁን ፡ አላቸው ። ፴፮ ሕፃንም ፡ ይዞ ፡ በመካከላቸው ፡ አቆመው ፡ አቅፎም ፡— ፴፯ እንደዚህ ፡ ካሉ ፡ ሕፃናት ፡ አንዱን ፡ በስሜ ፡ የሚቀበል ፡ ሁሉ ፡ እኔን ፡ ይቀበላል ፤ የሚቀበለኝም ፡ ሁሉ ፡ የላከኝን ፡ እንጂ ፡ እኔን ፡ አይቀበልም ፡ አላቸው ።

፴፰ ዮሐንስ ፡ መልሶ ፡— መምህር ፡ ሆይ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በስምህ ፡ አጋንንትን ፡ ሲያወጣ ፡ አየነው ፡ ስለማይከተለንም ፡ ከለከልነው ፡ አለው ። ፴፱ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ አለ ፡— በስሜ ፡ ተአምር ፡ ሠርቶ ፡ በቶሎ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ መናገር ፡ የሚችል ፡ ማንም ፡ የለምና ፡ አትከልክሉት ፤ የማይቃወመን ፡ እርሱ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ነውና ። ፵ የከርስቶስ ፡ ስለ ፡ ሆናችሁ ፡ በስሜ ፡ ጽዋ ፡ ውኃ ፡ የሚያጠጣችሁ ፡ ሁሉ ፡ ዋጋው ፡ እንዳይጠፋበት ፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ።

፵፪ በእኔም ፡ ከሚያምኑት ፡ ከእነዚህ ፡ ከታናናሾቹ ፡ አንዱን ፡ የሚያሰናክል ፡ ሁሉ ፡ ትልቅ ፡ የወፍጮ ፡ ድንጋይ ፡ በአንገቱ ፡ ታስሮ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ቢጣል ፡ ይሻለው ፡ ነበር ። ፵፫ እጅህ ፡ ብታሰናክልህ ፡ ቍረጣት ፤ ሁለት ፡ እጅ ፡ ኖሮህ ፡ ትላቸው ፡ ወደማይሞትበት ፡ እሳቱም ፡ ወደማይጠፋበት ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ ወደማይጠፋ ፡ እሳት ፡ ከመሄድ ፡ ጕንድሽ ፡ ሆነህ ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ መግባት ፡ ይሻላል ። ፵፭ እግርህ ፡ ብታሰናክልህ ፡ ቍረጣት ፤ ሁለት ፡ እግር ፡ ኖሮህ ፡ ትላቸው ፡ ወደ ፡ ማይሞትበት ፡ እሳቱም ፡ ወደማይጠፋበት ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ ወደማይጠፋ ፡ እሳት ፡ ከመጣል ፡ አንካሳ ፡ ሆነህ ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ መግባት ፡ ይሻልሃል ። ፵፰ ዓይንህ ፡ ብታሰናክልህ ፡ አውጣት ፤ ሁለት ፡ ዓይን ፡ ኖሮህ ፡ ትላቸው ፡ ወደማይሞትበት ፡ እሳቱም ፡ ወደማይጠፋበት ፡ ወደ ፡ ገሃነመ ፡ እሳት ፡ ከመጣል ፡ አንዲት ፡ ዓይን ፡ ኖራህ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ መግባት ፡ ይሻልሃል ። ፵፱ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በእሳት ፡ ይቀመማልና ፡ መሥዋዕትም ፡ ሁሉ ፡ በጨው ፡ ይቀመማል ። ፶ ጨው ፡ መልክም ፡ ነው ፤ ጨው ፡ ግን ፡ አልጫ ፡ ቢሆን ፡ በምን ፡ ታጣፍጡታላችሁ ? በንፍሳችሁ ፡ ጨው ፡ ይኑርባችሁ ፡ እርስ ፡ በርሳችሁም ፡ ተስማሙ ።

ምዕራፍ ፡ ፲ ።

፩ ከዚያም ፡ ተነሥቶ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ አገር ፡ መጣ ፡ ደግሞም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ተሰበሰቡ ፡ እንደ ፡ ልማዱም ፡ ደግሞ ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበር ።

፪ ፈሪሳውያንም ፡ ቀርበው ፡— ሰው ፡ ሚስቱን ፡ ሊፈታ ፡ ተፈቅዶለታልን ? ብለው ፡ ሊፈትኑት ፡ ጠየቁት ። እርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፡— ሙሴ ፡ ምን ፡ አዘዛችሁ ? አላቸው ። ፫ እነርሱም ፡— ሙሴስ ፡ የፍችዋን ፡ ጽሕፈት ፡ ጽፎ ፡ እንዲፈታት ፡ ፈቀደ ፡ አሉ ። ፬ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡— ስለ ፡ ልባችሁ ፡ ጥንካሬ ፡ ይህችን ፡ ትእዛዝ ፡ ጻፈላችሁ ። ፭ ከፍጥረት ፡ መጀመሪያ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አደረጋቸው ፤ ፮ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ይተዋል ፡ ከሚስቱም ፡ ጋር ፡ ይተባበራል ። ፯ ሁለቱም ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ይሆናሉ ፤ ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሁለት ፡ አይደሉም ። ፰ እግዚአብሔር ፡ ያጣመረውን ፡ እንግዲህ ፡ ሰው ፡ አይለየው ።

፱ በቤትም ፡ ደግሞ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ጠየቁት ። ፲ እርሱም ፡— ሚስቱን ፡ ፈትቶ ፡ ሌላ ፡ የሚያገባ ፡ ሁሉ ፡ በእርስዋ ፡ ላይ ፡ ያመነዝራል ፤ ፲፩ እርስዋም ፡ ባልዋን ፡ ፈትታ ፡ ሌላ ፡ ብታገባ ፡ ታመነዝራለች ፡ አላቸው ።

፲፫ እንዲዳስሳቸውም ፡ ሕፃናትን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አመጡ ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ያመጡአቸውን ፡ ገሠጹአቸው ። ፲፬ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ አይቶ ፡ ተቈጣና ፡— ሕፃናትን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ ተዉ ፡ አትከልክሉአቸው ፤ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ እንደነዚህ ፡ ላሉት ፡ ናትና ። ፲፭ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ የማይቀበላት ፡ ሁሉ ፡ ከቶ ፡ አይገባባትም ፡ አላቸው ። ፲፮ አቀፋቸውም ፡ እጁንም ፡ ጭኖ ፡ ባረከቸው ።

፲፯ እርሱም ፡ በመንገድ ፡ ሲወጣ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ሮጦ ፡ ተንበረከከለትና ፡— ቸር ፡ መምህር ፡ ሆይ ፡ የዘላለም ፡ ሕይወትን ፡ እወርስ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ላድርግ ? ብሎ ፡ ጠየቀው ። ፲፰ ኢየሱስም ፡— ስለ ፡ ምን ፡ ቸር ፡ ትለኛለህ ? ከአንዱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ ቸር ፡ ማንም ፡ የለም ። ፲፱ ትእዛዛትን ፡ ታውቃለህ ፡ አታመንዝር ፡ አትግደል ፡ አትስረቅ ፡ በሐሰት ፡ አትመስክር ፡ አታታልል ፡ አባትህንና ፡ እናትህን ፡ አክብር ፡ አለው ። ፳ እርሱም ፡ መልሶ ፡— መምህር ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ከሕፃንነቴ ፡ ጠብቄአለሁ ፡ አለው ። ፳፩ ኢየሱስም ፡ ተመለከተውና ፡ ወደደው ፡ አንዲትም ፡ ነገር ፡ ይጐድልሃል ፡ አለው ፡— ሂድ ፡ ያለህን ፡ ሁሉ ፡ ሽጠህ ፡ ለድኾች ፡ ስጥ ፡ መዝገብም ፡ በሰማይ ፡ ይሆንልሃል ፤ ተከተለኝም ፡ ና ። ፳፪ ነገሩ ፡ ግን ፡ አሳዘነው ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ነበረውና ፡ አዝኖ ፡ ሄደ ። ፳፫ ኢየሱስም ፡ ዙሪያውን ፡ ተመልክቶ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡— ባለጠጋ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ሊገባ ፡ እንዴት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ፡ አላቸው ። ፳፬ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ በቃሉ ፡ ተደነቁ ። ኢየሱስም ፡ ደግሞ ፡ መልሶ ፡— ልጆች ፡ ሆይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ለሚታመኑ ፡ እንዴት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ! ፳፭ ባለጠጋ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ከመግባት ፡ ግመል ፡ በመርፌ ፡ ቀዳዳ ፡ ቢያልፍ ፡ ይቀላል ፡ አላቸው ። ፳፮ እነርሱም ፡ እጅግ ፡ አደነቁ ፡ እርስ ፡ በርሳቸውም ፡ እንዲህ ፡ ማን ፡ ሊድን ፡ ይችላል ? አሉ ። ፳፯ ኢየሱስም ፡ አይቶ ፡ ተመለከተና ፡— ለሰው ፡ አይቻልም ፡ እንጂ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አይቻልም ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይቻላልና ፡ አላቸው ።

፳፰ ጴጥሮስ ፡ ይነግረው ፡ ጀመር ፡— እነሆ ፡ እኛ ፡ ሁሉን ፡ ትተን ፡ ተከተልንህ ፡ አለው ። ፳፱ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡— ስለ ፡ እኔና ፡ ስለ ፡ ወንጌል ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ እርሻ ፡ ወንድም ፡ እኅትም ፡ እናትም ፡ አባትም ፡ ልጆችም ፡ ስለ ፡ ተዉ ፡ ያለ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ፴ አሁን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ መቶ ፡ እጥፍ ፡ ቤቶች ፡ እርሻዎችም ፡ ወንድሞችም ፡ እኅቶችም ፡ እናቶችም ፡ ልጆችም ፡ ከመከራ ፡ ጋር ፡ ሳይቀበል ፡ በሚመጣው ፡ ዓለም ፡ የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ አይቀበልም ፡ አለ ። ፴፩ ብዙዎች ፡ የመጀመሪያዎች ፡ የኋለኞች ፡ የኋለኞችም ፡ የመጀመሪያዎች ፡ ይሆናሉ ።

፲፱ የለም ። ትእዛዛትን ፡ ታውቃለህ ፤ አታመንዝር ፥ አትግደል ፥ አትስረቅ ፥ በሐሰት ፡ አትመስክር ፥ አታታልል ፥ አባትህንና ፡ እናትህን ፡ አክብር ፡ 19 አለው ። እርሱም ፡ መልሶ ፡ — መምህር፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ከሕፃንነቴ ፡ ጀምሬ ፡ ጠብቄአለሁ ፡ 20 አለው ። ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ተመልክቶ ፡ ወደደውና ፡ — አንድ ፡ ነገር ፡ ጐደለህ ፡ ሂድ ፡ ያለህን ፡ ሁሉ ፡ ሽጠህ ፡ ለድሆች ፡ ስጥ ፡ በሰማይ ፡ 21 ይም ፡ መዝገብ ፡ ታገኛለህ ፥ መስቀሉንም ፡ ተሸክመህ ፡ ና ፡ ተከተለኝ፡ አለው ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ 22 ዚህ ፡ ነገር ፡ ፊቱ ፡ ጠቁረ ፡ ብዙ ፡ ንብረት ፡ ነበረ ፡ ውና ፡ እያዘነም ፡ ሄደ ።

23 ኢየሱስም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ አይቶ ፡ ደቀ ፡ መዛ ሙርቱን ፡ — ገንዘብ ፡ ላላቸው ፡ ወደ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ መንግሥት ፡ መግባት ፡ እንዴት ፡ ጭንቅ ፡ 24 ይሆናል ፡ አላቸው ። ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ እነዚ ህን ፡ ቃሉት ፡ አደነቁ ። ኢየሱስም ፡ ደግሞ ፡ መልሶ ፡ — ልጆች ፡ ሆይ ፡ በገንዘብ ፡ ለሚታመኑ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ መግባት ፡ 25 እንዴት ፡ ጭንቅ ፡ ነው ። በለ ፡ ጠጋ ፡ ወደ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ከሚገባ ፡ ግመል ፡ በመ ርፌ ፡ ቀዳዳ ፡ ቢያልፍ ፡ ይቀላል ፡ አላቸው ። እነ 26 ርሱም ፡ ያለ ፡ መጠን ፡ ተገረመና ፡ እርስ ፡ በር ሳቸው ፡ — እንግዲያ ፡ ማን ፡ ሊድን ፡ ይችላል ? 27 ተባባሉ ። ኢየሱስም ፡ ተመለከታቸውና ፡ — ይህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ እንጂ ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ አይቻልም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ 28 ሁሉ ፡ ይቻላልና፡ አለ ። ጴጥሮስም ፡— እነሆ ፥ እኛ ፡ ሁሉን ፡ ትተን ፡ ተከተልንህ ፡ ይለው ፡ ጀመር ። 29 ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— እውነት ፡ እላችኋለሁ ፥ ስለ ፡ እኔና ፡ ስለ ፡ ወንጌል ፡ ቤትን ፡ ወይም ፡ ወንድሞችን ፡ ወይም ፡ እኅቶችን ፡ ወይም ፡ አባትን ፡ ወይም ፡ እናትን ፡ ወይም ፡ ሚስትን ፡ ወይም ፡ ልጆችን ፡ ወይም ፡ እርሻን ፡ 30 የተው ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከስደት ፡ ጋር ፡ ቤቶችን ፡ ወንድሞችንም ፡ እኅቶችንም ፡ እናቶ ችንም ፡ ልጆችንም ፡ እርሻንም ፡ መቶ ፡ እጥፍ ፥ በሚመጣውም ፡ ዓለም ፡ የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ 31 የማይቀበል ፡ ማንም ፡ የለም ። ግን ፡ ብዙ ፡ ፊተ ኞች ፡ ኋለኞች ፡ ኋለኞችም ፡ ፊተኞች ፡ ይሆ ናሉ ።

32 ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ሊወጡ ፡ በመንገድ ፡ ነበሩ ፥ ኢየሱስም ፡ ይቀድማቸው ፡ ነበርና ፡ ተደ ነቁ ፡ የተከተሉትም ፡ ይፈሩ ፡ ነበር ። ደግሞም ፡ አሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አቅርቦ ፡ ይደርስ በት ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ይነግራቸው ፡ ጀመር ፡ — 33 እነሆ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንወጣለን ፥ የሰው ፡ ልጅም ፡ ለካህናት ፡ አለቆችና ፡ ለጻፎች ፡ አልፎ ፡ ይሰጣል ፥ የሞት ፡ ፍርድም ፡ ይፈርዱበታል ፥ ለአ 34 ሕዛብም ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡታል ፥ ያዘብጡበ ትማል ፡ ይተፉበትማል ፡ ይገርፉትማል ፡ ይገድ ሉትማል ፥ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ይነሣል ፡ አላ ቸው ።

35 የዘብዴዎስ ፡ ልጆች ፡ ያዕቆብና ፡ ዮሐንስም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀርበው ፡— መምህር፡ ሆይ ፥ የምን ለምንህን ፡ ሁሉ ፡ እንድታደርግልን ፡ እንወዳለን ፡ 36 አሉት ። እርሱም ፡— ምን ፡ ላደርግላችሁ ፡ ትወ 37 ዳላችሁ ? አላቸው ። እነርሱም ፡— በክብርህ ፡ ጊዜ ፡ አንዳችን ፡ በቀኝ ፡ አንዳችንም ፡ በግራህ ፡ መቀመጥን ፡ ስጠን ፡ አሉት ። ኢየሱስ ፡ ግን ፡— 38 የምትለምኑትን ፡ አታውቁም ። እኔ ፡ የምጠጣ ውን ፡ ጽዋ ፡ ልትጠጡ ፡ ትችላላችሁን ? ወይስ ፡ የምጠመቀው ንስ ፡ ጥምቀት ፡ ልትጠመቁ ፡ ትችላላችሁን ? 39 አላቸው ። እነርሱም ፡— እንችላለን ፡ አሉት ። ኢየሱስም ፡— እኔ ፡ የምጠጣውን ፡ ጽዋ ፡ ትጠ ጣላችሁ ፡ እኔ ፡ የምጠመቀውንም ፡ ጥምቀት ፡ ትጠመቃላችሁ ፤ በቀኜና ፡ በግራ ፡ መቀመጥ ፡ 40 ግን ፡ ለተዘጋጀላቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የምሰጥ ፡ እኔ ፡ አይደለሁም ፡ አላቸው ። አሥሩም ፡ ሰም ተው ፡ በያዕቆብና ፡ በዮሐንስ ፡ ይቈጡ ፡ ጀመር ። 41 ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ አላ 42 ቸው ፡— የአሕዛብ ፡ አለቆች ፡ ተብለው ፡ የምታስ በሉት ፡ እንዲገዙአቸው ፡ ታላላቆቻቸውም ፡ በላ ያቸው ፡ እንዲሠለጥኑ ፡ ታውቃላችሁ ። በእና 43 ንተስ ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፡ ማንም ፡ ከእናንተ ፡ ታላቅ ፡ ሊሆን ፡ የሚወድ ፡ የእናንተ ፡ አገልጋይ ፡ ይሁን ፡ ከእናንተም ፡ ማንም ፡ ፊተኛ ፡ 44 ሊሆን ፡ የሚወድ ፡ የሁሉ ፡ ባሪያ ፡ ይሁን ፡ እን 45 ዲሁ ፡ የሰው ፡ ልጅም ፡ ሊያገለግል ፡ እንጂ ፡ እንዲያገለግ ሉት ፡ አልመጣም ።

46 ወደ ፡ ኢያሪኮም ፡ መጡ ። ከደቀ ፡ መዛሙር ቱና ፡ ከብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ጋር ፡ ከእያሪክ ፡ ሲወጣ ፡ የጤሚያስ ፡ ልጅ ፡ ዕውሩ ፡ በርጤሜያስ ፡ አየለ መነ ፡ በመንገድ ፡ ዳር ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ። 47 የና ዝሬቱ ፡ ኢየሱስም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ — የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ኢየሱስ ፡ ሆይ ፡ ማረኝ ፡ እያለ ፡ ይጮኽ ፡ ጀመር ። 48 ብዙዎችም ፡ ዝም ፡ እንዲል ፡ ገሠጹት ። እርሱ ፡ ግን ፡— የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ ማረኝ ፡ እያለ ፡ አብዝቶ ፡ ጮኸ ። 49 ኢየሱስም ፡ ቆመና ፡— ጥሩት ፡ አለ ። ዕውሩንም ፡— አይ ዘህ ፡ ተንሣ ፡ ይጠራሃል ፡ ብለው ፡ ጠሩት ። 50 እር ሱም ፡ እየዘለለ ፡ ተንሣና ፡ ልብሱን ፡ ጥሎ ፡ ወደ ፡ 51 ኢየሱስ ፡ መጣ ። ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡— ምን ፡ ላደርግልህ ፡ ትወዳለህ ? አለው ። ዕውሩም ፡— መምህር፡ ሆይ ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ አለው ። 52 ኢየሱ ስም ፡— ሂድ ፤ እምነትህ ፡ አድኖሃል ፡ አለው ። ወዲያውም ፡ አየ ፡ በመንገድም ፡ ተከተለው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

1 ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ከደብረ ፡ ዘይት ፡ አጠ ገብ ፡ ወዳሉቱ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ፋጌና ፡ ወደ ፡ ቢታንያ ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ 2 ሁለቱን ፡ ልከ ፡— በፊታችሁ ፡ ወዳለችው ፡ መን ደር ፡ ሂዱ ፡ ወዲያውም ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡ ገብታ ችሁ ፡ ከሰው ፡ ማንም ፡ ገና ፡ ያልተቀመጠበት ፡ ውርንጫ ፡ ታስሮ ፡ ታገኛላችሁ ፡ ፈትታችሁ ፡ 3 አምጡልኝ ። ማንም ፡— ስለ ፡ ምን ፡ እንዲህ ፡ ታደርጋላችሁ ? ቢላችሁ ፡— ለጌታ ፡ ያስፈልገ ዋል ፡ ወዲያውም ፡ ይሰዋው ፡ ይሰደዋል ፡ 4 በሉት ፡ አላቸው ። ሄዱም ፡ ውርንጫውንም ፡ በመንገድ ፡ መተላለፊያ ፡ በደጅ ፡ ውጭ ፡ ታስሮ ፡ 5 አገኙት ፡ ፈቱትም ። በዚያም ፡ ከቆሙት ፡ አን ዳንዶቹ ፡— ውርንጫውን ፡ የምትፈቱት ፡ ምን ፡ 6 ልታደርጉት ፡ ነው ? አሉአቸው ። እነርሱም ፡ ኢየሱስ ፡ እንዳዘዘ ፡ አሉአቸው ፤ ተዉአቸ 7 ውም ። ውርንጫውንም ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ አመ ጡት ፡ ልብሶቹንም ፡ በላዩ ፡ ጣሉ ፥ ተቀመጠ 8 በትም ። ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ልብሶቻውን ፡ በመ ንገድ ፡ ላይ ፡ አነጠፉ ፥ ሌሎችም ፡ ከዛፍ ፡ ቅጠ 9 ሎችን ፡ እየቈረጡ ፡ ያነጥፉ ፡ ነበር ። የሚቀድ ሙትም ፡ የሚከተሉትም ፡— ሆሣዕና ፤ በጌታ ፡ 10 ስም ፡ የሚመጣ ፡ የተባረከ ፡ ነው ፤ በጌታ ፡ ስም ፡ የምትመጣ ፡ የአባታችን ፡ የዳዊት ፡ መንግሥት ፡ የተባረከች ፡ ናት ፤ ሆሣዕና ፡ በአርያም ፡ እያሉ ፡ ይጮኹ ፡ ነበር ።

11 ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ መቅ ደስ ፡ ገባ ፤ ዘወር ፡ ብሎም ፡ ሁሉን ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ ጊዜው ፡ መሽቶ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፥ ከአሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ቢታንያ ፡ ወጣ ።

12 በማግሥቱም ፡ ከቢታንያ ፡ ሲወጡ ፡ ተራበ ። 13 ቅጠልም ፡ ያላት ፡ በለስ ፡ ከሩቅ ፡ አይቶ ፡ ምና ልባት ፡ አንዳች ፡ ይገኝበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ መጣ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የበለስ ፡ ወራት ፡ አልነበረምና ፡ መዋቶ ፡ ከቅጠል ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አላገኘበትም ። 14 መልሶም ፡— ከአሁን ፡ ጀምሮ ፡ ለዘላለም ፡ ማንም ፡ ከአንቺ ፡ ፍሬ ፡ አይብላ ፡ አላት ። ደቀ ፡ መዛሙ ርቱም ፡ ሰሙ ።

15 ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ መጡ ። ወደ ፡ መቅ ደስም ፡ ገብቶ ፡ በመቅደስ ፡ የሚሸጡትንና ፡ የሚ ገዙትን ፡ ያወጣ ፡ ጀመር ፥ የገንዘብ ፡ ለዋጮች ንም ፡ ገበታዎች ፡ የርግብ ፡ ሻጮችንም ፡ ወን 16 በሮች ፡ ገለበጠ ። ዕቃም ፡ ተሸክሞ ፡ ማንም ፡ በመ 17 ቅደስ ፡ ሊያልፍ ፡ አልፈቀደም ። አስተማራቸ ውም ፡— ቤቴ ፡ ለአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ትባላለች ፡ ተብሎ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ? እና ንተ ፡ ግን ፡ የወንበዶች ፡ ዋሻ ፡ አደረጋችኋት ፡ 18 አላቸው ። የካህናት ፡ አለቆችም ፡ ጻፎችም ፡ ሰም ተው ፥ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ በትምህርቱ ፡ ይገረሙ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ይፈሩት ፡ ነበርና ፡ እንዴት ፡ አድር 19 ገው ፡ እንዲያጠፉት ፡ ፈለጉ ። ማታ ፡ ማታም ፡ ከከተማ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይወጣ ፡ ነበር ።

20 ማለዳም ፡ ሲያልፉ ፡ በለሲቱን ፡ ከሥርዋ ፡ ደርቃ ፡ አዩአት ። 21 ጴጥሮስም ፡ ትዝ ፡ ብሎት ፡— መምህር፡ ሆይ ፥ እነሆ ፡ የረገምሃት ፡ በለስ ፡ ደርቃ ለች ፡ አለው ። ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላ 22 ቸው ፡— በእግዚአብሔር ፡ እመኑ ። እውነት ፡ 23 እላችኋለሁ ፥ ማንም ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ እንዲደረግ ለት ፡ ቢያምን ፡ በልቡ ፡ ሳይጠራጠር ፡ ይህን ፡ ተራራ ፡— ተነቅለህ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ተወርወር፡ ቢል ፡ ይሆንለታል ። 24 ስለዚህ ፡ እላችኋለሁ ፡ የጸ ለያችሁትን ፡ የለመናችሁትንም ፡ ሁሉ ፡ እንዳገ 25 ኛችሁት ፡ እመኑ ፥ ይሆንላችኋል ። ለጸሎ ትም ፡ በቆማችሁ ፡ ጊዜ ፡ በሰማያት ፡ ያለው ፡ አባ ታችሁ ፡ ደግሞ ፡ ኃጢአታችሁን ፡ ይቅር ፡ እን ዲላችሁ ፡ በማንም ፡ ላይ ፡ አንዳች ፡ ቢኖርባችሁ ፡ ይቅር ፡ በሉት ። 26 እናንተ ፡ ግን ፡ ይቅር ፡ ባትሉ ፡ በሰማያት ፡ ያለው ፡ አባታችሁም ፡ ኃጢአታች ሁን ፡ ይቅር ፡ አይላችሁም ።

27 ደግሞም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ። እር ሱም ፡ በመቅደስ ፡ ሲመላለስ ፡ የካህናት ፡ አለቆ ችና ፡ ጻፎች ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ መጥ 28 ተው ፡— እነዚህን ፡ በምን ፡ ሥልጣን ፡ ታደርጋ ለህ ? ወይስ ፡ እነዚህን ፡ ለማድረግ ፡ ይህን ፡ ሥል ጣን ፡ ማን ፡ ሰጠህ ? አሉት ። 29 ኢየሱስም ፡ ፡— እኔም ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ እጠይቃችኋለሁ ፥ እና ንተም ፡ መልሱልኝ ፥ እኔም ፡ በምን ፡ ሥልጣን ፡ እነዚህን ፡ እንዳደርግ ፡ እነግራችኋለሁ ። 30 የዮሐ ንስ ፡ ጥምቀት ፡ ከሰማይ ፡ ነበረችን ፡ ወይስ ፡ ከሰው ? መልሱልኝ ፡ አላቸው ። እርስ ፡ በርሳቸውም ፡ 31 ሲነጋገሩ ፡— ከሰማይ ፡ ነው ፡ ብንል ፡— እንግዲያ ውስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አላመናችሁበትም ? ይለናል ፤ 32 ነገር ፡ ግን ፡— ከሰው ፡ ነው ፡ እንበልን ? አሉ ፤ ሁሉ ፡ ዮሐንስን ፡ በእውነት ፡ እንደ ፡ ነቢይ ፡ ያዩት ፡ ነበርና ፡ ሕዝቡን ፡ ፈሩ ። 33 ለኢየሱስም ፡ መልሰው ፡— አናውቅም ፡ አሉት ። ኢየሱ ስም ፡— እኔም ፡ በምን ፡ ሥልጣን ፡ እነዚህን ፡ እን ዳደርግ ፡ አልነግራችሁም ፡ አላቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

1 በምሳሌም ፡ ይነግራቸው ፡ ጀመር ። እንድ ፡ ሰው ፡ የወይን ፡ አትክልት ፡ ተከለ ፥ ቅጥርም ፡ ቀጠረለት ፥ መጥመቂያም ፡ ማሰለት ፥ ግንብም ፡ ሠራ ፥ ለገበሬዎች ፡ አከራይቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ሄደ ። 2 በጊዜውም ፡ ከወይን ፡ አትክልት ፡

ፍሬ ፡ ከገበሬዎቹ ፡ እንዲቀበል ፡ አንድ ፡ በረያ ፡ ወደ ፡ ገበሬዎቹ ፡ ላከ ፤ ይዘውም ፡ ደበደቡት ፡ በዶውንም ፡ ሰደዱት ። ዳግመኛም ፡ ሌላውን ፡ በረያ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ላከ ፡ እርሱንም ፡ ወግረው ፡ ራሱን ፡ አቁሰሉት ፡ አዋርደውም ፡ ሰደዱት ። ሌላውንም ፡ ላከ ፤ እርሱንም ፡ ገደሉት ፡ ከሌሎችም ፡ ከብዙዎች ፡ እንዳንዱን ፡ ደበደቡ ፡ እንዳንዱንም ፡ ገደሉ ። የሚወደው ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ገና ፡ ነበረው ፤ ልጁንስ ፡ ያፍናታል ፡ ብሎ ፡ እርሱን ፡ ከሁሉ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ላከ ። እነዚያ ፡ ገበሬዎች ፡ ግን ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ — ወራሹ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ኑ ፡ እንግደለው ፡ ርስቱም ፡ ለኛ ፡ ይሆናል ፡ ተባባሉ ። ይዘውም ፡ ገደሉት ፡ ከወይኑም ፡ አትክልት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ጣሉት ። እንግዲህ ፡ የወይኑ ፡ አትክልት ፡ ጌታ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ? ይመጣል ፡ ገበሬዎቹንም ፡ ያጠፋል ፡ የወይኑንም ፡ አትክልት ፡ ለሌሎች ፡ ይሰጣል ።

ግንበኞች ፡ የናቁት ፡ ድንጋይ ፡ እርሱ ፡ የማዕዘን ፡ ራስ ፡ ሆነ ፤ ይህም ፡ ከጌታ ፡ ዘንድ ፡ ሆነ ፡ ለዓይኖቻችንም ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡

የሚለውን ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ አላነበባችሁምን ?

ምሳሌውንም ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ አውቀዋልና ፡ ሊይዙት ፡ ፈለጉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሕዝቡን ፡ ፈሩ ። ትተውትም ፡ ሄዱ ።

በንግግርም ፡ ሊያጠምዱት ፡ ከፈረሰውያንና ፡ ከሄሮድስ ፡ ወገን ፡ የሆኑትን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ላኩ ። መጥተውም ፡ — መምህር ፡ ሆይ ፡ የሰውን ፡ ፊት ፡ ሳትመለከት ፡ በእውነት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንገድ ፡ ታስተምራለህና ፡ እውነተኛ ፡ እንደ ፡ ሆንህ ፡ ለማንም ፡ እንዳታደላ ፡ እናውቃለን ፤ ለቄሣር ፡ ግብር ፡ መስጠት ፡ ተፈቅዶአልን ፡ ወይስ ፡ አልተፈቀደም ? እንስጥን ፡ ወይስ ፡ አንስጥ ? አሉት ። እርሱ ፡ ግን ፡ ግብዝነታቸውን ፡ አውቆ ፡ — ለምን ፡ ትፈትኑኛላችሁ ? አየው ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ዲናር ፡ አምጡልኝ ፡ አላቸው ። እነርሱም ፡ አመጡለት ። ይህች ፡ መልክ ፡ ጽሕፈቷቱስ ፡ የማን ፡ ናት ? አላቸው ፡ እነርሱም ፡ — የቄሣር ፡ ናት ፡ አሉት ። ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ — የቄሣርን ፡ ለቄሣር ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አስረክቡ ፡ አላቸው ። በርሱም ፡ ተደነቁ ።

ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ የለም ፡ የሚሉ ፡ ሰዱቃውያን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ መጥተው ፡ ጠየቁት ፡ እንዲህም ፡ አሉት ፡ — መምህር ፡ ሆይ ፡ ሙሴ ፡ — የአንድ ፡ ሰው ፡ ወንድም ፡ ሚስቱን ፡ ትቶ ፡ ልጅ ፡ ሳያስቀር ፡ ቢሞት ፡ ወንድሙ ፡ ሚስቱን ፡ አግብቶ ፡ ለወንድሙ ፡ ዘር ፡ ይተክ ፡ ብሎ ፡ ጻፈልን ። ሰባት ፡ ወንድማማቾች ፡ ነበሩ ፤ ፊተኛውም ፡ ሚስት ፡ አግብቶ ፡ ዘር ፡ ሳያስቀር ፡ ሞተ ፤ ሁለተኛውም ፡ አገባት ፡ ዘርም ፡ ሳይተው ፡ ሞተ ፤ ሦስተኛውም ፡ እንዲሁ ፤ ሰባቱም ፡ አገቡአት ፡ ዘርም ፡ አላስቀሩም ። ከሁሉም ፡ በኋላ ፡ ሴቲቱ ፡ ደግሞ ፡ ሞተች ። ሰባቱ ፡ እግብተዋታልና ፡ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ሲነሡ ፡ ከእነርሱ ፡ ለማናቸው ፡ ሚስት ፡ ትሆናለች ?

ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ — መጻሕፍትንና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ኃይል ፡ አታውቁምና ፡ ስለዚህ ፡ የምትስቱ ፡ አይደለምን ? ከሙታንስ ፡ ሲነሡ ፡ በሰማያት ፡ እንዳሉ ፡ መላእክት ፡ ይሆናሉ ፡ እንጂ ፡ አያገቡም ፡ አይጋቡምም ። ስለ ፡ ሙታን ፡ ግን ፡ እንዲነሡ ፡ እግዚአብሔር ፡ —

እኔ ፡ የአብርሃም ፡ አምላክ ፡ የይስሐቅም ፡ አምላክ ፡ የያዕቆብም ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡

እንዳለው ፡ በሙሴ ፡ መጽሐፍ ፡ በቍጥቋጦው ፡ ዘንድ ፡ የተጻፈውን ፡ አላነበባችሁምን ? የሕያዋን ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሙታን ፡ አይደለም ። እንግዲህ ፡ እጅግ ፡ ትስታላችሁ ።

ከጻፎችም ፡ አንዱ ፡ ቀርቦ ፡ ሲከራከሩ ፡ ሰማና ፡ መልካም ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ መለሰላቸው ፡ አስተውሎ ፡ — ከሁሉ ፡ ፊተኛይቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ማናቸይቱ ፡ ናት ? ብሎ ፡ ጠየቀው ። ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ — ከትእዛዛቱ ፡ ሁሉ ፡ ፊተኛይቱ ፡ — አስራኤል ፡ ሆይ ፡ ስማ ፤ ጌታ ፡ አምላክህን ፡ አንድ ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ እንተም ፡ በፍጹም ፡ ልብህ ፡ በፍጹምም ፡ ነፍስህ ፡ በፍጹምም ፡ አሳብህ ፡ በፍጹምም ፡ ኃይልህ ፡ ጌታ ፡ አምላክህን ፡ ውደድ ፡ የምትል ፡ ናት ። ፊተኛይቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይህች ፡ ናት ። ሁለተኛይቱም ፡ — ባልንጀራህን ፡ እንደ ፡ ራስህ ፡ ውደድ ፡ የምትል ፡ እርስዋን ፡ የምትመስል ፡ ይህች ፡ ናት ። ከእነዚህ ፡ የምትበልጥ ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ የለችም ። ጸሐፊውም ፡ — መልካም ፡ ነው ፡ መምህር ፡ ሆይ ፤ አንድ ፡ ነው ፡ ከእርሱም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የለም ፡ ብለህ ፡ በእውነት ፡ ተናገርህ ፤ በፍጹም ፡ ልብ ፡ በፍጹም ፡ አእምሮም ፡ በፍጹም ፡ ነፍስም ፡ በፍጹም ፡ ኃይልም ፡ እርሱን ፡ መውደድ ፡ በልንጀራንም ፡ እንደ ፡ ራስ ፡ መውደድ ፡ በሙሉ ፡ ከሚቃጠል ፡ መሥዕዕትና ፡ ከሌላው ፡ መሥዋዕት ፡ ሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ነው ፡ አለው ። ኢየሱስም ፡ በአእምሮ ፡ እንደ ፡ መለሰ ፡ አይቶ ፡ — አንተ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ የራቅህ ፡ አይደለህም ፡ አለው ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ማንም ፡ ሊጠይቀው ፡ አልደፈረም ።

ኢየሱስም ፡ በመቅደስ ፡ ሲያስተምር ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ — ጻፎች ፡ ክርስቶስ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ እንዴት ፡ ይላሉ ? ዳዊት ፡ ራሱ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ —

ጌታ ፡ ጌታዬን ፡ — ጠላቶቻህን ፡ የእግርህ ፡ መረገጫ ፡ እስክደርግልህ ፡ ድረስ ፡ በቀኜ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ፡

፴፮ አለ ። ዳሂት ፡ ራሱ ፡ ጌታ ፡ አለው ፡ እንዴትስ ፡ ልጁ ፡ ይሆናል ? ብዙ ፡ ሕዝብም ፡ በደስታ ፡ ይሰሙት ፡ ነበር ።

፴፯-፴፰ ሲያስተምርም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ — ረጃጅም ፡ ልጎስ ፡ ለብሰው ፡ መዘርጋ ÷ በገበያም ፡ ሰላም ፡ ታን ÷ በምኩራብም ፡ የከበሬታን ፡ ወንበር ÷ በግብርም ፡ የከበሬታን ፡ ስፍራ ፡ ከሚወዱ ፡ ከጻፎች ፡ ተጠበቁ ፤ የመበለቶችን ፡ ቤት ፡ የሚበሉ ፡ ጸሎታቸውንም ፡ በማስረዘም ፡ የሚያመካኙ ፡ እነዚህ ፡ የበሰ ፡ ፍርድ ፡ ይቀበላሉ ።

፴፱ ኢየሱስም ፡ በመዝገብ ፡ አንጻር ፡ ተቀምጦ ፡ ሕዝቡ ፡ በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ ገንዘብ ፡ እንዴት ፡ እንዲጥሉ ፡ ያይ ፡ ነበር ፤ ብዙ ፡ ባለ ፡ ጠጎችም ፡

፵ ብዙ ፡ ይጥሉ ፡ ነበር ፤ አንዲትም ፡ ድሀ ፡ መበለት ፡ መጥታ ፡ አንድ ፡ ሳንቲም ፡ የሚያህሉ ፡ ሁለት ፡

፵፩ ናስ ፡ ጣለች ። ደቀ ፡ መዛሙርቱንም ፡ ጠርቶ ፡ — እውነት ፡ እላችኋለሁ ÷ በመዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ከሚጥሉት ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ይህች ፡ ድሀ ፡ መበለት ፡

፵፪ አብልጣ ፡ ጣለች ፤ ሁሉ ፡ ከትርፋቸው ፡ ጥሰዋልና ÷ ይህች ፡ ግን ፡ ከጕድለትዋ ፡ የነበራትን ፡ ሁሉ ፡ ትዳርዋን ፡ ሁሉ ፡ ጣለች ፡ አላቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

፩ እርሱም ፡ ከመቅደስ ፡ ሲወጣ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ አንዱ ፡ — መምህር ፡ ሆይ ÷ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ድንጋይዎችና ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ሕንጻዎች ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ እይ ፡ አለው ። ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ — እነዚህን ፡ ታላላቅ ፡ ሕንጻዎች ፡ ታያለህን ? ድንጋይ ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ ሳይፈርስ ፡ በዚህ ፡ አይቀርም ፡ አለው ።

፫ በመቅደስም ፡ ትይዩ ፡ በደብረ ፡ ዘይት ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ÷ ጴጥሮስና ፡ ያዕቆብ ፡ ዮሐንስም ፡

፬ እንድርያስም ፡ — ንገረን ፤ ይህ ፡ መቼ ፡ ይሆናል ? ይህስ ፡ ሁሉ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ እንዳለው ፡ ምልክቱ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ? ብለው ፡ ለብቻቸው ፡

፭ ጠየቁት ። ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ ይላቸው ፡ ጀመር ፡ — ማንም ፡ እንዳያስታችሁ ፡ ተጠንቀቁ ። ብዙዎች ፡ — እኔ ፡ ነኝ ፡ እያሉ ፡ በስሜ ፡

፮ ይመጣሉና ÷ ብዙዎችንም ፡ ያስታሉ ። ጦርነም ፡ የጦርነም ፡ ወሬ ፡ በሰማችሁ ፡ ጊዜ ፡ አትደንግጡ ፤ ይህ ፡ ሊሆን ፡ ግድ ፡ ነውና ÷ ነገር ፡

፯ ግን ፡ መጨረሻው ፡ ገና ፡ ነው ። ሕዝብ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ መንግሥትም ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ይነሣልና ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ የምድር ፡ መናወጥ ፡ ይሆናል ፤ ራብ ፡ ይሆናል ፤ እነዚህ ፡ የምጥ ፡ ጣር ፡ መጀመሪያ ፡ ናቸው ።

፱ እናንተ ፡ ግን ፡ ለራሳችሁ ፡ ተጠንቀቁ ፤ ወደ ፡ ሸንጎ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡአችኋል ፡ በምኵራብም ፡ ትገረፋላችሁ ፡ ምስክርም ፡ ይሆንባቸው ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ በገዦዎችና ፡ በነገሥታት ፡ ፊት ፡ ትቆማላችሁ ። አስቀድሞም ፡ ወንጌል ፡ ለአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ይሰበክ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ።

፲ ሲገሥትዙአችሁና ፡ አሳልፈው ፡ ሲሰጡአችሁም ፡ ምን ፡ እንድትናገሩ ፡ አስቀድማችሁ ፡ አትጨንቁ ÷ ዳሩ ፡ ግን ፡ በዚያች ፡ ሰዓት ፡ የሚሰጣችሁን ፡ ተናገሩ ፤ የሚነግረው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እናንተ ፡ አይደላችሁምና ።

፲፩ ወንድም ፡ ወንድሙን ፡ አሳትም ፡ ልጁን ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ÷ ልጆችም ፡ በወላጆቻቸው ፡ ላይ ፡ ይነሣሉ ፡ ይገድሉአቸውማል ፤ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ስሜ ፡ የተጠላችሁ ፡ ትሆናላችሁ ፤ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ የሚጸና ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ ይድናል ።

፲፪ ነገር ፡ ግን ፡ በነቢዩ ፡ በዳንኤል ፡ የተባለውን ፡ የዋፋት ፡ ርኵሰት ፡ በማይገባው ፡ ስፍራ ፡ ቆሞ ፡ ብታዩ ÷ አንባቢው ፡ ያስተውል ÷ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በይሁዳ ፡ ያሉ ፡ ወደ ፡ ተራሮች ፡ ይሽሹ ÷ በሰገነትም ፡ ያለ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ አይውረድ ፡ ከቤቱም ፡ አንዳች ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ አይግባ ÷ በእርሻም ፡ ያለ ፡ ልብሱን ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ አይመለስ ። በዚያን ፡ ወራትም ፡ ለርጉዞችና ፡ ለሚያጠቡ ፡ ወዮላቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሽሽታችሁ ፡ በክረምት ፡ እንዳይሆን ፡ ጸልዩ ፤ በዚያን ፡ ወራት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፈጠረው ፡ ከፍጥረት ፡ መጀመሪያ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ ያልሆነ ፡ ደግሞም ፡ የማይሆን ፡ የመከራ ፡ ዓይነት ፡ ይሆናልና ። ጌታስ ፡ ወራቶቹን ፡ ባያሳጥር ÷ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ሁሉ ፡ በሕያንም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ መረጣቸው ፡ ምርጦች ፡ ወራቶቹን ፡ አሳጠረ ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ማንም ፡ — እነሆ ፡ ክርስቶስ ፡ ከዚህ ፡ አለ ÷ ወይም ፡ — እነሆ ÷ ከዚያ ፡ አለ ፡ ቢላችሁ ፡ አትመኑ ፤ ሐሰተኞች ፡ ክርስቶሶችና ፡ ሐሰተኞች ፡ ነቢያት ፡ ይነሣሉና ÷ ቢቻላቸውስ ፡ የተመረጡትን ፡ እንኳ ፡ ያስቱ ፡ ዘንድ ፡ ምልክትና ፡ ድንቅ ፡ ያደርጋሉ ። እናንተ ፡ ግን ፡ ተጠንቀቁ ፤ እነሆ ÷ አስቀድሜ ፡ ሁሉን ፡ ነገርኋችሁ ።

፳፫ በዚያን ፡ ወራት ፡ ከዚያ ፡ መከራ ፡ በኋላ ፡ ፀሐይ ፡ ይጨልማል ፡ ጨረቃም ፡ ብርሃንዋን ፡ አትሰጥም ÷ ከዋክብትም ፡ ከሰማይ ፡ ይወድቃሉ ÷ የሰማያትም ፡ ኃይላት ፡ ይናወጣሉ ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በብዙ ፡ ኃይልና ፡ ክብር ፡ በደመና ፡ ሲመጣ ፡ ያዩታል ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ መላእክትን ፡ ይልካል ፡ ከአራቱ ፡ ነፋሳትም ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ዳርቻ ፡ የተመረጡትን ፡ ይሰበስባቸዋል ።

፳፰ ምሳሌውንም ፡ ከበለስ ፡ ተማሩ ፤ ጫፍዋ ፡ ሲለሰልስ ፡ ቅጠልዋም ፡ ሲያቈጠቍጥ ÷ ያን ፡ ጊዜ ፡ በጋ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ ታውቃላችሁ ፤ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ እናንተ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ መሆኑን ፡ ስታዩ ፡ ቀርቦ ፡ በደጅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እወቁ ። እውነት ፡ እላችኋለሁ ÷ ይህ ፡ ሁሉ ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ ትውልድ ፡ አያልፍም ። ሰማይና ፡ ምድር ፡ ያልፋሉ ፡ ቃሌ ፡ ግን ፡ አያልፍም ።

ስለዚያች ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ስለዚያች ፡ ሰዓት ፡ ግን ፡ የሰማይ ፡ መላእክትም ፡ ቢሆኑ ፡ ልጅም ፡ ቢሆን ፡ ከአባት ፡ በቀር ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ። ጊዜው ፡ መቼ ፡ እንዲሆን ፡ አታውቁምና ፡ ተጠንቀቁ ፡ ትጉ ፡ ጸልዩም ። ቤቱን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ሄደ ፡ ሰው ፡ ነው ፦ ለባሮቹም ፡ ሥልጣን ፡ ለእያንዳንዱም ፡ ሥራውን ፡ ሰጥቶ ፡ በረኛውን ፡ እንዲተጋ ፡ አዘዘ ። እንግዲህ ፡ በማታ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በእኩለ ፡ ሌሊት ፡ ወይም ፡ ዶሮ ፡ ሲጮኽ ፡ ወይም ፡ በማለዳ ፡ ቢሆን ፡ በለቤቱ ፡ መቼ ፡ እንዳመጣ ፡ አታውቁምና ፡ ድንገት ፡ መጥቶ ፡ ተኝታችሁ ፡ እንዳያገኛችሁ ፡ ስለዚህ ፡ ትጉ ። ለእናንተም ፡ የምነግራችሁን ፡ ለሁሉ ፡ እላለሁ ፡ ትጉ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

ከሁለት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ፋሲካና ፡ የቂጣ ፡ በዓል ፡ ነበረ ። የካህናት ፡ አለቆችም ፡ ጸፎችም ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ በተንኰል ፡ እንደሚይዙትና ፡ እንደሚገድሉት ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ። የሕዝብ ፡ ሁከት ፡ እንዳይሆን ፡ በበዓል ፡ አይሁን ፡ ይሉ ፡ ነበርና ።

እርሱም ፡ በቢታንያ ፡ በለምጻሙ ፡ በስምዖን ፡ ቤት ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ በማዕድ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ዋጋው ፡ እጅግ ፡ የከበረ ፡ ጥሩ ፡ ናርዶስ ፡ ሽቱ ፡ የመላበት ፡ የአልባስጥሮስ ፡ ቢል ቃጥ ፡ ይዛ ፡ መጣች ፤ ቢልቃጡንም ፡ ሰብራ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አፈሰሰችው ። አንዳንዶችም ፡ — ይህ ፡ የሽቱ ፡ ጥፋት ፡ ለምንድር ፡ ነው ? ይህ ፡ ሽቱ ፡ ከሦስት ፡ መቶ ፡ ዲናር ፡ በሚበልጥ ፡ ዋጋ ፡ ተሸጠ ፡ ለድሆች ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻል ፡ ነበርና ፡ ብለው ፡ በራሳቸው ፡ ይቈጡ ፡ ነበር ፤ እርስዋንም ፡ ነቀፉአት ። ኢየሱስ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ተዉአት ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ታደክሙአታላችሁ ? መልካም ፡ ሥራ ፡ ሠርታልኛለች ። ድሆች ፡ ሁልጊዜ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ይኖራሉና ፡ በማናቸውም ፡ በወደዳችሁት ፡ ጊዜ ፡ መልካም ፡ ልታደርጉላቸው ፡ ትችላላችሁ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ሁልጊዜ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ አልኖርም ። የተቻላትን ፡ አደረገች ፤ አስቀድማ ፡ ለመቃብሬ ፡ ሥጋዬን ፡ ቀባችው ። እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ ይህ ፡ ወንጌል ፡ በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ በሚሰበክበት ፡ በማናቸውም ፡ ስፍራ ፡ እርስዋ ፡ ያደረገችው ፡ ደግሞ ፡ ለእርስዋ ፡ መታሰቢያ ፡ ሊሆን ፡ ይነገራል ።

ከአሥራ ፡ ሁለቱም ፡ አንዱ ፡ የአስቆሮቴቱ ፡ ይሁዳ ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጠው ፡ ወደ ፡ ካህናት ፡ አለቆች ፡ ሄደ ። ሲሰሙም ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ ብርም ፡ ይሰጡት ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ ሰጡት ። በሚመች ፡ ጊዜም ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ አሳልፎ ፡ እንዲሰጠው ፡ ይፈልግ ፡ ነበር ።

ፋሲካን ፡ በሚያርዱበት ፡ በቂጣ ፡ በዓል ፡ መጀመሪያ ፡ ቀን ፡ ደቀ ፡ መዘሙርቱ ፡ — ፋሲካን ፡ ትበላ ፡ ዘንድ ፡ ወዴት ፡ ሄደን ፡ ልናሰናዳ ፡ ትወዳለህ ? አሉት ። ከደቀ ፡ መዘሙርቱም ፡ ሁለት ፡ ላነ፡ እንዲህም ፡ አላቸው ፡ — ወደ ፡ ከተማ ፡ ሂዱ ፡ ማድጋ ፡ ውኃ ፡ የተሸከመ ፡ ሰውም ፡ ይገናኛች ኋል ፡ ተከተሉት ፡ የሚገባበትንም ፡ የቤቱን ፡ ጌታ ፡ — መምህሩ ፡ ከደቀ ፡ መዘሙርቴ ፡ ጋር ፡ ፋሲካን ፡ የምበላበት ፡ የእንግዳ ፡ ቤት ፡ ወዴት ፡ ነው ? ይላል ፡ በሉት ። እርሱም ፡ በደርብ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የተሰናዳና ፡ የተነጠፈ ፡ ታላቅ ፡ አዳራሽ ፡ ያሰያችኋል ። በዚያም ፡ አሰናዱልን ። ደቀ ፡ መዘሙርቱም ፡ ወጡ ፡ ወደ ፡ ከተማም ፡ ሄደው ፡ እንዳላቸው ፡ አገኙ ፡ ፋሲካንም ፡ አሰናዱ ።

በመሸም ፡ ጊዜ ፡ ከአሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ጋር ፡ መጣ ። ተቀምጠውም ፡ ሲበሉ ፡ ኢየሱስ ፡ — እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ ከእናንተ ፡ አንዱ ፡ እርሱም ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ የሚበላው ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጠኛል ፡ አለ ። እነርሱም ፡ ያዝኑ ፡ እያንዳንዳቸውም ፡ — እኔ ፡ እሆንን ? ይሉት ፡ ጀመር ። እርሱም ፡ መለሰ ፡ — ከአሥራ ፡ ሁለቱ ፡ አንዱ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ወጭቱ ፡ እጁን ፡ የሚያጠልቀው ፡ ነው ። የሰው ፡ ልጅስ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ይሄዳል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ አልፎ ፡ ለሚሰጥበት ፡ ለዚያ ፡ ሰው ፡ ወየ ፡ ለት ፤ ያ ፡ ሰው ፡ ባልተወለደ ፡ ይሻለው ፡ ነበር ፡ አላቸው ።

ሲበሉም ፡ ኢየሱስ ፡ እንጀራን ፡ አንሥቶ ፡ ባረከ ፡ ቈርሶም ፡ ሰጣቸውና ፡ — እንካችሁ ፤ ይህ ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ፡ አለ ። ጽዋውንም ፡ አንሥቶ ፡ አመስግኖም ፡ ሰጣቸው ፡ ሁሉም ፡ ከእርሱ ፡ ጠጡ ። እርሱም ፡ — ይህ ፡ ስለ ፡ ብዙዎች ፡ የሚፈስ ፡ የአዲስ ፡ ኪዳን ፡ ደሜ ፡ ነው ። እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ከወይኑ ፡ ፍሬ ፡ አዲሱን ፡ እስከምጠጣበት ፡ እስከዚያ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ደግሞ ፡ አልጠጣውም ፡ አላቸው ።

መዝሙርም ፡ ከዘመሩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ወጡ ። ኢየሱስም ፡ — በዚች ፡ ሌሊት ፡ ሁላችሁ ፡ በእኔ ፡ ትሰናከላላችሁ ፤ እረኛውን ፡ እመታለሁ ፡ በጎችም ፡ ይበተናሉ ፡ የሚል ፡ ተጽፎአልና ። ነገር ፡ ግን ፡ ከተነሣሁ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ እቀድማችኋለሁ ፡ አላቸው ። ጴጥሮስም ፡ — ሁሉም ፡ ቢሰናከሉ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ከቶ ፡ አልሰናከልም ፡ አለው ። ኢየሱስም ፡ — እውነት ፡ እልሃለሁ ፡ ዛሬ ፡ በዚች ፡ ሌሊት ፡ ዶሮ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ሳይጮኽ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ትክደኛለህ ፡ አለው ። እርሱም ፡ ቃሉን ፡ አበርትቶ ፡ — ከአንተ ፡ ጋር ፡ የምሞት ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ ከቶ ፡ አልክድህም ፡ አለ ። ሁሉም ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ዚሁ ፡ አሉ ።

ጌቴሴማኒ ፡ ወደምትባልም ፡ ስፍራ ፡ መጡ ፡ ደቀ ፡ መዘሙርቴንም ፡ — ስጸልይ ፡ ሳለሁ ፡ በዚህ ፡ ተቀመጡ ፡ አላቸው ። ጴጥሮስንና ፡ ያዕቆብን ፡ ዮሐንስንም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ወሰደ ፤ ሊደነግ ጥም ፡ ሊተክዝም ፡ ጀመረና ፡ — ነፍሴ ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ እጅግ ፡ አዘነች ፤ በዚህ ፡ ቈዩ ፡ ትጉም ፡ አላቸው ። ዋቂትም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ በምድርም ፡ ወድቆ ፡ ይቻልስ ፡ ቢሆን ፡ ሰዓቲቱ ፡ ከእርሱ ፡ እንድታልፍ ፡ ጸለየና ፡ — አባ ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ ሁሉ ፡ ይቻልሃል ፤ ይህችን ፡ ጽዋ ፡ ከእኔ ፡ ውሰድ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንት ፡ የምትወደው ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ የምወደው ፡ እያሁን ፡ አለ ። መጣም ፡ ተኝ ተውም ፡ አገኛቸው ፡ ጴጥሮስንም ፡ — ስምዖን ፡ ሆይ ፡ ተኝተሃልን ? አንዲት ፡ ሰዓት ፡ ስንኳ ፡ ልት ተጋ ፡ አልቻልህምን ? ወደ ፡ ፈተና ፡ እንዳትገቡ ፡ ትጉ ፡ ጸልዩም ፤ መንፈስስ ፡ ተዘጋጅታለች ፡ ሥጋ ፡ ግን ፡ ደክማ ፡ ነው ፡ አለው ። ደግሞም ፡ ሄዶ ፡ ያንኑ ፡ ቃል ፡ ጸለየ ። ደግሞም ፡ መጥቶ ፡ ዓይናቸው ፡ በእንቅልፍ ፡ ከብዶው ፡ ነበርና ፡ ተኝተው ፡ አገኛቸው ፡ የሚመልሱለትንም ፡ አላወቁም ። ሦስተኛም ፡ መጥቶ ፡ — እንግዲህስ ፡ ተኙ ፡ ዕረፉም ፤ ይበቃል ፡ ሰዓቲቱ ፡ ደረሰች ፤ እነሆ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በኃጢአተኞች ፡ እጅ ፡ አልፎ ፡ ይሰጣል ። ተነሡ ፡ እንሂድ ፤ እነሆ ፡ አሳልፎ ፡ የሚሰጠኝ ፡ ቀርቦአል ፡ አላቸው ።

ወዲያውም ፡ ገና ፡ ሲናገር ፡ ከአሥራ ፡ ሁለቱ ፡ አንዱ ፡ ይሁዳ ፡ መጣ ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሰይፍና ፡ ጕመድ ፡ ይዘው ፡ ከካህናት ፡ አለቆችና ፡ ከጻፎች ፡ ከሽማግሌዎችም ፡ ዘንድ ፡ መጡ ። አሳልፎ ፡ የሚሰጠውም ፡ — የምስመው ፡ እርሱ ፡ ነው ፤ ያዙት ፡ ተጠንቅቃችሁም ፡ ውሰዱት ፡ ብሎ ፡ ምልክት ፡ ሰጥቶአቸው ፡ ነበር ። መጥቶም ፡ ወዲያው ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀረበና ፡ — መምህር ፡ ሆይ ፡ መምህር ፡ ሆይ ፡ ብሎ ፡ ሳመው ። እነርሱም ፡ እጃቸውን ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ጭነው ፡ ያዙት ። በአጠገብ ፡ ከቆሙት ፡ ግን ፡ አንዱ ፡ ሰይፉን ፡ መዘ ፡ የሊቀ ፡ ካህናቱን ፡ ባሪያ ፡ መታ ፡ ጆሮውንም ፡ ቈረጠ ። ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ — ወንበዴ ፡ እንደምትይዙ ፡ ሰይፍና ፡ ጕመድ ፡ ይዛችሁ ፡ ልትይዙኝ ፡ መጣችሁን ? በመቅደስ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ እያስተማርሁ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ስኖር ፡ አልያዛችሁኝም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መጻሕፍት ፡ ይፈጸሙ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ሆነ ፡ አላቸው ። ሁሉም ፡ ትተውት ፡ ሸሹ ።

ዕርቃኑን ፡ በነጠላ ፡ የሸፈነ ፡ አንድ ፡ ጎበዝ ፡ ይከተለው ፡ ነበር ፤ ጎበዛዝቱም ፡ ያዙት ፤ እርሱ ፡ ግን ፡ ነጠላውን ፡ ትቶ ፡ ዕራቁቱን ፡ ሸሸ ።

ኢየሱስንም ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ወሰዱት ፡ የካህናት ፡ አለቆችም ፡ ሁሉ ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ጸሮችም ፡ ተሰበሰቡ ። ጴጥሮስም ፡ እስከ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ በሩቁ ፡ ተከተለው ፤ ከሎሌዎችም ፡ ጋር ፡ ተቀምጦ ፡ እሳት ፡ ይሞቅ ፡ ነበር ። የካህናት ፡ አለቆችም ፡ ሸንጎውም ፡ ሁሉ ፡ እንዲገድሉት ፡ በኢየሱስ ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ፤ አላገኙምም ። ብዙዎች ፡ በሐሰት ፡ ይመሰክሩበት ፡ ነበርና ፤ ምስክርነታቸው ፡ ግን ፡ አልተስማማም ። ሰዎችም ፡ ተነሥተው ፡ — እኔ ፡ ይህን ፡ በእጅ ፡ የተሠራውን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አፈርሰዋለሁ ፡ በሦስት ፡ ቀንም ፡ ሌላውን ፡ በእጅ ፡ ያልተሠራውን ፡ እሠራለሁ ፡ ሲል ፡ ሰማነው ፡ ብለው ፡ በሐሰት ፡ መሰከሩበት ። ምስክርነታቸውም ፡ እንዲህ ፡ እንኳ ፡ አልተሰማማም ። ሊቀ ፡ ካህናቱም ፡ በመካከላቸው ፡ ተነሥቶ ፡ — አንዳች ፡ አትመልስምን ? እነዚህስ ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ የሚመሰክሩብህ ፡ ምንድር ፡ ነው ? ብሎ ፡ ኢየሱስን ፡ ጠየቀው ። እርሱ ፡ ግን ፡ ዝም ፡ አለ ፡ አንዳችም ፡ አልመለሰም ። ደግሞ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ጠየቀውና ፡ — የቡሩክ ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ ፡ አንተ ፡ ነህን ? አለው ። ኢየሱስም ፡ — እኔ ፡ ነኝ ፤ የሰው ፡ ልጅም ፡ በኃይል ፡ ቀኝ ፡ ሲቀመጥ ፡ በሰማይም ፡ ደመና ፡ ሲመጣ ፡ ታያላችሁ ፡ አለ ። ሊቀ ፡ ካህናቱም ፡ ልብሱን ፡ ቀደደና ፡ — ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ምስክሮችን ፡ ምን ፡ ያስፈልገናል ? ስድቡን ፡ ሰማችሁ ፡ ምን ፡ ይመስላችኋል ? አለ ። እነርሱም ፡ ሁሉ ፡ — ሞት ፡ ይገባዋል ፡ ብለው ፡ ፈረዱበት ። አንዳንዶችም ፡ ይተፉበት ፡ ፊቱንም ፡ ሸፍነው ፡ ይጐሰሙትና ፡ — ትንቢት ፡ ተናገር ፡ ይሉት ፡ ጀመር ፡ ሎሌዎችም ፡ በጥፊ ፡ እየመቱ ፡ ወሰዱት ።

ጴጥሮስም ፡ በግቢ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ሳለ ፡ ከሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ገረዶች ፡ አንዲቱ ፡ መጣች ፡ ጴጥሮስም ፡ እሳት ፡ ሲሞቅ ፡ አይታ ፡ ተመለከተችውና ፡ — አንተ ፡ ደግሞ ፡ ከናዝሬቱ ፡ ከኢየሱስ ፡ ጋር ፡ ነበርህ ፡ አለችው ። እርሱ ፡ ግን ፡ — የምትዪውን ፡ አላውቅም ፡ አላስተውልምም ፡ ብሎ ፡ ከደ ። ወደ ፡ ውጭም ፡ ወደ ፡ ደጅ ፡ ወጣ ፡ ዶሮም ፡ ጮኸ ። ገረዲቱም ፡ አይታው ፡ በዚያ ፡ ለቆሙት ፡ — ይህም ፡ ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ስትል ፡ ሁለተኛ ፡ ትነግራቸው ፡ ጀመር ። እር ሱም ፡ ደግሞ ፡ ካደ ። ጥቂት ፡ ቈይተውም ፡ በዚያ ፡ የቆሙት ፡ ዳግመኛ ፡ ኢየሱስን ፡ — የገሊላ ፡ ሰው ፡ ነህና ፡ ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ በእውነት ፡ ነህ ፡ አሉት ። እርሱ ፡ ግን ፡ — ይህን ፡ የምትሉትን ፡ ሰው ፡ አላውቀውም ፡ ብሎ ፡ ይረገምና ፡ ይምል ፡ ጀመር ። ወዲያውም ፡ ዶሮ ፡ ሁለተኛ ፡ ጮኸ ። ጴጥሮስ ፡ ኢየሱስ ፡ — ዶሮ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ሳይጮኽ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ትክደኛለህ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ትዝ ፡ አለው ፤ ነገሩንም ፡ አስቦ ፡ አለቀሰ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

፩ ወዲያውም ፡ ማለዳ ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ከሽማግሎችና ፡ ከጸሮች ፡ ከሸንጎውም ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ከተማከሩ ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስን ፡ አሰሩት ፡ ወሰዱትና ፡ ለጲላጦስ ፡ አሳልፈው ፡ ሰጡት ። ፪ ጲላጦስም ፡— አንተ ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ነህን ? ብሎ ፡ ጠየቀው ። እርሱም ፡— አንተ ፡ አልህ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ፫ የካህናት ፡ አለቆችም ፡ ብዙ ፡ ያሳጡት ፡ ነበር ። እርሱ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አልመለሰም ። ፬ ጲላጦስም ፡ ደግሞ ፡— አንዳች ፡ አትመልስምን ? እነሆ ፡ በስንት ፡ ነገር ፡ ያሰጡሃል ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ፭ ኢየሱስም ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ጲላጦስ ፡ እስኪደነቅ ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ አልመለሰም ።

፮ በዚያም ፡ በዓል ፡ የለመኑትን ፡ አንድ ፡ እስረኛ ፡ ይፈታላቸው ፡ ነበር ። ፯ በግመዕም ፡ ነፍስ ፡ ከገደሉት ፡ ከዓመፀኞች ፡ ጋር ፡ የታሰረ ፡ በርባን ፡ የተባለ ፡ ነበረ ። ፰ ሕዝቡም ፡ ወጥተው ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ያደርግላቸው ፡ ዘንድ ፡ እየጮኹ ፡ ይለምኑት ፡ ጀመር ። ፱ ጲላጦስም ፡— የአይሁድን ፡ ንጉሥ ፡ አፈታላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ትወዳላችሁን ? ብሎ ፡ መለሰላቸው ፤ የካህናት ፡ አለቆች ፡ በቅንዓት ፡ አሳልፈው ፡ እንደ ፡ ሰጡት ፡ ያውቅ ፡ ነበርና ። ፲ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ግን ፡ በርባንን ፡ በእርሱ ፡ ፈንታ ፡ ይፈታላቸው ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡን ፡ አወከአቸው ። ፲፩ ጲላጦስም ፡ ዳግመኛ ፡ መልሶ ፡— እንግዲህ ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ የምትሉትን ፡ ምን ፡ ላደርገው ፡ ትወዳላችሁ ? አላቸው ። ፲፪ እነርሱም ፡ ዳግመኛ ፡— ስቀለው ፡ እያሉ ፡ ጮኹ ። ፲፫ ጲላጦስም ፡— ምን ፡ ነው ? ያደረገው ፡ ክፋት ፡ ምንድር ፡ ነው ? አላቸው ። እነርሱ ፡ ግን ፡— ስቀለው ፡ እያሉ ፡ ጩኹት ፡ አበዙ ። ፲፬ ጲላጦስም ፡ የሕዝቡን ፡ ፈቃድ ፡ ሊያደርግ ፡ ወዶ ፡ በርበንን ፡ ፈታላቸው ፡ ኢየሱስንም ፡ ገርፎ ፡ እንዲሰቀል ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ።

፲፭ ወታደሮችም ፡ ጥራይቶሪዮን ፡ ወደሚባል ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ወሰዱት ፡ ጭፍራውንም ፡ ሁሉ ፡ በእንድነት ፡ ጠሩ ። ፲፮ ቀይ ፡ ልብስም ፡ አለበሱት ፡ የእሾህ ፡ አክሊልም ፡ ጐንጕነው ፡ ደፉበት ። ፲፯ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ሰላም ፡ ለአንተ ፡ ይሁን ፡ እያሉም ፡ እጅ ፡ ይነሡት ፡ ጀመር ። ፲፰ ራሱንም ፡ በመቃ ፡ መቱት ፡ ተፉበትም ፡ ተንበርክከውም ፡ ሰገዱለት ። ፲፱ ከተዘበበቱበትም ፡ በኋላ ፡ ቀዩን ፡ ልብስ ፡ ገፈፉት ፡ ልብሱንም ፡ አለበሱት ፡ ሊሰቅሉትም ፡ ወሰዱት ።

፳ አንድ ፡ መንገድ ፡ አላፊም ፡ የአሌክሳንድሮስና ፡ የሩፎስ ፡ አባት ፡ ስምዖን ፡ የተባለ ፡ የቀሬና ፡ ሰው ፡ ከገጠር ፡ ሲመጣ ፡ መስቀሉን ፡ ይሸከም ፡ ዘንድ ፡ አስገደዱት ። ፳፩ ትርጓሜውም ፡ የራስ ፡ ቅል ፡ ስፍራ ፡ ወደሚሆን ፡ ጎልጎታ ፡ ወደ ፡ ተባለ ፡ ስፍራ ፡ ወሰዱት ። ፳፪ ከርቤም ፡ የተቀላቀለበትን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንዲጠጣ ፡ ሰጡት ፤ እርሱ ፡ ግን ፡ አልተቀበለም ። ፳፫ ሰቀሉትም ፡ ልብሱንም ፡ ማን ፡ ማን ፡ እንዲወስድ ፡ ዕጣ ፡ ተጣጥለው ፡ ተካፈሉ ። ፳፬ በሰቀሉትም ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ነበረ ። ፳፭ የክሱ ፡ ጽሕፈትም ፡— የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ የሚል ፡ ተጽፎ ፡ ነበር ። ፳፮ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ሁለት ፡ ወንበዶች ፡ አንዱን ፡ በቀኙ ፡ አንዱንም ፡ በግራው ፡ ሰቀሉ ። ፳፯ መጽሐፍም ፡— ከዓመፀኞች ፡ ጋር ፡ ተቈጠረ ፡ ያለው ፡ ተፈጸመ ። ፳፰ የሚያልፉትም ፡ ራሳቸውን ፡ እየነቀነቁ ፡ ይሰድቡት ፡ ነበርና ፡— ፱ ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ የምታፈርስ ፡ በሦስት ፡ ቀንም ፡ የምትሠራ ፡ ከመስቀል ፡ ወርደህ ፡ ራስህን ፡ አድን ፡ አሉ ። ፴ እንዲሁም ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ደግሞ ፡ ከጸሮች ፡ ጋር ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እየተዘባበቱ ፡— ሌሎችን ፡ አዳነ ፤ ራሱን ፡ ሊያድን ፡ አይችልም ፤ ፴፩ አይተን ፡ እናምን ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ክርስቶስ ፡ አሁን ፡ ከመስቀል ፡ ይውረድ ፡ አሉ ። ፴፪ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የተሰቀሉት ፡ ይነቅፉት ፡ ነበር ።

፴፫ ስድስት ፡ ሰዓትም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ጨለማ ፡ ሆነ ። ፴፬ በዘጠኝ ፡ ሰዓትም ፡ ኢየሱስ ፡— ኤሎሄ ፡ ኤሎሄ ፡ ላማ ፡ ሰበቅታኒ ? ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸ ፤ ትርጓሜውም ፡ አምላኬ ፡ አምላኬ ፡ ለምን ፡ ተውኸኝ ? ማለት ፡ ነው ። ፴፭ በዚያም ፡ ከቆሙት ፡ ሰዎች ፡ ሰምተው ፡— እነሆ ፡ ኤልያስን ፡ ይጠራል ፡ አሉ ። ፴፮ አንዱም ፡ ሮጦ ፡ ሆምጣጤ ፡ በሰፍነግ ፡ ሞላ ፡ በመቃም ፡ አድርጎ ፡— ተዉ ፤ ኤልያስ ፡ ሊያወርደው ፡ ይመጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንይ ፡ እያለ ፡ አጠጣው ። ፴፯ ኢየሱስም ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኾ ፡ ነፍሱንም ፡ ሰጠ ። ፴፰ የቤተ ፡ መቅደስም ፡ መጋረጃ ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ከሁለት ፡ ተቀደደ ። ፴፱ በዚያም ፡ በአንጻሩ ፡ የቆመ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ እንደዚህ ፡ ጮኾ ፡ ነፍሱን ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡— ይህ ፡ ሰው ፡ በእውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፡ አለ ።

፵ ሴቶችም ፡ ደግሞ ፡ በሩቅ ፡ ሆነው ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ። ከእነርሱም ፡ በገሊላ ፡ ሳለ ፡ ይከተሉትና ፡ ያገለግሉት ፡ የነበሩ ፡ መግደላዊት ፡ ማርያም ፡ የታናሹ ፡ ያዕቆብና ፡ የዮሳም ፡ እናት ፡ ማርያም ፡ ሰሎሜም ፡ ነበሩ ። ፵፩ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የወጡ ፡ ሌሎች ፡ ብዙዎች ፡ ሴቶች ፡ ነበሩ ።

፵፪ አሁንም ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ የሰንበት ፡ ዋዜማ ፡ የሆነ ፡ የማዘጋጀት ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ፵፫ የከበረ ፡ አማካሪ ፡ የሆነ ፡ የአርማትያስ ፡ ዮሴፍ ፡ መጣ ፡ እርሱም ፡ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ፤ ደፍሮም ፡ ወደ ፡ ጲላጦስ ፡ ገባና ፡ የኢየሱስን ፡ ሥጋ ፡ ለመነው ። ፵፬ ጲላጦስም ፡ እሱኑ ፡ እንዲት ፡ ሞተ ፡ ብሎ ፡ ተደንቆ ፡ የመቶ ፡ አለቃውንም ፡ ጠርቶ ፡ ከሞተ ፡ ቆይቶአልን ? ብሎ ፡ ጠየቀው ፤ ከመቶ ፡ አለቃውም ፡ ተረድቶ ፡ በድኑን ፡ ለዮሴፍ ፡ ሰጠው ። ፵፭ በፍታም ፡ ገዝቶ ፡ አውርዶም ፡ በበፍታ ፡ ከፈነው ፡ ከዓለትም ፡ በተወቀረ ፡ መቃብር ፡ አኖረው ፡ በመቃብሩ ፡ ደጃፍም ፡ ድንጋይ ፡ አንከባለለ ። ፵፮ መግደላዊትም ፡ ማርያም ፡ የዮሳም ፡ እናት ፡ ማርያም ፡ ወዴት ፡ እንዳኖሩት ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

፩ ሰንበትም ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ መግደላዊት ፡ ማርያም ፡ የያዕቆብም ፡ እናት ፡ ማርያም ፡ ሰሎሜም ፡ መዋተው ፡ ሊቀቡት ፡ ሽቱ ፡ ገዙ ። ፪ ከሳምንቱም ፡ በፊተኛው ፡ ቀን ፡ እጅግ ፡ በማለዳ ፡ ፀሐይ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ መጡ ። ፫ እርስ ፡ በርሳቸውም ፡— ድንጋዩን ፡ ከመቃብር ፡ ደጃፍ ፡ ማን ፡ ያንከባልልናል ? ይበባሉ ፡ ነበር ። ፬ ድንጋዩ ፡ እጅግ ፡ ትልቅ ፡ ነበርና ፤ አሻቅበውም ፡ አይተው ፡ ድንጋዩ ፡ ተንከባሎ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ተመለከቱ ። ፭ ወደ ፡ መቃብሩም ፡ ገብተው ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ የተጐናጸፈ ፡ ጕልማሳ ፡ በቀኝ ፡ በኩል ፡ ተቀምጦ ፡ አዩና ፡ ደነገጡ ። እርሱ ፡ ግን ፡— አትደንግጡ ፤ የተሰቀለውን ፡ የናዝሬቱን ፡ ኢየሱስን ፡ ትፈልጋላችሁ ፤ ተነሥቶአል ፡ በዚህ ፡ የለም ፤ እነሆ ፡ እርሱን ፡ ያኖሩበት ፡ ስፍራ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሂዳችሁ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ለጴጥሮስም ፡— ወደ ፡ ገሊላ ፡ ይቅድማችኋል ፤ እንደ ፡ ነገራችሁ ፡ በዚያ ፡ ታዩታላችሁ ፡ ብላችሁ ፡ ንገሩአቸው ፡ አላቸው ። ፰ መንቀጥቀጥና ፡ መደንገጥ ፡ ይዞአቸው ፡ ነበርና ፡ ወጥተው ፡ ከመቃብር ፡ ሸሹ ፤ ይፈሩ ፡ ነበርና ፡ ለማንም ፡ አንዳች ፡ አልነገሩም ።

፱ እነርሱም ፡ ያዘዛቸውን ፡ ሁሉ ፡ ለጴጥሮስና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ላሉት ፡ በአጭሩ ፡ ተናገሩ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ ራሱ ፡ ለዘላለም ፡ ድኅነት ፡ የሆነውን ፡ የማይለወጠውን ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ ከፀሐይ ፡ መውጫ ፡ እስከ ፡ መጥለቂያው ፡ ድረስ ፡ በእጃቸው ፡ ላከው ።

፲ ከሰምንቱም ፡ በመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ ማልዶ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ ሰበት ፡ አጋንንት ፡ ላወጣላት ፡ ለመግደላዊት ፡ ማርያም ፡ ታየ ። ፲፩ እርስዋ ፡ ጌታ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ ለነበሩት ፡ ሲያዝኑና ፡ ሲያለቅሱ ፡ ሰሙ ፡ አወራችላቸው ። ፲፪ እነርሱም ፡ ሕያው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለእርስዋም ፡ እንደ ፡ ታያት ፡ ሲሰሙ ፡ አላመኑም ።

፲፫ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከእነርሱ ፡ ለሁለቱ ፡ ወደ ፡ በላ ፡ ገር ፡ ሲሄዱ ፡ በመንገድ ፡ በሌላ ፡ መልክ ፡ ተገለጠ ። ፲፬ እነርሱም ፡ ሄደው ፡ ለሌሎቹ ፡ አወሩ ። እነዚያንም ፡ ደግሞ ፡ አላመኑአቸውም ።

፲፬ ኋላም ፡ በማዕድ ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፡ ለአሥራ ፡ አንዱ ፡ ተገለጠ ፡ ተነሥቶም ፡ ያዩትን ፡ ስላላመኑአቸው ፡ አለማመናቸውንና ፡ የልባቸውን ፡ ጥንካሬ ፡ ነቀፈ ። ፲፭ እንዲህም ፡ አላቸው ፡— ወደ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ሂዱ ፡ ወንጌልንም ፡ ለፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ስበኩ ። ፲፮ ያመነ ፡ የተጠመቀም ፡ ይድናል ፡ ያላመነ ፡ ግን ፡ ይፈረድበታል ። ፲፯ ያመኑትንም ፡ እነዚህ ፡ ምልክቶች ፡ ይከተሉአቸዋል ፤ በስሜ ፡ አጋንንትን ፡ ያወጣሉ ፤ በአዲስ ፡ ቋንቋ ፡ ይናገራሉ ፤ ፲፰ እባቦችን ፡ ይያዛሉ ፡ የሚገድልም ፡ ነገር ፡ ቢጠጡ ፡ አይጐዳቸውም ፤ እጃቸውን ፡ በድውዮች ፡ ላይ ፡ ይጭናሉ ፡ እነርሱም ፡ ይድናሉ ።

፲፱ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ቀኝ ፡ ተቀመጠ ። ፳ እነርሱም ፡ ወጥተው ፡ በየስፍራው ፡ ሁሉ ፡ ሰበኩ ፡ ጌታም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ይሠራ ፡ ነበር ፡ በሚከተሉትም ፡ ምልክቶች ፡ ቃሉን ፡ ያጸና ፡ ነበር ።